# በዚያን ጊዜ

From: P/r Mihret K.
05/08/02

በተስፋዬ ጋቢሶ

To: Our Beloved family Pastor Almaz D. and Her family

2002 ዓ/ም

አሳታሚ፡-


## የኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተክርስቲያን

## Ethiopian Full Gospel Believers' Church

☎ 011 5-53 17 17

011 5-53 17 19

✉ 30740

Fax 251-0115531718

E-mail-emulwong@ethionet.et

አድራሻ፡

አዋሬ ከገደራ ሆቴል ዝቅ ብሎ

ቀበሌ 15 ስፖርት ማዘውተሪያ

ሜዳ ፊት ለፊት

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ



ያለ አሳታሚው ፈቃድ በማንኛውም መልክ ማባዛትም ሆነ ማሰራጨት የተከለከለ ነው።



ዲዛይን፡- በትዕግስት ታሪኩ


**ይህች ጽሑፍ ፡-**

ሳንወደው ለወደደን፣

ዕዳችንን ለተወልን

በመስቀል ላይ ለሞተልን

ጸጋውን ለገለጠልን

ሞታችንን ለሻረልን፣

የዘላለምን ሕይወት ለሰጠን፣

ለኢየሱስ ክርስቶስ ለመድኃኒታችን፣

ለቸሩ ጌታችን መታሰቢያ ትሁን።

## ምስጋና

ከሁሉ በላይ ባለፍንበት አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ በጸጋው ለደገፈን ለመድኃኒታችንና፣ለአምላካችን ለእግዚአብሔር ክብር ይሁን።

በዚያን ጊዜ በጸሎት የቆማችሁልንን፣ በገንዘባችሁና፣ በደብዳቤ ያበረታታችሁንን፣በጉልበታችሁና በንብረታችሁ እኛን ለማገልገል የደከማችሁትን፣ ረጅም መንገድ እየተጓዛችሁ ልታጽናኑን የመጣችሁትን፣በአንዳንድ የግል ጉዳዮች የተጋፋችሁትን፣ ስድባችንን የተካፈላችሁትን፣ በጥርጣሬም በሩቅም ሆናችሁ ቢሆንም ሲቃያችን እየተሰማችሁ ዕንባችሁን በእግዚአብሔር ፊት ያፈሰሳችሁትን ቅዱሳን ወገኖች ሁሉ እግዚአብሔር እጅግ አብዝቶ ይባርካችሁ።

ይህንን ጽሑፍ ለማዘጋጀት ብቻዬን በተቀመጥሁባቸው ቀናትና የተራዘሙ ሰዓታት ሁሉ የታገሡኝንና የደገፉኝን፣ ውድ ባለቤቴን ወ/ሮ ሐና ንጉሤንና ልጆቻችንን፣ ጸጋዬንና ጽዮንን፣ ሳላመሰግን አላልፍም።

በተጣበበ ጊዜዋ፣ የጽሑፉን ረቂቅ በከፊል በኮምፒዩተር ላይ በመጻፍ የረዳችኝን፣ የቤተ ክርስቲያናችንን የቀድሞ ጸሐፊ፣ ወ/ሮ እቴነሽ እንዳለን፣ ከልብ አመሰግናለሁ። እግዚአብሔር ይባርክልኝ።

ውድ ጊዜአቸውን መሥዋዕት በማድረግ፣ ረቂቁን አንብበው ገንቢ አስተያየትና ጠቃሚ ምክር የለገሡኝ፣ እህት ሙሉ እመቤት መንበረ ፣ፓስተር ጻድቁ አብዶ፣ ፓስተር በቀለ ወልደ ኪዳን፣ዶ/ር ንጉሤ ተፈራ፣ ወንድም ዝናቡ አየለ፣ ወንድም ንጉሤ ቡልቻ፣ ቄስ ዶ/ር ደበላ ብሪ፣ ዶ/ር ተስፋዬ ያዕቆብ፣ ዶ/ር ደሲታ ሄልሶ፣ ወንድም ገዛኸኝ ሙሴ፣ እንዲሁም ወንድም ዮሐንስ አባተ ......ባለ ውለታዎቼ ናቸው ። የሰውን ድካም የማይረሳው ጌታ ይህንንም ይቁጠርላቸው።

ይህንን ጽሑፍ እንዳዘጋጅ ካበረታቱኝ መካከል በተለይ ዶ/ር ገርማ አበበን ከልብ አመሰግናለሁ።

## ይቅርታ

አምልጠው ለሚያልፉ የጽሑፉ ግድፈቶች፣ ከወዲሁ ይቅርታ እጠይቃለሁ።

## ግንዛቤ

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የሚገኙ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ከሞላ ጎደል ከአዲሱ (ተ.ጋ.ሥ.) ትርጉም የተወሰዱ ናቸው።

*አቤቱ ጌታችን ስምህ በምድር ሁሉ እጅግ ተመሰገነ!*

*ምስጋናህ በሰማያት ላይ ከፍ ከፍ ብሎአልና።*
(መዝ 8:1)

*ወደ ችግረኞች ጸሎት ተመልሶ*
*ልመናቸውንም አልናቀም።*

*ይህ ለሚመጣ ትውልድ ይጻፍ፤*

*የሚፈጠርም ሕዝብ ለእግዚአብሔር እልል ይላል፤*

*እግዚአብሔር ከመቅደሱ ከፍታ ሆኖ ተመልክቶአልና፤*
*ከሰማይ ሆኖ ምድርን አይቶአልና፤*

*የእስረኞችን ጩኸት ይሰማ ዘንድ፤*

*ሊገደሉ የተፈረደባቸውን ያድን ዘንድ፤*

*የእግዚአብሔርን ስም በጽዮን*

*ምስጋናውንም በኢየሩሳሌም ይናገሩ ዘንድ፤*
(መዝ 102:17-21)

*...ከጨለማና ከሞት ጥላ አወጣቸው፤*

*እስራታቸውንም ሰበረ።*

*...የናሱን ደጆች ሰብሮአልና፤*

*የብረቱንም መወርወሪያ ቆርጦአልና።*

*...በመከራቸውም ጸጥ አደረገ፤ ሞገዱም ዝም አለ።*

*ዝም ብለዋልና ደስ አላቸው፤ ወደ ፈለጉትም ወደብ መራቸው።*

*ለሰው ልጆች ስላደረገው ተአምራት*

*ስለ ምሕረቱም እግዚአብሔርን ያመስግኑ።*
(መዝ 107:1-31)

## ማውጫ


| | ገጽ |
|---|---|
| ስለዚያ ወቅት | 1 |
| ስለዚህ መጽሐፍ | 2 |
| መቅድም | 4 |
| መግቢያ | 5 |
| **ምዕራፍ አንድ - ጅማሬው** | **8** |
| ከጨለማ ጋራ ብርሃን ሲዋጋ | 8 |
| አጀማመር በደርጋ ዓለም | 9 |
| በተቃውሞ መሐል | 12 |
| ማስጠንቀቂያና ማንቂቂያ | 17 |
| የሁለቱ አገልጋዮች መያዝ | 19 |
| የመጨረሻው ዝግጅት | 22 |
| **ምዕራፍ ሁለት - የቀበሌው እንግልት** | **25** |
| የተጠበቀው ሲመጣ | 25 |
| የቀበሌው ቆይታ | 27 |
| በአዲሱ ቦታ | 30 |
| «የመከራ ጉዞ» | 36 |
| «አትሸበር በርታ» | 39 |
| ጭካኔው ሲገለጥ | 40 |
| በስፖርት ስም | 42 |
| ከሁሉ በላይ | 44 |
| ጊዜው ባያጥር ኖሮ | 46 |
| የዝምታ ወራት | 48 |
| **ምዕራፍ ሦስት - የወኅኒው እስራት** | **51** |
| መኖ ወዳለበት | 51 |
| ኑሮ በማረሚያ ቤት | 52 |
| ተጨማሪ ሁነቶች | 55 |
| ከልምምድ ወደ ሥራ | 57 |
| መነቃቃትና መፈተን | 58 |
| ውስጣዊ ስደት - በእስር ቤት | 60 |
| ፅንቁ - ጣጣሽ! | 64 |
| ያቺ ምሽት | 68 |
| **ምዕራፍ አራት - ወረና ደርሶ መልስ** | **70** |
| ጉዞ ወደ ቦረና | 70 |
| እግዚአብሔር ሲረዳ | 73 |
| መለኮታዊው ጥንቃቄ | 80 |
| በሩቅ አገር ሳሉ | 82 |
| ተመልሶ ደፈ.ጋ ዓለም | 83 |
| የሰማይ መስኮቶች | 86 |
| የእግዚአብሔር ድምጽ | 88 |
| ኃጢአት ስታሳድድ | 89 |
| የመዝሊያው መነቃንት | 91 |
| የመጨረሻው ዝምታ | 99 |
| **ምዕራፍ አምስት - ቀንበሩን ሰበረው!** | **103** |
| «የታሰሩት በቁ ሆኖ» | 103 |
| የመጨረሻው «ንቃት» | 106 |
| አንድም «ስዛ» ሳይቀር | 108 |
| ዜናው ሲሰማ | 109 |
| መልዕክት ለተፈቱት | 110 |
| ክብር ሁሉ ለእግዚአብሔር | 111 |
| ከዚያ በኋላ | 112 |
| ማጠቃለያ | 114 |

## ስለዚያ ወቅት

ጊዜው በኢትዮጵያ አቆጣጠር 1966 ዓ.ም ነበር። ወሆዱ የቋጠረውን አንዳች ነገር ሊዘረግፍ፡ የጠቆረው የለውጥ ደመና በምድሪቱ ላይ ወረድሁ ወረድሁ እያለ ያስፈራራል። አገሪቱን ከአራት አሰርት ዓመታት በላይ ያስተዳደሩት ንጉሥ ስውጡን ሊቆጣጠሩት እንደተሳናቸው ግሃድ እየሆነ መጣ። በአገሪቱ የተፈጠረውን ሁለገብ ወቀሳ ለማብረድ የተወሰዱ ርምጃዎች እጅግ የዘገዩና መሠረታዊ ለውጥ ለማምጣት ፋይዳ ያልነበራቸው በመሆናቸው አቅጣጫ የሰሽ ሰውጥ አይቀሬ ሆነ። የመሰዮ ሰባሹን ጥያቄ ዳር ያደርሱ ዘንድ ፍ ከፍተኛ የጦሩ ክፍሎች፣ የተወከሉ የበታች ሹማምንት እያየለ የመጣው የለውጥ ፍላጎት ከቶውንም ያሳለቡትን አሳብ እያሳለባቸው ነበር። የንጉሡ ክንዶች የፖለቲካ መዘውሩን ለመቆጣጠር አለመቻል፣ ተማሪዎች፣ ምሁራንና የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ብርቱና የማያባራ ግፊት ለዓመታት በንጉሡ እጅ ተጠብቆ የቆየውን ፍፁማዊ ስልጣን ከ4ኪሎ ቤተ መንግስት ውስጥ አስፈንጥሮ አወጣው።

ነቅናቂ አንጂ ሁነኛ ተቀባይ ያልነበረው ሥልጣን የጦሩን ጥያቄ ከንጉሡ ጋር ለመደራደር አዲስ አበባ ተገኝቶ በነበረው ወታደራዊ እጅ ላይ ወደቀ። የተፈጠረው የአመራር ክፍተት የፈጠረላቸው ያልተጠበቀ ሲሳይ ያጋጠማቸው ወታደሮች አዝጋሚ በሆነ ንጉሡን ከስልጣን የማስወገድ ሥራ የተሳካላቸው ቢሆኑም አገሪቱን የሚመሩበት ቅድመ ዝግጅት ያልነበራቸው ነበሩ። በታሪክ አጋጣሚ ወደ ሥልጣን መንበር ያቀኑት የመሰዮ ሰባሹ ተወካዮች ስልጣን አድል ብቻ ሳይሆን ተግዳሮቶችንም አንካችሁ አሏቸው። በምስራቅ በስሜንና በመሀል አገር የተፈጠረው ሁኔታ ተደምሮውንም ያልታሰበት ኃላፊነትን የተረከቡትን እነዚያን ሰዎች ጭንቅ ውስጥ ከተታቸው። ካፒታሊዝምና ሶሻሊዝም በሚል ከተፋጠጡት የምዕራብና የምስራቅ መንግስታት ጎራዎች በአንዱ ውስጥ መግባት አምቢ የማይሉት ግዴታ ሆነባቸው። እናም የወታደራዊው ደርግ መመሪያ ሶሻሊዝም ሆነ። መመሪያውም በቀናነት ከማያቀነቅናቸው መርሆዎች እንደ አንዱ ተቆጥረና እግዚአብሔር የለም ተባለ። ሐይማኖተኝነት ሐሳባዊነት፣ ሐይማኖት ደግሞ የወደቀው ስርዓት ሥልጣን ድጋፍ፣ እና የኢምፔሪያሊዝም ማደንዘዣ ዕፅ ሆኖ ተፈረጀ። ቀጠለ። የለም ያሉትን እግዚአብሔርን በአስተማማኝ ሁኔታ ከህዝብ ልብና ከአገር ጠራርጎ ለማውጣት የእግዚአብሔር የሆኑትን ለማስገበር የጥፋት ነጋሪት ተጎሰመ። የእምነት ተጋዦችም ፍፃሜ የሌለው ወደሚመስለው ትልቅ ጦርነት ውስጥ ሰተት ብለው ገቡ። ቀደም ሲል የተሞከሩ የማስፈራሪያና የማስቃያ ትዕዛዝ ተግባራት "ከወዳጅ" ሀገራት ተጋዙ። እናም ታላቁ ጦርነት ተጀመረ። "ያለና የሚኖር እኔ ነኝ" ባለ በሕያው እግዚአብሔር አሸናፊነትም ተፈፀመ።

ይህ በነፍሳቸው ተወራርደው ስለ ስሙ መከራ የተቀበሉትን ተከታዮቹን ደህንነት በመጠበቅ ሰባት ፈታኝ ዓመታትን በድል የደመደመ የታመነ አምላክ ዕፁብ ድንቅ የተጋድሎ ታሪክ ነው።

ከላይ ደፍ፣ ከታች ማዕበል፣ በማያንገላታት ታንኳ ውስጥ በሚዳሰስ ጨለማ ከባቢ ሁኔታ ተከበው ተስፋ ባልሆናቸው ጊዜ የተሰጣቸውን ተስፋ ይዘው ያመኑትን ወዳጆቹን ወደ ወደቡ ዳርቻ በደህና ያደረሳቸው አምላክ የተባረከ ይሁን። አሜን።

መምህር ዮሐንስ አባተ
ከኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል ሥነ-መለኮት ኮሌጅ





## ስለዚህ መጽሐፍ

በክርስቶስ ኢየሱስ በእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት መኖር የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ። (1ኛ ጢሞ. 3፡12) በየሱ ይና በአዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር መልዕክተኞች ተሰደዱ፣ በ20ኛው ክፍለ ዘመን በአፍሪካ በኢትዮጵያም የወንጌል መልእክተኞች ስደት ደርሶባቸዋል፣ በ20ኛው ክፍለ ዘመን በአፍሪካ ከሌሎቹ አገሮች የበለጠ ሰማዕታት የነበሩት በኢትዮጵያ ነው። ይህም ለምን እንደሆነ የሚያውቀው እግዚአብሔር ነው። የኢትዮጵያ ወንጌል አማኞች ታሪክ በስደት ተጀምሮ እና በስደት ተጉዞ ወደ 21ኛ ክፍለ ዘመን ተሸጋግሯል። በ1916 በወንጌል አማኝ በአለቃ ታየ የተቀበር ቦታ ሰበብ በአዲስ አበባ ብርቱ አምቦቸርና ጥል ተነስቶ ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ የምክር ቃል መሳካቸውን ብላታ መርስኤ ሐዘን ወልደ ቂርቆስ ጽፈዋል።

የዚህ መጽሐፍ ታሪክ በአብዛኛው የተፈጸመበትን ደርጋ ዓለም ከተማን የሆኑት ራስ ደስታ ለወንጌል መልእክተኞች በይርጋ ዉኤፈ አካባቢ ለወንጌል አገልግሎት የሚሆን የሚሲዮ ቦታ ለመፍቀድ በ1925 ዓ/ም የጠየቁት ደብዳቤ የግንባታ መሰ ድጋፍ ሲሆን፣ 1400 ቤቶች ግንባታ ላይ የተሳተፉት ክሊፍ ሚሼል የተባሉ ሚሲዮናዊ ግንቦት 1928ዓ/ም ተሰውተዋል።

በጣሊያን ወረራ ወቅት የወንጌል አማኞች የደረሰባቸውን ብርቱ ስደት በአንድነትና በፍቅር ዘልቀዋል። ከዚያም በኋላ በእምነት ሰበብ ቀላል ያልሆነ ስደት ደርሷል። በእምነት ምክንያት ወጣቶች አባቶች፣ እናቶች፣ ወጣቶች ሁሉን ትተው ተደበደቡ፣ ታሰሩ፣ ተሰቃዩ፣ በስለት ተወጉ፣ ሬሳቸውም የቀብር ቦታ እንዳያገኝ ተደረገ። የደረሰባቸው መከራ ስተቀበሉት የእግዚአብሔር ልጅነት የበለጠ ጽኑና ታማኝ አደረጋቸው፣ ከጠላቶቻቸውም በረቱ።

በቅርቡ በዘብርና በድል ምድራዊ ጉዞአቸውን አጠናቀው ወደሚጠሩት አምላካቸው የሄዱት ከ1942 ዓ/ም ጀምሮ በወንጌል አማኞች አንድነት ማሕበር መሥራች ቤተሰሮዊ ጉባኤ ለብዙ ዓመታት መሪ ተሳታፊ የነበሩት የፀሐፊው አባት አቶ ጋቢሶ ዶያሞ፣ በአንድ ወቅት በወንጌል ምክንያት ስደት ደርሶባቸው በይርጋ ዓለም ወህኒ ቤት ታስረው፣ እንግልት ደርሶባቸው በነበረ ጊዜ "ጌታ ሆይ ስለ ወንጌል የሚታሰር ልጅ ስጠኝ" በማለት ጸልየው እን ደነበረ ለምኛ፣ የጸሎታቸው ጥልቀት ከስደትም ነበር። እውነትም ጸሎታቸው ተመልሷል። እግዚአብሔር አምላክ አሠራሩ ድንቅ ነው።

የእግዚአብሔር ሥራ ታሪክ ይነገር፣ ይጻፍና ለትውልዶችም ይቀባበል ዘንድ ፈቃዱ ስለሆነም ይህ መጽሐፍ ተጻፈ። በስደትና በመከራ ውስጥ በጌታ ፀጋ አልፈው ያንን የጌታን ከሥራር በጽሁፍ ለትውልድ ለመመስከር ደጅ ሰ ልእርግጥ ጥቂት ናቸው። በኢትዮጵያ በ21ኛው ክፍለ ዘመን መባቻ፣ በብዙ ወንጌላዊያን አማኞች ሕይወት ውስጥ ያለ ትኩስና በመሻር ላይ ያለ የመከራ ቀስል አስተማሪነቱ ሳስሁኑና ስቀጣዩም ትውልድ መሆን ይገባዋል። የዚህ መጽሐፍ ታሪክ የኢትዮጵያ ወንጌል አማኞች የደረሰባቸው ስደት፣ ብርቱ ፍቅርን፣ ጥብቅ አንድነትን፣ ልባዊ የጸሎት ሕብረትና ውስጣዊ ጥራትን ለወንጌላውያን የፈጠረ መሆኑን ያመለክታል።

በዚያ የመከራ ወቅት፣ ሁሉም የወንጌል አማኞች እንደ አንድ አካል አብረው ተሰቃዩ። የሰፈር የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና የጸሎት ሕብረቶች እንዲሁም ያልተዘጉ አብያተ ክርስቲያናትና ከንፍራንሶች ሁሉን አማኞች አገለገሉ። በስደት የታጀበ ታሪክ ከእግዚአብሔር ፀጋና ምህረት የተነሳ ፍሬ አፍርቶ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ የወንጌል አማኞች ሆኑ። የሕይወት ምንነት፣ የጸሎት ተጋድሎ፣ የሰው ክፋት፣ በእግዚአብሔር ፀጋ በመሸፈን ያለ

ቸርነት፣ እንዲሁም ሕይወትን ለዘለዓለማዊ ዕሴት የማስገዛት ተውኔት በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ታይተዋል። እንደ እንፋሎት የሚጠፋን ሕይወት ከዘላለም አንጻር መኖር ታላቅ ትርፍ የመሆኑ ምስክርነትም አለበት። ክርስቶስን በመምሰል፣ በምድር የተሰጣቸውን ዘመን በአምላካቸው ፈቃድ ሥር የሚኖሩ ጥበበኞች ናቸው።

ቤተ ክርስቲያን ግን ኢየሱስን እየመሰሉ ሲኖሩ የሚወዱ ሰዎች ብርቱ እጥረት እንዳለባት ይታያል። ይህ እጥረት እየባሰ በመሄድ ላይ ያለ ይመስላል። በዘመናችን፣ በአህጉራችንና በአገራችንም ቤተክርስቲያን የክርስቶስ ታማኝ ደቀ መዛሙርት ጥቂት ናቸው። ኢየሱስ ሊከተለኝ የሚወድ ራሱን ይካድ ብሏል (ማቴ.16፡24)። የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ለሞተላቸውና ከሙታን ለተነሳላቸው እንጂ ለእራሳቸው እንዳይኖሩ ታዘዋል። ስለዚህ ደቀ መዛሙርት እርሱን ለመምሰል የሚያደርጉት ጥረት የሕይወታቸው ዓላማ ይሆናል (ሉቃ. 6፡40)። (2ኛ. ቆሮ. 5፡15)

በየዘመናቱ በአምላክ ምህረትና ቸርነት ፀጋውን ተቀብለው በታማኝነት ለጌታ የኖሩ፣ እንዲሁም ምድራዊውን ሕይወት በዘለዓለማዊ ዕሴት ሥር ለመገዛት የወሰኑ ወቢያን የተማሩትን ለተከታዩ ትውልድ ያወርሳሉ። መለኮታዊ አመራርን የዕለታዊ ኑሮ ፍልስፍና የማድረግ ብርታትንና በመሰጠት የእግዚአብሔርን ድምጽ ሰምቶ መታዘዝን ለሌሎች ማካፈል ባለ አደራነትን መገንዘብ ነው። ልጆቹ በዕለታዊ ኑሮአቸው የማያመች ልምምድ እንዲከሰት ሁሉን ቻዩ አምላክ ፈቅዶ ይህንንም በቅርብ የተመለከቱ የሚሰጡት ምስክርነት አስተማሪነቱ ብርቱና መሠረታዊ ነው። በዚህ ረገድ አንዳንዴም ከመቃብር ወዲህ መልስ የማይገኝላቸው ጥያቄዎች ያሉ ቢሆንም በዘላለማዊ አምላክ ለቅድ ውስጥ ናቸው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም "ሰዎች በእኔ ምክንያት ቢሰድቧችሁ ቢያሳድዷችሁ ክፉውን ሁሉ በሐሰት ቢያስወሩባችሁ ብፁዓን ናችሁ" ብሏል (ማቴ. 5፡11)። ስለዚህ፣ አምላካዊ አሠራርን ለመረዳት የሚደረግ ጥረት ወደ መንፈሳዊ ዕድገትና ጌታን ወደ መምሰል የሚያስኬድ ነው፣ የእግዚአብሔር ፀጋና ቸርነትም የልጆቹ ብዕናና የደስታ ምንጭ ነው።

ዘርስትና ዋጋ ያስከፍላል፤ መስዋዕትነትም አለበት። ይህም መጽሐፍ፣ በአገራችን በነበረው ከባድ የወንጌል አማኞች ስደት ውስጥ በጌታ በመታመን በጽኑ መከራ ውስጥ በትዕግስት፣ በእምነትና በብርታት፣ በመንፈስ ቅዱስም ረድኤት የዘለቀ የኢየሱስ ክርስቶስ ታማኝ ደቀ መዛሙርት ታሪክና ምስክርነት ነው። ስለሆነም ምዕመናን፣ አገልጋዮችና መሪዎች ሁሉም እጅግ አስፈላጊ፣ ዘላቂና መሠረታዊ ትምህርት የሚቀስሙበት ስለሆነ ብጥንቃቄ፣ በጸሎትና ለመማር በተዘጋጀ ልብ እንዲያነቡት አደፋፍራለሁ።

ክብር ሁሉ ለኢየሱስ ይሁን።

ተስፋዬ ያዕቆብ /ዶ/ር
ስኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ዋና ጽ/ቤት
ጥር 2002 ዓ/ም





## መቅድም

በፓስተር ተስፋዬ ጋቢሶና በሌሎች ክርስቲያን ወንድሞችና እህቶች ላይ በደርግ ዘመን የደረሰው ከባድ ስደት፣ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "በሁሉም ስለ ስሜ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ፥ እስከ መጨረሻ የሚጸና ግን እርሱ ይድናል"(ማቴ 10፡22) "እኔን አሳድደውኝ እንደ ሆነ እናንተን ደግሞ ያሳድዱአችኋል" (ዮሐንስ 15፡20) "በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ይከተለኝ" (ማር 8፡34) ባለው መሠረት የተፈጸመ ነው።

ጌታ ራሱ ከሕፃንነቱ ጀምሮ ይሰደድ ነበር። በመጨረሻም የሞት ቅጣት ተፈረደበት ለሰው ልጆች ደህንነት ሲል መሥዋዕት ሆኗል። ከአሥራ ሁለቱ የጌታ ደቀመዛሙርት የተፈጥሮ ሞት የሞተው ሐዋርያው ዮሐንስ ብቻ ነበር፣ እርሱም ቢሆን በእሥር ቤት ብዙ ሥቃይ ደርሶበታል። ታላቁ ቈስጠንጢኖስ እስከተነሣበት አራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ ክርስቲያኖች በከባድ ሥቃይ ውስጥ እንደ ነበሩ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ያስረዳል። ታሪክ ራሱን ይደግማል እንደሚባለው በእነ ፓስተር ተስፋዬ ላይ የደረሰው ከዚሁ ተራ ይቆጠራል ብል ስህተት አይሆንም።

የጥንት ክርስቲያኖች ለሮም ቄሣሮች መሥዋዕት አንሠዋም፤ ቄሣሮችንም "ጌታ" ብለን አንጠራም፤ "ጌታ" የሚለው ማዕረግ ለአዳኛችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ይገባል ስላሉ በአሠቃቂ ሁኔታ ተሰውተዋል። እነ ፓስተር ተስፋዬም "ለአብዮት ቄሣር" አንሠዋም ስላሉ ብቻ እጅግ ተንገላተዋል፣ ጌታ ግን ደርሶ ታድጓቸዋል። በጣም ያሳዝን! ልክ ፓስተር ተስፋዬ የደረሰባቸውን እንደ መዘገቡት በሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን ለጌታ ስትል የመሠቃየት ዕድል የገጠማት ዚቢያ ፔርፔትዋ የምትባል ክርስቲያን እህት የደረሰባትን በጽሑፍ አስቀርታለች። ስትያዝ ዕድሜዋ 20 ዓመት ነበር። በቅርብ ጊዜ የደረሰባትን ወንድ ልጅ የወለደች አራስ ነበረች። ከነልጅዋ እሥር ቤት ተጣለች። የአባትዋና የልጅዋ ሁኔታ ፈተና ቢሆንባትም በእምነትዋ ጸንታ እንድትቆም ጌታ ረድቶአታል። በመጨረሻ በአብድ ላም ተወግታ እንድትሞት ተፈረደባት። ከላምዋ ጋር ግብ ግብ ገጠመች። ግን ከላምዋ በደረሰባት ቁስል ሳትሞት ስለቀረች በጎራዴ አንገትዋ ተቆርጦ ሞተች።

የፔርፔትዋ አገልጋይ የነበረች ፌሊሲታስ የምትባል እህት ከፔርፔትዋ ጋር ስትያዝ የ8 ወር እርጉዝ ነበረች። ስለ ጌታ ስትል መሠቃየትን እንደ ታላቅ ዕድል ብትመለከትም የዘመኑ ሕግ ዕርጉዝ ሴት እንድትገደል ስለማይፈቅድ በቶሎ እንድትገላገል አጥብቃ ትጸልይ ነበር። እግዚአብሔር ጸሎትዋን ሰምቶ በዚያው ወር ውስጥ ወንድ ልጅ ተገላገለች። በእምነትዋ ጸንታ በመቆምዋ ሞት ተፈረደባት። ልክ እንደ እመቤትዋ እንደ ፔርፔትዋ በአብድ ላም ተወግታ የሞት ጽዋ ጠጣች። ይህም ሲሆን የአይን ምስክሮች እንደዘገቡት ከጡቶችዋ ወተት እንደ ውኃ ይፈስ ነበር። አሠቃቂ ሞት ነበር፣ ነገር ግን ድል አድራጊና የክብር ሞት ነበር። ጌታ "እስከ ሞት ድረስ የታመንህ ሁን የሕይወትንም አክሊል እሰጥሃለሁ" (ራዕይ 2፡10) ብሎ የለ?

ቄስ ዶ/ር ደበላ ብሬ
በኢትዮጵያ ድኅረ ምረቃ ሥነ መለኮት ት/ቤት 2ኛ ዳይሬክተርና የቤተ ክርስቲያን ታሪክ መምህር

# መግቢያ

ይህ «ተመጣኝ» የቀረበ ታሪካዊ ማስታወሻ ነው:: ትረካው፣ እኒን ዉጤም፣ በተወሰኑ የወንጌል አማኝ ክርስቲያኖች ላይ ደርሶ ያለፈውን ስደትና መከራን ይመለከታል:: ለመንደርደሪያና ለመደምደሚያ ተብለው የገቡ ቀዳሚና ተከታይ ጉዳዮችም ይኖሩታል:: ጊዜው፣ በጥቅሉ *የአብዮቱ ዘመን* እየተባለ የሚጠቀሰው ሲሆን፣ ቦታው በደቡብ ኢትዮጵያ፣ በቀድሞው የሲዳሞ ክፍለ ሃገር፣ ይርጋ ዓለምን በረና ነገሌንና ሀዋሳን ያጠቃልላል:: ዋናው ዓላማ የታላቁን አምላክ የእግዚአብሔርን ምሕረት፣ ታማኝነትና ታዳጊነት ለትውልዳችን በመንገር ለክርስቶስ ወንጌል ብዬሚሆን ሙሉ መስጠት እንዝቢን መጋበዝ ነው::

በእምነት ምክንያት መከራን መቀበል እንግዳ ነገር አይደለም:: ከጥንትም የነበረና የሚኖርም ነው:: በብሉይ ኪዳን ዘመን ዳንኤል፣ ሲድራቅ፣ ሚሳቅና አብደናጎ ስለ እምነታቸው መከራ መቀበላቸውን ቅዱሱ መጽሐፋችን ይነግረናል:: በአዲስ ኪዳን ውስጥ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ እንዲሁም ሐዋርያቱ የመከራና የትዕግሥት ምሳሌዎቻችን ናቸው:: ያለፉት 2000 ዓመታትም በዓለም ዙሪያ - በሰማዕታትና በሌሎችም ምዕመናን መንፈሳዊ ተጋድሎ የተሞሉ ናቸው:: ተርቱሊያን የሚባል የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን የእምነት ተሟጋች እንደተናገረውም፣ *የሰማዕታቱ ደም የክርስቲያንነት ዘር* እየሆነ፣ የክርስቶስ የመከራው ውጤት የሆነችው ቤተ ክርስቲያን፣ በመከራ ውስጥ እያለፈችም ቢሆን፣ ማደግዋ እየቀጠለና የእግዚአብሔርም መንግሥት እየሰፋ ይሄዳል::

*በዚህችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፣ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም* ያለ መሥራችዋና ባለቤትዋ ክርስቶስ ሕያውና ኃያል ጌታ ነው (ማቴ 16:18):: ስለዚህም በእርሱ ተደግፋ የሚያሳድዱትን የሚያስጨንቁትን ሁሉ ተቋቁማ አሸንፋ ቤተ ክርስቲያን በድል ትገሰግሳለች:: ፈተናው ስደቱና መከራው ከማዳከም ይልቅ የበለጠ እያጠነከራት፣ እያጠራትና እያስፋት ባለ መሄዱ ታሪክም እኛም ምስክሮች ነን::

በአገራችን በኢትዮጵያም፣ ባለፉት ዘመናት፣ በተለይም በመጨረሻው ዓመታት በተቀሰቀሰ ኃይለ ሥላሴ ዘመን፣ መንግሥት ከነበሩት ኢትዮጵያ የተሰደዱ አካባቢዎች በነበሩት ባለሥልጣናት እጅ በእምነት አባቶች ላይ ክብድ ያለ ስደት ደርሷል:: የነበረው ተጽዕኖና ስለ ወንጌል እውነት የተከፈለውም ዋጋ በቀላሉ የሚታይ አይደለም:: የደርግ ዘመን በመባል የሚታወቀው የገዛ መንግሥት የፈጠረን ሕልውና ከዶ ለማስከድ የታሰበውና ለማስፈጸም የሕሊና ነጻነት ዉጪስ የማይገዛው ሥርዓት፣ ለበርካታ ክርስቲያኖች መሰቃየትና መንገላታት ምክንያት መሆኑ የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው::

ይህን ከመሰለ ረጅምና ሰፊ ታሪክ ካለውና ጥልቅ የሆነ ስሜትም ከሚያሳድረው፣ የክርስቲያኖች ከባድ መከራ አኳያ፣ በዚህ ማስታወሻ ላይ ለማስፈር የተሞከረውና በጥቂቶቻችን ላይ የደረሰው ችግር የሚኖረውን ሥፍራ ለመገመት አንችልም:: ጉዳዩ ግን የሰው ሳይሆን የእግዚአብሔር ነው:: ስለዚህ ሥራውን ማሳወቅና ክብርን ለባለቤቱ መስጠት ተገቢ ይሆናል::





በየክፍላቱ እንዲሁ፣ ሁሉንም ቤተ እምነት ከተፈታተነው ስደት አኳያ፣ ይህ ማስታወሻ በጥቂት አማኞችና በተወሰነ አካባቢ ላይ ስለሚያተኩር፣ የትረካው ወሰን በእርግጥ ጠበብ ያለ ነው:: ሆኖም በወቅቱ ሁኔታውን ተከትሎ በትዳሳን ልብ ላይ ያረፈው የሕሊናና የምልጃ ሸክም እጅግ አቀፍና ከዚያም የበለጠ ነበር:: *ይህ አንድ ብልት ቢሠቃይ ብልቶች ሁሉ ከእርሱ ጋር ይሠቃያሉ* የሚለውን የቅዱስ ቃሉን እውነት ያረጋግጥልናል(1ቆሮ 12:26):: ስለዚህ፣ ጉዳዩ የማይመለከተው አማኝ አልነበረም:: አሁንም ምስጋናውና ትምህርቱ *ሁሉን* የሚመለከት ሆኖአል::

ይህን ማስታወሻ ለአንባብያን ለማቅረብ የግድ የሚሉ ምክንያቶች አሉ:: ዋነውና የመጀመሪያው በእኛ ሕይወት ላይ የተፈጸመውን የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ ለትውልድ የመግለጽ ኃላፊነት ነው:: ሌላው፣ ቢቃልም ሆነ በጽሑፍ ይህንኑ እንድናደርግ የሚጎተጉቱን በርካታ ወገኖች ያልተቋረጠ ጥያቄ ነው:: በተ እንደምናደርግ የሚጎተጉቱን ... በእንዳንድ ቦታ፣ የሰማናቸው ተያያዥ ጉዳዮች በሚያስገርም ዉጣሬም፣ መልኩ ከእውነት የራቁ፣ የተዛቡ፣ አልያም የተጋነኑ ሆነው አግኝተናቸዋል:: ስለዚህ ያኔ በእኛ በኩል የሆነውን፣ አሳጥርም ቢሆን፣ በጽሑፍ ማቅረቡ ወገኖቻችን እግዚአብሔርን በእውነት ብቻ እንዲያከብሩት ሊያግዛቸው ይችላል በሚል እምነትም ነው::

ከዚህ ቀደም፣ እህታችን ሙሉ አሰፋ፣ መንዝረም *በታ ሊል አቤቶ* በሚል ርዕስ ተጨማሪ መጽሐፍ አሳትማለች:: መጽሐፉ በዚህኛው ጽሑፍ ያልታዩትን ተጨማሪ እቅጣጫዎች ያሳያል:: ስለዚህ ሁለቱንም ዘገባዎች የተመለከተ አንባቢ ሰፋ ያለ እውቀት በጉዳዩ ላይ እንደሚኖረው ይታመናል::

የዚህ፣ የአሁኑ ማስታወሻ አቀራረብ በአመዛኙ «እኛ» በሚል መልክ ሆኖአል:: ምክንያቱም በወቅቱ፣ አሥራ ሦስት ወንድሞችና አምስት እህቶች፣ በድምሩ አሥራ ስምንት በመሆን፣ ያንን መከራ፣ እስር ቤት ውስጥ የተካፈልነው በጋራ ነበር:: ... ያ የመከራ ዘመን፣ በግለሰቦች ላይ፣ በተናጠል ሳይሆን፣ በዚያ በነበርን አማኞች ... ማለትም በክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ላይ ያረፈ ነበር:: ስለዚህም፣ በኅብረት ... ለማውሳት በይርጋ ዓለም ከተማ፣ ስለ ኅብረት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ለማውሳት ... ይህ የሆነው በትረካው ድግግሞሽ አካባቢ የተወሰኑ ገጾች መያዛቸው አልቀረም:: ይህ የሆነው በትረካው ጅማሬ አካባቢ የተወሰኑ ገጾች መያዛቸው የዋናውን ታሪክ ዳራና መንደርደሪያ ለአንባቢ መስጠቱ አግባብነት ይኖረዋል ከሚል እምነት በመነሣት ነው::

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ፣ በቅርብ የምናውቃቸው ወዳጆቻችን የቀረቡታቸውን ልክ የማመልከት፣ «አንቱ» ከመባል ይልቅ «አንተ» በሚል መልኩ ተጠቅሰዋል:: ... በሌላ በኩል፣ አስፈላጊ ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር፣ በእስር ቤት እያሰን ካንገላቱን ግለሰቦችና ባለ ሥልጣናት መካከል የተወሰኑት፣ በስማቸው ሳይሆን በልዩ ግዕ ሪጋቸው ብቻ ተወስተዋል:: የጽሑፉ ዓላማ ሰውን መውቀስ አይደለም:: ያንን የጨለማውን ገዥ ጨካኝ ሥርዓት፣ የአስከፊነቱንና የአስቃቂነቱን እንዲሁም የተሸናፊነቱን ገጽታ መግለጥ ግን የግድ ነው:: ይሁንና፣ እሱታችንና ጥረታችን፣ በዚያን ጊዜ የነበሩትን ባለ ሥልጣኖች ጨምሮ፣ ሰው ሁሉ ክርስቶስንና የወንጌሉን እውነት አውቆ፣ በንስሐና በእምነት ወደ መዳን ይደርስ

ዘንድ ነው:: አምላካችን በባለጸግነቱ የማራቸውንና በጸጋው ወደ ቤቱ ያመጣቸውንም ለማየት ችለናልና ከዚህ የበለጠ ምን እንሻለን?

እንግዲህ፣ ይህንን የሁነቶች ቅደም ተከተላዊ ማስታወሻ፣ በዚህ መልኩ፣ በትልቅ አክብሮት ለማቅረብ ተሞክሮአል:: ርዕሱም *በዚያን ጊዜ* የሚል ሆኖአል:: ስያሜው ከማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 24 ላይ የተወሰደ ነው:: በዚህ ምዕራፍ ላይ፣ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከዳግም ምጽዓቱ በፊት ደቀ መዛሙርት ግና ሊቀበሉት ስላላቸው መከራ ሲገልጽ፣ በተደጋጋሚ «በዚያን ጊዜ» የሚል ሐረግ ተጠቅሟል:: በዚህ ጽሑፍ ላይ ደግሞ *በዚያን ጊዜ* ያለፈውን ሁኔታ ለማስታወስ ሥራ ላይ ውሏል:: የክርስቶስ ዳግም ምጽዓት እውን እስኪሆን ድረስ ግን የ«በዚያን ጊዜ» ትንቢታዊ ገጽታ እንደ ተጠበቀ ይቀጥላል:: በዚያን ጊዜ፣ በእኛ ዘንድ የሆነው ነገር፣ ለዛሬና ለነገ የሚኖረው መልዕክት ምን ሊሆን እንደሚችልም እንባብያን በጽሑፉ ፍጻሜ ላይ የሚደርሱበት ይሆናል::

*ይህ ጽሑፍ ግን ዕኔ በትኩሱ መቅረብ ሲገባው ለምን ይህን ያህል ዘገየ?* የሚል ጥያቄ ይኖር ይሆናል:: እንደ ሰው ስናስበው መዘግየቱ ለሁላችንም ይሰማናል:: ዘግይቶም ቢሆን፣ በዚህ ጊዜ መቅረቡ ግን ምናልባት የእግዚአብሔር ፈቃድ ይሆናል ብለንም እናስባለን::

ክብር ሁሉ ለእግዚአብሔር ይሁን !

ተስፋዬ ጋቢሶ

2002 ዓ/ም

ሀዋሳ





# ምዕራፍ አንድ - ጅማሬው

## ከጨለማ ጋራ ብርሃን ሲዋጋ

***ብርሃንም በጨለማ ይበራል :: ጨለማም አላሸነፈውም( ዮሐ 1:4-5)::***

... ከጥቂት ቀናት በኋላ፣ ሚያዝያ 10 ቀን 1968 ዓ/ም በጸሎት ቤቱ ውስጥ በአምልኮ ላይ የነበሩ ምዕመናንና አዳዲስ ጎብኚዎች በድንገት ተከበቡ:: ከዚያም እንዲወጡና ተሰልፈው በከተማይቱ ዋናው መንገድ ላይ እንዲዞሩ ተገደዱ:: አስገዳጆቹ በወቅቱ የነበረው የቀበሌ አመራርና ወጣቶች ነበሩ:: የእምነት ጥላቻው በተግባር በታገዘ ጠንካራ ተቃውሞ ተገለጠ::

...በዕለቱ የነበረው ዙረት ...ሲያበቃ የተያዙትን ምዕመናንና አገልጋዮቹን ወደ ቀበሌ 08 ግቢ ወሰዷቸው:: በእጆቻቸውም የተገኙትን መጽሐፍ ቅዱሶች በመሰብሰብ ጋዝ ከርከፈከፉባቸው በኋላ አቃጠሏቸው:: ከዚያ በኋላ ጭስን «ታጠኑት» አሏቸው!...

...በ1970 ዓ/ም አጋማሽ ላይም በምዕመናን ላይ ቀላል የማይባል ስደት ደርሷል:: ...በዚህ ጊዜ አንዳንድ እህቶቻችን መሬት ላይ ተጥለው እንደ እባብ ጭንቅላታቸውን ተቀጥቅጠዋል:: ሌሎች ደግሞ ከደረሰባቸው አሰቃቂ ድብደባ የተነሣ ራሳቸውን እየሳቱ ለሕክምና እርዳታ ሆስፒታል ተወስደዋል:: በተጨማሪም፣ ከተፈሪ ኬላ እንደኔ አለማየሁ መንግሥቱ ያሉ በሰደፍ እየተፈነከቱ ደማቸው የታሰሩበትን ክፍል ወለል አጥለቅልቆታል::

... ከፖሊስ ጣቢያው እንደወጣን፣ በአውራው ጎዳና ላይ ፊታችንን ወደ ምዕራብ አድርገን ጥቂት እንደተራመድን፣ *ሶምሶማ ሩጫ ጀምሩ!* የሚል ትዕዛዝ ተሰጠን:: መሮጥ ጀመርን:: ጥቂት እንደ ሮጥን አልማዝ አስም ተቀስቅሶ አፈናትና ወደ ኋላ ቀረች:: ሙሉ አመቤትም ብትሆን የእኛን ያህል መሮጥ ስላልቻለች ዘወር ብዬ ሳይ ተራርቀን አየሁ:: ፍጥነቴን ለመቀነስ ሞከርሁ:: ወንዶቹን እያጣደፉ አስቸገሩን:: እንደ ምንም ኳስ ሜዳ ደረስን:: ...ትዕዛዙም *ሩጥ! ተመለስ! ተኛ! ተንከባለል! ተነሥ! እምራ ጉብ ጉብ ዝለል!* በሚል እየተፈራረቀ ተፋፋመ:: ይህ ሁሉ ትዕዛዝ ከዱላ፣ ከጉማሬ አለንጋና ከእርግጫ ጋር ያጣድፈን ገባ::

... ስፖርቱ - ወታደራዊ ቅጣቱ ቢባል ይሻላል - ብዙ ታሪክ ነበረው:: ...በስፖርት ስም ማንገላታቱ፣ እየነረፉ፣ እየደበደቡና እየረገጡ ማሰቃየት፣ እንዲሁም በጭቃ ላይ እያንከባለሉ መጫወት፣ ሁሉም ጋ የተደረገ ሲሆን ለየት የሚሉ ጥቂት ድርጊቶችም አልጠፉም:: በቀበሌ 01 ለየት የሚለው ደግሞ፣ ሌሊት ሌሊት ወደ ወንዝ ወስዶ በቀዝቃዛ ውኃ ውስጥ መንክርና ከዚያም አውጥቶ በአቧራ እንዲለወሱ ማድረግ ነበር:: እነ ከበደ አርጋው፣ እየለ አበራ፣ ማርታና ሐና አሰፋ የሚባሉ እህትማማች የዚህ ጽዋ ተካፋዮች ነበሩ::

.... በቀበሌ 05 የነበሩትን ግን ለ12 ቀናት ያህል አልፍተዋቸዋል:: ከሌሎቹ ሥፍራዎች ይልቅ መከራው ተጠናክሮ የተራዘመው እነርሱ ጋ ነበር ማለት ይቻላል:: ጫካ እያወረዱ በየገደሉ ላይ ቁልቁል እያንከባለሉአቸው ነበር የተጫወቱባቸው:: ከዚህ ሁሉ ጋር ዱላውና እርግጫው ርኅራኄ የማይታይበትና

ፋታ የማይሰጥ ነበር:: ከኃይሉ በቀለ ሌላ ምንትዋብ አረሩ ከድብደባ ብዛት የተነካ ራስዋን ስታ ለታንሬ አለደጊንጭ ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር:: ማርታና ወርቅነሽም ከቤቱ ጭንዛሬና አስቀቂነት የተነካ ቁስቶቻቸውን የተመኘበት ተገ እንደ ነበረ ይናገራሉ::

*——— የተባሉ አባቶቱ የማይፈልገውን አትዋጣ ሲያስቆቱ በመገኘታቸው ቢ...እስክ በቁጥጥር ሥር ከዋሉ በኋላ የታሠሩት በፋ ሆና እንዲፈቱ ስለ ተወሰነ ተለቀዋል::*

የጨለማው ገዥ ዲያብሎስ፣ በሕይወታችንና በግርዝብት አዛዢ የበራውን የክርስቶስን ብርሃን ለማስወገድ፣ ያደረገው ብርቱ ትግልና ሽንፈት በጨረፍታ ሲገለጽ ይህን ይመስላል::

*ከጨለማ ጋራ ብርሃን ሲዋጋ*
*ብርሃን ለዘለዓለም ፍጹም ድል ነሣ*
*ያ ሞት ተደምሮ ድል ነሣ ሕይወት*
*ተስፋችን በረታ ለማጽናት እምነት*
*እናንተ ዛሬንተኞች ከልብ ተቀኙ*
*ከሞት አዳነን በቸርነቱ*
*ሲኖር ከእኛ ጋራ ሃሌሉያ!*

## አጀማመር በይርጋ ዓለም

የይርጋ ዓለም ከተማ፣ ከሀዋሳ ወደ ሀረና ሞያሌ በሚያመራው መንገድ ላይ፣ ከአቦስቶ ወደ ግራ ገባ በማለት የምትገኝ መለስተኛ ከተማ ናት:: ርቀትዋ ከሀዋሳ ወደ 48 ኪ.ሜ. ገደማ ይሆናል:: ከተማይቱ፣ በግራና በቀኝ ጊዳሞ ወይማ በሚባሉና በገደላማ ሥፍራ በሚፈሱ ጅረቶች መሐል ትገኛለች::

ከተማይቱን የቆረቆሯትና ስም ያወጡላት ራስ ደስታ ዳምጠው ነበሩ ይባላል:: ቦታው አለቃ፣ ሬቀባና ገርቢቾ የሚባሉ ጎሳዎች ሲጋጩበት የቆየ እንደነበረ ይነገራል:: ወቅቱ፣ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት የሚካሄድበት ነበርና ራስ ደስታ ሁሉቱንም፣ የዓለሙንና የአካባቢውን ግጭቶች አጣምሮ በሚያስታውስ መልኩ ከተማይቱን ይርጋ ዓለም በማለት ሰየሚት ይባላል::

በስድስተኛ ምሥራቅ በኩል፣ በሰውየው ስም ሲጠራ ቆይቶ በኋላ መጠሪያው የተቀየረ፣ የተሰም ት/ቤት አሁንም አለ:: ከተማይቱ በዘመንዋ ከዛሬይቱ ሀዋሳ የማይተናነስ ታዋቂነት የነበራት በትሆን ይሆን ታዋቂነት የለባት በዋናነት እምስት ነገሮች እንደሆኑ ይታሰባል:: እነርሱም የቀድሞው ጠቅላይ ግዛት ዋና ከተማ መሆንዋ፣ በከተማው መግቢያ ላይ የሚገኘውና በኖርዌጂያን ሚሲዮኖች ይመራ የነበረው ትልቅ ሆስፒታል፣ ከሆስፒታሉ ፊለፊት የሚገኘው የፍል ውኃ፣ በአካባቢው ብቸኛ የነበረው ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትና ጠንካራው የተማሪዎች የፖለቲካ ንቅናቄ ናቸው::

ቸሩ ኢቦሳ ሊበንስ ጋን ጸሐፊ ከፍል፤ መዝሙር በዕዝራ ለአምላክ፤ የተጠቀሰ አተማዎች ... አዲስ አበባ፤ 1975 ዓ/ም ገጽ 26::





ሕዝቡ በአመለኝ፣ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ተከታይ እንደሆነ የሚያመለክቱ ሦስት ቤተ ክርስቲያኖች - የአማኑኤል ፣ የሚካኤልና የማርያም - በከተማይቱ አማካይ ርቀቶች ላይ ተተክለው ይታያሉ:: እነዚህ ነገሮች፣ ማለትም ጥንታዊነቷ፣ የፖለቲካ፣ የጤና፣ የትምህርትና የሃይማኖት ገጽታ ሙሉ ተደማምረው ለከተማይቱ ወትታዊ ታዋቂነት እንደ ሰጧት ለመገንዘብ ይቻላል:: እኛም በዚህችው ከተማ ውስጥ ተገኝተን የእምነትን ፈተና ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ድንቅ ጸጋና ማዳኑን አየን::

በ1964 ዓ/ም፣ እኔ ለትምህርት ጉዳይ ከአሰላ ወንዶ ወደዚህች ከተማ ስመጣ በመጀመሪያ ያገኘኋትና የተገለገልሁባት የይርጋ ዓለም ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ ነበረች:: ወላጆቼ ከዚያ በፊትም ሆነ በኋላ፣ የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን አባላት ስለሆኑ፣ በእነርሱ አማካይነት እኔም ክርስቶስን ከልጅነቴ ጀምሮ የማወቅ ዕድል አግኝቼአለሁ:: ቢሆንም ትልቁ የሆነና መንፈሳዊ የሕይወት ለውጥ የተለማመድሁት ከ1965 ዓ/ም ጀምሮ ነው:: ይህ የሆነው በዚያው ዓመት በይርጋ ዓለም ከተማ ውስጥ ባገኘኋቸው፣ በተለወጡና በመንፈስ ቅዱስ ሥራ ላይ አጽንዖት በሚሰጡ ወንድሞችና እህቶች የቃልና የሕይወት ምስክርነት ሰበብ ነበር::

በዚያን ወቅት፣ በተለምዶ ‹‹ሐረሩ›› እየተባለ በሚጠራው የከተማይቱ ምሥራቃዊ ክፍል አቶ አዲሱ አምደና ወ/ት ጽጌ ኢሳይያስ የሚባሉ የራስ ደስታ ት/ቤት መምሕራን፣ የዚሁ ት/ቤት ተማሪ የነበረች እህት ፋንቱ ተስፋዬ፣ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች የነበሩ እህት ፈንታዬ ዓለሙና ወንድም አለማየሁ ጦና ነበሩ::

‹‹ስድተኛ›› ሰፈር ይባል በነበረው የከተማይቱ ክፍል ውስጥ ደግሞ፣ በወቅቱ ያወቅኋቸው በመካነ ኢየሱስ ት/ቤት በመምህርነት ይሠራ የነበረና አሁን ወንጌላዊ የሆነው አንዷለ ገ/መስቀል፣ በኋላ ደብረ ዘይት ከተማ ቆይቶ ወደ ጌታ የተሰበሰበው በቀለ ሀብቴ፣ እንዲሁም አበበ ፋንታና እምሩ የሚባሉ ተማሪ ወንድሞች ይኖሩ ነበር::

በአሩዳ ይኖር የነበረው መምህር አዲሱ ወደ ከተማይቱ *አዲስ ኃይማኖት* እመጣ፣ *ጴንጤ ሆነ*፣ ተብሎ በተበሳጩ ሕዝብ - በዕድር - ተወግዞ፣ ቤቱ በድንጋይ እየተደበደበ መከራ ሲያይ ቆይቶአል:: በዚህም ባለቤቱ ወ/ሮ አሐዶ ቀንና ሌሊቻቸው በምን ያህል መሳቀቅ እንዳሳለፉ መገመት ይቻላል::ይሁንና፣ በየምሽቱ እየተደበቁ ቤቱ ለሚገቡ ሁሉ አቶ አዲሱ መጽሐፍ ቅዱስን እየገለጠ ሳይመሰክርና ሳይጸልይ አያሰናብትም ነበር:: እኔንም እዚያው ቤት አለማየሁ ጦና በምሽት ወሰደኝ፤ በመንፈስና በልሳን መጸለይ የሚባለውን ጉዳይ፣ አንድ ከሌላ ቤት የመጣ እንግዳ ሰው፣ ወንጌላዊ አርጋው ንዳ፣ ቃለ እግዚአብሔርን ከነገሩን በኋላ ሲጸልዩበት፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ለመመልከት በቅቻለሁ::

ይሁንና፣ እነዚህ ከላይ ከፍ ብሎ የተጠቀሱት ጥቂቶች፣ መደበኛ ባልሆነ መንገድም ቢሆን፣ እርስ በርስ እየተበተቡ የሚጠያየቁና ጠለቅ ያለ ፍቅር

ያሳቸው ወገኖች ነበሩ:: ይህም ፍቅራቸው፣ ቁም ነገረኝነታቸው፣ **መንፈሳዊ ኃይልና** ጸጋን የተሞላው ሕይወታቸው፣ የራሴን ጨምሮ የብዙዎቻችንን **የሕይወት** አቋም በጸሎት ለማስመርመርና ለማስለወጥ የራሱን **ድርሻ አበርክቷል**::

በአራዳና በስደተኛ የምንኖርና በአብዛኛው ተማሪዎች የነበርን ወገኖችም፣ በሳምንት አንድ ቀን ረቡዕ ረቡዕ፣ ከቀኑ አሥር ሰዓት ላይ፣ የአምልኮ ፕሮግራም ጀመርን:: ጊዜው 1966 ዓ/ም ነበር:: የፕሮግራሙ ይዘት እርስ በርስ ከመጽናናት ያለፈ አልነበረም:: ቀደም ሲል ስደተኛ አካባቢ የነበሩት ጥቂት ወገኖች የ«ኢየሱስ ብቻ» እምነት ከነበራቸው ጋር ያመልኩ ነበር:: የእኛ ፕሮግራም የተጀመረው ያኛው የአምልኮ ግንኙነት በእምነት አቋም ልዩነት ምክንያት በ1965 ዓ.ም ላይ ከተቋረጠ በኋላ ነው::

ፕሮግራሙን የጀመርነው፣ ከአራዳ ወደ ሰኮ መሄጃ መንገድ ላይ ከአቶ ካሣ ዶጊሶ በተከራየናት ጠባብ ክፍል ውስጥ ነበር:: ክፍልዋ ባለ አንድ ሰው የሆነ ሦስት ታጣፊ አልጋ የምታዘረጋ ነበረች:: በዚያችም ክፍል ውስጥ የምናድር አራት ተማሪዎች ብቻ ነበርን - አለማየሁ ጦና፣ አራጋ አጋሞ፣ በራሳ ባንቡሮና እኔ ::

እግዚአብሔርም ፕሮግራማችንን ይበልጥ እየባረከው መጣ:: ከዚህም የተነሣ ሌሎች ተጨማሪ ወገኖች መምጣት ስለ ጀመሩ ቁጥራችን በረከተ:: መጣበብና መቀመጫ ማጣትም ተፈጠረ:: ቀድሞም ቢሆን እንቀመጥ የነበረው በአልጋዎቹና በሳጥኖች ላይ ነበር:: ይህም ሲሆን ከጎን የነበረችውን የወንድም ኃይለ ሚካኤል አባተን ጠባብ ክፍል የመሃል ግድግዳ በፈቃድ አስፈርሰን መሰብሰቢያችንን ማስፋት ነበረብን:: ሆኖም የተጨማሪ መቀመጫዎች ጥያቄ መቀጠሉ አልቀረም:: በዚህ ሁኔታ ላይ ሳለን፣ ከዕለታት አንድ ቀን፣ በድንገት፣ አነሳሱ ከቀድሞው የአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን የሆነና በጊዜው ወንጌላዊ የነበረ፣ የአሁኑ ፓስተር ተሾመ ወርቁ ወደ ከተማችን መጣ:: አለማየሁ ጦና በድንገት ከተማ ውስጥ መንገድ ላይ አግኝቶት ነበር ያመጣው:: ጊዜው 1966 ዓ/ም የካቲት ወር እንደ ነበረ ፓስተር ተሾመ ያስታውሳል:: በዚህ ወቅት ላይ እርሱም በረቡዕ ስብሰባችን ላይ ተገኝቶ በእግዚአብሔር ቃል አገለገለን:: በሌሎች ጊዜያትም እየተመላለሰ ሲያገኘን ቆየ:: ሲመጣም ያርፍ የነበረው በአቶ ተክስተ ተክሉ ቤት ነበር::

አቶ ተክስተ ተክሉ (ዛሬ ዶክተር ሆኖአል)፣ በወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ የመምህራን ማሰልጠኛ በመምህርነት፣ በኋላም በሆስቴል ዳይሬክተርነት የሠራ ሲሆን፣ በከተማይቱ ውስጥ እኛን በሚመስሉ ወጣቶች መኻል ይካሄድ የነበረውን መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ይደግፍ የነበረና ለእግዚአብሔር መንግሥት የሚሆን ሰፊ ልብ የነበረው ወንድማችን ነበር:: የእርሱም ሩቅ ተመልካችነቱ፣ ለወንጌል የነበረው ቅንዓቱና ጥበብን የተሞላ ምክሩ፣ እንዲሁም ወንድማዊ ፍቅሩ በሕይወታችን ላይ አሳድሮት ያለፈውን በጎ ተጽዕኖ የምናውቀው እናውቀዋለን:: በ1966 ዓ/ም በቀድሞ አጠራሩ አርጌ ማሺን ግቢ በሚባለው





ቦታ፣ በየእሁዱ ከሰዓት በኋላ በቤቱ ውስጥ ይካሄድ በነበረው **ሁሉን አቀፍ የመነቃቂያ ፕሮግራምም** በወቅቱ የነበርን በእጅጉ ተጠቅመንበታል::

በዚህ ሁኔታ ላይ ሳለን በ1967 ዓ/ም ላይ ለብዙዎቻችን አዲስ የነበረ ሃሳብ ስደተ
ኛ ሠፈር ከነበሩት ወንድሞች አንዱ በነበረው በቦጋለ ዱከሌ በኩል መጣ::
ሃሳቡም ወደ ጌታ የሚመጡ፣ ማለትም በክርስቶስ የሚያምኑ ሰዎች ቁጥር
እየጨመረ ስለ ሄደ እነዚህን ሰዎች እያስተማረና እየመከረ የሚያጠናክር
ወንጌላዊ ያስፈልገናል የሚል ነበር:: በዚህም ጉዳይ ላይ መጸለይ ጀመርን::
ፓስተር ተሾመም እኛን መጎብኘቱ እንደቀጠለ ነበር:: ለወደፊትም ከእኛ ጋር
ለመሥራት እንደሚፈልግ ገለጸልን:: የጸሎት ቤት ፈልገን እንድንከራይም ነገ
ረን::

በዚህ መሐል ጥቅምት ወር 1967 ዓ/ም ላይ 12 የሚሆኑ ወገኖችን ፓስተር ተሾመ በውኃ ሲያጠምቅ በደርጋ ዓለም ለምትገኝ የሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን የአጥቢያ መሠረት ተጣለ:: ወጥ የሆነ የቤተ እምነት ቅርጽ ሳይኖረው በሕብረትነት ብቻ ሲካሄድ የቆየው አገልግሎትም ከዚህ በኋላ የሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ እምነት አቅጣጫ እየያዘ መጣ::

ሲፈለግ የነበረው የጸሎት ቤትም ከሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ጀርባ በኩል ተገኘና
በ1967 ዓ/ም መጋቢት ወር ላይ በኪራይ ተያዘ:: ቤቱ ከእጃችን ገብቶ ፓስተ
ር ተሾመ በምስጋና ጸሎት ሲረከበው *የዘሩባቤል እጆች ይህን ቤት መሠረቱ፣*
*የእርሱም እጆች ይፈጽሙታል* የሚለውን ቃል ከዘካርያስ 4:9 ላይ አንብቦ
ነበር:: ፓስተር ተሾመም የጸሎት ቤቱን አንድ ክፍል ይዞ ያድርበት ጀመር::

ለመጀመሪያም ጊዜ በጸሎት ቤትነት በያዝነው በዚህ የኪራይ ቤት ውስጥ የወንጌል ሥራ በደሩ ቀጠለ:: አሁን እንገዲህ የጸሎት ቤቱ ሁለት ሆነ ማለት ነው:: አራዳ ላይ የእኛ የነበረችው ጠባብዋ ክፍልም በባለቤቱ ፈቃድ ጎንዋ በስተ ቀኝ በኩል ተከፍቶ እንድትሰፋ ተደረገና ፕሮግራሙ ቀጠለ:: አዲሱ ጸሎት ቤት ግን ሻል ያለ ስፋት ያለው ሆኖ የራሱ ግቢ ነበረው:: ስለዚህም ዋናው የእሁድ ቤት ፕሮግራምና የማማከር ሥራዎች እዚህኛው ላይ ይካሄዱ ነበር:: ይህን ቤት ትርፍ የከተማ ቤትና መሬት የውርስ አዋጅ በታወጀ ማግሥት ማለትም በ1968 ዓ/ም መስከረም ወር ላይ ለአከራይዋ መመለሱ የግድ ሆነና ተለቀቀ::

## በተቃውሞ መሐል

ሥራው ግን እያደገና እየሰፋ ሄደ:: ተቃውሞና ስደትም አልጠፋም:: በተለይም 1968 ዓ/ም የጸሎት ቤቶቹ ጣሪያዎች በፕሮግራም ሰዓት የድንጋይ ውርወራ የሚያዘወትራቸው፣ አማኝ ተማሪዎች በትምህርት ቤታቸው ቅጥር ግቢ ውስጥ የሚያታወኩ የሚደበደቡበትና በየመኖሪያ ቤታቸውም በተቃዋሚ ሰዎች እየታወኩ እንቅልፋቸውን የሚያጡበት ዓመት ሆኖ ተጋመሰ:: በመጨረሻም፣ በ1968 ዓ/ም

ሚያዝያ ወር ላይ፣ የአራዳው ጸሎት ቤት በወቅቱ በነበረው የቀበሌው ጽሕፈት ቤት ትዕዛዝ ተዘጋ።



የአራዳው ፀሎት ቤት -ከመዘጋቱ በፊት



*እነዚህ የፀሎት ቤቱ የመጀመሪያ መዘምራን ሲሆኑ አብሯቸው ቆሞ የሚታየው ከበስተኋላ ከግራ ወደ ቀኝ ሁለተኛው ፓ/ር ተሾመ ወርቁ ነው።*

የአራዳው ጸሎት ቤት ከመዘጋቱ በፊት በሚያዚያ ወር ላይ ፓስተር ጻድቁ አብዶ (ያኔ ወንጌላዊ ነበር) ከባሌ ጎባ ተጋብዞ በመምጣት ያገለገለበት የሦስት





ቀን መንፈሳዊ ስብሰባ (ኮንፈረንስ) ለመጀመሪያ ጊዜ ተደርጎበት ነበር። በዚህ ጊዜ እኔ *ለዕድገት በሕብረት የዕዉቀትና የሥራ ዘመቻ* ወደ ሻኪሶና ክብረ መንግሥት ከሄድሁበት ለጥቂት ቀናት ተመርቼ በመምጣት ለዘማሪና መዘምራንን በጊታር በማጀብ አገልግዬአለሁ። ከዚያም በኋላ ተመልሼ ስለ ሄድሁ ቀጣዩን ሁናቴ በወሬ ደረጃ ብቻ ነበር የሰማሁት።

ከጥቂት ቀናት በኋላ፣ ሚያዝያ 10 ቀን 1968 ዓ/ም በጸሎት ቤቱ ውስጥ በአምልኮ ላይ የነበሩ ምዕመናንና አዳዲስ ጎብኚዎች በድንገት ተከበቡ። ከዚያም እንዲወጡና ተሠልፈው በከተማይቱ ዋናው መንገድ ላይ እንዲሄዱ ተገደዱ። አስገዳጆቹ በወቅቱ የነበረው የቀበሌ አመራርና ወጣቶች ነበሩ። የእምነት ጥላቻው በተግባር በታገዘ ጠንካራ ተቃውሞ ተገለጠ።

በዚህ ታሪካዊ ትዕይንት ላይ *የሙሉ ወንጌል አማኞች ጸሎት ቤት* የሚል ትልቅ ጽሑፍ ያለበት የማስታወቂያ ሰሌዳም ከተተከለበት የጸሎት ቤት ደጃፍ ላይ ተነቅሎና በግራ በቀኝ በምዕመናን ተይዞ ከተማይቱን ዞሯል። በከተማይቱ ነዋሪዎች እየታየና እየተነበበ ማለት ነው! በዚሁ ዕለት አዟሪዎቹ የሚያሰሙት አጭር ዘፈንም ነበራቸው *ይዘን መጣን ጴንጤውን ይዘን መጣን አሃሃ... ተሸከመ ባንክ ቤት ተሸከመ አሃሃ!* የሚል። «ተሸከመ ባንክ ቤት» ያሉት በቅርቡ ጌታ ክርስቶስን አምኖ የነበረውንና በወቅቱ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የይርጋ ዓለም ቅርንጫፍ ሥራ አስኪያጅ የነበረውን፣ አቶ በቀለ ወ/ኪዳንን ነበር። የያኔው አዲስ አማኝ፣ አቶ በቀለ፣ በአሁኑ ጊዜ አዲስ አበባ ላይ በቀጣና ሁለት የሙሉ ወንጌል አማኞች አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በመጋቢነት ያገለግላል።

በዕለቱ የነበረው ዙረትና ዘፈኑ ሲያበቃ የተያዙትን ምዕመናንና አገልጋዮች ወደ ቀበሌ 08 ግቢ ወሰዷቸው። በእጆቻቸውም የተገኙትን መጽሐፍ ቅዱሶች በመሰብሰብ ጋዝ ካርከፈከፉባቸው በኋላ አቃጠሏቸው። ከዚያ በኋላ ጭሱን «ታጠኑት» አሏቸው ! የባንክ ቤቱንም ሥራ አስኪያጅ፣ አቶ በቀለን፣ በገንዘብ አከፋፋይነት ስለ ጠረጠሩት ኪሱ ይፈተሽ አሉና ሲፈተሽ ስድሳ ሳንቲም አገኙበት! ፈታሹ ወጣት የባንክ ቅርንጫፍ ሥራ አስኪያጅ ከሆነ ሰው ኪስ ውስጥ የተገኘው ገንዘብ ስድሳ ሳንቲም ብቻ በመሆኑ በአቶ በቀለ ላይ «እንትፍ» ብሎ ተፋበትና፣ «እንደ አንተ ካለ ሰው ኪስ እንዴት ስድሳ ሳንቲም ብቻ ይገኛል?» እንዳለው ፓስተር በቀለ ወ/ኪዳን አጫውቶኛል።

ይሁንና፣ ከፍ ብሎ ከላይ በተገለጸው ሁኔታ ሁሉም በአንድ ላይ እስከ ቀኑ **10:00** ሰዓት እንዲቆዩ ተደረገና የሚበዙቱ እዚያው ተለቀቁ። ከመካከላቸው ሰባት የሚሆኑት ደግሞ ወደ ፖሊስ መምሪያ ከተወሰዱ በኋላ በዕለቱ ተፈቱ ።

**የወንጌል** ጠላት የሆነው ሰይጣን የጌታን ሥራ ለማስተጓጎል አልቻለም። ስለዚህም፣ ሰዎች በክርስቶስ እያመኑ ይድኑና የዳኑትም ይጸኑ ነበር። ምዕ መናኑ በየቤታቸው ጌታን በታማኝነት ማምለካቸውን ቀጠሉ። በ1969 ዓ/ም በድሮው አርጌ ምሺን ግቢ ውስጥ በርከት ያልን ተማሪዎች ከ05 ቀበሌ ተ ከራይተን በነበረው ሰፋ ያለ ክፍል ውስጥም ቋሚ የአምልኮ ፕሮግራም ሊካሄድ

**ጀመረ**:: ክፍሉ ግን እንደ ተለመደው በተሰብሳቢ ሰው መጨናነቁ አልቀረም::

***የነበረው ሁኔታ አመቺ ባይሆንም፣*** ይህ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የሚበዙበት ***የምዕመናን ጉባዔ፣*** የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አቅጣጫ እንዲይዝ ጥረት ተ ደርጓል:: ይኸውም በፓስተር፣ ማለትም በቀድሞው ወንጌላዊ በተሾመ ወርቁ ***የሚመሩ ዲያቆናትን*** *መርጦ* በመሾም ነበር:: *ከመጀመሪያዎቹም ዲያቆናት* ***መካከል መምህር*** አዲሱ አምዴ፣ ቦጋለ ዱከሌ፣ ሐይሉ በቀለ፣ አስቻለው ከበደና እኔም ተጠቃሾች ነን::

*ቀደም ሲል* በ1968 ዓ/ም ተቋቁመው የነበሩ ጥቂት መዘምራንም በቀበሌ 05 ውስጥ፣ ከጤና ጣቢያው ፊት ለፊት፣ ፓስተር ተሾመ ወርቁ ተከራይቷት በነበ ረችው ጠባብ ቤት ውስጥ፣ በሹክሹክታ እያጠኑ እስከ 1969 ዓ/ም ድረስ በቤት የአምልኮ ፕሮግራሞች ላይ ማገልገላቸውን ቀጠሉ:: ጌታም አዳዲስ የዝማሬ መልእክቶችን ከነ-ዜማቸው ይሰጣቸው ጀመር:: ለምሳሌ ያህል *ወደ አንተ መጥተናል፣ ምሕረቱ አያልቅም፣ ድል ለማድረግ ወጣ* ና የመሳሰሉት ዝማሬ ዎች በዚህ ወቅት የተገኙ ናቸው::

በእርግጥ፣1969 ዓ/ም የጣፋጭ አምልኮና የድል ዓመት ሆኖልናል:: ጌታ በአስደናቂ መንገድ፣ ትልቅ የአምልኮ ቤት፣ ከትልቅ ግቢ ጋር፣ በከተማው አማካይ ቦታ፣ በከፍተኛ አንድ ቀበሌ 05 ውስጥ ለመከራየት አበቃን:: ቤቱ በቀበሌ ከመወረሱ በፊት የጠበቃው የአቶ ልዑል ለገድ ቤት ነበር ይባላል:: የዚህ ቤት መገኘት፣ ከፓስተር ተሾመ ፣መታሠርና መፈታት ጋር ተያይዟል:: ነገሩም እንዲህ ነበር፡- በቀድሞው አሮጌ ሚሺን ግቢ በነበረችን የኪራይ ቤት ውስጥ ሐሙስ ዕለት የከተማይቱ ምዕመናን ለአምልኮ ተሰብሰበናል:: ፓስተር ጻድቁ በእንግድነት በመጣበት ከዕንባቆም ምዕራፍ 3 ላይ እግዚአብሔርን በተስፋ ስለ መጠባበቅ እየሰበከ ቆሞአል:: በመሐሉ፣በድንገት፣ አንድ የቀበሌ ሚሊሺያ ወታደር ወደ ተሰበሰብንበት ክፍል ገባ:: ስለ ሚሊሺያው የማስታውሰው አንድ ነገር ብቻ ነው:: ጠብ መንጃ ይዟል!!! ከውጭም ሌላ ሚሊሺያ ቆሞአል:: ቀጣዩ፣*ሁላችሁም ውጡ፤ ቀበሌ ስጥያቄ ትፈለጋላችሁ* የሚል ትዕዛዝ ሆነ:: ከ80 የማናንስ ነበርን:: አሰልፎ ሲወስደን፣ ትምህርታችን ሲደናቀፍ፣ ስንደበደብ ወይም ከዚያም የከፋ ሲሆንብን፣ በዓይነ ሕሊናዬ ለአፍታ ታየኝ:: ፓስተር ተሾመ ብድግ አሉ:: *ኃላፊው፣ይህን ስብሰባ የጠራሁ እኔ ነኝ:: ስጥያቄ ከፈለጋችሁ እኔን ልትወስዱኝ ትችላላችሁ፤ ተሰብሳቢዎቹ የሚሄዱበት ምክንያት የለም* በማለት አጥብቆ ተከራከረ:: እርሱን ይዘውት ሄዱ:: በመጀመሪያ ወደ ቀበሌ፤ ከዚያም ወደ ፖሊስ መምሪያ:: እኛ ትንሽ ተንፈስ አልን:: የጀመርነውንም የአምልኮ ፕሮግራም በሥርዓት አጠናቀቅን::

የፓስተር ተሾመ ጉዳይ ብዙም ሳይቆይ በወቅቱ የአውራጃው አስተዳዳሪ ወደ ነበሩት አቶ ወልደ አማኑኤል ዱባለ ደረሰ:: ፓስተር ተሾመም ተለቀቀና በአካል ወደ አስተዳዳሪው ቀርቦ የነበረውን ሁኔታ አመለከተ:: በመቀጠል የከተማይቱ ቀበሌዎች ሹማምት በእርሳቸው ሰብሳቢነት' ***ጴንጤዎችም*** *እንደ ሌላው ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅት በየቤቱ በህቡዕ ይሰበሰባሉና ተለይተው እንዲታወቁ ለምን አንድ መሰብሰቢያ አይሰጣቸውም ?* የሚል ሃሳብ ማንሸራሸራቸውን ሰማን::





እርሳቸውም *ለቁጥጥር እንዲያመች ቤት ይሰጣቸው* የሚል ውሳኔና ማዘዣ ሰጡ:: ከዚህ በኋላ ቤቱን ስመከራየት ቀበሌውን አመለከትን:: ምላሹም አዎንታዊ ሆነ:: ይህ የሆነው በግንቦት ወር ላይ ነበር::

በዚያ ቤት ውስጥ 1970 ዓ/ምን ተገለገልንበት:: በጥር ወር አቶ በቀለ ወልደ ኪዳን፣ወንጌላዊ ደሳለኝ ደምሴና ፓስተር ተስፋ ወርቅነህ ከአዲስ አበባ፣ በሰኔ ወር ላይ ደግሞ ወንጌላዊ (አሁን ዶክተር ሆኖአል) ዓለማየሁ መኮንን ከባሌ ጎባ ለትምህርት ያገለገሉባቸው ሁለት የማነቃቂያ ኮንፈረንሶችንም በማካሔድ ተ ጽናናንበት::



*ተለቅ የሚለው የቀበሌ 05 ቱ ፀሎት ቤትና በወቅቱ የነበሩ ምዕመናን (1970 ዓ/ም)*

በዚህ በ1970 ዓ/ም አጋማሽ ላይም በምዕመናን ላይ ቀላል የማይባል ስደት ደርሶአል:: ለአገልግሎት ጉዳይ ወደ አዲስ አበባ በመውጣቱ ምክንያት ከፓስተ ር ተሾመ በስተቀር ሳይታሠር የቀረ የቤተ ክርስቲያኒቱ አባል አልነበረም ማለት ይቻላል:: በዚህ ወቅት ይጠየቅ የነበረውን የመራገሚያ መፈክር ካላስማችሁ በሚል ሰበብና ሽፋን ብዙዎች በየቀበሌው ታጎርን:: ሲጎበኘን ከባሌ መጥቶ የነበረው ወንጌላዊ በለጠ ኃብተ ጊዮርጊስም ይህንን እስር አብሮን የመካፈል ዕጣ ደርሶት ነበር::

በዚህ ጊዜ አንዳንድ እህቶቻችን መሬት ላይ ተጥለው እንደ እባብ ጭንቅላታቸውን ተቀጥቅጠዋል:: ይህ ከደረሰባቸው መካከል፣ ውድነሽ ዓለሙ ከህገረ ሰላም፣ትገኛለች:: ሌሎች ደግሞ ከደረሰባቸው አሰቃቂ ድብደባ የተነሣ ራሳቸውን እየሳቱ ለሕክምና እርዳታ ሆስፒታል ተወስደዋል:: ከእነዚህ መሐል፣ ሰብለ ወንጌል ገደቡ ከይርጋ ዓለም፣ ሁለቱ እህትማማች ጀማነሽና አልማዝ ልሣነ ወርቅ ከህገረ ሰላም፣እንዲሁም እህት አገኘሁ ኮያሞ ከዱራሜ ተጠቃሽ ናቸው:: በወቅቱ፣ ጀማነሽ በተለይ «ወፌ ይላላ» በሚባለው ግርፍ፣ ውስጥ እግርዋን ተገርፋ ለተወሰኑ ቀናት ተሰቃይታ እንደ ነበረ ትናገራለች::

በተጨማሪም፣ ከተፈሪ ኬላ እንደነ አስማየሁ መንግሥቱ ያሉ በሰደፍ እየተ ፈነከቱ ደማቸው የታሰሩበትን ክፍል ወለል አጥለቅልቆታል:: ይህ ሁሉ የሆነው በመፈክር መልክ መራገም ከእግዚአብሔር ቃል አንጻር ለህሊናችን ከበደን፥ ጌታን በባረክንበት አፋ ሰውን እንዴት አድርገን እንርገም? ከአንድ አፋ በረከትም መርገምም እንዴት አድርገን እናፍልቅ? ከዚህ ይልቅ ክፋውን በተግባር መቃወሙ ይቀለናል ስላሉ እንጂ ማንም ቢሆን የተረገሙት ሥርዓቶች ደጋፊ አልነበረም:: ለሁሉም ወገን ይህ የተገለጠ ነበር:: ሽፋኑ መፈክር ሆነ እንጂ መሠረታዊው ችግርስ በአምላክ የለሽ ሰዮተ ዓለም ዘመን እግዚአብሔር በሚባል ፈጣሪ እምኖ መገኘቱ ነበር! ... በግዳጅም ቢሆን እንዲባል ከተደረገ በኋላ ቀጣዩ ተግባር ፈጣሪን የማስካድ - «ዳሩን ከደፈሩ በኋላ መሐሉን ዳር» የማድረግ - ጥረት ሲሆን በተደጋጋሚ ታይቷል::

ያንን የመከራ ጊዜ ግን እግዚአብሔር አሳጠረው:: በየቀበሌውም የነበረው እስራትና፣ እንግልት በሁለት ሳምንት ጊዜ ውስጥ አበቃ:: ለዚህም ምክንያቱ፣ እግዚአብሔር አቶ ሲዩፉ ተክለ ሃይማኖት የሚባሉትን ክርስቲያን ወንድም ከአዲስ አበባ የሕዝብ ደኅንነት መ/ቤት አስነሥቶ ስለ ተጠቀመባቸው እንደሆነም ይታወሳል:: አቶ ሰይፉም የክፍለ ሀገሩን ባለ ሥልጣኖች በእስር ላይ ስለነበርነው ምዕመናን በማነጋገር ጉዳያችንን በውል ለማስረዳት ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል::

የታሰርነውም ምዕመናን በወቅቱ ከየቀበሌው እስር ቤት ከወጣን በኋላ መፈክር በማስማት - አለማስማት ምክንያት የተከሰተውን መሰስተኛ ልዩነት በውይይትና በመቀባበል አስተካክለን በቀደመው ፍቅራችን አብረን ማምለክና ማገልገል ቀጠልን:: በድንገት የተነሣው የስደት ማዕበልም ቤተ ክርስቲያንን ሊያጠፋት አልቻለም ማለት ነው:: ባዶውን የቀረውም የጸሎት ቤት ተመልሶ በቀበሌው ሳይወሰድ መቆየቱ ሌላው ተአምር ነበር::

በዚህ ሁሉ ግን፣ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በእምነትና ንስሐ የሚጨመሩ ሰዎች፣ ተጨማሪ አገልግሎቶችና አገልጋዮች እየተበራከቱ መሄዳቸው አልቀረም:: ቀደም ሲል፣ በ1969 ዓ/ም ኃይሉ በቀለ፣ በ1970 ዓ/ም ደግሞ እኔ ራሴ፣ ለሙሉ ጊዜ የወንጌል አገልግሎት ተለይተን ተጸልዮልናል:: ጌታ የሰጠኝ ዝማሬዎቼም ለመጀመሪያ ጊዜ በካሴት ታትመው ለሕዝብ አገልግሎት ውለዋል::በ1970 ዓ/ም አጋማሽ ጀምሮ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናችን መዘምራን በደንብ ልብስና በሙዚቃ መሣሪያ (ጊታር) ጭምር ታጥቀዋል:: የጸሎት ቡድን አገልግሎት ተጠናክሯል:: የእግዚአብሔር እጅ በርትታ፣ ጥበቡም እጅግ ልቃ ስትገለጽ፣ በአንጻሩ የሰይጣን ውጥን በተደጋጋሚ ፈርሷል::

## ማስጠንቀቂያና ማነቃቂያ

ወደ 1971 ዓ/ም ስንመጣ ደግሞ፣ ያ ዓመት፣ ገና ከመስከረም መግቢያ ጀምሮ፣ በይርጋ ዓለም ብቻ ሳይሆን፣ በምድረ ኢትዮጵያ ባሉት አማኞች ላይ፣ የስደት ዋዜማ ደወል ያስተጋባበት እንደ ነበረ በጊዜው የነበርን ሁላችን እናስታውሳለን:: መስከረም 2 ላይ፣ በአብዮት በዓል ቀን፣ የደወሉ ድምጽ በመገናኛ ብዙኃን






የተለማው ለምርትና ባሕል ዕድገት ዘመቻ ወደ ፊት በሚል መፈክር ነበር:: መፈክሩ በጥቅሉ ሲታይ በጎ ገጽታ ነበረው:: የምርት ዕድገት ዘመቻው ምርትና ምርታማነትን በማሻሻል አገራዊ ልማትን ለማምጣት የታለመ ለመሆኑ ከማንም የተሰወረ አልነበረም:: የባሕል ዕድገቱም፣ መሠረተ ትምህርትን በማስፋፋት ማይምነትን ለማስወገድ እንዲሁም ሥራ ወዳድነትና ታታሪነትን ከፍ ለማድረግ የታሰበ መሆኑንም አላጣነውም ነበር:: የእምነታችን መሠረት የሆነው መጽሐፍ ቅዱሳችንም ይህንኑ ጥረት የሚያበረታታ ስለሆነ፣ በወቅቱ፣ እግዚአብሔር በየቦታው ያስቀመጣቸው ክርስቲያን ወገኖቻችን በዕድገቱ ዘመቻ ላይ ከሙሉ ልባቸው መሳተፋቸውም የሚታወቅ ነው::

ሆኖም፣ የባሕል ዕድገቱ ጉዳይ ከዘመኑ ፍልስፍና ጋር የማይሄደውን «ማንኛውንም» እምነት የማጥቃት አንድምታ እንዳለው የገመቱም አልታጡም:: የእምነት ተቃዋሚ የነበሩ የቀበሌ ወጣቶች፣ የባሕል አብዮት እንደታወጀብን ቆጠሩ:: ከዚሁ ጋር በተያያዘም፣ የማስጠንቀቂያ መልዕክቶችን በተከታታይ መቀበል ጀመርን:: የሚደመጠውና የሚነበበው ወቅታዊ ነገር ሁሉ በአብዛኛው የስደትን ምልክት የሚሰጥ ነበር:: የመንደር ሕጻናት ሳይቀሩ ጴንጤዎች ዘንድሮ አለቀላችሁ አሉን:: ዛቻዎች ቀጠሉ:: የታወጀውም «ዘመቻ» ቀስ በቀስ፣ በየቦታው፣ ያለ መንገዱ ሲተገበር ጀመረ:: የኸውም፣ ከከተሞች እስከ ገጠር ቀበሌዎች ድረስ በዘለቀ መልኩ ክርስቲያኖችን በማሳደድ፣ በማሰር፣ በመደብደብ፣ እእምሮን በማስጨነቅና በአካል በማንገላታት፣ እንዲሁም ቤተ ክርስቲያኖችን በመዝጋት ወዘተ... ሆነ::

በዚሁ ዓመት መግቢያ ላይ ትልቁን የጸሎት ቤታችንን በማስነጠቅ ያለ መሰብሰቢያ ሊያስቀረንና ሊበትነን ሰይጣን በብዙ ጣረ:: እግዚአብሔር ግን ጣልቃ ገባ:: በእርግጥ ትልቁን ቤት ማስረከባችን አልቀረም ነበር:: በምትኩ ግን አነስ ያለ ሌላ ቤት እዚያው በነበርንበት ቀበሌ እንዲሰጠን ስለ ተደረገ ለተጨማሪ አንድ ዓመት ሥራው የሚቀጥል ሆነ::



ከእሥራር በሬት በቀበሌ 05 የነበረን የመጨረሻው ፀሎት ቤት (1971 ዓ/ም)

በዚህች አዲስ ጸሎት ቤት ውስጥ እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሊያንቃቃን ጀመረ:: በተለይ ከመስከረም ወር እስከ ጥር ወር ድረስ የነበረው መነቃቃት የሚረሳ አይደለም:: በጸሎትም ሆነ በቃል አገልግሎት ወቅት በብዙዎች ላይ ከወትሮው ለየት ያለ በመለኮታዊ ኃይል የመነካት ሁኔታ ይታይ ነበር::

ዓመቱ የአገልግሎት ራዕይ የሰፋበት፣ አብዛኛው ምዕመን በአገልግሎት የተጋበት፣ ወደ ገጠር ጭምር በአለታና በበንሳ ወረዳዎች የአገልግሎት በሮች የተከፈቱበት፣ የምስክር ቡድን አባላት በየመንገዱ በመውጣት የክርስቶስን የምሥራች ቃል በድፍረት የተናገሩበት፣ የጸሎት ቡድን የበረታበት፣ አንድ ተጨማሪ የወንጌል አገልጋይ፣ አስቻለው ከበደ(አሁን ዶክተር ሆኖአል)፣ በሙሉ ጊዜው ወንጌልን ለማገልገል ወስኖ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በመመለስ ራሱን የሰጠበት ዓመትም ሆነ::

ዝማሬዎችም በመካከላችን መፍሰቃቸውን ቀጠሉ:: *ተነሥ ተነሥ፣ የእግዚአብሔር ክንድ እንደ ጥንቱ ተነሥ፣ የናዝሬቱ ኢየሱስ ከእኛ ጋር ያለኸው፣ ሕዝቤ ሆይ ና ይላል እግዚአብሔር*፣ የተሰኙ ዝማሬዎች መጡ:: በ1971 ዓ/ም ሕዳር ወር ውስጥ፣ በአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን፣ ለመጀመሪያ ጊዜ የማምለኪያ ቤት ሕንጻ ሊመረቅ አንድ ቀን ሲቀረው፣ ለእኛ ይርጋ ዓለም ላይ በተሰጠን የ *ሕዝብን አበዛህ* ዝማሬ፣ ጌታ መዘምራንንና ምዕመናንን ምን ያህል እንዳነቃቃን እናስታውሳለን::

የመነቃቃቱና የመባረኩ ወራት ከመስከረም እስከ ጥር ወር ድረስ ቆየና ከየካቲት መግቢያ ጀምሮ እስከ ሚያዝያ ድረስ *የመንፈስ ክብደት* የሚጫጫንበት ጊዜ ሆነ:: ከፍተኛ የሆነ መንፈሳዊ ውጊያ የነበረበት ሁኔታ ውስጥ ገባን:: ጸሎት *ትርጉም አልሰጥ፣ ቃልም አልገሰጥ* ያለበት ጊዜ መሰለ::

በዚህ ወቅት፣ ፓስተር ኃይሉ በቀለ ሲያስተባብረው የነበረ የምስክር ቡድን፣ በአራዳ ክፍተኛ 1 ቀበሌ 08 ጽ/ቤት ለሁለት ሳምንት ያህል ከታሰረ በኋላ ተፈቷል:: እነዚህ ሁኔታዎች፣ ከመነቃቃቱ ጋር ተያይዘው የመጡ መሰናከሎችና የመንፈሱ ክብደት፣ ሊመጣ ላለው ከበድና ረዘም ያለ መከራ በቂ የማስጠንቀቂያ ምልክቶች ነበሩ ለማለት ይቻላል::

## <u>የሁለቱ አገልጋዮች መያዝ</u>

ሚያዝያ 21 ቀን 1971 ዓ/ም፣ በዕለተ ዕሁድ፣ በቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ጊዜ ነበረን:: በአምልኮውም ላይ የሰበከው ፓስተር ተሾመ ነበር:: ያም ስብከት ከረቸሮሙ የእስር ቤት ቆይታው በፊት የመጨረሻው ሆነ:: የአምልኮ ፕሮግራሙ አብቅቶ ወደ መኖሪያ ቤታችን ከተመለስን በኋላ ደግሞ ጓደኛችን አስቻለው ከበደ አንድ መዝሙር ያንጎራጉር ነበር:: መዝሙሩ የዶክተር ለገሰ ወትሮ ሲሆን ቃሉ በከፊል እንዲህ ይነበባል:-

*ዓለምን ጥዬአት ንቄያትም ትቼያት*
*አዘንኩኝ የራስዎን ስታቅፍ እኔን ስታጥላላ ተመልክቼያት*





*ኩርኩሟ ቢመር ቢያይል ጡጫዋ*
*ቢሆንም እኔ አላመልካትም ተዳርሶላታልና ጊዜዋ*

*ችጋር እየላጠኝ ብርድ እየገረፈኝ ብንገላታ*
*ላንገቴ ማስገቢያ ጎጆ አጥቼ ብሆንም አውታታ*
*እየጠነቆለች ዓለም እንደ ድሃ ብታሳየኝ*
*ጸጋህ እስካስቻለኝ ክንድህ እስካገዘኝ ካንተ ጋር ነኝ*

ፓስተር ተሾመም መዝሙሯን በመቀበል መላልሶ አንጎራጎረና *ይህ አልደረሰብንም፣ እንዲሁ ዝም ብለን ነው የምንዘምረው* ሲል ከዚህ በኋላ ይደርስ ይሆናል ተባብለን አለፍነው:: የዕለቱን ሁኔታ ለማስታወስም የጻፍኩት የሚከተለውን ይመስላል:-

ከፋሲካ ማግሥት ገና በሳምንቱ፣
ሀ ብሎ ሊጀምር ረጅም እስራቱ፣

በመከረኛዋ ምድር ካራተኛ ጸሎት ቤቱ፣
ከእሁዱ አምልኮ መልስ ከመኖሪያው ተመልሶ፣
መዝሙር ከመዝሙሮች መሐል ከማሕደሩ ተቀስቅሶ፣
ምክንያቱ ባይገባውም ሲያንጎራጉረው መላልሶ::
*ችጋር እየላጠኝ ብርድ እየገረፈኝ ብንገላታ*
*ለአንገቴ ማስገቢያ ጎጆ አጥቼ ብሆንም አውታታ...*
*... ክንድህ እስካገዘኝ ከአንተ ጋር ነኝ*

በማለት ዘምሮ ቃል ኪዳን አድሶ፣
ይጠብቀው ኖሮ ድግስ ተደግሶ፣
ክርስቶስን ሊመስል መከራውን ቀምሶ፣
አክሊል ለመሸለም የሱስን እንግሦ::
ድል ለማድረግ ወጣ ዕቃ ጦሩን ለብሶ::

ባሪያው ከጌታው ከቶ አለመብለጡን፣
ጌታው እንደ ተጠላ እርሱም መጠላቱን፣
ተምሮአል ከቃሉ አውቆታል እቅጬን፣
*በኃጢአተኞች እጅ አልፎ መሰጠቱን::*

እንደ ስንዴ ቅንጣት በምድር ወድቆ መሞት፣
ሞትን ድል አድርጎ እንዲወጣ ሕይወት፣
የመከራው መንገድ አስፈልጓል በ'ውነት፣
ዕዳ ሳይኖርበት ዕዳችንን ሊከፍል፣
የባሪያን መልክ ይዞ ኢየሱስ ዝቅ ቢል፣
ራስን እየገዙ በትህትና መኖር፣

የመዳንን መንገድ ሰላምን ሊያስተምር፣
በትዕቢት በዕብሪት ሰላም የለምና፣
በኢየሱስ ትሕትና ሕይወት ሆኖእል ጤና::

መልካም አንተ በጎ ታማኝ ባሪያ ተብሎ፣
ከታመኑቱ ጋር እክሊል ተቀብሎ፣
የእግዚአብሔርን ክብር በክብር ለመካፈል ፣
ማለፍ ያስፈልጋል የመከራን ማዕበል፣
የናስ ቅጥር አድርጎ ከቶ 'ማይደፈር፣
ጸጋውን እያበዛ እኛን ለማጠንከር፣
ጌታ ኃይላችን ነው ስሙን ለማስከበር::

ከፍ ብሎ በተጠቀሰው ዕለት ማለትም ሚያዝያ 21 ቀን በቀበሌ 06 ውስጥ ሁለት የክርስቲያን ሠርጎች ነበሩ:: አንዱ ሠርግ፣ ከሀዋሳ የመጡ የወንድም ጌቱ እያሌው(የአሁኑ ፓስተር)ና የእህት ንጋት በቀለ ሲሆን ሁለተኛው ከደብረ ዘይት፣ የአየር ኃይሉ መኮንን፣ የኮሎኔል መንገሻ ሁንዴና የሲስተር ታደለች አሰፋ ነበር:: ሲስተር ታደለች፣ የቤተ ክርስቲያናችን አባላት የነበሩ የሰናይትና የአብነት እሰፋ እህት ናት:: ፓስተር ተሸመና ፓስተር ኃይሉ የተያዙት በተለይ በሁለተኛው ሠርግ ላይ ተገኝተው ሲመለሱ፣ በዚያው ሰሞን በቀበሌው ጽ/ቤት የታሰረውን አባላችንንና ቆይቶ ባጋጠመው አደጋ ምክንያት ወደ ጌታ የሄደውን ደባልቄ መስፍንን ለመጠየቅ ጎራ ባሉበት ነበር::

እንግዲህ፣ በዚያው የአምልኮ ዕለት ነበር ከፍ ብሎ ወደ ተጠቀሱት ሠርጎች የተሄደው:: ለመሄድ ስንዘጋጅ ግን እስቻለው ከበደ ምን እንደተሰማው እናውቅም፣ አልሄድም አለ:: በተለይ *የሙሽሪት እህቶች ሠናይትና አብነት ምን ይሰማቸዋል? ሽረ ባክህ* ብንለውም እሻፈረኝ እለና ቀረ:: ሦስታችን፣ ፓስተር ተሸመ፣ ፓስተር ኃይሉና እኔ ግን ሄድን:: ::

በምሳው ቦታ በጎ ባልሆነ እስተያየት ትኩር ብለው ከሚመለከቱን ዓይኖችም ጋር ሳንገጣጠም እልቀረንም:: ነጻነት አልተሰማንም:: የምሳው መስተንግዶ እንዳበቃ ከዚህኛው ሠርግ ቤት ሠርገኞቹ ሲወጡ እኛም እብረን ወጣን:: መንገዳችን ላይ ነበርና ሰሞኑን የታሰረውን ደባልቄን ለመጠየቅም ወደ ቀበሌው ጽሕፈት ቤት ጎራ ማለት ነበረብን:: ከጽ/ቤቱም ስንመለስ ከኋላችን *ተመለሱ* እያለ የሚከተለን ሰው ድምጽ ተሰማን:: ድምጹ የጥበቃ ሠራተኛው ነበር:: እየተጣራ የሚከተለን የቀበሌው የጥበቃ ሠራተኛም ከመካከላችን ዘለግ ያለ ቁመናና ቀላ ያለ መልክ ባለው በፓስተር ተሸመና በፓስተር ኃይሉ ላይ በደብልጥ እነጣጠረ:: ይዟቸውም በመመለስ እቀበሌው ጽ/ቤት ገባ:: በጥቂት ሰዓት ውስጥ የእኔም ዕጣ ተመሳሳይ እንደሚሆን እሰብሁ:: እኔ በቀበሌው ፊት ለፊት በቅርብ ርቀት ላይ ነው የነበርሁት:: በቅጽበት፣ በሁለት እማራጮች መሐል መወሰን ነበረብኝ:: ወደ ቀበሌው ተመልሼ እጅ በመስጠትና ወደ ቤት ሄጄ የተበታተኑ ነገሮቻችንን በማስተካከል መሐል:: እናም ወሰንኩ:: መታሰሩ ዞሮ ዞሮ ካልቀረ፣





መውሰድ የነበረብኝ የተሻለው እማራጭ፣ ያንን እድል በመጠቀም እስቻለው ጋ መመለስና ቤታችንንና ቤተ ክርስቲያናችንን ሊሆን ለሚችለው ሁሉ በቶሎ ማዘጋጀት ነበር:: እኔም፣ በቀበሌው ፊት ለፊት ከተማይቱን ለመልቀቅ ይዘጋጁ የነበሩትን ሠርገኞች ለመሰናበት የተወሰኑ ደቂቃዎችን ከወሰድሁ በኋላ ለዝግጅቱ ወደ ቤት እመራሁ::

ሁለቱ እገልጋዮች *ገብተዋል* - ፓስተር ተሸመና ፓስተር ኃይሉ :: አሁን ሁለት እገልጋዮች ቀርተናል - አስቻለውና ተስፋዬ :: ቀጥሎስ?

## የመጨረሻው ዝግጅት

በሠርጉ ዕለት፣ ከግብዣው መልስ፣ ወደ ቤት በመምጣት የተፈጠረውን ሁናቴ ለእስቻለው ነገርኩት:: ከዚያም፣ የቤት ዕቃዎችን ቦታ ቦታቸውን እስይዘንና አስተካክለን ስናበቃ፣ የራሳችንን ሕይወት ሊመጣ ለሚችለው ማንኛውም ነገር ማዘጋጀት ጀመርን:: ይህንንም ያደረግነው የአምስት ቀናት ተከታታይ ጾምና ጸሎት በማድረግ ነበር::

እግዚአብሔርም የሁለታችንን ሕይወት ለመጪው ችግር ለማዘጋጀት ጊዜ እንደ ሰጠን ሁሉ የምዕመናኑንም ሕይወት በመዳሰስ ለማነቃቃት ጥቂት ጊዜ ሰጠን::በዚህ ጊዜ ውስጥ፣ ማለትም ከሚያዝያ እስከ ሰኔ ወር እጋማሽ ድረስ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ቀጥሎ መደበኛዎቹ ፕሮግራሞች በቦታቸው ይካሄዱ ነበር:: ጊዜው አጠቃላይ የጸሎትና የጌታ እራት፣ 12ኛን ክፍል ላጠናቀቁና በዚህም ምክንያት ወደ ሌላ ቦታ መሄድ ለሚኖርባቸው ወጣት ምዕመናንና ለእህቶች የትምህርት ጊዜ ሆኗል::

12ኛ ክፍል ላጠናቀቁቱ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ስለ ማወቅ በተስፋዬ ጋቢሶ፣ ጡት ስለ መጣልና ስለ ማደግ በአስቻለው ከበደ፣ የእግዚአብሔርን ቤት ስላለመተው - እስራት ስለ መከፈል - በዓመቱ ዲያቆን በእቶ እስማረ ጸጋዬ ትምህርቶች ተሰጥተዋል:: በዚህ ወቅት በተደጋጋሚ የዘመርነው *ተራራ ሸለቆ ወንዙ ወንዛ ወንዙ፣ ምቹ ነው ጌታ ሆይ ከአንተ ጋር ሲጓዙ* የሚለው የሽዋዬ ዳምጤ ዝማሬ አሁን ድረስ ትዝ ይለናል:: በትምህርቱ ፍጻሜ ላይ ሁሉም በመጨረሻይቱ ጸሎት ቤት ግቢ ውስጥ እጃቸውን ወደ ቤትዋ በመዘርጋት ከነህምያ 10:39 *የአምላካችንን ቤት ከቶ አንተውም* የሚለውን ቃል በመደጋገም አሰሙ::



*እኛ ግን የአምላካችንን ቤት ከቶ አንተውም በሚለው ቃል መሠረት ለመንፈሳዊ አገልግሎት የተገባ ተምሳሌታዊ ቃል ኪዳን*

**1971 ዓ/ም በቀላሉ የማይረሱና ዋጋቸው የላቀ ትዝታዎችን ጥሎልን አልፏል:: ከእነዚህ መካከል አንዱ የእግዚአብሔር መንፈስ በኃይል በመውረድ የኀበኘበትና ከፊታችን ያለውን ሁናቴ በማስመልከት ግልጥ የሆነ መልዕክት የሰጠበት አስደናቂ የእሁድ አምልኮ ቀን ነው:: ቀኑን በትክክል ባናስታውስም ጊዜው የሰኔ ወር መጀመሪያ ግድም ነበር::**

በዚያን ዕለት የእግዚአብሔር ክብር በቃሉና በዝማሬ አማካይነት ተገልጧል:: ከተሰበከው ቃል የተነሳ እጅግ የሚበዙቱ ምዕመናን ታላቅ ሃሴት እያደረጉ ጌታን በልዩ ልሳን አስከ ማመስገን ሲደርሱ ለማየት ያ የመጀመሪያ ቀን ሆነ:: የዕለቱ መልዕክት አቅራቢ አስቻለው ነበር:: የሰበከው ከሐዋ 1:11 ነበር:: ማስታወሻዬ ላይ ያገኘኋቸው የስብከቱ ጥቂት ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው::

*የገሊላ ሰዎች ሆይ ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ ስለምን ቆማችኋል? ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት እንዲሁ ይመጣል::* (የመግቢያ ጥቅስ)





- *ለምን የኢየሱስ መሬት ብቻ ይታያችኋል?*
- *ለምን ዳግም ምጽአቱን አታዩም?*
- *ለምን ትፈዛላችሁ?...*
- *ነጻ ያወጣናል ብለው ሲጠብቁ ሳሉ ሄደባቸው::*
- *የስንቱን ቤት አስተካከሉ ነበር::*
- *ሽባውን በሽተኛውን፣ 38 ዓመት ሙሉ በአልጋው ላይ ተጭኖ የኖረውን አልጋውን እንዲሸከም አድርጎታል...*
- *የስንቱን ፕሮግራም አሳክቷል - በቃና ዘገሊላ የነበረውን ሠርግ::*
- *በቃልና በሥራ ብርቱ ነበረ እሱ::...*
- *አሁን ግን በሞት ላይ አልበረታም ይሆን?*
- *ሐዋርያቱ ሂያጂነቱንና መራቁን ብቻ ስላዩ ፈዘው ቀሩ::...*
- *ኢየሱስ ቀራቢ ነው - በፍጥሞ ደሴት - ዮሐንስን - አስቲ እስሩን እርሳውና ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት እንዲህ ብለህ ጻፍ ይለዋል::* አዎን፣ በፍጥሞ ደሴት፣ በግዞት ሥፍራ፣ ኢየሱስ በእርግጥም ቀራቢ በመሆን እስርን አስረስቶ የመጽናኛ መልዕክቶችን ያስጽፋል::

እግዚአብሔር በዚህ ከፍ ብሎ በተጠቀሰው የስብከት መልዕክት ወደ ልባችን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተናገረ:: በዚህ ዕለት መልዕክት፣ በእጅጉ ከተባረኩት መካከል በዝምተኛነትዋ የምትታወቀው ዘማሪት በቀለች ገብረ ሃና፣ ያለ ወትሮዋ እየጮኸች፣ በልሳን እግዚአብሔርን አከበረች:: መልዕክቱ አብቅቶ፣ *አስቀድሞ ኃይል ይሰጣል* የሚለው ዝማሬ በመዘምራን ሲቀርብ ደግሞ፣ ከወትሮው በተለየ መንገድ፣ ከፍ ባለ ድምጽ በመጮህ ጌታን የመባረክ ሁኔታ በሌሎችም ላይ ታይቷል:: ለእኛ፣ ያ ሁኔታ፣ ከተራ ስሜታዊነት ያለፈ ጠለቅ ያለ ትርጉም ነበረው:: «ስሜቱ» የዘመኑ ነባራዊ ሁኔታ ሲፈጥር የታገለውን የምጥና የትካዜን ጫና የሚጋፋና የሚገፈትር ኃይል ነበረውና:: ያ ዕለቷ በእርግጥ ልዩ ዕለት ነበር:: በኋላ ላይ፣ ዓመታትን በእስር ከእኛ ጋር የሳለፈው ወንጌላዊ ታፈሰ ቦኤም በመንፈስ ቅዱስ የተሞላሁት በዚሁ ዕለት፣ በዚሁ ፕሮግራም ላይ ነበር በማለት በቅርቡ ገልጾልናል::

እንዲህ ባለ ሁኔታ እግዚአብሔር በመንፈሱ ኃይል ዳሰሰንና አነቃቃን:: ሳምሶንን በ[illegible]ን ሠፈር ውስጥ እያነቃቃ እንዳዘጋጀው ዓይነት ማለት ነው (መሣ 13:25):: ለእኛም፣ ይህ ለመጠነ ሰፊው እስራት የመንፈሳዊ ዝግጅታችን መደምደሚያ ሆነ::

# ምዕራፍ ሁለት - የቀበሌው እንግልት

## የተጠበቀው ሲመጣ

ከአንድ ዓመት ተኩል በፊት፣ በ1970 ዓ/ም፣ በትልቁ ጸሎት ቤታችን በተ ዘጋጀው ኮንፈረንስ ጊዜ ከምስባኩ ከፍ ብሎ በቤቱ ግድግዳ ላይ በትልቁ ተጽፎ የተሰቀሰ አንድ መሪ ጥቅስ ነበረ:: ያም ከዮሐንስ ወንጌል 9:4 ላይ የተወሰደና :- *ቀን ሳለ የላከኝን ሥራ ላደርግ ይገባኛል፣ ማንም ሊሠራ የማይችልባት ሌሊት ትመጣለች* የሚል ነበር:: ሌሊት ምን ጊዜም ጊዜአዊ ናት:: ተመልሶ መንጋቱ ስለማይቀር! እስከዚያውም ቢሆን የማምለክና የማገልገል ሕጋዊ ነጻነት ሙሉ ለሙሉ የሚወገድባት ናት - ሌሊቷ:: ቀደም ሲል ካየናቸውና ከተቀበልናቸው ምልክቶች የተነሣ ግን እየጠበቅናት ነበር::

ይህ ዓመት፣ ማለትም 1971 ዓ/ም፣ ሌሊቷ ሳትመጣ ምዕመናን ሁሉ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም በሙሉ ኃይላቸው የተጉበት ዓመት ሆነ:: ዓመቱ የሥራ ማጠናቀቂያና የዝግጅት ዓመት ስለነበረ ማንም ቢሆን ታክተኝ ሳይል ለጌታ ሥራ ከፍተኛ ትጋት አሳይቷል::

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው፣ በ1971 ዓ/ም ገና ከጅምሩ፣ በምድሪቱ ላይ በምትገኝ ቤተ ክርስቲያን ላይ የስደት ደወል ተሰምቷል:: ደወሉን የሰማ ሁሉም የልብ ጥንቃቄ ማድረግ ጀምሯል:: ዛቻውና ማስጠንቀቂያውም እያበቃ፣ የታሰበው በድርጊት የሚገለጽበት ሁኔታ እጅግ ተቃረበ:: ከየከተማው፣ ለምሳሌ ፣ ከባሌ ጎባና ከአርባ ምንጭ አካባቢ፣ የእስራት ዜና እየተሰማ ቆየና ወደ ይርጋ ዓለምም ደረሰ:: እኛም አስፈላጊውን ዝግጅት ሁሉ አድርገን ራሳችንን በጸሎት ለጌታ አደራ በመስጠት መጠባበቁን ተያያዝነው::

ሰኔ 15 ቀን 1971 ዕለተ ዓርብ የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች ፈተና የጨረሱበትና ክርስቲያን ተማሪዎች እንዲያዙበት ተወስኗል የተባለበት ቀን ነበር:: በዚያን ዕ ለት መንፈሴ እየቃተተ ብቻዬን ውያለሁ:: ጌታ ኢየሱስ በጌቴሴማኒ ሳለ ያደረበት ስሜት በተወሰነ መጠን የተሰማኝ ይመስለኛል:: በዚያን ዕለት፣ ከአቶ አዲሱና ከአቶ አስማረ ጋር:-

> *ሰይጣን እንደ ስንዴ ሊያበጥራችሁ ለመነ እኔ ግን እምነትህ እንዳይጠፋ ስለአንተ አማለድሁ አንተ ግን በተመለስህ ጊዜ ወንድሞችህን አጽና* የሚለውን ቃል ከሉቃስ ወንጌል ተካፈልን::
> *መታሰሩ ከመጣ፣ አንዳንዶቻችንን በውስጥ የመዘግየት ሁኔታ ሊያጋጥመን ይችላል:: እናንተን ግን መንግሥት ለራሱ ሥራ ሲል ምናልባት ብዙ ሳይቆይ ይለቃችኋል:: እናንተም በተመለሳችሁ ጊዜ ወገኖችን አገልግሉ* የሚል አደራ አዘል ማሳሰቢያ በመስጠት ጸልየን ተለያየን::

የሚበዙቱ ክርስቲያን ወንድሞችና እህቶች፣ በዚያው ሳምንት ውስጥ፣ ወደ የዘመዶቻቸው እንዲሄዱ ስለ ተደረገ፣ በከተማ ውስጥ የቀረነው ቁጥራችን





ጥቂት ነበር:: ወንድማችን እስቻለውም፣ ምንም ያህል ሳያገለግል እንዳይታሠር በሚል ስስት ሌሎቻችን ካደረግንበት ብርቱ ግፊት የተነሳ፣ ከተማይቱን ከሁለት ቀን በፊት ለቋል:: የሁኔታው ውጥረት በከተማይቱ ውስጥ ግን እንዳለ፣ የመከራውም ደመና እንዳንዣበበ ቀጥሏል::

የሆነው ሆና፣ ሰኔ 16 ቀን 1971 ዓ/ም ቅዳሜ ላይ፣መደበኛ ፕሮግራም ስለ ነበ ረን ወደ ጸሎት ቤታችን አመራን:: በዚያች ጸሎት ቤት በአንደኛዋ ክፍል ውስጥ ሺመልስ ለማና ጌታሁን አጋፋሪ ይኖሩባታል:: ከእነርሱ ዕቃ በተጨማሪ በዚያ ቤት ውስጥ፣ አንድ አሮጌ ጊታር ፣ አግዳሚ ወንበሮችና ምስባክ እንዲሁም ጥቂት መጻሕፍት ነበሩ::

ሰዓቱ ሊደርስ፣ በከተማይቱ የቀሩ ጥቂት ወገኖች መጡ:: በወንድም ጌታሁን አጋፋሪ መሪነትና በእኔ ሰባኪነት የአምልኮ ፕሮግራም ተካሄደ:: ከዚያም ፕሮግራሙን አብቅተን ወጣንና በቤቱ ቅጥር ግቢ ሰላምታ እየተለዋወጥን ሳለን፣ ጥቂት የከተማው ወጣቶች ትንፋሻቸው ቁርጥ ቁርጥ እያለ በሩጫ ወደ ነበርንበት ቦታ መጡ:: አንዳንዶቹ ቆመጥ ይዘዋል:: እንደ መጡ ግር ብለው ወደ ቤቱ ውስጥ ዘለቁ:: ከዚያም አንዳንድ መንፈሳዊ ስዕሎችና ጥቅሶችን ከግድግዳ እየገነጠሉ ካወረዱ በኋላ ጊታር፣ መጻሕፍትና ምስባክ ተሸክመው አወጡ::

***ድራማው*** **ቀጠለ**:: በወቅቱ ቡድኑን እየመራ የመጣው የከተማይቱ ቀበሌዎች የወጣት ሊቀ መንበር ነበር:: ምን ልንሠራ እዚያ እንደ ተሰበሰብን *ለማጣራት ጥያቄዎች ተጀመሩ*:: ወደ አቶ አዲሱ አምዴ በመቅረብ :- *ምንድነው እዚህ የምትሠሩት? ለምን መጣችሁ?* አለው:: *ለጸሎት ነው የመጣነው* ብሎ መለሰለት:: ከዚህ ሌላ ምንም አልጠየቀውም:: ይህ ሲሆን ግን፣ ከእኛ ወገን የመ ረጋጋት ሁኔታ እንጂ ድንጋጤና መርበትበት አልታየም:: የመጣው ነገር ስንጠብቀው የነበረ ነውና:: መረጋጋቱ ግን ሊይዙን የመጡት ወጣቶች የጠበቁት እንዳልነበረ ገምተናል::

በመጨረሻም እኔንና ጌታሁንን ምስባክ፣ ወርቅነሽ ይመርንና ማናለብሽ መስፍንን መጻሕፍቱን አሸክመውን - በሉ ቅደሙ አሉን:: ወደ ፖሊስ መምሪ ያም ሊወስዱን ከቃጡ በኋላ ሃሳባቸውን ቀየሩና ወደ ቀበሌ 05 መሩን:: እኛን እዚያ እንዳደረሱን ሌሎቹንም ምዕመናን ከየቤታቸውና ከየመንገዱ እያመጡ ጨመሯቸው:: በመጨረሻም ጉዳዩ የማይመለከታቸውን ተጠርጣሪዎች ጨማምረው ቁጥራችንን እንደ ምንም ወደ 28 አደረሱት:: ኋላማ *እንዴ! ከተ ማዋን የሞሉ የት ደረሱ? ማን ነገራቸውና አመለጡ?* በማለት ሲቆጩ ሰማናቸው::

ማምሻውን የደንቡ እንዳይቀር ዕቃዎቹን እየመዘገቡ አስገቡ፤ ስዚያውም አቶ አስማረ፡ *ዕቃው የእግዚአብሔር* ነው ይመዝገብ ብሎ ስላስጠጣቸው ነው:: በዚያች ምሽት ያዩኋቸው የሚበዙቱ ወጣት ክርስቲያኖች ነበሩ:: ከዚህ ጊዜ በ1979 ዓ/ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለየችው እህታችን በቀለች ጋሜ ብቻ ነበ

እራሱ ሕጻንም፤ ከቤት ተይዞ በመምጣት ለጥቂት ቀናት ከእኛ ጋር ታመሐለች።

ግን ወንዶቹ በተባለው ጽሕፈት ቤረንዳ፤ በበርድ ላይ፤ እንደገንቶች ሲደረግ ሴቶቹ ከቤቱ ጀርባ ያለ ክፍል ተሰጣቸው። እንግዲህ፤ በጥቅሉ ስናየው፤ የተጠበቀው መጣ ማለት ነው። የመከራ ጊዜ ገና ገና አልተቀበልንም። ለማንኛውም፤ የቢያን ሌሊት ሁናቴ ብሎ አለፈ።

## የተባለው ቀዳታ

በማግሥቱ፤ ማለትም በ17/10/71 ጠዋት፤ የአውራጃው የፖሊስ ኃይሬ፤ ከተባለው የአመራር አባላት ጋር በመሆን መጡና ከተባለው ጽሕፈት ጀርባ ለጠበቁን። ኃይሬው ቀድሞ ሲል በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ውስጥ በመምህርነት ያገለገለ ነበሩ። እንግዳዎቻችንም ተማሪዎቻቸው ስለ ነበርን እንተዋወቃለን። በዕለቱ ያነጋገሩው ግን ቀድሞ የምናውቀው የመምህርነት ፊገጎታቸውን አልነበረም። ለምን ብለዋል፤ ሰሚታቸው ተቀምጠዋል፤ ንግግራቸውም ሻከር ብሏል። የሚገርም ነው! እርሳቸውም መጀመሪያውን ዘር ትምህርት አይደለምን ማለፈራይ ስለማኝ ተመልሰው ሄዱ። ከተናገሩአቸውም ዋናዎቹ ውስጥ የሚከተለው ይገኙበታል።

- *ወሬያ ወሬህ ወልደጥ ማለት ነው። መረከር ስማለት ጀምሮ አዳማቾትን ማስጠንቀቅ አለባችሁ።*
- *ኢምፔሪያሊስቶች በኢትዮጵያ ያለውን ተሰደዱ አሰቡ ያቅዳሉ። የአውራ ክፍል ግብሮች ለመሬሰም ግን ምንም አይቻሉም።*
- *— አባቶቻችሁ መረከር አለምታችሁ ወጣ የሚል መመሪያ አገኘተ ላሰራላችሁ ይርበተታል።*
  የተባለውን መመሪያ ከእኛ ማንም የሰማ ባይኖርም የእርሳቸው አነጋገር በሁሉ እንዳለተገኘም የሚል ዓይነት ነበር።
  እንደ ተማሪና መምህር በበረን ትውውቅ መሠረት ወደ እኔም ዘወር አሉና—
- *አንተ ደግሞ እዚህ ምን ትሠራለህ ትምህርትህን አጠናቀህ በሆነ ሥራ ወደ ስራ አልሄድክም ? የሚሉ ጥያቄዎችን አከታተሉ። በዝርዝሩ፤ የተመለሰውን እያዳመጡ ሳለሁ*
- *እዚህ ስትኖር ቤታችን (የእስታዊት) ኢትዮጵያ ወጣቶች ማለብ ለሀገሮች ተቀናቅ ታውጃለህ አሉኝ።*
- *አለወትም አልሁትም።*
- *አምንኛለው የማትሰራው? ጊዜ ለሁሉሁ ነው? በማለት መልሱን አመቻቹልኝ።*
- *አምን ስለቸው ለጊዜው ለቀቅ አደረጉኝ።*

ከዚህ በኋላ ከእሱቶች አንዳልንነኝ አለው ሄዱ። እኛም ከቢያን ቀን ጀምሮ ለሰማይ በረንዳው አካባቢ በተፈልፍ በበርድ ላይ የምንወልና የምንድር ሆነ። ወንዶቹ ደግሞ ከቤቱ ክፍል ጎን ላለ ክፍል ተዛውረው ገቡበት። ከጥቂት ቀናት በኋላ የአሊ መኪና ምግብ ጥሬም እንደለለው ተገዝቶ መጣና





ወደ ወንዶቹ ክፍል ጨመረኝ። በዚህ ጊዜ በትተገባው ውስጥ እኛን የሚመለከተው ሁሉ እየታየን በመያዝ ወደ እኛው ይተላለፍ ጀመር።

የእስሬቱ ምክ ጎላግ፤ የክርስቶስን ስምና ምስክሮች ከትተገደቱ ማጥፋት ቢሆንም በዚያቱ ጅማሬ ላይ መሬከር ማስማት ይልቅ ነበር፤ ማለትም፤ ተጠያቂው የእስሮቱ ጠላቶች የተባሉትን እንዲረግም ይጠይቃል። የተፈለገውን ከረጅ ለጊዜውም ቢሆን ችግሩ የሚታለል ይመስለል።

በዚህ ጉዳይ ሁላችንም በጋራ ተወያየን። እያንዳንዱ አማኝ በጸሎት ለራሱ መወሰን የሚችል ቢሆንም ተመራጭ በአንድ አቋም በጋራ መቆም ነበር። ጉዳዮችን የመረዳት ሁኔታ ግን በሁሉም ዘንድ አንድ ላይሆን ይችላል። ከአቅም በላይ የሚሆኑ ነገሮችም ይገጥማሉ። በዚህም ሆነ በዚያ የውሳኔ ልዩነቶች ቢከሰቱ እርስ በርስ ከመፈራረድ መቆጠብ እንደሚገባንም ተገነዘብን። ተፈቶ በሚገደልና በሚተረው ወገን መካከል መተያየም አይኖርም በሚል ሃሳብ ከምባ ኃይል ተሰማምተን ተቀመጥን። በዚህ በምንነት መንፈስ የሆነን ከንመት በፊት በዚህ ጉዳይ ዙሪያ ያገኘው ተሞክሮ ነው። በክርስቶስ ባገኘው ወንድምነትና እህትነት ላይ ትልቅ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባን ነበር። በተጨማሪት ይቀርብ የነበረውና እኛን የከበደው ግን *ክህደት ወይ ማነው?* የሚለው ጥያቄ ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ *ክህደ* የሚመጣው *ክህደት ወይ* ነው በማለት የክርስቶስን የበላይነት ይነግረናል (ዮሐ 3፡31)። ታዲያ፤ በጠያቂዎቻችን የሚፈለገው ምላሽ *አምልኮ* የሚል ሆኖ ስለ *ክህደት ወይም እንዲአበል* ነው ከተባለ ችግሩ ሲዊስ ታይቷል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ብዙም ሳንቆይ በሳምንት ሁለት ቀን የጾምና የጸሎት ጊዜ መወሰድ ጀመርን። እያንዳንዳችን እንደ ተሰጠው የግሉን ተጨማሪ ፕሮግራም እየያዘ አጥብቆ መጸለዩን ተያያዝነው። እየቆየን ስንሄድ የጸሎት ቀኑን በሳምንት ወደ አንድ ቀን (ረቡዕ) በማምጣት በጽሚነት ያዝነው። የጸሎታችንም ምኝ ርእስ ሆና እስክተፈታንበት ጊዜ የዘለቀው *ለእስራታችን* ጌታ እንዲአበር የሚለው ነበር። ክርስቶስን ለማያውቁ ሰዎች መዳን፤ በውጭ ለተረው የአገልግሎት ሕዝብ ጥበቃና እድገት መጸለያም ሌላው የጸሎታችን አትኩሮት ነበር።

በመጀመሪያዎቹ ቀናት በማንም እጅ ምንም መጽሐፍ ቅዱስ አልነበረም። የምንጸናናው በእሬት ጊዜ ስንሰፍ የምናስታውሰውን ጥቅስ ለሌሎችን በመሰጠት ነበር። ከጥቂ ቀናት በኋላ መጽሐፍ ቅዱስ በድብቅ ሊገባን በመቻሉ ከፍተኛ ናፍቆት ተቀባለው የነበረ ነበር።

በእነዚሁ ቀናት ውስጥ ማንም ያልነካቸው ወጣቶች ለራሳቸው ተሰብስበው እየመጡ ሲጠይቁን ይውላሉ። የፈለጉትን ያህል ተናግረውና ተከራክረው ይሄዳሉ። የተባለው አመራር አባላትም በተለያ ምክር ቢጤ ይሰጡናል።

ቀናት እየገፉ ሲሄዱ ደግሞ የጉልበት ሥራ እንድንሠራ ያስገድዱን ጀመር። በዚህ ወቅት ወደ ጊዜያ ወንዝ እየሄድ በመወረድ ካስር ዋና ተስፍያለ። የተ

ጎንደሉ የቡና ዛፎች እየተሸከምን አግዘናል:: ወዘተ...

አንድ ቀን የአውራጃው ካድሬ በድጋሚ በሞተር ቢስክሌት መጡ:: ቆጣ ቆጣ ብለዋል:: ቋንቋቸውም ከያኔው ጠንከር ብሏል:: ሰበሰቡንና አቋማችንን አስተካክለን እንደሆን ጠየቁን:: መልስ ሰጪ ጠፋ:: በዚያ ሰዓት ከእኛ ማንም ለመናገር አልወደደም ነበር:: ካድሬው መሬቱን በኃይል ረገጡና *አፈር ዲሜ ትበላላችሁ፤ በእናንተም መቃብር ላይ ሶሻሊዝምን እንገነባለን* አሉ:: ወትሮውንም ሳቂታ የነበረችው ታናሽ እህታችን፣ ፍቅርተ ገ/ ሃና፣ ይህን ስምታ እንደ መሳቅ ስትል አይዋትና ተናደው *ሳቂ! ነገ ታለቅሻለሽ* አሏት:: በመጀመሪያው ዕለት የተናገሩትንም ቃል በመደጋገም፣ ሌላም ዛቻካሰሙ በኋላ፣ በዚያው የቁጣ ስሜት ተመልሰው ሄዱ::

የጉልበት ሥራው፣ የቃላቱ ንዝንዝ፣ የምግብ ዕጥረቱ፣ የቦታውና የመኝታው ጥበት፣ አንዳንዴም የብርዱ ነገር እንዳለ ቀጠለ::

ከዕለታት አንድ ቀን ደግሞ ድንገት መጡና ወደየቀበሌው ከፋፈሉን:: ዓላማው አልገባንም:: የሄዱት ሄዱና እኔ፣ ጌታሁን አጋፋሪ፣ ተስፋዬ ካሣ፣ አቶ አዲሱ አምዴ፣ ወርቅነሽ ይመር፣ መቆየቱ ከበደ፣ ምንትዋብ አረሩ፣ አበራሽ ሞገስ፣ ጥሩነሽ አባተ፣ መንበረ በቀለና ሽዋዬ ነጋሽ ቀበሌ 05 ቀረን::

ከዚያ በኋላ የቀበሌው የቀይ ሽብር ኮሚቴ እንደ ተቋቋመልንና ጉዳያችን በእነርሱ አማካይነት እንደሚፈታልን የቀበሌው ምክትል ሊቀመንበር ነገሩን:: በዚያው ሰሞን የቀበሌው የሕዝብ ደኅንነት ኃላፊ የነበሩት ግለሰብ ከወጣት ክፍልም አንድ ሰው በመጨመር ሌሊት ላይ መጡ:: ማምሻውን የጌታን ቃል ስናጠና በተለይም በ2ቆሮ 11፡24 ላይ ጳውሎስ *አይሁድ አንድ ሲጎድል አርባ ግርፋት አምስት ጊዜ ገረፉኝ* ባለው ክፍል ላይ ስንጠይይ ነበር ሰዎቹ የመጡት:: እንደመጡም እህቶቻችንን ተራ በተራ ከማደሪያ ክፍላቸው እያወጡ በቁማቸው በጉማሬ አለንጋ ሊገርፏቸው ጀመሩ:: የገረፏቸው፣ከጎናችን በነበረው ክፍል ውስጥ ስለ ነበረ የግርፋቱንም ሆነ የተገራፊዎቹን የሲቃ ድምጽ ለመስማት ችለን ነበር:: ሌሎቻችን ጭንቀንና የስቃዩን ስሜት እየተጋራን በተንበሰበሰ ልብ ሆነን ተራችንን ተጠባበቅን::

በዚህ ምሽት ገራፊዎቹ፣ ምንትዋብ አረሩን፣ ጥሩነሽ አባተንና መቆየቴ ከበደን ተራ በተራ ጀርባቸውንና እግራቸውን እስኪበቃቸው ከገረፏቸውና ከደበደቧቸው በኋላ ወጥተው ሄዱ:: የቀበሌው ቀይ ሽብር ሥራውን ጀመረ ማለት ነው! በማግሥቱ ይቀጥላሉ ብለን በመጠበቅ ላይ ነበርን፤ ሆኖም አልመጡም:: በተከታዮቹ ቀናት ጥሩነሽ አባተን፣ አሳመነች ሞገስን፣ አቶ አዲሱ አምዴንና ተስፋዬ ካሣን ለቀቋቸው::

በመጨረሻ እኔ፣ ጌታሁን አጋፋሪ፣ አበራሽ ሞገስ፣መቆየቴ ከበደ፣ወርቅነሽ ይመርና ምንትዋብ አረሩ ቀርተን ሰሞኑን እንግዳ ይመጣል በሚል ምክንያት ግቢውን ስናጸዳ ሰነበትን:: በዚህ ጊዜ አበራሽ ሞገስ የአስም በሽታዋ ተቀስቅሶ





ስላስቸገራት መሰቀቅዋን ወርቅነሽ ታስታውሳለች:: እንግዳ የተባሉት የአውራጃው ዋና አስተዳዳሪ የአውራጃውን የፖሊስ አዛዥና ሌሎችንም የመንግሥታዊና የሕዝባዊ ድርጅት ባለሥልጣኖችን አስከትለው ቀበሌ 05ን ለመጎብኘት መጡ:: ቢሮ ገብተው ተቀመጡ፤ የተሰጣቸውን ገለጻ አዳመጡ:: ግቢውንም ተዘዋውረው ጎበኙ:: ሊወጡ ሲሉ የቀበሌው ሊቀመንበር *እዚህኮ ጴንጤዎች አሉ* አላቸውና ወደ ነበርንበት ክፍል ይዟቸው ገባ::

ሁላችንም ተነስተን ተቀበልናቸው:: አስተዳዳሪው የትምሕርት ክፍላችንንና ሌሎች ጥቂት ነገሮችን ጠየቁን :: 12ኛ ክፍል ያጠናቀቅን ስለ መሆናችን በቀበሌው ሊቀመንበር ተነገራቸው:: የአውራጃው ፖሊስ አዛዥ ም/የመቶ አለቃ ወደ እኔ እየተመለከቱ፡- *ማንም አይለማመጥህም:: ግን ጭንቅላትህን ተጠቀም:: ይኸ የሃይማኖት ጉዳይ ....ያስፈልገዋል* አሉና በዛቻ ዓይነት ጣታቸውን አወዛውዘውብኝ ወጡ:: አዛዡ ገና ተሹመው ያረጋ ዓለም መምጣታቸው ነበር አሉ:: እና እኛን በማየታቸው የተገረሙ ይመስላሉ::

ሳምንት የሞላ አይመስለኝም፤ በቀበሌ 05 አንድ ወር ከአምስት ቀን እንደቆየን በ21/11/71 በቀበሌ 07 ወደ ነበረው ፖሊስ ጣቢያ ተዛወርን:: ሌሎችንም ከየነበሩበት ቀበሌ ወደ ፖሊስ ጣቢያው በጥቂት ቀናት ውስጥ ሰበሰቡአቸው:: በዚያም ከእኛ ቀድማ ከአለታ ወንዶ የመጣች የባንክ ቤት ሠራተኛ እህት አልማዝ ታደሰ ነበረች:: በመቀጠል ከቀበሌ 06 ማናለብሽ መስፍንና አዳነ አለማየሁ፣ ከቀበሌ 03 ሙላቱ መለሰ፣ ከአፖስቶ መምህር በቀለ ኩምሳ ከሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያንና መምህርት እታገኘሁ ከይሖዋ ምስክር መጡ:: በዚህ ዓይነት ሁኔታ በፖሊስ ጣቢያው ተጠረቃቀምን::

## በአዲሱ ቦታ

የፖሊስ ጣቢያው አቀማመጥ ረባዳ ሥፍራ ላይ ሆኖ ሦስት የእስረኛ ማቆያ ክፍሎች ነበሩት:: የቀረው የጣቢያው ዋና አዛዥ ቢሮ፣ የምርመራ ክፍልና የዕቃ ማስቀመጫ ክፍሎች ናቸው:: እኛ እንደ ሄድን ከነበሩት ክፍሎች ወንዶቹ በሁለተኛው ክፍል ስንገባ ሴቶቹ አልማዝ በነበረችበት ክፍል እንዲገቡ ተደረገ:: በዕለቱ የተቀበሉን ወታደር ታዬ የሚባሉ ነበሩ:: እርሳቸውም ከፈታተሹን በኋላ እየገፈታተሩ አስገቡንና ዘጉብን:: በአዲሱ ቦታ የተደረገልን አቀባበል ይህን ይመስላል:: ቀጥሎ የሚጠብቀንን ገና አላወቅነውም:: ለማንኛውም፣ ዕቃችንን አስቀምጠን ስሌናችንን ዘረጋግንና ጥቂት ጌታን አመስግነን እረፍት አደረግን::

በዚህ ሥፍራ - በፖሊስ ጣቢያው - ጌታ ወደ ልቤ ያመጣው ቃል በመጽሐፈ ኢያሱ 1:3 ላይ ያለ *የእግራችሁ ጫማ የሚረግጠውን ቦታ ሁሉ ለእናንተ ሰጥቼአለሁ* የሚል ነበር:: ይህ መጀመሪያ ለእስራኤላዊያን የተሰጠ የተስፋ ቃል ቢሆንም፣ ለእኛም ከአንድ እስር ቤት ወደ ሌላ እስር ቤት በተወሰድን ቁጥር መሪ ቃላችን ሆነልን:: እግዚአብሔርም፣ እንደ ቃሉ ደርሰን የረገጥነውን ሥፍራ ሁሉ እያመቻቸ ሲሰጠንና ቀስ በቀስ ከቁጥጥራችን ሥር ሲያደርግልን በዓመታት ውስጥ አየን::

የፖሊስ ማቢያው ክፍል፣ መጀመሪያ እኛ ስንገባበት ቆንጆ የወረረውና መጥፎ ጠረን የሞላው ነበር። እኛ ለንፅህና ከጀመርን በኋላ ግን ያ ሁሉ ተለውጧል። በመጀመሪያ እንደ ልዩ ፍጥረት አድርገው ይመለከቱን የነበሩ ወታደሮችም ሊያናግሩንና ሊጠብቁን በትተዋል። እንግሊዝ ኤምባሲ በየደናቸው ራት ምግብን ስጥቶን ነበርና።

የአውራጃው ፖሊስ አዛዥም በሆኑ መጀመሪያ ላይ ተበሳ ወሰጥ ሲያገኙን ያሳዩትን ንቀት የኋላ ኋላ እየተው ሲመጡ ተመልክተናል። ከተበሳው ወደ ፖሊስ ማቢያ እንድንዛወር ከተደረገ በኋላ በተም ሳይዘገዩ በመምጣት ሲያነጋግሩን በአለባበስ በሚያሳዩት አኳኋን ነበር። ያም እኛን እንደገና በማግኘት ለማየናት የተያዘ ግብዝ እንደሆነ በለገመትን ተለዋዋጭነታችን በተም አልሳበውም ነበር።

በመጀመሪያ እንደ መጡ ወደ ፖሊስ ማቢያው ጽ/ቤት አስጠርተውን ስማችንንና ሥራችንን እንደ በአንድ ጠይቀውን ሲያበቁ፣ ስለ እምነታችን ነበር ያነጋገሩን ፦

- እውን የእናንተ እምነትስ እንዲጠብቁ አዝተዳረገ ነው! በጣሙ አዋቂዎቹ ያለውን ነገር አላስተማርኩህም? ፈረንጅ አታመልከም፣ አልፋ እታገዙም መሰለኝ።
- ለምትናገሉ። ይህ ለተደረገ ያለው ነገር ግን ለክርስትና ሃይማኖት ይለመጥል እንደ አያስፋልጉም።
- እንዴ! መምህሩም አለ።
- ምንም ቢመጣ ደስ ይለናል። ምክንያቱም የእንግሊዝኛ ቃል መልእክት ይዞልና መታገም የሚይዘውበት ሆኖው ይገባው ይልል። በዚህ በመጠራጠር ተን እንደምንገባ እናውቃለን።
- እንደምንገባ?
- አዎ እንደምንገባ እናውቃለን።
- ምን የተባለ ማንን አይታችሁአል?
- ሊያቦስ ክርስቶስን አይተናል። እርሱ ከሙታን እንደተነሣ በክርስቶስ ያመኑም እንደሚነሡ እናምናለን።
- ሊያቦስ ክርስቶስ ማነው? የት አለ?
- ሊያቦስ ክርስቶስ ጌታ ነው። የእንግሊዝኛ ልጅ ነው። በታላቅም የታወቀ ነው። ያ ከሐዋሪያም ዝርዝሩ ላይ የተጻፈው ወንጌል ፖለቲካ የክርስቶስን ሕልውና ይመስክራል። 1970…ዓ/ም የሚለው ከማን ልደት ጀምሮ ነው?

ይህን የሚመስሉና ሌሎች ምልልስ ካደረግን በኋላ፣ አዛዡ ሊያቦስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅና አምላክ አይደለም በማለት እንደገና የተለያዩ ታሪኮችን በመጠቃቀስ ላይ እያሉ፣ በልክ ተጸዕኖአቸውና አድርገው መናገር ጀመረ። ለለ ተን እንደሚወታለን በማለት ሲወጡ

- እርምጃ ወሰደው እትቀጥለም፣ እትሙት፣ ውሳ እየሰጠው አዋር ተ ተዘውቶ፣ ብሬይ መቶ ለሉን፣
- እኛ ሁልጊዜ በጌታ ደስ ይለናል። እናገምም አለናቸው።





- እርግጠኛም፣ እውነ ተወለዳችሁማችኋል! ቆታወርኛ ደሃ ትተዋላችሁ? በማለት እየተሳለቁ ወጥተው ሄዱ።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አዛዡ የትም ሥራፉ ክርስቲያኖችን ሲያገኙ እምነ መሞናቸውን ጠይቀው ሲያረጋግጡ በመተባበል የሚጠይቁት ጥያቄና እለባበው ጥያቄ፦

- እሁ - ምንሁ ትትገባለህ? የሚል ሆኑ። እኔንም እንደ ተን በንዴት
- ሰዶ ጥፋግ ሊበዛ ምንሁ ትትገባው በለውኝ ነበር። ጭለው ጊዜ ስለ ትምህርቱ በቢጋራ ከመጽሐፍ ትዳስ መልእክት ይዘሌ። የሚለውን ዋነው እንደጠጣበን በማለታቸው ነበር አዛዡ ጥፋግ ሊበዛ ያሉት።

በሌላ ጊዜ፣ እንደ ተን ጠዋት፣ እኔን ከሌሎች ወንድሞች ጋር በአንድ ክፍል እንደማደር ተመልክቶና ለፖሊስ ማቢያው አዛዥ፣ ለምግባል ቁጥ ተበተሚጊኢል፣ እርሱን ለብቻው እሥረው የሚል ትዕዛዝ ስጥተችው ሄዱ። ምክንያቱም የእነርሱ፣ የዝርዝሩ አስተማሪ እኔ እንደ ሆንኩ በለቀጠሩ ነው።

በምግባቱም ተመልሰው ሲመጡ እኔ እዚያው እንደነበርሁ ሲያዩ በማቢያው አዛዥ ላይ ተቆጥተው ለምን አላስወገድኸውም? በማለት ጮኹባቸው። የምግባል ቁጥሩ፣ በእኛ ላይ የተሰጠ ጫና ከማይደር ይልቅ፣ የሚፈራራለን በለነበሩ፣ እኔን የማስወጣቱን ጉዳይ ችላ ብለውት ነበር። በዚህ ጥያቄ አዛዡ፣ ለብቻ እለምጠው በማለት ድጋሚ ትዕዛዝ ሰጡ። እኔም በትዕዛዙ መሠረት እርሳቸው እያዩኝ ከእስርኮቹ ወጥቼ ሌላ ክፍል ገባሁ። በመጠራጠርም፣ ጥያቄው አዛዡ፣ እውን ደግም እዚህን ለምን ለሰጣቸው አለና ተመልሰው ሔዱ።

በ1971 ክረምት መጠረሻ ላይ፣ የደርጋ ግፍም ከተማ የመጀመሪያዎቹ የአብዮት ጥበቃ ጓዶች ሲሰማሩ፣ ስትከታታይ ቀናት፣ ወደ ጎጋት እየሄደ፣ በፋሚ፣ ወታደራዊ ወኪት እያሰሙ ሲያልፉ መስማት ጀምረን ነበር። በዚህ ወቅት ደግሞ ጥያው የፖሊስ አዛዥ ከውነት ለእኛዎችን እንደገለፁን ዛቻው እውን ለለፉት ወቅቱ ለልዋኞች ጋር ሴሰለፍናቸው በማለት ሲቀኛም ወንድቹም ማፍናር ጀመሩ። እሰሩና ጊታሁን በመጀመሪያ የቀየና ከዚያ በኋላ እንደ ጃ ሊትየቀያሮ ተተግሪ ለሌላገን አሉ። እስሩኛ ሆኒ እለለሰገም ማለታቸው ነበር። ለሌቶች ደግሞ በማለቸው፣ ጊዜ ወቢሮ ለአለቢና የእግዚአብሔርን ፈቃድ እውነቱ በኋላ መለለን ለበምአለ። ከዚያ በኋላ እሰሩና ጊታሁንን ዘሌቸውና እኔ ወላሁበት ክፍል እንዲጠራሩ ትዕዛዝ በመስጠት ከእዮው ጋር እለለው ይለለያ ብለው ሔዱ።

በለለውም ተን እንዲሁ የፖሊስ አዛዡ በዚሁ ጉዳይ እያነጋገሩን ባለ የአውራጃው ጥና አስተዳዳሪ ከተፍ አሉ። የወታደር ልብስ ለብሰዋል። ከምርኮት ሥራፉ ምናልባት ስሞቱን ግድት ከተፈጠረበት ክፍል ወረዳ የሚመጡ ይመስለኛል። ጊዜው መሸት ብሏል። ጥያው አዛዥ ስለእኛ ለአብዮት ጠባቂት ቁልጣናቸው ነው ይለቸዋል። አስተዳዳሪውም ለለ አለልገው አለሩኝ! በማለት ተተጠገቤቸውን ሲያዩ ነገሩ በዚሁ ተቋጨ። ያቺ ሌሊት እኛን ከፈተናው ለማውጣት የመጣች የእግዚአብሔር እጅ ነበረች ብለናል።

በአንድ ወቅት፣ በዚያው ክረምት ውስጥ፣ የአውራጃው ካድሬም ወደ ፖሊስ ጣቢያ መጥተው አነጋግረዉን ነበር:: በንግራቸው መሐል ለእኛ የጥያቄም ሆነ የመናገር ዕድል ብዙም አልተገኘም:: የሚለማንን «እንድንተነፍስ» ባይፈቀድልንም በእኛ በኩል ጥቂት ጥረት ግን አደረግን:: እርሳቸው ግን እንደ በቀደሙ በቁጣና በዛቻ የተሞላ መልእክታቸውን አሰምተውን ሄዱ:: ዋና ዋና ነጥቦቹም የሚከተሉት ነበሩ፡-

- *ማንም እንዲናገር አልፈቅድም ::*
- *አቋማችሁን እያንዳንዳችሁ በተሰያየ ወረቀት ጽፋችሁ መግለፅ አለባችሁ::*
- *የአንዱ ሃሳብ ከሌላው መመሳሰል የለበትም ::*
- *የምንነጋገረውን እዚሁ እንነጋገር እንጂ የምንጽፈው ነገር አይኖረንም* አለች፣ *መቆየቴ ::*
- *አንዳንድ የንዑስ ከበርቴ ቅብጥብጥ ጠባይ ያጠቃቸው፣ መፈክር እሰምተው ለክረምት ኮርስ ሄደዋል::*
  *ሌቦች ናቸው!.....::*
- *ሌላው ስንቅ እየተዘጋጀ ስለሚመጣለት ተቀምጦአል ወዘተ ...* አሉ፣ ካድሬው::
- *እርስዎ አስተማሪአችን ሆነው ከመጡ እኛም እንደ ተማሪዎች የሚኖ ረንን ጥያቄ ይቀበሉ እንጂ! ለምን የመናገር መብት ይነፍጉናል? (ተስፋዬ)*
- *ዝም በል ሌባ አወናባጅ ! ለእናንተ ደግሞ የማወናበጃ መድረክ ማንም አይከፍትላችሁም::* (ንግግራችን ግራ እንዳያጋባቸው የሰጉ ይመስላል::)
- *ሩቅ እንዳይመስላችሁ፣ ትናንት በኢህአፓ ላይ የተፋፋመው ቀይ ሽብር ነገ በእናንተ ላይ ይፋፋማል:: (ካድሬው)*
- *ስለ ክርስቶስ መሞት ክብር ነው (ተበፋዬ)::*
- *ዝም በል ሌባ አወናባጅ! በተለይ አንተ ቆይ ጠብቅ!(ካድሬው)*
- *ማን ? እኔ?*
- *አዎ በተለይ አንተ ፤ ጠብቅ ታገኛታለህ!*
- *ምንድነው? ግፋቢል ጥይት ነው!* አለ፣ *ጌታሁን::*
- *ዝም በል ! ላንተ ደግሞ ጥይት ማን ያጠፋል? ሆነ፣* ምልልሱ::

ውዝግቡ በዚሁ አበቃና ካድሬው ተመልሰው ሄዱ:: ሁኔታዎች እየተለዋወጡና እየተጨማመሩ፣ እየከባበዱም **ቀጠሉ**:: ሦስት ወር ተፈርዶባቸው ከአለታ ወንዶ ወደ ይርጋ ዓለም ማረሚያ ቤት የተላኩና የተወሰነባቸውን ጊዜ **ለመጨረስ** የተ ቃረቡትን የፕሮቴስታንትና ያይሆዋ ምስክር አማኞችንም እኛው ወዳለንበት ጣቢያ አመጡዋቸው::

እነርሱም:-

1) አቶ አዲሴ ቀልብለው - ከቃለ ሕይወት - **መምህር**
2) ወ/ት ሙሉእመቤት መንበረ - ከሕይወት ብርሃን - መምህርት
3) ከበደ እርጋው - ከሙሉ ወንጌል - ተማሪ





4) ወ/ሮ ሕይወት - ከይሖዋ ምስክሮች - የቤት እመቤትና ነጋዴ
5) ወ/ሮ ብዙነሽ - ከይሖዋ ምስክሮች - የስልክ ኦፕሬተር -
6) አቶ በላይ - ከይሖዋ ምስክሮች - የግል ስራ ያለው - ነበሩ::

እነኝህን ለምን እንዳመጧቸው አልገባንም ነበር:: ምናልባት በአንድ ላይ ለብስበው ***ትምህርትና ምክር*** ሰጥተው ሊለቁን ይሆናል ብለው የገመቱ የዋሆችም አልጠፉም :: ምክንያቱም፣ ለግርፍ ነው እንዳይባል፣ ከተገረፉ በኋላ ነበር ሦስት ወር የተፈረደባቸው :: በተለይም ሙሉ እመቤትና ከበደ እርጋው፣ ተሰቅለው የውስጥ እግራቸውን በጊዜው ከነበሩ ከማናቸውም ክርስቲያን እስ ረኞች ያበልጥ እንደ ተገረፉ ሰምተናል :: የከበደ የውስጥ እግር ቆዳም፣ ለተ ወሰኑ ወራት እየተገለፈፈ ሲነሣ እኔም በዓይኔ አይቻለሁ:: ከግርፋና ከወህኒ እስራት ወዲያ ምን ቀራቸው? የሚል ጥያቄ አልጠፋም ነበር:: ገና ተጨማሪ መከራ እንደሚኖር የጠረጠረ ብዙ ሰው አልነበረም :: ሰውን በማስቃየት የመደሰት ባሕርይ ላለው ግን የማሰቃያ ዘዴዎች መች ያልቁበትና !

እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁንና በማንኛውም ሁናቴ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ልባችንን የሚያጸና መልእክት ከማስተላለፍና እኛን ከማዘጋጀት ወደ ኋላ አላለም::

በዚያ ክረምት ውስጥ መንፈስ ቅዱስ በመጪው ሁኔታ ላይ አጥብቄ እንድፀልይ ይገፋፋኝ ስለነበረ የ17 ቀን የፀሎት ጊዜ ወስጄ ነበር:: በዚህ ወቅት ቀን ቀን ምግብ አልበላሁም :: እነዚህ ቀናት እጅግ ከባድ የሆነ የመንፈስ ውጊያ ቀናት ነበሩ :: ስፀልይ የትግል እንጂ የመፅናናት ስሜት አልነበረኝም :: ፍሬ አልባ መቃተት የምቃትት መስሎኛል፤ ቢሆንም ገፋሁበት :: በኋላ እንደ ተ ገነዘብኩት፣ እነዚህ ቀናት በመንፈስ ቅዱስ አሳሳቢነት፣ በሰይጣን ላይ በመቅደም ጦርነትና ጽኑ ግብ ግብ የተገጠመባቸው ቀናት ነበሩ:: ጸሎቴን ባበቃሁበት ቀን ጌታ ዳሰሰኝ:: በዚያ ቀን ያለወትሮዬ እጅግ ተነቃቃሁ:: የድል አድራጊነት ስሜትም ነበረኝ:: ለብቻዬ በነበርሁበት ክፍል ውስጥ በቀስታ፣ በልሳን እየጸለይኩ እግዚአብሔርን አመሰገንሁት::

በጸሎቴ ቀናት ውስጥ፣ በእግዚአብሔር ፊት የቆየሁት ዕብ 4፤16 ላይ የሚገኘውን ቃል በልቤ ይዤ ነበር :: ቃሉም ***«እንግዲህ ምሕረትን እንድንቀበል በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ እንድናገኝ ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት እንቅረብ::»*** ይላል:: እኔም፣ በሚያስፈልገን የድብደባ ጊዜ፣ ልባችን እንዳይዝልና እምነታችን እንዳይላላ የሚረዳንን ፀጋ እንድናገኝ፣ መንፈስ ቅዱስ በእነዚያ 17 ቀናት ውስጥ እንደ ማሰደልን ተገነዘብኩ::

ጸሎቱን ካበቃሁበት ቀን ጀምሮም ተራ በተራ ሁኔታዎች እየከባበዱ መጡ:: በማግሥቱ *ሁላችሁም ለሥራ እንድትወጡ ተብሎአል* አሉን:: አልማዝ ታደሰን ጨምሮ እንዳንዶች፡- *መና - የእስረኛ ቀለብ - በሌለበት ሥፍራ ነው ያለነው:: ብፈልግ ላልወጣ እችላለሁ:: ወደን እንጂ ተገደን እንሠራም* አሉ:: በአልማዝና በዘበኛው መካከል ትንሽ ጭቅጭቅ ሆነ:: የሆነው ሆኖ ገሚሉ ቁርሱንም- ከገብስ የተዘጋጀ በሶ - ሳይበላ እዋክበው እወጡን:: ከዚያም በአብዮት ሎራ ት/ቤት

ትግር ግቢ የገበረውን የወቅሉ እንዳመራ ውስጡን በባንጋና በተገኘ ነገር ሁሉ እየመከበርን፣ ሲቶቹም ሳግ ቢለበልባቸውም «ሃሽ ሃሽ - እለይ እለይ» እያሉ ሲሳሱቁ ዋልጎና ነባን።

ከሰዓት በኋላ የአውራጃው ፖሊስ አዛዥና ካድሬው እየከነፉ መጡ። «እሳት ለብሰው እሳት ጎርሰው» እንደሚባለው ዓይነት ነበር የሚታዩት። በብሔርና በእናንተ ማኅው ላይ በግመልከት አስተዳደር አዋዩ ሐዲ የገበረው? እኔና ጓደኞቼ ፊት በፊ ደስል ፈገግ ነው። ከሊ እኛ ሥራ ቢታ ወሰን ነው የመጣው። አስተዳደር አዋዩ ማናቸውም አልፈርም የሚል ምላሽ ሰጠን። ጥያቄው ተቀየረ።

- ለእናንተ ማኅው ሥራ አለመኖም ያበ? አለ።
- ወታደሩ አልማዝ ናት አለ።
- አልማዝ ለምንድነው አለመኖም ያልሽው?
- መና - መንግሥት ለአለፍ የሚያቀርበው ተዕብ - በአለበት ነው ያለውን፣ ብሎሚም ወርደ ነው እንጂ ወገድ አለመኖም - አልደረርም አለች።
- መና በአለበት እንደንተመጥ ተደርጎ ለምንድነው ጉለበታችሁን የምንጋብበው? አለ በተለ ከንግ ደገም።
- ጉለበቱ ተወበበ ኳስ ውጭና ታገለ! ጉለበቱ ተወበበ እያቸው እዚሁ እዚሁ ላይ አብታድ ታላተ እየተከሚጨልቸው ትናንሌችው። ውጭና ታገለ። አለበለደ በሌሁ ታርጋታለሁ ! አለ ካድሬው።
- ላይ የመጣው ወደፊቱሁ ሳይሆን ተገሶቹሁ እንደምትመሩ ልንገንራችሁ ነው። መና ትተላችሁ፣ የእናንተ ምግብ በለላው እንጂ የሚተርፍ ነው የሚል የሚያበበርም እኒጋጉር አለምተውን ሐሳ።

ግን ይህን እንደፉት ሊናገሩ ቻሉ? ከሰአቱ እንደ ተን ገበሬ በዋላ የሚባል በሌ በኋት ተወርጥር፣ የተያዘ አስረኛ የአውራጃውን ፖሊስ አዛዥ ሽሬ ቤርቁ ምንትሆቹ ፍርድ ቤት አቅርቦኝ በማለት ሥሙቸው ነበር። አለካ ላይ እንደፉት ቀየሁ ? ቢሉት ወደ እኛ እየመሰከተ፣ አገዛር ይለማቸውና እነዚህ እየሰውኝ ነው በማለት የመለሰው ተደዞ ናሬል ማለት ነው።

እኛ እንዲ ተርፎን ሳይሆን፣ ሳያመገበን ከሚያደትብን ምግብ አየተረሰን፣ ከሰብእዊ ርኅሩኅ የተነግ ያከፈለነው ነበረ። ሆኖም ይህ አድፉትት ምግብ እንደሚተርፈን አስቆጠረብን። በሩት ፊቱ ውስጥ አስተምሮ፣ ከልተወበቱ እትመጨ፣ ዝሄን አ ልያስን የመገብ አምላክ የእኛም አባቢ እባት ነውና ፣እንዲገሌ ምስ ቁርጥ እሬት አለለማገም። በተድስትም ሆነ በመላት ለእርሱ ክብር እየሰጠን ተደስተን ስለናርን ግን ሁሉ የምላና የተፈፈን መስከል። በወደፍና በጭንቅ ሥፍራ እብርን በመግለት በፃሃቻ መሐል ፍትርን፣ በሁከት መሐል ሰላምን፣በረሃብ መሐል ምግብን፣በጥማት መሐል ተዘቀለ ውኃን፣ጉለበቱ ዓለቀ ጊዜ ኃይልን፣ ተስፋ ባለሆነ ጊዜ ተስፋን እየሰጠ፣ እኛን በማንቃቱ በመመሰከሩና በመምራት ውስታ የሆለለን ግን እግዚአብሔር ብቻ ነው።





እንገዳሁ፣ ከተወለና ከለላው አበር ቤት እንደንወረታተም የተደረገነበት ይህ እዳስ ቦታ፣ በአመቢት ቢታላት ገዝገዝ የተፈተንገበትና እላፊዎቻችን ወገኝር ሰገል መጨ ሁኔታ እኛን እያዳገጂ ያቀዋት ነበር ማለት ይቻላል።

«የመከራ ገም»

የመከራ ገም በላይ ቢያገኛቸዉ
እስና ሊያነሱ ፍጹም አታቱበ
ቢመለበሁ ዝናው ፍጹም ተፈራ
ደጋፊ እለሁ ምንም አትፍሩ
ተራመድ ንዝማም ሬደም
ሕይወትህንም አድን

ከንግሥታት በፊት፣ ይህን የተተኘተተ፣ የመሉ ወንጌል ዘማርያን ነበር። የመከራ ገም ምን እንደሆነ ይበልጥ የሚገባው ያ ገም በላዩ ሲመጣበትና ሲያልፍበት ያ ሰው ብቻ ነው። ስንገኝ ወደ እስሱ ወር ማንቲያ ላይ፣ የዓለ ሥልጣናቱ ፊት ከወተርው በቦየ መገድ ከበር ወሰቱለ። የዓለ ሥልጣን ፊት አየበደ በመጣበን ቁጥር ደግሞ ወደ እእምሮአችን የሚመጣ እንደ የመድሐፍ ትዳሰ በመማበን ነበር። በሐዋርያት 31:3 ላይ የሚገኘው ይህ የገባበ ክፍል እንደዚህ ይነበባል፦

የአቢታችሁ ፊት ከእኔ ጋር እንደ ዱር እንዳልሆነ አያለሁ ነገር ግን የአባቴ አምላክ ከእኔ ጋር ነው ።

ይህ ቃል፣ ያዕቆብ ለራሔልና ለልያ የተናገረው ነበር። ያዕቆብ አባቱ የሚለው በመጀመሪያ ደረጃ ይሰሐትን ሲሆን፣ የአባቱ አምላክ የአያቱ የአብርሃም በመጀመሪያ ደረጃ ይሰሐትን ሲሆን፣ የአባቱ አምላክ የአያቱ የአብርሃም ፈርዖንና አቢሜሌክን አምላክም ነው። እግዚአብሔር ስለ አብርሃም ፈርዖንና አቢሜሌክን ገሥጸአል። ስለ ይስሐቅም ቢሆሚሌክ፣ ብእነዚትና በፊኮል ላይ ፍርዶትን ሰይፈለ (ዘፍጥ 26:26-31)። መዝሙረኛው በመዝ 105:14፣ 15 የሚናገረውን አተኮቡል። በቢያዩም ክፉ እንደርጉ ብሎ ሰው ግና ያደርግባቸው ዘንድ አልፈቀደም። ስለ እነርሱ ነገሥታትን ገሥጸ ያለው ይህንን በማስታወስ ነበር።

እግዚአብሔር የመጻተኞች ጠባቂ ነው። ያዕቆብን በአገግደሁቱ አገር ጠብቆታል። ከወንድሙ ከዔሳው በሸሸ ጊዜ፣ በመንገድ ተገለጦለት ብዙ የተስፋ ቃል የሰጠት ከወንድሙ ከዔሳው በሸሸ ጊዜ ተገለጦለት ጋር እንደሆነ በመገለጥ ያዕቆብ ይጸናናል። ስለዚህ አምላክ፣ አሁንም ከእርሱ ጋር እንደሆነ በመገለጥ ያዕቆብ ይጸናናል። ስለዚህ የራሔልም አባት የዓለ ፊት ቢለወጥበትና ቢክደበት፣ ፊቱ የሚያበራለር አምላክ እብርት እንዳለ በማረጋገጥ ነገር ግን የአባቴ አምላክ ከእኔ ጋር ነው አለ።

መለወጥ በእርሱ ዘንድ የሌለ፣ ሕያውና ዘለዓለማዊ የሆነው የአባቶቻችን አምላክ፣ በእያንዳንዱ ሁኔታ ውስጥ ከእኛም ጋር ነበረ። ይህናልም። ሐዋርያው በእያንዳንዱ ሁኔታ ውስጥ ከእኛም ጋር ነበረ። ይህናልም። ሐዋርያው ጳውሎስም ጊዜ ቢሆን ለመሞት ቆም አበረታች ከእነዚህ እናም ብቻም እንዳለ

ሁሉ፣ እኛም ከጌታ አጋርነት የተነሣ ብዙ ጊዜ ከከፋ ነገር ስንድን እናያለን፡፡

ከፍ ብሎ ከላይ እንደተጠቀሰው፣ የባለሥልጣናቱ ፊታቸው ብቻ ሳይሆን፣ ንግግራቸውም፣ የሚጭኑብን የችግር ቀንበርም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከባበደ መጥቶአል፡፡ ለአንድ ጠንከር ላለ እርምጃ የተዘጋጁ ይመስላሉ፡፡ የእኛም የልብ ጭካኔ፣ ከጌታ ጸጋ የተነሣ፣ እየጨመረ ሲሄድ ይታወቀን ነበር፡፡ በምን ቀን ምን ነገር ሊሆን እንደሚችል ግን ስለማይታወቅ፣ በእኛ በኩል የነበረው አማራጭ ሁኔታውን በጥርጣሬ መከታተል ብቻ ነበር፡፡ ሌላው ቀርቶ በሌሊት ከነበርንበት ፖሊስ ጣቢያ በር ላይ ደርሳ የምትቆምን መኪና ለማመን አስቸጋሪ ነበር፡፡ መኪናዋ ምን ልትሠራ አምሽታ እንደ ተላከች እስካልታወቀ ድረስ፣ ሞተርዋ ዳግም ተነስቶ ከሠፈራችን እስከትርቅ ድረስ፣ ጆሮአችንም ልባችንም ይከተላት ነበር!

የምናከናውነውም የጉልበት ሥራ በየቀኑ ቀጥሎአል፡፡ እየተያዙ ከእኛ ጋር የሚደመሩ ታሣሪዎችም አልጠፉም፡፡ አብነት አሰፋ፣ማርታ ጋዲሳና ሰናይት ተሰማ አንድ ቀን ሊጠይቁን በመጡበት የአውራጃው ፖሊስ አዛዥ አገኟቸውና አስገቧቸው፡፡ አብነት ከአዲስ አበባ የመጣችው፣ የማትሪክ ውጤትዋን ልትወስድ ነበር፡፡ አሳብዋ፣ እግረ - መንገድዋን እኛን ጠይቃ ልትመለስና ኮሌጅ ልትገባ ነበር፤ በዚሁ ቀረች እንጂ! ማርታ ጋዲሳ ግን፣ ምግብ ይዛልን ነበር የመጣችው፡፡ ከፖሊስ አዛዡ ጋር፣ *ከቤት ነው ይህንን ምግብ ያመጣሽው* በሚል ጥያቄ ጥቂት ውዝግብ ከሆነ በኋላ እርስዋም ገቢ ሆነች፡፡ በዚህ ሁኔታ ጳጉሜን አልቆ መስከረም ገባ፡፡

ዕለቱ መስከረም 5 ቀን 1972 ዓ/ም ነበር፡፡ ገና ከጠዋቱ እጅግ አድርጎ ሲጠላን የቆየ ወታደር ወደ ክፍሎቻችን ድንገት በመግባት መኝታችንን - ሰሌናችንን - እያገላበጠና የብርድ ልብሳችንን እያራገፈ ፍተሻ ጀመረ፡፡ ከዚያ ሁሉ ብርበራ በኋላ አንድ አዲስ ኪዳን አገኘና ይዞ ወጣ፡፡ ለካስ ከሴቶቹም ሆነ ከእኛ ከሁለተኛ ክፍል አንዳንድ አግኝቶ ኖሮአል፡፡ አብረውን ታሥረው የከረሙ የሚሊሺያ ሻምበል፣ የምናነበው መጽሐፍ ቅዱስ እንዳለን ሳይጠቁሙብን እንዳልቀሩ ለምተናል፡፡

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ም/የመቶ አለቃው መጡ፡፡ የመጡት ተጠርተው ይመስላል፡፡ በመቀጠል ወታደሩ የዕለቱን ሁናቴ ሪፖርት አደረገላቸው፡፡ ሪፖርቱ ሲያበቃ ም/የመቶ አለቃው ወደ የክፍሉ በመግባት የአዲስ ኪዳኖቹን ባለቤቶችና ከየት እንዳመጡአቸው ጠይቀው አረጋገጡና እኔ፣ አዳነና ጌታሁን ወዳለንበት ክፍል መጡ፡፡ ከዚያም የምርመራ ጥያቄው ቀጠለ፡፡

- *ይህ አዲስ ኪዳን የማነው?*
- *የሦስታችንም ነው(የጌታሁን ምላሽ)*
- *እንዴት የሦስታችሁም ይሆናል? የግድ የአንዳችሁ መሆን አለበት፡፡*
- *የሦስታችንም ፡፡*
- *የማነው ይህ አዲስ ኪዳን - አዳነ -?*
- *የሦስታችንም ፡፡*
- *የማነው ይህ አዲስ ኪዳን - ተስፋዬ -?*





- *የሦስታችንም ፡፡*

ወጥተው ሄዱና እንደገና ተመልሰው በመምጣት ያንኑ ጥያቄ ጌታሁንን ሲጠየቁት ጌታሁንም ያንኑ ምላሽ ሰጣቸው፡፡ ተበሳጩና የጌታሁንን ግንባር በጫማቸው ተረከዝ ሲረግጡት ከቅንድቡ አካባቢ ደሙ መፍሰስ ጀመረ፡፡ ደግመው ጠየቁት፡፡ አሁንም ያንኑ ምላሽ ሰጠ፡፡

- *ይህ ጋዜጣ የእኔ ነው አሉ በእጃቸው የያዙትን ጋዜጣ እያሳዩ፡፡ ግን እኔና ጓድ መንግስቱ ልናነበው እንችላለን፡፡*
- *እናንተም እንዲሁ ይህችን አዲስ ኪዳን በጋራ ልታነቡአት ትችላላችሁ፡፡*
- *የአዲስ ኪዳኑ ባለቤት ግን ከእናንተ አንድ ሰው መሆን አለበት፡፡*
- *ተስፋዬ - የማን ነው ይህ አዲስ ኪዳን?*
- *የሦስታችንም ነው፡፡*

በእኛ በኩል እንደዚያ ባለ ሥፍራ በመካከላችን የተገኘ ማናቸውም መንፈሳዊ ጽሑፍ የሁላችንም ንብረት ይሆናል እንጂ እንደግል ንብረት ሊታይ የማይቻል ነበር፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ማንኛውንም መጽሐፍ ከክፍል ወደ ክፍልም እየተቀባበልን ነበር የምንጠቀመው ፡፡ ውዝግቡ ግን ቀጠለና ወደ ምርመራ ክፍል ተወሰድን፡፡

- *ይህ የእልማዝ፣ ይህ ደግሞ የሙላቱ አዲስ ኪዳን ነው፡፡ ይህኛው የማነው ነው የምላችሁ ያለሁ፡፡*
- *የሦስታችንም ነው - አለ - ጌታሁን አሁንም ሳይፈራ፡፡*
- *አዲስ ኪዳኑ በጋራ የምንጠቀምበት የሦስታችንም ነው፡፡ ግን የእኔ ነው በል የሚሉኝ ከሆነ እሺ የእኔ ነው አለ አዳነ፡፡*
- *መሥዋዕትነት ለመክፈል ብለህ እንጂ የአንተ አይደለም፡፡*
- *እሺ ምን ልበል ከዚህ በላይ?*
- *ተስፋዬ*
- *አዲስ ኪዳኑ በጋራ የምናነበው ነው፡፡ ስለዚህ የሦስታችንም ነው፡፡*
- *ይህ መጽሐፍ ቅዱስ የማንበቢያ ሥፍራ ነው?*
- *እግዚአብዘሔርን ማምለክ ትችላላችሁ እኛ ከእናንተ የምንፈልገው መፈከር ብቻ ነው ብላችሁናል (የሚፈልጉት ግን መፈክር ብቻ* አለመሆኑን ቃላቸውን እየቀያየሩ መናገራቸው ባይዘነጋም)
- *ታዲያ እግዚአብሔርን የማምለኪያ ሥፍራ ይህ ነው እንዴ?*
- *እግዚአብሔርን በማንኛውም ሥፍራ ማምለክ ይቻላል፡፡*
- *እዚህ ማምለክ እንደማይቻል መች አጣኸውና፤ ቆይ ብቻ! እንዲህ እንደደረቅህ ትቀራለህ!*

  እሉና ወጥተው ሄዱ፡፡

የሚያስደንቀው ነገር ወታደሩ ያንን ሁሉ ፍተሻ ሲያደርግ በቀላሉ ሊታይ ይችል የነበረውን ትልልቁንና ሙሉውን መጽሐፍ ቅዱስ አለማግኘቱና ከየክፍሉ ትንንሹን አዲስ ኪዳን ብቻ ይዞ መውጣቱ ነበር። እርሱ በልቡ ባዶ እጃቸውን አስቀረኋቸው ብሎ ይሆናል፡፡ ለእኛ ግን፣ ጌታ የወታደሩን ዓይኖች ይዞልን ትላልቆቹን መጽሐፍ ቅዱሶችን አስተረፈልን፡፡
ይህ፣ ከፍ ብሎ የተጠቀሰው የመስከረም ወር፣ የተሰመደው የጉልበት ሥራ

እየተሠራበትና የተለያየ ወሬም እየተፈፈረባት ተገበደደ። እዚስ የተመረቀት የአብዮት ጥበቃ ጓዶችም እየተሰበሰቡ እኛን እንዴት እድርገው እንደሚቀጡ በመመከር ላይ እንደነበሩ ተዋሬሬ ወሬ ይደርሰን ነበር። የሁኔታው ክብደት እየጨመረ፣ አዳዲስና ያልተጠበቁ ነገሮችም መሆናቸው እየተጠለ ሄደ።

ተደም ሲል፣ ሚያዝያ 29 ቀን 1971 ዓ/ም፣ ፓስተር ተሾመ፣ ፓስተር ኃይሉና ደባልቄ፣ ከአውራጃው ፖሊስ ጣቢያ ወደ ዋናው ወህኒ - ማረሚያ - ቤት ተ ልከው ነበር። ዐሌያም እስከ መስከረም 29 ቀን 1972 ዓ/ም ድረስ ለ5 ወር ያህል ቆይተዋል። አሁን ደግሞ፣ ማለትም በ29/01/72 እኛ ወደቆየንበት ፖሊስ ጣቢያ እንዲመጡ ተደረገ። ከእነርሱም ጋር የደሆቹ ምስክሮች እምነት ተከታይ የሆኑት አቶ ነበሬ አጅናና ተማሪ ሥዩም ኪዳኑ መጥተዋል።

በማረሚያ ቤት ለወራት የከረሙትን ለምን ወደ ፖሊስ ጣቢያ እንዳመጧቸው ማናችንም ለማወቅ አልቻልንም። የአውራጃው ፖሊስ አዛዥና የአውራጃው ካድሬ ግን ወደዚያው፣ ወደ ማረሚያ ቤቱ፣ በመሄድ አንድ ቀን ሙሉ እነርሱን ገንዘብ እድርገውባቸው ተመልሰዋል። ምንም ይሁን ምን፣ በአንድነት የመሰብሰብ እጋጣሚ በማግኘታችን፣ እኛ ደስ ብሎናል። ጠቃሚ ዜናዎችና ምስክርነቶችንም በሌሁ እጋጣሚ ለመለዋወጥ ችለናል።

ማምሻውን፣ ስለ እኛ በነ እመለካከት የነበረውና ትጉሕ ታዳ እየለገ የምንወደው የፖሊስ ወታደር ሲመጣ ሁሌፊቶችን በሰው ብዛት ተጣበ ይመለከታል። ዛሬ ከማረሚያ ቤት የመጡትንም ያያል። እየ እየና ቢታ የማገም መሪዎች ልትሆኑ ነው! ሲል በቀልድ ተናገረ። የተመከረብንን ከፉ ነገር ለመንገር የመጣ ይመስላል። የመከረው ነገሩና የችግሩ ጭጋግም መገለጫችንን እየሸፈነው ሲመጣ ይታያል።

ይህም ቢሆን ያ፣ የተደገሰብንን መከራ እንድንገነዘብ ጌታ ራሱ ልባችንን አስጨነቀናል። እንተበል ዘንድ ያለውን መከራና እንተርፍበው ዘንድ የሚጠቅሙንን ክብርና ድልም አስተደም በቃሉ አመልክቶናል። እንዲህ ሲል፦

*በዓለም ሳላችሁ መከራ አላችሁ ፡ ነገር ግን አይዞአችሁ እኔ ዓለምን አሸንፌያለሁ(ዮሐ 16:33)።*
*ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል? መከራ ወይስ ጭንቀት ወይስ ስደት ወይስ ራብ ወይስ ራቁትነት ወይስ ፍርሃት ወይስ ሰይፍ ነውን?... በዚህ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን (ሮሜ 8 35-37)።*

## «አትሸበር በርታ»

በሌላም በኩል፣ በ29/01/72 ምሽት፣ ጌታ በመንፈሱ አማካይነት፣ አጽናኝ ድምጹን አሰምቶናል። በወጅብና በአውሎ ነፋስ ውስጥ መንገድ ያለው ጌታ፣ ጥልቅ በሆነ ሁኔታ ውስጥ አለፎ፣ ወደ ወዳጆቹ ልብ ይደርሳል።

በዚች ምሽት እኔና ፓስተር ተሾመ በአንድ ክፍል አብር የማደር ዕድል



አጋጥሞናል። በክፍሉ ውስጥ በመስከረም ሁለት ጥግ ላይ ታስሮው ከእኛ ጋር ጣቢያ የቆዩ አረጋውያን ነበሩ። እነርሱም፣ ፊደር ይዘው የገቡ በመሆኑ፣ እያበረታቱንናቸው፣ ከሲሾልስ በአማርኛ የሚተባበሩን መንፈሳዊ ስብከትና መዝሙር፣ ድምጹን ዝቅ አድርገን በናዝምትበት ቆይተናል።

ዛሬም ሰዓቱ ደርሶ ፊደሮችን በንዘቡት የዕለቱ መልእክት እትሩፊቢ ከሌፊያን 6፡10 ላይ በተረጠበ ጠጊታና በኃይሉ ችሎት የበረታችሁ ሁኑ አያለ ሰበከ። በመተጠልም፦

*ለምን ክፉ ይከፋሃል?*
*ጌታ የሰላ ደርሶሃል*
*በርሱም ያገዝሃል።*

*አትሸበር በርታ ተግል መንገድህን*
*በርሱም ሁሉ ይለየሃል ኃይልን*
*በትግሉህ ጌዜ አለሁኝ የሚልህ*
*የሰላ ዝግጅ ነው ከእሳት ውስጥ ሊያወጣህ።*
*ወገሬል ይዞህ መንተርህ*
*ተነግሮሃል ራት በሰዓትህ*
*እዲስ ነው ወይ መዓትህ?*
*አትሸበር በርታ...*

የሚል መዝሙር በለሆሳት ሲዘመር፣ ፓስተር ተሾመ በትኩት ብቻ አለቀሰ። ሁለት ምክንያቶች ሳያስለቅሱት እንዳልቀሩም ነግሮኛል። 1) እንዚህን የአዲስ አበባ መሉ ወገሬል መዝሙራን በትርብ ያውቃቸዋልና ትዝታው ሳይመጣበት አልቀረም። 2) አትሸበር የሚለው መልእክት ልክ በወቅቱ የመጣና አስፈላጊ ነበር። እግዚአብሔር ለልብ ሲናገር ምንኛ እንዳሚደ ጌዜ የዕቃ ሰዓን ይችላል። በእርግጥ፣ የምሽቱ መልእክት ለሁላችንም የመጣ ነበር። እጽናኝኙን እግዚአብሔር ከዘ ጀምር በሚሆነው ነገር አትሸበሩ፣ በርቱ እያለ እለን ማለት ነው።

## ጭካኔው ሲገለጥ

*የዚያን ጊዜም ናቡከደነፆር በሲድራቅና በሚሳቅ በአብድናጎም ላይ ተቆጣ ... የእቶኑም እሳት ይነድድ ከነበረው ይልቅ ሰባት እጥፍ እድርገው እንዲያነድዱት አዘዘ። ሲድራቅንም ሚሳቅንም አብድናጎም ያስሩ ዘንድ ወደሚነድደውም ወደ እቶን እሳት ይጥሉአቸው ዘንድ በሠራዊቱ ውስጥ ከነበሩት ኃያላን አዘዘ (ዳን 3:19-20) ።*

ሲይጣን ያሰራተውን ቀጣና ጭካኔውን በአደባባይ የሚገልጥበት ጊዜ ደረሰ ሰለሆነም፣ በመጀመሪያ፣ ከጠባቃው በፖሊስ ጣቢያው ውስጥ ስንሰቃይበ የቆየነው፣ ወደምንተለው እንድንገባበት ተደረገና ሁኔታው ተመቻቸ። ቀተናውም፣ መስከረም 30 ቀን 1972 ዓ/ም ተጀመረ።

በዚሁ መሠረት፣ ለምንቱ ወገኖች፣ ፓስተር ተሾመ ወርቁ፣ ፓስተር ኃይሉ በቀለ፣ አቶ ነበሬ አጅና፣ ተማሪ መቶቲ ከበደ፣ ተማሪ ማርታ ጋዲሳ፣ ተማሪ ወርቅነሽ ይመር፣ ተማሪ ምንትዋብ እሬና፣ ከፖሊስ መምሪያ ደግሞ ተማሪ

እሸቱ ገዳን ጨምሮ ወደ ቀበሌ 05 ተላኩ:: የአውራጃው ፖሊስ አዛዥ *የአብዮት ጥበቃና የቃሬር አባላት ትምህርት ይሰጡአችኋል:: እኛም እየመጣን እናናግራችኋለን* ብለው ሸኟቸው::

አቶ አዲሴ ቀልብበለው፣ ደባልቄ መስፍን፣ ማንአለብሽ መስፍን፣ እብነት እሰፋ፣ ወ/ሮ ህይወትና አቶ በላይ ወደ ቀበሌ 08፣ ለገስ ቀቀቦ፣ ከፖሊስ መምሪያና ሙላቱ መሰለ ከዚሁ ከእኛው ዘንድ፣ ወደ 03 ተላኩ ::

ወ/ሮ ብዙነሽ፣ ወ/ሮ አታገኝ፣ ወ/ም ከበደ አርጋው፣ መምህር በቀለ ኩምሳ፣ ከዚያው አካባቢ ማርታ አሰፋን፣ ሃና አሰፋንና አየለ አበራን ጨምሮ ቀበሌ 01 (አፖስቶ) ተመደቡ ::

ሙሉ አመቤት መንበረ፣ አልማዝ ታደሰ፣ አዳነ ዓለማየሁ፣ ጌታሁን አጋፋሪ፣ ለዩም ካዩሰና እኔ፣ እዚያው ቀበሌ 07፣ ክልል በነበርንበት ፖሊስ ጣቢያ ቀ ረን ::

ከረምቱን ሁሉ ሲያጠራቃቅሙን ለምን እንደ ቆዩ አሁን ገባን:: የሰይጣን የቁጣው ትኩሳት የሚለቀቅበት ወቅት ስለ ደረሰ እንደሆነም ተገነዘብን:: ከጥቅምት ወር መጀመሪያ አንስቶ፣ በተለይም እስከወሩ መጨረሻ ድረስ፣ በየቀበሌው የተፈፀመብንን ጭካኔ የተሞላበት ድርጊት ዘርዝሮ ለመጨረስ፣ ሰፋ ያለ ጊዜና በዛ ያለ ምዕራፍ ይጠይቃል :: ስለዚህ፣ ከተነሣንበትም ዓላማ አንጻር፣ በዚህ ሁኔታ ላይ መጠነኛ ነገር ብቻ መግለጹ የግድ ይሆናል::

ከብተናው በኋላ፣ በ07 የቀረነው በ06 ቀበሌ ለነበረው የድግስ ዝግጅት ውኃ በበርሜል እየሞላን ከ05 ቀበሌ ወደ 06 ስንገፋና ስናንከባልል ዋልን:: መንገዱ ጭቃማ ነበር:: የእውራጃው ፖሊስ አዛዥና ካድሬው በአጠገባችን በመኪና ሲያልፉ በመስኮት አዘቅዝቀው እያዩንና እየሳቁብን ማለፋቸውም ይታወሰናል:: እኛም የፈገግታ አጸፋ መልሰንላቸዋል:: ብዙም ሳይቆይ ወሬ ከየአቅጣጫው ይደርሰን ጀመር:: ወደ ቀበሌ 05 የተወሰዱትን ኳስ ሜዳ አውጥተዋቸው ስፖርት እንደሚያሠሯቸው ሰማን:: አካፋ አሸከመው ሩጡ ይሏቸዋል:: መቆየቱ ከበደ በሩጫ ኃይለኛ ናት ...ወዘተ አሉ::

ሌላው መንገደኛ ደግሞ፣ አራዳ ቀበሌ 08 የተወሰዱትም በከባድ ስፖርት እንደሚንገላቱ ነገረን:: ሌላ ቦታ ያሉት ስፖርት እየሠሩ እኛ ዝም ብለን እንድንቀመጥ መደረጉም ተገቢ አይደለም ተባለ:: በሳምንት ጊዜ ውስጥ ለጉልበት ሥራ አራዳ አካባቢ ወደሚገኘው የአብዮት ሙራ ት/ቤት ተወሰድን:: አንድ ወጣት ተመለከተንና፣ *እነዚህ ገና ናቸው፣ እኛ ጋ ያሉት በስፖርት ዳብ ረዋል* በማለት ቀለደ::

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ በቀበሌ 08 የነበሩት አቶ አዲሴ፣ ደባልቂና አብነት መጡና ተቀላቀሉን:: ለናያቸው እጅግ ተጎሳቁለዋል:: ከስተዋል:: ልብሳቸውና ሰውነታቸው አቧራ ለብሶአል:: እያንገላቱ ድቅቅ እንዳደረጉአቸው ገጽታቸው ያስታውቃል:: ብዙ እንድንነጋገር አልፈቀዱልንም:: ቃል ለመለዋወጥ ጭንቅ





ነበር:: በዓይናችን አይተን ከምንረዳው በቀር የደረሰባቸውን ዝርዝር ሁኔታ ለመ ረዳት አላመቸም::

የዕለቱ ሥራ በቆሎ መሸልቀቅ፣ መከመርና በጆንያ ውስጥ በመጨመር ወደ ትምህርት ቤት ክፍሎች ማጋዝ ነበር:: እያጣደፉና ፋታ ሳይሰጡ ያሠሩን ስለነበረ ሁኔታው አድካሚ ነበር:: ደባልቄ፣ ከሁላችንም ይልቅ በዕድሜው ታናሽ ስለነበረ፣ በእርሱ ላይ ስድቡንም የሸክሙንም ጫና ያከብዱ ነበር:: በአንጻራዊ ሁኔታ፣ እኔ በሰውነት ከእርሱ እጠንክር ነበር:: ለእኔ እንኳ ይከብድ የነበረውን ሸክም፣ በርሱ ላይ ጭነው አቀበቱን ያስወጡት ነበር:: በልጅ አቅሙ እየተንገዳገደና ደፋ ቀና እያለ። ሸክሙን ልጋራለት ሞከርኩ:: አልተ ፈቀደልኝም:: ከልባችን ብቻ ሳይሆን ከአቅማችን በላይ እየሠራን ቢሆንም፣ *ቆዩ እሳግጡ!* እያሉ ግራ ሲያጋቡን ነበር - አሠሪዎቻችን::

በዚያን ዕለት ወንዱም ሴቱም የጊዳቦን ዳገት እየወጣ በቆሎውን ተሸክሞ ሲያግዝ ዋለና ተለያየን:: እነዚያ ወደ ተመደቡበት ቀበሌያቸው ሲገቡ፣ እኛም ወደ ፖሊስ ጣቢያችን በተዳከመ ጉልበት አዘገምን:: እንደ እውነቱ ከሆነ በጣም ተርበንም ነበር::

ከቀኑ 9:00 ሰዓት፣ ከጣቢያችን ስንደርስ አባቴ አቶ ጋቢሶ ዶያሞ በበራፉ ቆሞ ሲጠብቀን አገኘነው:: ስንቅ ይዞአል!! ለጊዜው ራባችንን ሊያስታግስ የሚችል ከእንሰት ተክል የሚዘጋጅ የበሰለ ቆጮ ነበር:: የጭካኔው ትዕይንት ግን መጋረጃው ገና ተገለጠ እንጂ በዚህ አላበቃም::

## <u>በስፖርት ስም</u>

አንድ ቀን ማምሻውን፣ *ነገ ጠዋት ለስፖርት ትወጣላችሁና ተዘጋጁ* የሚል መልእክት ተነገረን:: እኛም ልባችንን በጸሎት አዘጋጅተን አደርን:: በዋዜማው ከፍ ብሎ ከላይ የተጠቀሱትን መልእክቶች ከቅዱስ ቃሉ ተካፈልን:: በሚሆነውም ሁሉ የክርስቶስን ምሳሌነት እንድንከተል ማሳሰቢያ ወሰድን::

በማግሥቱ፣ ገና በማለዳ፣ አንድ ወጣት፣ አንድ የአስር አለቃና ከዘቦቻችን አንዱ፣ ወታደር ጎንፋ መጡና ቀሰቀሱን:: እኔ ከላይ ቪ-ሼፕ ሹራብ፣ ከውስጥ አንድ ሸሚዝ ለብሼ ሱሪ ታጥቄአለሁ:: ለስፖርት የሚሆን ጫማ ግን ስላልነበረኝ ለእግሬ ቆዳ ጫማ አድርጌ ነበር የወጣሁት:: ጌታሁንና አዳነም እንደ እኔው ነበር ያደረጉት:: ሙሉ አመቤት ብቻ ሸራ ጫማ አጥልቃለች:: እርስዋና አልማዝ ታደሰ ሱሪያቸውን ታጥቀው ጉርድ ቀሚስ ከላይ ለብሰዋል::

ከፖሊስ ጣቢያው እንደወጣን፣ በአውራው ጎዳና ላይ ፊታችንን ወደ ምዕራብ አድርገን ጥቂት እንደተራመድን፣ *ሰምሰማ ሩጫ ጀምሩ!* የሚል ትዕዛዝ ተ ሰጠን:: መሮጥ ጀመርን:: ጥቂት እንደሮጥን አልማዝ አስም ተቀስቅሶ አፈናትና ወደ ኋላ ቀረች:: ሙሉ አመቤትም ብትሆን የእኛን ያህል መሮጥ ስላልቻለች ዘወር ብዬ ሳይ ተራርቀን አየሁ:: ፍጥነቴን ለመቀነስ ሞከርሁ:: ወንዶቹን እያጣደፉ አስቸገሩን:: እንደ ምንም ኳስ ሜዳ ደረስን::

በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ፊት ለፊት፣ ከፖሊስ መምሪያው ጎን የነበረውና ቆይቶ የፓርቲ ጽ/ቤት የተሠራበት ሜዳ ማታ ከወረደው ኀይለኛ ዝናብ የተነሣ ጨቅይቷል:: አልፎ አልፎም ዳርና ዳሩ ላይ ውኃ ተኝቶበታል:: እዚያ እንደደ ረሰን ጫማዬ ጭቃ ተሸክሞ አላንቀሳቅስ አለኝና አውልቄው በካልሲ ብቻ ለጥቂት ጊዜ ቀጠልኩ:: ካልሲውም በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ጭቃ ለብሰበና ለየት ያለ ጫማ መሰለ!!

በዚህ ሜዳ ላይ ሰሞኑን ሌላ «ድራማ» ሲታይበት ቆይቷል:: የቀበሌ 05 ወገኖቻችን ተረግጠውበታል::በጭቃው ተለውሰውበታል:: ዛሬ ደግሞ እኛ ከሜዳው ስንደርስ የተራችንን ልንረገጥበት ሆነ:: አሁን እንግዲህ እየነጋ ሲሄድ ተመልካችም ጠርቀምቀም አለ:: ትዕዛዙም *ሩጥ! ተመለስ! ተኛ ! ተንከባለል! ተነሥ! አምራ ጉብ ጉብ ዝለል!* በሚል እየተፈራረቀ ተፋፋመ:: ይህ ሁሉ ትዕዛዝ ከዱላ፣ ከጉማሬ አለንጋና ከእርግጫ ጋር ያጣድፈን ገባ::

አልማዝ አንድ ቦታ ወድቃለች:: አዳነም ጥቂት እንደ ሞከረ እጥወለወለውና ዓይኑ ግልብጥብጥ ሲል አንድ የፖሊስ መምሪያ ወታደር አይቶት *እህ! ልትሄድ ነው? ሊቀበልህ መጣ?* እያለ አሾፈበት:: አንዳንዴ እነርሱንም አሠሪዎቻችንንም ሰለሚደክማቸው ጥቂት እረፍት ይወስዱና ለእኛም እረፍት ይሰጡናል:: በየእረፍቱ መሐል ጥያቄዎች ይኖራሉ:: ለምሳሌ *ከሁሉ በላይ ማነው? እናንተ ከእኔ የበለጠ የተማራችሁ ናችሁ:: ሳይንሱን ከእኔ ይበልጥ ታውቃላችሁ:: ከሳይንስና ከኃይማኖት የቱ ይበልጣል?* ወዘተ የሚሉ ነበሩ:: ምላሻችን የሚፈለግ ዓይነት ካልሆነ እንግልቱ ከግርፋት፣ ከድብደባና ከስድብ ጋር ይቀጥላል::

በዚህ ሁሉ ውስጥ የውጭው ሰውነታችን ሥቃይ ቢሰማውም፣ የውስጡ ማንነታችን ሃሴት ያደርግ ነበርና የፊታችን ገጽታ ብሩሕ ሆኖ መታየቱ አልቀረም:: በተለይም ጌታሁን እጋፋሪ ቀድሞም ቢሆን ሳቂታ ስለነበረ በዚያን ዕለት እየተሰቃየም ቢሆን ሲስቅ አይቶት የፖሊስ መምሪያው እስር አለቃ *ቆይ ብቻ! በአብዮታችን ላይ ነው የምትስቀው?* ብሎታል:: ወደ እስር ቤታችን ረፈድ አድርገው ሲመልሱንም ክፍላችን ውስጥ ገብተን ተቆጥበና ተጠራቅሞ የቆየውን ሳቃችንን ለቀቅነው:: እነዚያ አረጋዊያን እስረኞች አሁንም እዚያው ጣቢያ ውስጥ ነበሩና ሳቃችንን ተመልክተው *ትስቃላችሁ? አይ ልጅነት! ልጅነት ነው የሚያስቃችሁ! ለነገሩ 12ኛ የጨረሳችሁ - የተማራችሁ - ናችሁ:: ከእናንተ ማን ሙጠ የሚጠባ ሕጻን ይሻላል* አሉን:: በጎርፍ ኩሬ ውስጥ ተዘፍቀን፣ ከእንገት በታች ጭቃ ለብሰን ስንገባና አዝነን ማልቀስ ሲገባን እየሳቅን ሲያዩን፣ ታዲያ ምን ይበሉ? እግዚአብሔር ይክበር:: እንደ ተስፋ ቃሉ በመከራችን መሐል የክብርን መንፈስ በእኛ ላይ በማሳረፍ ያጽናናን እርሱ ነውና::

ስፖርቱ - ወታደራዊ ቅጣቱ ቢባል ይሻላል - ብዙ ታሪክ ነበረው:: በቀበሌ 05 የነበሩትን እንደተባለው የአብዮት ጥበቃ ጓዶቹ ይጫወቱባቸው ነበር:: በዚህኛው ቀበሌ ውስጥ በነበሩት ላይ የማሰቃየቱ ተግባር ሲጀመር ቀደም ሲል ከሐምሌ ወር ጀምሮ ፖሊስ መምሪያ ቆይተው የነበሩ እነይዲድያ መስፍን፣ ተሾመ ጣንተይዳኛና በቀለች ጸጋዬ እንዲቀላቀሏቸው ተደርጓል::





ከአብዮት ጠባቂዎቹ መካከል አንዱን፣ ረዘም ያለና ሙሉ ሰውነት የነበረውን፣ ከዚህም የተነሳ ለገራፊነት የተመረጠውን ሰው፣ ጓደኞቹ ምብጣው በሚል ቅጽል ስም ይጠሩት ነበር:: ሰውየው በርኅራኄ የለሽነቱ ስለታወቀ ማስፈራሪያ እስከ መሆን ደርሶ ነበር:: ሰውየውና አንድ ሌላ ጓደኛው፣ ሲፈጽሙት ከነበረው አሰቃቂ ድብደባና እንግልት የተነሳ፣ ፓስተር ኃይሉ በቀለ በተደጋጋሚ እራሱ እረፋ እስኪደፍቅና በተለይም አንድ ቀን፣ ራሱን እስከ መሳት ደርሶ፣ በይዲድያ መስፍንና በበቀለች ጸጋዬ ድጋፍ፣ ጤና ጣቢያ ተወስዶ ስለነበረ፣ በደብዳቢዎቹ ላይ ከፍተኛ ድንጋጤ ፈጥሮ እንደ ነበረ ይታወሳል:: ይህ ሰው በራሱ ክልል የነበሩትን ወገኖቻችንን፣ በሚለበልብ የሳማ ተክል ላይ እንዲንከባለሉ ያደረገና ለሁለት ምሽት ያህል ያለምንም ርኅራኄ በውርጭ/በጤዛ ላይ እስተኝቶ ያሳደረ «ኃይለኛ» ነበር:: የተወሰኑ ወገኖቻችን በተለይም የመጀመሪያውን ምሽት እንዲያሳልፉ የተደረጉት ከወገባቸው በላይ እራቁታቸውን ሆነው ነበር:: ከዚህም የተነሣ ለረጅም ወራት በብርድ በሽታ እየተሰቃዩ የከረሙና በሌላም በሽታ የተጠቁ ቢኖሩም በኋላ ጌታ ሁሉንም ፈውሷቸዋል::

በቀበሌ 01 የተፈጸመውም ድርጊት ክምላ ጎደል ተመሳሳይ ነበር ማለት ይቻላል:: በስፖርት ስም ማንገላታቱ፣ እየገረፉ፣ እየደበደቡና እየረገጡ ማሰቃየት እንዲሁም በጭቃ ላይ እያንከባለሉ መጫወት፣ ሁሉም ጋ የተደረገ ሲሆን ለየት የሚሉ ጥቂት ድርጊቶችም አልጠፉም:: በቀበሌ 01 ለየት የሚሰው ደግሞ ሌሊት ሌሊት ወደ ወንዝ ወስዶ በቀዝቃዛ ውኃ ውስጥ መንክርና ከዚያም አውጥቶ በእሷራ እንዲለወሱ ማድረጉ ነበር:: ከበደ አርጋው፣ እየለ አበራ፣ ማርታና ሐና-አሰፋ የሚባሉ እህትማማች የዚህ ጽዋ ተካፋዮች ነበሩ::

ሙላቱ መለሰና ለገሠ ቀቀቦ በነበሩበት ቀበሌ 03 ደግሞ የራሱ የሆነ የማስቃያ ታሪክ ተፈጽሟል:: ሌሊት ሌሊት እያወጡና ጫካ እየወሰዱአቸው ክፉኛ ይደበድቧቸው እንደ ነበረ እነ ሙላቱ ይገልጻሉ:: በተለይም ሙላቱ በአሰቃቂ ሁኔታ ከመደብደቡ የተነሳ ብዙ ደም ከጆሮውና ከአፍንጫው ፈስሶ ስለ ተዳከመባቸው በመደናገጥ ሆስፒታል ወስደውት ሳለ፣ አባቱ መጥተው እንዲረከቡት እንደ ተደረገ ታውቋል::

## ከሁሉ በላይ...

በ1972 ዓ/ም ጥቅምት ጀምሮ በአብዛኛው የጴንጤቆስጤ አማኞችንና በአጠቃላይ ጌታን በእውነት የሚጠሩትን ክርስቲያኖች፣ ከይርጋ ዓለም ምድር ጨርሶ ያጠፋል በሚል ተስፋ፣ በስፖርት ሽፋን፣ የተወሰደው እርምጃ እጅግ ጥብቅ ነበር:: በዚሁ መሠረት፣ በሰኔ ወር ውስጥ አብረውን ታስረውና እንደሚባለው የውግዘት - የእርግማን - መፈክር አሰምተው የተለቀቁም እንደገና ተይዘው ከእኛው ጋር ተንገላተዋል:: የእርግማን መፈክርን ማስባል ቀድሞም ቢሆን ዋናው ግብ አልነበረማ! ስለዚህ፣ በድጋሚው እስር ጊዜ የቀረበላቸው ጥያቄ *ከሁሉ በላይ ማነው?* የሚል ነበር:: መልሳቸው *እግዚአብሔር ነው* የሚል ሆነና በዚህ ምክንያት ተሰቃዩ::

በድጋሚ ከታሰሩት ወገኖቻችን ውስጥ አንዳንዶቹ፣ የመንግሥት ትምህርት

ቤት መምሕራን፣ ምሁራን ስለ ነበሩ፣ እንደ መሪዎቻችን ሳይቆጥሯቸው አልቀሩም:: አሳሪዎቻችን የገመቱት፣ መምሕራኑ በወቅቱ ይፈለግ የነበረውን የሽፋን ጥያቄ እንደሚፈለግባቸው መልሰው - መፈክር አሰምተው የወጡት - ሳይወጡ የቀሩትን እስረኞች ለመቀለብ እንደ ነበረ ነው:: ሆኖም ግምታቸው የተሳሳተ ነበር:: እያንዳንዳችንን በሁሉ እየተጠነቀቀ የሚመራን መልካሙ እረኛችን፣ ከሁሉ በላይ የሆነው፣ የሊቀችም ሁሉ ሊቅ፣ ጌታ ኢየሱስ እንጂ ሆነ ማን በነገራቸው!

አቶ አስማረ በሁለተኛው ዙር የገባው ፤ የዋናው አዛዥ ቢሮ ባለበት ፖሊስ መምሪያ ነበር:: አንድ ቀን፣ አቶ አስማረ ይህንኑ የመምሪያ አዛዥ እንዲህ ሲል ይጠይቀዋል:- *አሁን እኔ ታስሬያለሁ :: ታዲያ እዚያኛው ፖሊስ ጣቢያ ያሉት ልጆች ቀለብ በማጣት ለምን አልሞቱም ?* :: የአዛዡም መልስ የሚከተለው ሆነ :- *አንተ ታሠርክ እንጂ እሠራርህ መቼ ታሠረ ?* የሚል:: እግዚአብሔር ይመስገን ! የእግዚአብሔር ሰው በሥጋው ቢታሰር፣ እግዚአብሔር አይታሰር !

ከከተማይቱ ውስጥ የክርስቶስን ምስክርነት ጨርሶ ለማጥፋት ዘመቻው የተካሄደው በሁሉም መስክ ነበር :: ለምሳሌ 12ኛ ክፍልን አጠናቀው የነበሩ ክርስቲያን ተማሪዎች፣ ትራንስክሪፕቶቻቸውን - የትምህርት ማስረጃዎቻቸውን - ለማግኘት የነበረባቸው ፈተና ቀላል አልነበረም:: ተማሪዎቹ ውጤታቸውን ለመቀበል ት/ቤት ሲሄዱ በቃላትም በእጅም ጥፊ የመቅመስ ዕጣ ገጥሟቸዋል:: በክርስቲያንነቱ የሚታወቅ ወይንም የሚጠረጠር ተማሪ ቢሮ ገብቶ ሲቆም የሚደረደሩለት የማጥመጃ ጥያቄዎች ነበሩ *1) ሃይማኖት አለህ ? 2)መጤ (ጴንጤ) ነህ ? 3) ከሁሉ በላይ ማን ነው ? 4) ሰማይንና ምድርን ማን ፈጠረ፤* የጥያቄዎቹ እድገት ከቀላል ወደ ከባድ እንደነበረ ልብ ይሏል!!

የመጨረሻዎቹ ሁለት ጥያቄዎች ወሳኝ ናቸው:: *ከሁሉ በላይ የሆነ፣ ወይም ሰማይንና ምድርን የፈጠረ እግዚአብሔር ነው* የሚል ምላሽ የሚሰጥ ቢኖር የትምህርት መረጃውን በመከልከል ተዋርዶና ተደብድቦ የመውጣት ዕጣ ይገጥመው ነበር::

እግዚአብሔር ግን በውርደታቸው ያከበሩትን አከብሮአቸዋል:: ያለ ምንም ትራንስክሪፕት ሥራ ለመያዝ አብቅቶአቸው፣ ከዚህም የተነሣ፣ ዛሬ በማሕበራዊ ኑሮአቸው ትልልቅ ሰዎች የሆኑ አሉ:: ከእነዚህ መሐል ያለ ትራንስክሪፕት፣ በማትሪክ ውጤት ብቻ፣ ሥራ ለመያዝ ከበቁት መሐል ወንድም ተስፋዬ ከበደ ይገኙበታል:: ወንድም ተስፋዬ ለተወሰኑ ዓመታት የአርሻ ኮሌጅ ትምህርት ተከታተለና በሀዋሳ እርሻ ጣቢያ ውስጥ ሠራ:: በመቀጠልም፣ በኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክስ ኢንስቲትዩት ሰልጥኖ አሁን በኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን መ/ቤት በኃላፊነት ደረጃ ተመድቦ እየሠራ ይገኛል:: ሌሎቹም እንደዚሁ፣ ወ/ሮ ጀማነሽና ወ/ሮ አልማዝ ልሣነ ወርቅ የሚባሉትን እህትማማች የመሳሰሉ፣ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ በመንግሥትና በግል ድርጅቶች ውስጥ በየሞያቸው እየሠሩ ይገኛሉ::
ዳዊት:- *ጎለመስሁ፣ አረጀሁም፤ ጻድቅ ሲጣል ዘሩም እህል ሲለምን አላየሁም::*





ያለው ቃል እውነት ነው:: (መዝ 37:25) እግዚአብሔር *በለልፍ ጊዜ* ከሰይፍ እጅ፣ ስራብ ጊዜ ከሞት አድኗቸው፣ በነፍሳቸውም በሥጋቸውም ሕያዋን ሆነው፣ ለጌታ ክብርና ምስክርነት የቆሙትን ብዙዎች ወገኖቻችንን በዓይናችን ስናይ፣ ልባችን ደስታን አፋችን ደግሞ ምስጋናን ይሞላል:: አሁንስ ከሁሉ በላይ ማነው?...

## ጊዜው ባያጥር ኖሮ

*በዚያን ወራት እግዚአብሔር ከፈጠረው ከፍጥረት መጀመሪያ ጀምሮ እስከአሁን ድረስ ያልሆነ ደግሞም የማይሆን የመከራ ዓይነት ይሆናልና:: ጌታስ ወራቶቹን ባያሳጥር፣ ሥጋ የለበሰ ሁሉ ባልዳነም፤ ነገር ግን ስለ መረጣቸው ምርጦች ወራቶቹን አሳጠረ(ማር 13:19-20)::*

እግዚአብሔር ርኅሩኅ አባት ነው:: እኛም ያልጠፋነው ከእርሱ ምሕረት የተነሣ ነው:: ርኅራኄው አያልቅምና:: ሰይጣን ያለርኅራኄ አሳደደን:: ጌታ ግን በፍቅሩ ታደገን:: የነፍሳችንን መቃተት ሰምቶ ደረሰልን::የመከራችንንም ወራት አሳጠረልን::

*የስፖርቱ* ቅጣት፣ እኔ በነበርኩበት የቀበሌ 07 ፖሊስ ጣቢያ ሱሪ አጥፎ እጆችን ወደ ግራና ቀኝ ዘርግቶ መኪና በሚሄድበት ኮረኮንች - የድንጋይ ጠጠር መንገድ - ላይ በእምብርክክ መሄድንና መንከባለልን ያጠቃለለ ነበር:: ይህም *ልምምድ* ከቀድሞው ኳስ ሜዳ አንስቶ እስከ አራዳ የለኩ መገንጠያ መንገድ ባለው አውራ ጎዳና ላይ ተካሂዷል::

ስለዚህ ባለ መኪናዎች ሞተራቸውን ቀዝቀዝ እያደረጉ በዝግታ እያዩን አልፈዋል:: እግረኞችም እንደ ጉድ ተመልከተውናል:: ለአንዳንዶች ትዕይንቱ ዘግናኝ ነበር:: ሌሎቹም ዘብተውብናል:: አንዲት ሴት ደግሞ ተገርመው *የእነዚህስ ቀላቸው ኃይለኛ ነው!* ማለታቸው ይታወሳል:: እውነታቸውን ነበር:: ሊቀ ካሕናታችን ክርስቶስ መከራችንን በመስቀል ላይ ታግሦ በመሸከም ኃይለኝነቱን አስመስክሮአልና::

ቅጣቱ በእኛ ቀበሌ ከሶስት ቀን የበለጠ ጊዜ አልወሰደም:: ከእነዚህ ቀናት በአንደኛው፣ በኳስ ሜዳው ላይ፣ *አምራ ጉብ ጉብ* ቁጥጥ ብዬ እየዘለልኩ ሳለሁ የቀኝ እግሬ ቅልጥሙ አካባቢ በተወረወረ ድንጋይ የተመታ መሰለኝ:: የእግሬ ጡንቻ ላይ የተሰማኝ የኃይለኛ ምት ስሜት ነበር:: ከዚያች ደቂቃ ጀምሮ መንቀሳቀስ ስለተሳነኝም ወደቅሁ::

አንደኛው የአብዮት ጠባቂ ተነሥ አለኝ:: እግሬ ተሰብሯል አልችልም አልኩት:: *እንክት ይበል! ተነሥ፣* አለኝ:: *እንክት ብሏል!* አልኩት:: ከዚያ በኋላ ትንሽ ገራረፈኙና እንግልቱ አብቅቶ ወደ ጣቢያችን ሌሎች ቀድመውኝ እኔ ከኋላ እያነከስኩ ተመልሰን ገባን:: በኋላ የአብዮት ጠባቂዎቹ *ስትራፖ ይዞሃል* ብለውኛል::
በእኛ ቀበሌ ሦስተኛው ቀን ለስፖርቱ የመጨረሻው ሆነ:: የጉልበት *ሥራው*

ግን ቀጠሰ:: እኔም በመታሻ እየታሸሁ የእግሬ ሕመም ከቀናት በኋላ ቀስ በቀስ ለቀቀኝ

በቀበሌ 05 የነበሩትን ግን ለ12 ቀናት ያህል አልፍተዋቸዋል:: ከሌሎቹ ሥፍራዎች ይልቅ መከራው ተጠናክሮ የተራዘመው እነርሱ ጋ ነበር ማለት ይቻላል:: ጫካ እያወረዱ በየገደሉ ላይ ቁልቁል እያንከባለሉአቸው ነበር የተጫወቱባቸው:: ከዚህ ሁሉ ጋር ዱላውና እርግጫው ርኅራኄ የማይታይበትና ፋታ የማይሰጥ ነበር:: ከኃይሉ በቀለ ሌላ ምንትዋብ አረሩ ከድብደባ ብዛት የተነሣ ራስዋን ስታስታጓራ አስደንጋጭ ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር:: ማርታና ወርቅነሽም ከስቃዩ ጥንካሬና አስቃቂነት የተነሣ ሞታቸውን የተመኙበት ቀን እንደነበረ ይናገራሉ:: ፓስተር ተሾመ የውስጥ እግሩን በእጣናና በጉማሬ አለንጋ እያፈራረቁ ሲቀጠቅጡት ኢየሱስ! ኢየሱስ! ኢየሱስ! እያለ በልቡ እየተጣራ ያቺን ከባድ ሰዓት እንዳሳለፈ ይናገራል:: በዚህ ሁሉ ላይ የቀናት ራብና ጥም እየታከለ መከራቸውን አከብዶት ነበር!!!

የሆነው ሆኖ በመጨረሻ የደብዳቢዎች ክንዳቸው ዛለ:: በጭካኔያቸውም መሐል የኢየሱስ ብርታቱ ታየ፡፡ ሰወዳጆቹ መከራን የሚታገሡበትን ጸጋ አብዝቶ ሰጥቷልና:: የወቅቱም «ጦርነት» በኢየሱስ አሸናፊነት ተፈጸመ:: በቀበሌ 05ም ላይ የስፖርቱ ቅጣት አበቃ::

የመጨረሻው ትንቅንቅ የተካሔደው በአራዳ፣ በቀበሌ 08፣ በወንድማችን ከበደ አርጋው ላይ ነበር:: ከበደ በቀበሌ 01 ስለ ጠነከረባቸው ነበር ወደ ቀበሌ 08 የወሰዱት:: ለምን ቢባል ወደዚህኛው ቀበሌ ቀደም ሲል የተላኩት ከስቃዩ ብዛት የተነሣ የተጠየቁትን ሁሉ እየፈጸሙላቸው ስለተለቀቁ ያ ቀበሌ ተመስግኖ ነበር ይባላል:: ስለዚህ፣ እነዚያ ከተሰቀቁ በኋላ አሳሪዎቻችን እኛንም ወደዚያ ለማዛወር እንዳሰቡ ሰማን:: እኛም ከተወሰድን በዚያው ሰመሞት ቁርጥ ውሳኔ አደረግን:: ሆኖም ባልታወቀ ምክንያት የታሰበው ተግባራዊ ሳይሆን ቀረ::

በመጀመሪያ አራዳ ከተላኩት ውስጥ የቀሩትን ሲፈቱ መምህር አዲሴ ቀልብሴና ይዲዲያ መስፍን ወደ እኛ እንዲመለሱ ተደርጓል::

አሁን ደግሞ፣ ከበደ አርጋውን ከአፖስቶ ወስደው በቀበሌ 08 ሲገርፉት ጀመሩ:: ከበደም ጾም ይዞ እህል አልቀምስ፣ ሻይ እንኳን አልወስድ አለ:: እንደዚያ ሆኖ ከአምስት ቀናት ያላነሰ ሲቆይ በዚህ ሁሉ ውስጥ እያወጡ ሜዳ ላይ ይገርፉት ነበር:: በፀሐይ ላይ እንደ እህል እያንቃቁ ያደርቁት ነበር:: በመጨረሻ ሰውነቱ እየደከመና እየገረጣ ሲሄድ ለፖሊስ መምሪያው አዛዥ ሪፖርት ያደረጉ ይመስላል:: እርሳቸውም ሄደው ሲያዩት ይደነግጣሉ:: *ሃንገር ስትራይክ - የረሃብ አድማ - አድርጓል ፣ምን እስኪሆን ነው የምትጠብቁት? ለመሆኑ ማነው የሚገርፈው?* ብለው ሲጠይቋቸው አንድ ጡረተኛና ፈቃደኛ የሃምሳ አለቃን ያመለክቱአቸዋል:: እርሱንም *በቁጣ ስሜት፣ ማን አዘዘህና ነው ይህን የምትሠራው? ሁለተኛ እዚህ እንዳትረግጥ!* በማለት አስጠነቀቁት:: ወደ ጣቢያው ሠራተኞችም በመዞር *ለመሆኑ እናንተ ለዚህ አንሳችሁ ነው እርሱን የምታሠሩት?* የሚል ወቀሳ ከሰነዘሩባቸው በኋላ፣ ከበደን ወደ ፖሊስ መምሪያው አስወሰዱት::





አቶ አስማረም፣ እዚያው ፖሊስ መምሪያው ግቢ ውስጥ ስለ ነበረ የመምሪያው አዛዥ አገናኝቶአቸው ከበደን በሚያግባባ መልኩ እንጋገረው:: ከበደም ምግብ መውሰድ ጀመረ:: የ08ቱም ቀበሌ መንፈሳዊ ውጊያ ይህን በመሰለ መሥዋዕትነትና ድል ተደመደመ::

በየቦታው የነበረው ሥቃይ፣ ከላይ በጥቂቱ በተጠቀሰው መንገድ፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ እየቀነሰ መጣና ቀዝቃዛው መከራ ቀጠለ:: በከፍተኛ ደረጃ የያዙንንም ባለ ሥልጣናት እግዚአብሔር እኛ ባላወቅነው መንገድ ሳይገሥጻቸው አልቀረም:: ከታሠሩት መካከል የሚበዙቱን ለቀቋቸው:: መምህራኑም በዚህ ወቅት ተለቀቁ:: በእኛም በቀረነው ላይ የነበረው ተጽዕኖ ቀለል እያለ መጣ::

አዎን! ጌታ የመከራችንን ቀናት አሳጠረልን:: ይህ ባይሆን ኖሮ፣ ምናልባት ከደረሰብንም በላይ የሚከብድና የሚከፋ ጉዳት ሊደርስ ይችል ነበር:: እግዚአብሔር ግን ስለ ስሙ ሲል ፈጥኖ ደረሰልንና ከከፋ ነገር ታደገን:: ክብር ለስሙ ይሁን::

## <u>የዝምታ ወራት</u>

ከህዳር አስከ ጥር 21 ቀን 1972 ዓ/ም ድረስ ያለው ጊዜ የዝምታ ጊዜ ነበር:: ግፋ ቢል ለጉልበት ሥራ መውጣት ብቻ ነበር:: በተለይ በእኛ ቀበሌ ዋናው ሥራ ቡና መልቀም፣ ማስጣትና የደረቀውን መከተት ነበር:: በቀበሌያችን በ07 ክልል የነበረውን ቡና ለቅመን ያጠናቀቅን እኛ ነበርን ለማለት ያስደፍራል:: አልፎ አልፎ የቀበሌው ሕዝብም እየወጣ ለቅሟል:: እኛ ግን ቋሚ «ሠራተኞች» ነበርን:: የገብስ ወቀጣ ማካሄድ፣ አትክልት መከትከትና አትክልቱን ውኃ ማጠጣትም ነበረብን::

በዚህ መሐል፣ በጣም አልፎ አልፎ የፖለቲካ ንቃት ለመስጠት አስተማሪዎቹ ብቅ እያሉ ሄደዋል:: መንገድ አላፊዎች ሳይቀሩ እኛን በማንቃቱ ጥረት ውስጥ የድርሻቸውን አበርክተዋል:: አንድ ቀን፣ የቀበሌው ነዋሪ የነበሩ አንድ ሽምግል ያሉ አባት:-

> *ኧረ እናንተ ልጆች ተው! ሰው መሣሪያ ከያዘ መንግሥት ጋር ይታገላል? እንደ ንጉሡ አጎንብሱ የሚባል ነገር አልሰማችሁም? በአንድ አገር ጎንበስ ብሎ የሚሄድ አንድ ንጉሥ ነገሠ ይባላል:: እርሱም በሚያልፍበት መንገድ የተገኘ ሰው ሁሉ ጎንበስ እያለ እንዲያሳልፈው ትዕዛዝ ሲያስተላልፍ ነበር:: ይህንን አለማድረግም ስለሚያስቀጣ ትዕዛዙን የሰማ ሁሉ ጎንበስ እያለ ንጉሡን በማሳለፍ ነፍሱን ያተርፍ ነበር:: ታዲያ፣ መንግሥት እግዚአብሔር የለም ካለ የልብን በልብ ይዞ አብሮ የለም ማለት ነው እንጂ እልኸ መያያዝ መልካም አይደለም::* በማለት መካከረውናል::

የማንቃቱ ሥራ ተፋፍሞ የነበረው ግን በስፖርታዊ ቅጣቱ ሰሞን ነበር:: ያ

የማንቃት ዘዴ በቀስታ ከማባበል አንስቶ እስከ ዛቻና ድብደባ ድረስ ያለውን ሁኔታ ያካተተ ነበር:: መጀመሪያ፣ በድብደባው ሰሞን፣ እንድናነባቸው፣ የርዕዮተ ዓለም መጻሕፍት አድለውን ነበር:: የመጻሕፍቱ ርዕሶች ዲያሌክቲካዊና ታሪካዊ ቁስ አካልነት፣ፖለቲካዊ ኤኮኖሚና የአፍሪካ እውነታ፣ የኮሚዩኒስት ማኒፌስቶ ወዘተ የሚሉ ነበሩ:: አሳሪዎቻችን፣ በተለይም ወታደሮቹ፣ እነዚህን ካነበብን እንደምንለወጥ ተስፋ አድርገው ነበር:: መጻሕፍቱን እኛም አነበብናቸው:: ሆኖም የፍልስፍናውን መሠረት ከፊት ይልቅ ከመገንዘብ በቀር የመጽሐፍ ቅዱሳችንን ያህል ነፍስን የሚያሳርፍና የሚያረካ ነገር ሳናገኝባቸው ቀረን:: ቅዱሱ መጽሐፋችን፣በመዝሙረ ዳዊት 119:85 ላይ፣ *ኃጢአተኞች ጨዋታን ነገሩኝ፣ አቤቱ እንደ ሕግህ ግን አይደለም* የሚለው እውነቱን እንደሆነ አረጋገጠልን::

መጻሕፍቱም አልለወጡንም:: ዱላውም - ድብደባውም - የተጠበቀውን ያህል አጥጋቢ የሆነ ውጤት ሊያመጣ አልቻለም:: ድብደባው ከብዶባቸውና ያለ ፈቃዳቸው የተፈለገውን ፈጽመውላቸው የተሰቀቁቱም ቢሆኑ እግዚአብሔርን ማምለካቸው እንደሚቀጥል በቃላቸው አስገንዝበዋቸዋል፤ በተግባርም አሳይተዋቸዋል:: አሣሪዎቻችን እንደጠበቁት *እግዚአብሔር የለም፣ ከእንግዲህም በኋላ የእግዚአብሔርን ስም ሁለተኛ አላነሣም* ወደ ማያስብል አቋም አልመጡላቸውም:: ስለዚህ ከእስር ሲለቁአቸው፣ *ሙሉ ለሙሉ ባይመለሱም፣ በተሰጣቸው ትምሕርትና ምክር መሠረት መጠነኛ ለውጥ ብቻ ከሳሳዩ፣ ጥብቅ የሆነ ክትትል እንዲደረግባቸው* በማለት የሚመለከታቸውን ቀበሌዎች ያሳስቡ እንደነበር ይታወሳል:: ሌሎቹ ደግሞ «በቅርብ ጊዜ ውስጥ» *ለአብዮታዊ ፍርድ እንደሚቀርቡ* ያስገነዘቡባቸው ሁኔታዎች አልጠፉም::

ፈተናው መልኩን እየለዋወጠ ቢመጣብንም፣ ተስፋ ያደረግነው አምላካችን አልተለወጠብንም፤ ጸጋንና ኃይልን አብዝቶ ሰጠን:: በወደረኞቻችን ፊት እግሮቻችንን አጽንቶ፣ አቆመን:: በመንፈሱ የውስጥ ሰውነታችንን አጠነከረልን:: ከእምነታችንም እንዳንነቃነቅ ደገፈን:: የዝምታው ወራት በእርግጥ አስቃቂው የአካል ግርፋት ተቋርጦ የእእምሮ ግርፋት የቀጠለባቸው ወራት ነበሩ:: ቻል የተባልንበትና ምናልባትም ዝም መባላችን እንዲያሳስበን የተተውንበት ጊዜም ይመስል ነበር::

ከዕለታት አንድ ቀን ደግሞ የአውራጃው አስተዳደሪ ከጥቂት አጃቢዎቻቸው ጋር በመሆን ፖሊስ ጣቢያ ድንገት ከተፍ አሉና ወደ ምናድርበት ክፍል ገቡ:: ዓይናቸውንም አቶ አዲሴ ላይ ተክሉና *አንተ በምን ታሰርክ* አሉት:: አቶ አዲሴም የታሰረበትን ምክንያት በቂ አለመሆን በመናገር የነበረውን ቅሬታ ገለፀ:: አስተዳዳሪውም *ተበሳጨህ እንዴ? አትበሣጭ አየህ አሁን ምሥራቅ ጀርመን ስትሄድ ኮንሴንትሬሽን ካምፕ ውስጥ ለ30 ዓመት የታሰረ ሰው ታገኛለህ* አሉትና ወጥተው ሄዱ::





በዚህ ሁኔታ ላይ ቆይተን አቶ አዲሴ ቀልብሰው፣ ከበደ እርጋው፣ ሥዩም ካየሰና ሙሉ እመቤት መንበረ ወደ መጡበት ወደ አሰታ ወንዶ ወረዳ እንዲመለሱ ተደረገና ከወረዳው ፖሊስ ጣቢያ ገቡ::ይህ የሆነው በታህሣሥ ወር ላይ ነበር:: ከነ አቶ አዲሴ በኋላ ሦስት ወር ተፈርዶበት ወደ ይርጋ ዓለም ማረሚያ ቤት ተልኮ ከዚያም ወደ አራዳ፣ ወደ ቀበሌ 08፣ እንዲዛወር የተደረገው ወንድም ሰሎሞን ኃቢያም አብሯአቸው ወደ ወንዶ ተመለሰ::

ቀናት እየገፉ ሄዱ:: የጌታ ልደት በዓልም ደረሰ:: እኛም የልደቱን በዓል ለመጀመሪያ ጊዜ በእስር ላይ ሆነን ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ አከበርን:: በዚህ ወቅት አንድ ላይ የነበርን እኔ፣ ጌታሁን፣ አዳነና ይዲድያ ነን:: ይዲድያ ከቀበሌ 05 ወደ 08 ተወስዳ ወደ እኛ የተዛወረችው በቅርቡ ነበር:: እኛም ልደቱን ቡናና ቆሎ አዘጋጅተን ሌሎች እስረኞችና ፖሊሶችን በመጋበዝና ስለ ልደቱ አጭር ምስክርነት በመስጠት አከበርን:: በተለይም ጠባዩ እየተለዋወጠ ተጽዕኖ እያሳደ ረብን፣ ሲያስቸግረንና ድንገት እየተነሣ ሲመታን በነበረ ፖሊስ ፊት በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ የጌታን ስም ልናነሳ መቻላችንን እንደ ትልቅ ድል ነበር የቆጠርነው::

እኛም የዝምታ ባልናቸው ወቅት ውስጥ፣ እግዚአብሔር ግን ዝም አላለም:: በዚህ የልደት በዓል ወቅት መዝሙርም ሰጥቶናል:: መዝሙሩ በከፊል እንደዚህ ይነበባል:-

*የምሥራች አማኑኤል ተወልዶልናልና*
*እግዚአብሔር ከእኛ ጋራ ለዘላለም ሆኗልና*

*ሸለቆም ቢሆን ተራራ፣ቢያስገነት መከራ*
*አማኑኤል መከታችን፣ አብሮን አለ ከሁላችን*

*የምሥራች ..............ተወልዶልናል፤*
*እግዚአብሔር ከእኛ ጋራ በየሥፍራው ሆኗልና::*

# ምዕራፍ ሦስት - የወኅኒው እስራት

## መኖ ወዳለበት

በቀበሌና በፖሊስ ጣቢያ በተለይም እኔ አዳነና ጌታሁን፣ ለባት ወር እንደታሠርን፣ ለአውራጃው አስተዳደር ጽ/ቤት፣ የደረሰብንንና ያለንበትን ሁኔታ ገልጸን ለችግራችን መፍትሔ በመጠየቅ፣ አቤቱታ ጻፍን:: የጻፍነው ያዲድያ (ይመኙሻል) መስፍንን ጨምረን አራት በመሆን ነበር::

የአቤቱታችንን ቅጂ እነ ፓስተር ተሾመ ወርቁ ወዳሉበት ቀበሌ 05 ልከን ከእነርሱ የተሰጠንን አስተያየትም በመጠቀም አርመን አዘጋጀነው:: ከዚያም የእዳነ እለማየሁን እናት ከእለታ ወንዶ አስጠርተን በእርሳቸው እጅ ላክን:: እርሳቸውም እንደ ሄዱ፣ የአውራጃውን ዋና አስተዳዳሪ አግኝተው ከሰጡአቸው በኋላ የእዘኔታ መልክ እሳይተዋቸው ማመልከቻውን ለምክትል አስተዳዳሪው እስተላልፈዋል ተባለ::

በዚያው ሰሞን፣ የአውራጃው ምክትል አስተዳዳሪ የአውራጃውን ፖሊስ አዛዥና አንድ ካድሬ አስከትለው ወደ ነበርንበት ፖሊስ ጣቢያ ድንገት ከተፍ አሉ :: ምክትል አስተዳዳሪውም *የት አሉ የሃይማኖት እስረኞች የሚባሉት?* እያሉ ወደ እኛ ቀረቡ:: እኔ፣ አዳነና ጌታሁን በፖሊስ ጣቢያው የምናድርበትን ክፍል ግድግዳ ተደግፈን ከውጭ ቆመናል ፤ ይዲድያም በክፍሏ ውስጥ ነበረች:: ለውየውን *እኛ ነን* አልናቸው:: *መኖ ወዳለበት ትላካላችሁ:: መቶ አለቃ፡- ያንን ደብዳቤ የጻፉ እነዚህ ሳይሆኑ አይቀሩም* አሉና *ሰፊው ሕዝብ እስኪነቃ ድረስ* የትም ብንጽፍ ማንም እንደማይፈታን ገልጠው፣ በቅርቡም ወህኒ እንደምንላክ ጨምረው ተናገሩና ወጥተው ሄዱ::

በዚሁ መሠረት ጥር 22 ቀን 1972 ዓ/ም በዕለተ ሐሙስ ወደ ማረሚያ ቤት እንድንዛወር ሆነ:: በዕለቱም የተላክነው በቀበሌ 05 ከቆዩት ጋር ቁጥራችን 11 ነበር:: የስም ዝርዝራችንም የሚከተለው ነበር:-

1. ተሾመ ወርቁ
2. ኃይሉ በቀለ
3. እዳነ እለማየሁ
4. ጌታሁን አጋፋሪ
5. ተስፋዬ ጋቢሶ
6. መቆየቴ ከበደ
7. ማርታ ጋዲሶ
8. ወርቅነሽ ይመር
9. ያዲድያ መስፍን
10. ምንትዋብ አረሩ
11. ገብሬ አጃና (የይሖዋ ምስክር)

እኛም ዕቃችንን በጋሪ አስጭነን ወደ ማረሚያ ቤቱ አመራን:: እንደ ደረስንም ዕቃችን እየተፈተሸ በየኪሳችን የተገኘ ገንዘብ፣ ጥቂትም ቢሆን፣ እየተመዘገበ በማረሚያ ቤቱ ጸሐፊ ተያዘ:: ሲያስፈልገን እየመጣን ከገንዘቡ ጥቂት ጥቂት እየቀናነስን በመውሰድ መጠቀም እንደምንችልም ተገለጸልን:: የስማችንና የገንዘባችን ምዝገባ እንዳበቃ ከፖሊስ መምሪያ ተመድቦ ያመጣን ፖሊስ ተመልሶ ሲሄድ እኛ ወደ «ወህኒው ውስጠኛ ክፍል» - የእስረኞች ክልል - እንድንገባ ተደረገ::





እንደ ገባን ብዙ እስረኞች አየን:: አንዳንዱ የምናውቀው ሲሆን አብዛኛው የማናውቀው ነበር:: በነፍስ ግድያ፣ በሌብነት፣ በድብደባ፣ መብት በመድፈር፣ እምነት በማጉደል ወንጀልና በፖለቲካ ምክንያት የታሠሩ በርካታ ሰዎች በክልሉ ውስጥ ነበሩ:: ሁሉም እንደ ጉድ አዩን:: የሚያውቁን ቀርበው አነጋገሩን::

ከዚያ በኋላ፣ የእስረኞቹ አጠቃላይ መሪዎች፣ በማንም አዲስ ገቢ እንደሚደረግ ሁሉ ሁላችንንም ለያይተው፣ ማለትም ሁለት ሁለት ወይም አንድ አንድ እያደ.ጉ በየክፍሉ መደቡን:: ይህንን የሚያደርጉት ከማረሚያ ቤቱ አስተዳደር በሚሰጣቸው መመሪያ መሠረት ነበር:: እህቶቻችን ግን በሌላ በኩል ወደ ሴቶች ማረፊያ ተወሰደዋል::

## ኑሮ በማረሚያ ቤት

የ1972 ዓ/ም የመጀመሪያ አጋማሽ በቀበሌ እስር ቤት ካገባደድን በኋላ ቀሪውን አጋማሽ በይርጋ ዓለም ማረሚያ ቤት ሥፍራውንና ሁኔታውን በመለማመድ አሳለፍን:: የማረሚያ ቤቱን፣ ወታደሮቹን፣ እስረኛውንና ኑሮውን መልመድ ነበረብን:: ከፓስተር ተሾመና ኃይሉ በቀለ በስተቀር፣ የማረሚያ ቤቱ በአጠቃላይ ፤ ለእኔና ለሌሎቹ እንግዳ ነበር::

የእስረኛው ክልል አደባባዩ አግር ስለሚበዛበት ሣር አልነበረውም:: በበጋ አቧራው በክረምት ጭቃው ከዚህ አደባባይ አይጠፋም:: በዚያው ላይ ምንም ጠባብ ቢሆን የስፖርት ስሜቱ ያላቸው የእጅም ሆነ የእግር ኳስ ይጫወቱበታል::

ሣርና ጥላ ያለው ከየማደሪያው ጀርባና በየአጥሩ ጥግ ነበረና እስረኞች እየተቀመጡበት ይዝናናሉ፤የእጅ ሥራ፤ዘንቢል፣ፌስታል ፣ሽምቀቆ የሚባሉ የዕቃ መያዣዎችን ይሠራሉ:: እነዚህን ከዘንባባ ቅጠል የሚያዘጋጁ ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ ሹራብ ይሠራሉ፤ ፀጉር ያስተካክላሉ፤ የእንጨት ውጤቶችን ለምሳሌ ወንበር፣ ጠረጴዛ፣ ጊታርና ማበጠሪያ ይሠራሉ:: አንዳንዶች ደግሞ እንደ ቀሚስ ፣ነጠላ፣ጋቢ የመሳሰሉ የሸማ ምርቶች ያዘጋጃሉ:: ከሱፍ ክር የሚዘጋጁ ልብሶችም ነበሩ:: ልብስ ሰፊዎች የሆኑ እስረኞች ደግሞ የስፌት መኪናቸውን እያስመጡ ይሠሩበታል::

ማደሪያ ክፍሉቹ ደግሞ ለአዲስ ገቢ አፍንጫ ከበድ የሚል ልዩ ጠረን አላቸው:: በአንድ ክፍል ውስጥ ከ30 - 80 የሚደርስ እስረኛ ያድራል:: ሰፋ የሚሉ ክፍሎችም ወደ 120 የሚሆን ሰው የሚያምቁበት ጊዜ አለ:: በየክፍሉ ቆየት ያሉ እስረኞች አልጋ ላይ ሲተኙ የዕቃ ማስቀመጫ ሥፍራቸውም በመጠኑ ሰፋ ያለ ነው:: አዲስ ገቢ መሬት ላይ፣ ለሴን ብቻ ያለው በለሴን ላይ፣ ፍራሽ ያለው ደግሞ ፍራሹን አንጥፎበት ይተኛል:: እኛም እንደ ገባን ፍራሽ ስላልነበረን የምንተኛው ለሴን ላይ ነበር ::

እያንዳንዱ ሰው ከየራስጌው፣ በአንጻሩ ካለው ግድግዳ ላይ፣ ከፍ አድርጎ የሽንት ፖፖውን ይሰቅላል:: ፖፖው ወደ ክፍል የሚገባው ከእስረኛ ቆጠራ ጥቂት ቀደም ብሎ ወይም በዚያው በቆጠራ ሰዓት ነው:: ቀን ቀን ግን ፖፖው ሽንት ቤቱ አካባቢ ነፋስ እየተቀበለ ይውላል:: ከራስጌው በላይ የሚሰቀለው ፖፖው ብቻ አልነበረም፤ የእስረኛው ልብስ፣ሌላው አነስተኛ ንብረት፣ ሻንጣም ጭምር እንጂ::

ከግርጌው ደግሞ የምግብ ዕቃ፣ እንደባልዲ፣ ድስት፣ የእንጀራ መሶብ የመሳሰሉት ይቀመጣሉ:: የቆዩ እስረኞች፣ የምግብ ዕቃቸውን ከግርጌ በማስቀመጥ ፋንታ ከጎናቸው ባለው ሥፍራ ወይም በቤቱ ማዕዘን አካባቢ ያስቀምጣሉ::

የእያንዳንዱ ሰው የጽዳት አጠባበቁ የተለያየ ነው:: አንዳንዱ ሰውነቱን በየሳምንቱ ይታጠባል፤ ልብሱንም ያጥባል:: ሌላው ደግሞ፣ ስለ ግል ንጽህናው እምብዛም የማይጨነቅ ነው:: የማደሪያ ክፍሎቹ ደስ የማይል ጠረን የሚኖራቸውም ለዚህ ነበር::

የማደሪያ ክፍሎቻችን ጠዋትና ከሰዓት በኋላ በተረኛ እስረኞች ይጠረጋሉ:: ሲጠረግ የሚቦነው አቧራ በየምግቡ ዕቃ ላይ በየመኝታውና በየግድግዳው ዕቃ ላይ ያርፋል:: እያንዳንዱ ክፍል በሁለት ሳምንት ወይም በወር አንድ ጊዜ ዕቃ ሁሉ ወጥቶ ፀሐይ ላይ እንዲሰጣ ይደረግና አጠቃላይ ጽዳት ይካሄዳል:: ይህንን ጽዳት ሁሉም እስረኛ ተባብሮ ያከናውነዋል:: ይህም ሁሉ አየሆነ ትኋን ቁንጫና ቅማል ጠፍቶ አያውቅም::

አመጋገባችን ደግሞ የሚከተለውን ይመስል ነበር:: በእስር ቤቱ አስተዳደር ለእያንዳንዱ እስረኛ በቀን 72 ሳንቲም ለመኖው - የእስረኛ ቀለብ - ወጪ ተመድቧል ይባላል:: አብዛኛውን ጊዜ ጠዋት ጠዋት ዳቦ የሚታደል ሲሆን ለቀንና ለማታ እንጀራና ወጥ ይቀርባል:: ዳቦውም ሆነ እንጀራው ስንዴ ወይም ጤፍ ለዐመል ያህል ይቀላቀልበት እንጂ አብዛኛው እጅ በቆሎ ነው:: በወር አንድ ጊዜ ስኳርና ሥጋ ይሰጣል:: ስኳሩ ለዳቦው ማባያ - ለሻሂ - ሲውል ሥጋው ለወጥ መቀየሪያ የታሰበ ነው::

በየዕለቱ የሚሰጠውን ወጥ እንዳለ ተቀብሎ ለመብላት የማይመች ነው:: አንዳንድ ጊዜ በሚገባ አይበስልም:: ሌላ ጊዜ ደግሞ ያረረ ይሆናል:: ስለዚህ እያንዳንዱ እስረኛ ወጡን ከተቀበለ በኋላ እንደገና ከዘይቱም፣ ከሽሮውም፣ ከጨውም ጨማምሮና አጣፍጦ ማብሰል የግድ ይኖርበታል:: መደበኛ አመጋገቡ ከዓመት እስከ ዓመት፣ ያለ ምንም ለውጥ፣ ይኸው ነበር:: ከዚህ በተረፈ፣ ዘመድ ያለውን ዘመዱ ይጠይቀዋል:: በዘመድ መጠየቂያ ቀን - ማክሰኞ፣ ሐሙስና እሁድ - የቤት ምግብ እንዲቀበል ይፈቀድለታል:: በእነዚህ ቀናት ውስጥ ዘመድ ወዳጆቻችን በበለጠ ነጻነት ከቅርብና ከሩቅ ጎብኝተውናል:: በትጋት አጽናንተውናል:: በመጠየቂያ አጥር ላይ እንባቸውን አፍስሰዋል::

የመጠጥ ውኃው ደግሞ በመጀመሪያ ወቅት ላይ ከጉድጓድ ነበር የሚቀዳው:: እኛ እንደገባን የነበረው የቧንቧ ውኃ ብዙም ሳይቆይ ጠፋ:: ከ1973 ዓ/ም በኋላ





ግን እስረኛው ራሱ ባዋጣው - መንግሥት ከሚሰጠው መኖ ላይ በፈቃደኝነት በተወው ገንዘብ - የቧንቧ ውኃ በአዲስ መልክ ተሠርቶ ስለገባ ከመጠጥ ተርፎ ለሰውነት መታጠቢያ ሻወርም እንኳ በቅቷአል::

ሕክምና በሳምንት አንድ ወይም ሁለት ቀን ይፈቀዳል:: ይኸውም፣ ተመዝግቦና ወረፋ ተጠብቆ፣ ተራው የደረሰለት ሰው ወደ ጤና ጣቢያ ወይም ሆስፒታል ይላካል ማለት ነው:: ከእስረኞች መካከል የሚመረጡት የጤና ተጠሪዎች አንዳንዴ ችግር ይፈጥራሉ:: አድልዎ በማድረግ ጓደኞቻቸውን፣ ያውም ያልታመሙትን በማስወጣት፣ የታመሙትን ግን በማስቀረት የሚበድሉበት ጊዜ ነበር:: ሐኪም ቤት ለመላክ ብቻ እጅ መንሻ የሚቀበሉም አልፎ አልፎ አልታጡም:: ያ ብቻ አይደለም:: በዕለቱ ሕመምተኞችን ሐኪም ቤት ይዞ እንዲሔድ በእስረኛው አስተዳደር የጸጥታ ክፍል የሚመደበው ወታደርም ቢሆን የሚጠላውን በሽተኛ ትቶ ይሄዳል:: እኛን፣ በሃይማኖት ጉዳይ የታሠርነውን የሚጠሉ ወታደሮች፣ ታመን ወጥተን ብዙ ጊዜ ከሐኪም ቤት አስቀርተውናል:: ከሐኪም ቤት ሲመለሱ መጠጥ የማይጋብዛቸውን ሕመምተኛ ይዘው መሔድን አይወዱም ነበር::

በእርግጥ፣ ብዙዎቻችንን የሚበዛው በሽታ ያገኘን ከታሠርን በኋላ ነው:: የአሜባ፣የጨጓራ፣ የብርድ፣የዓይን፣ የኪንታሮት ወዘተ ሕመም ያገኘን እዚያው እስር ቤት እያለን ነበር:: በሕመም ምክንያት እንድንሞት የሚመኙ ወታደሮችም አልታጡም ነበር:፤ *ሰምን ድብን አይልም ! ራሱን በገዛ እጁ አስሮ !* እያሉ እኛን ጥለው ሌሎችን እየያዙ ሐኪም ቤት የመሄድ ሁኔታዎች ነበሩ:: ጌታ ምሕረቱን ይስጣቸው:: ይህ ማለት ግን የሚራሩልን ወታደሮች አልነበሩም ማለት አይደለም:: በዚህም ሆነ በዚያ፣ እግዚአብሔር ታላቅ ጥንቃቄ ስላደረገልን፣ ከበሽታ የተነሣ አንዳችንም ሳንሞት፣ ከእስር ቤት በደኅና እንድንወጣ ረድቶናልና ስሙ የተመሰገነ ይሁን::

የማረሚያ ቤቱ ግን «ከቀበሌ» የሚለይባቸው መልካም ገጽታዎች እንደ ነበሩት አይካድም:: አስተዳደሩ በመጠኑም ቢሆን ሕጋዊ አሠራር እንደሚከተል አይተናል:: በቀበሌ እስር ቤት ማንም ተራ ሰው እስከ እስረኛው ዘልቆ በመግባት መጨቃጨቅና መሳደብ ይችል ነበር:: የማረሚያ ቤት ግን አሣሪው ባለ ሥልጣን ራሱ ወይም እርሱ የላካቸዉ ሰዎች ካልሆኑ በቀር፣ አስጠርቶ ወይም ወደ ማረፊያችን ገብቶ ማንም ሊያናግረን አይችልም ነበር::

ሌላው የማረሚያ ቤቱ ብልጫ፣ ሰፋ ያለ እስር ቤት እንደ መሆኑ መጠን፣ በእስረኛው ክልል ውስጥ ለመንሸራሸርና ነፋስ ለመቀበል መቻሉ ነው:: የእስረኛ ክፍሎች ከጠዋቱ 1 ሰዓት ተኩል ጀምሮ ይከፈታሉ:: ከዚያ በኋላ እስከ ቀኑ 11 ሰዓት ተኩል አንዳንድ ጊዜም፣ እንደ ተረኛው ዘብ ኃላፊ ደግነት፣ እስከ ቀኑ 12:30 አይዘጋም:: በቀበሌ እስር ቤት ግን ማንም የቀበሌ ዘበኛ ክፍሎቹን እንደ ፈለገው ከፍቶ ወይም ዘግቶ ያውለን ነበር:: የተወሰነ ሥርዓት አልነበረም::

እኛ ስንገባ የነበሩት የማረሚያ ቤቱ ኃላፊ ሻምበል አበበ ሀደሩ በአስተዳደር ተለጥአዋቸው የሚደነቁ ነበሩ:: በጊዜው የነበሩ የፖለቲካ እስረኞች ጭምር

ሲወዱእቸውና ሲያደንቁእቸው አይተናል:: *ሥራ ወዳድ እንደ መሆናቸዉ* መጠን፣ እስረኛውን በመጠቀም የማረሚያ ቤቱን ጓሮ በሚያስመሰግን ሁኔታ አልምተውት ነበር:: እስረኛው አልወጣ ብሎ ሲያስቸግር ደግሞ፣ ራሳቸው ገብተው በመቀስቀስ አስወጥተው አንዳንድ ጊዜም ዶማ በመያዝ፣ እንደ መቆፈር እያደረጉ «ሞራል» በመስጠት ያሠሩ ነበር:: በዚህ መልኩ፣ በቡና ተክል፣ በቦሎቄና በቦቆሎ ምርት *ሥራ*፣ የማረሚያ ቤቱንም ሆነ የራሳቸውን ስም በመልካም አስጠርተዋል::

የሻ/ባሻ እስጢፋኖስ «ድምፃቸው የማይሰማ » የማረሚያ ቤቱ ምክትል አስተ ዳዳሪ ነበሩ:: እርሳቸውም ከሻምበል አበበ ቀደም ብሰው ተዛውሩና ሌላ ቦታ ሄዱ::

ሌሎቹ ወታደሮች ሁኔታቸው የተለያየ ነበረ:: አንዳንዶቹ ደጎች ሲሆኑ የሚበዙት ግን እጅግ ከፉብን:: የመረረ ጥላቻቸውን በግብር ይገልጡ ነበር:: ሊጠይቁን የሚመጡትን ዘመዶቻችንን እየሰደቡ በማዋረድ እኛንም በእነርሱ ፊት በመሳደብና በመገፈታተር፣ እንደ ልብ ተጫውተን ናፍቆታችንን እንዳንወጣ በመከላከልና ስንቃችንን ከሌላው እስረኛ ስንቅ በተሰየ ሁኔታ በመፈተሽ፣ እንዳንዴም ያለ ምክንያት በመማታት፣ እስቀድሞ እንደ ተጠቀሰው በሕክምና ጉዞ ቀን እኛን በማስቀረት፣ ሠርተን ወደ ውጭ በምንልከዉ የእጅ ስራ ዕቃችን ላይ ቀረጥ በማብዛትና በመሳሰለው ሊያበሳጩን ብዙ ጣሩ:: ሆኖም ጌታ ካበዛልን ጸጋ የተነሣ *ታገሥን* :: እነርሱ ደከሙ:: እኛ ግን በእምላካችን ጸናን::

በገባን ጊዜ በእስረኞች መሐል የሚታዩት የፖለቲካ እስረኞች፣ ከነበረው እስረኛ ሁሉ ይልቅ የተማሩ ስለነበሩ፣ በማረሚያ ቤቱ ጠቅላላ እንቅስቃሴ ላይ ከፍ ያለ አስተዋጽኦ ነበራቸው:: በእስረኛ አስተዳደር ቢሮ የጽሕፈት እርዳታ በመስጠት፣ ለአስተዳደሩ ምክር በመለገስና በተማረ ሰው ሲሠሩ የሚችሉ *ሥራዎችን* በማከናወን፣ ብዙውን ነገር ይቆጣጠሩ ነበር::

ከእስረኞች እንዳንዶቹ ጉዳያቸው በፍርድ ቤት እየታየላቸው በቀጠሮ የቆዩ፣ ሌሎቹ ተፈርዶባቸው የተቀመጡ ሲሆኑ፣ የተወሰኑቱ ደግሞ እንደ እኛው ፍርድ ቤት ሳያውቃቸው ያለ ውሳኔ ቀናቸውን የሚቆጥሩ ነበሩ:: እኛን በሚመለከትም፣ የሚበዙቱ እስረኞች ግድ አልነበራቸውም:: አንዳንዶቹ ግን፤ የሐሰት ወሬ በማሰራጨት ሊያሳጡንና ከማረሚያ ቤቱ እስተዳደር ጋር ሊያጋጩን፣ እስረኞች እንዲጠሉንና በክፉ እንዲነሳሱብን ለማድረግም የተቻላቸውን ሁሉ ጥረዋል:: በዚያው አንፃር ደግሞ፣ ቁጥራቸው ጥቂት ቢሆንም፣ የሚያዝኑልንና የሚወዱን ሰላማዊ እስረኞች አልታጡም::

## <u>ተጨማሪ ሁነቶች</u>

ዓመቱ ከማለቁ በፊት የተፈጸሙ ሁለት ዓበይት ነገሮች አሉ:: አንደኛው፣ በ4/9/72 ወደ እውራጃው አስተዳደር ቢሮ ተጠርተን የመጠየቃችን ጉዳይ ነበር:: የተጠራነው እንድንፈታ ነበር ተብሏል:: *የመፈቻ* ወረቀት ሁሉ ተጽፎና





ተፈርሞበት እንደ ተዘጋጀም ሰምተናል:: ሆኖም በጣም ቀላል በሚመስል ምክንያት ሁኔታው ተሰነካከሰና ተመልሰን ከማረሚያ ቤቱ ገባን:: የእግዚአብሔር ጊዜ ስላልደረሰ መመለሳችንን ግን አወቅነው:: ሁኔታውም የሚከተለውን ይመስል ነበር፤

ከፍ ብሎ ከላይ በተጠቀሰው ዕለት፣ ወደ ሲዳማ አዉራጃ አስተዳደር ቢሮ ስንገባ፣ በክፍሉ ውስጥ የነበሩት ዋናው አስተዳዳሪ፣ እኛ ከገባን በኋላ ምክትል አስተዳዳሪ የነበሩትን፣ አቶ ጀንበሩ ተካንና አንዳንድ የቀበሌ ሊቃነ መናብርትን በስልክ ሲፈልጓቸው አይተናል:: ሆኖም ማንም ሳይመጣላቸው ቀረ:: ብቻቸውን ለመወሰንና ለመልቀቅ ማመንታት የያዛቸውም ይመስሉ ነበር:: በዚህ መካከል እያንዳንዳችንን እያነጋገሩ - እየመረመሩን - ቆዩ::

ጥቂት እንደ ቆየን የማረሚያ ቤቱ ዋና አዛዥ፣ ሻምበል አበበ ዘግይተው ገቡና ከአውራጃው አስተዳዳሪ ጎን ተቀመጡ:: በዕለቱ ወደ አስተዳደር ቢሮው የመጣን፣ የእምነት ጉዳይ እስረኞች ብቻ አልነበርንም :: በፖለቲካ ጉዳይ ከታሠሩትም ጥቂቶች መጥተዋል:: ከእነርሱም መካከል አቶ ሙሉጌታ፣ እፖሎ በሚባል ቅጽል ስም የሚጠሩት ባለ ታክሲ ይገኛል::

የአውራጃው አስተዳዳሪ እኛን በጥሞና አነጋግረው ሲያበቁ አቶ ሙሉጌታን *አንተ ደግሞ ጴንጤ ነህ እንዴ?* አሉት እርሱም መሰሰና *ኧረ እኔ ጴንጤ አይደለሁም* አሰና ግራ እጁን አንስቶ ያልተጠየቀውን መፈክር ደረደረ:: *እናንተ ስ መፈክር አታሰሙም?* አሉን ዋናው አስተዳዳሪ ወደ እኛ ተመልሰው:: *እስቲ እጃችሁን አንሡ* አሉን:: ግራ እጅ ማለታቸው ነበር:: ከመሐላችን፣ አቶ ገብሬ አጃና ሁለት እጁን ወደ ላይ ዘረጋ:: ሌላ ምንም አልተናገረም፤ አልተጠየቀም:: ዋናው አስተዳዳሪ፣ *አሱ ከዛሬ ጀምሮ ተፈቷል! እናንተ ግን ወደ ማረሚያ ቤቱ ትመለሳላችሁ:: በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥም ውሳኔ እንሰጣችኋለን* አሉ:: *አልገባንም! ጥያቄ አለን* አልን:: *ሃሳቤን ጨርሻለሁ* አሉና ገብሬ አጃናን ግንቦት 4 ቀን 1972 ፈተውት፣ የቀረነው ተመልሰን ወደ ማረፊያችን ሄድን::

ተመልሰን ወደ ማረሚያ ቤቱ ስንመጣ፣ እንደምንፈታ በጉጉት ከጠበቁት መካከል፣ተማሪዎች የነበሩት በላይነሽ ናራሞና ጌጤነሽ አባተ፣ በማረሚያ ቤቱ በራፍ ላይ አግኝተውን አለመፈታታችንን ሲገነዘቡ፣ ያፈሰሱት እንባ በቀላል ለመግለጽ የሚቸግር ነበር::

ሳምንታትና ወራት አለፉ:: ይሰጣችኋል የተባለው ውሳኔ ጉዳይም የውሃ ሽታ ሆኖ ቀረ:: በ1972 ማለቂያ ግድም የተፈጸመ ሌላው 2ኛ ድርጊት፣ በ5/10/72 በይርጋ ዓለም ሁለተኛ ፖሊስ ጣቢያ ማልትም በቀበሌ 08 የነበሩ ስድስት ወንድሞችና አንዲት እህት እኛ ወዳለንበት ማረሚያ ቤት መላካቸው ነበር:: እነርሱም:-

1. ማርቆስ ተፈራ -በ03/3/72 የታሰረ
2. ታፈሰ ቦኤ - በ12/4/72 »
3. ተስፋዬ ቃሚሶ - በ28/4/72 »

4. በራሣ ባንቡሮ -በ2/8/72 »
5. ሰገሠ ዲኬ - በ13/8/72 »
6. ሺመልስ ሰማ - በ5/9/72 »
7. ዝናሽ ኃይሉ - በ9/9/72 የታሰረች ነበሩ።

እሁን ቁጥራችን ወደ 17 ደረሰ ማለት ነው። ወንድሞች 11፣ እህቶች 6። በዚሁም መልክ 1972 ዓ/ም አሰቀ።

## ከልምምድ ወደ ሥራ

ያለፈው ዓመት፣ አካባቢያችንን በማጥናትና ራሳችንን በማለማመድ የተዘጋጀንበት ሲሆን ፣ ይህ ዓመት፣ 1973 ዓ/ም፣ ለረጅም ጊዜ የሚታሠር ሰው የሚሠራውን ሥራ ተደላድለን መሥራት የጀመርንበት ነው። በዚሁ መሠረት፣ ለእስር ቤት የሚያስፈልጉንን የመኝታና የመመገቢያ እንዲሁም ለእጅ ስራ የሚጠቀሙንን ዕቃዎች እያስገዛን ማሟላት ነበረብን። በየዝንባሌአችንም፣ አንዳንድ የዕደ ጥበብ ሥራዎችን ከእስረኞች ተምረን፣ የሥራ እንቅስቃሴ ማድረግ ጀመርን። እኔ ወደ እንጨት ሥራ አዘነበልኩ። በዚህ መሠረት ጊታር የሚባለውን የሙዚቃ መሣሪያ የመሥራት ጥበብ ቀሰምኩ። ይህንን ለራሴም ባይሆን ለአንዳንድ ወዳጆቼ ማዘጋጀት ደስ ይለኝ ነበር።

ፓስተር ተሾመ በዘንባባ ሥራ ጎበዝ ነበር። በቃበሌ እስር ቤት ሳለ ከደረሰበት የድብደባ ጉዳትና ሃይለኛ የብርድ በሽታ የተነሣ በተለይ ከ1972-1974 ብዙ መሥራት ባይቻለውም ሲሻለው ሲሻለው ጥራት ያለዉ ዕቃ፣ ለምሳሌ፣ ባለ ሁለት ዚፕ ሻንጣ፣ሽምቀቆ ሥጋጃ . . ወዘተ ይሠራ ነበር።

ፓስተር ኃይሉ በቀሰም እንደዚሁ፣ በዘንባባ ሥራ ጎበዝ ነበር። ኃይሉ ደከመኝን የማያውቅ እውነተኛ አገልጋይ ነው። በግቢው የምንገኘውን ወገኖች የምግብና የአመጋገብ ሥርዓት በትጋት ይቆጣጠር የነበረ እርሱ ነው። ከትህትናውና ከትጋቱ፣ ከትዕግሥቱም ብዙ ተምሬያለሁ። ለብዙዎቹ ታናናሽ ወንድሞቻችን ጨጋ አቀዳድ፣ሻሂ አፈላል፣ወጥ አሠራር አግባብ ያለው የቁሳቁስ አጠቃቀም ያስተማረ እርሱ ነው። ፓስተር ተሾመም እልፎ እልፎ ከእኔ በተሻለ መንገድ ጥሩ አሳብ በማቅረብ የአመጋገብ ሥርዓታችን መልክ እንዲኖረው ጥሯል።

ሽመልስ ለማና ታፈሰ ቦሌ፣ በግቢዉ የተዋጣላቸው የሽመና ጥበብ ባለሞያ ሆነዋል። በራሣ ባንቡሮ፣ እስከ ተፈታንበት ቀን ድረስ የወንድሞችን ፀጉር ሲያስተካክል ኖረ። ከዚህ ውጪ፣ በራሣ የሌሎችንም ጸጉር በገንዘብ እያስተካከለ ራሱን ለመርዳት ይሞክር ነበር ። ከፀጉር ሥራ ሌላ ደግሞ እርሱም እንደ እኔው ወደ እንጨት ሥራ በማዘንበል ማበጠሪያዎችን እየሠራ ይሸጥ ነበር።
ጌታሁን አጋፋሪ፣ ለዘንባባና በሹራብ ሥራ ብርቱ ነበር። በእርግጥ፣ የኩላሊት በሽታ ነበረበት። ከሥራ ወዳድነቱ የተነሣ ግን እያመመው ሳለ እንኳ አያርፍም። ልብሶችን ያጥባል፣በሳምንት ሁለት ቀን በተለይም እሁድና ሐሙስ፣ የማዕድ አገልግሎት በሚበዛባቸዉ ቀናት፣ የማዕድ ተረኛ ሆኖ ይሠራል፣





መንግሥት ሥጋ በሚሰጥበት ቀን ሥጋው እንዳይበላሽ እየዘለዘለ ያዘጋጃል፣ሻንጣና ፌስታል ይሠራል። ዘንባባ በቀሰም ይነከራል። ፍራሽ ይሠራል - ይሠራል - ይሠራል !

ከተወሰነ ጊዜ በኋላ፣ ከየመሥሪያ ቤቱ ኮከብ - ምስጉን ሰራተኞች - ተመርጠው ሽልማት ይሰጣቸዋል ተብሎ ከኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ አደራጅ ኮሚሽን - ኢሠፓአኮ - ወደ ማረሚያ ቤቱ መመሪያ በተላከ ጊዜ እስረኞች ጌታሁንን የመ ረጡት በከፍተኛ ድምጽ ነበር። የማረሚያ ቤቱ አዛዥ እስቀሩትና ሄዶ ሳይሸለም ቀረ እንጂ። ይህን ያደረጉት ጴንጤ አቅርቤ ያሳፍረኛል በሚል ስጋት ነው።

አዳነ ዓለማየሁ፣ በሥራው በአብዛኛው ጌታሁንን ይመስላል። ወንድሞቻችን ሁሉም ሥራ ወዳዶች ነበሩ። አንዳንዶቹ በተወሰነ ሥራ ላይ ሲተጉ ሌሎቹ ደግሞ ሁስገብ ዓይነት ናቸው።

## መነቃቃትና መፈተን

በዚያ ቦታ የተገኘነው፣ ከሁሉ በፊት፣ ለመንፈሳዊ ጉዳይ ስለሆነ፣ ከፍ ብሎ ከላይ የተመለከተው ዕለታዊ እንቅስቃሴያችን ወደ አንድ ወገን አመዝኖ፣ መንፈሳዊ ሕይወታችንን እንዳያዳክምብን መጠንቀቅም ነበረብን። በእርግጥ፣ በእምነት እየጠነከርን፣ በመንፈስ እየተነቃቃን፣ በምስክርነታችንም እየተጋን፣ የመበርታት መሻት በሁላችንም ልብ ውስጥ ነበር። ፈተናዎችም እልፎ እልፎ ማጋጠማቸው አልቀረም።

እንዲህም እየሆነ፣ እስከተፈታንበት ጊዜ ድረስ፣ በሳምንት አንዱን ቀን፣ ረቡዕን፣ ለጋራ ጾምና ጸሎት እያዋልን ተጠቀምንበት ። እንደ አመችነቱም የመጽሐፍ ቅዱስ የቡድን ጥናትና በጋራ የምንጽናናባቸው ጊዜያት ነበሩን ። ያንን ያደረግነው ተመችቶን ሳይሆን በብዙ ተጋድሎና ጌታን በመታመን ነበር። በመጀመሪያ ላይ ፕሮግራሞቻችንን በሚያረካ ሁኔታ ለመቀጠል በማያስችል ጠበብ ያለ ሁኔታ ውስጥ ነበርን። በኋላ በኋላ ግን ጌታ እግዚአብሔር ቀስ በቀስ እያሰፋልን መጣ።

የታሰሩትን እህቶቻችንን በፊት ለፊት አግኝተን የምናነጋግርበት መንገድ አልነበረም። ጌታ ግን፣ እስከ መጨረሻው ድረስ፣ የማበረታቻ መልእክቶችን የምንለዋወጥበትን ስውር መንገድ ሰጠን፤ ጠበቀልንም።

ከዚህ በቀር፣ እያንዳንዳችን በልባችን እንደ ተሰማን የግል ጊዜያት - የጾምና የጸሎት ቀናት - እየወሰድን በጌታ ፊት እንሆን ነበር። ጊዜያቱ፣ ራሳችንን በጌታ ፊት በመመርመር፣ በመንፈሳዊ ጉድለቶቻችን ላይ ንስሐ በመግባት፣ አብረውን ሳሉት ወንድሞችና እህቶች በመማለድ፣ ቅዱስ ቃሉን በማጥናት፣ ከራሳችንም ክልል እየወጣን ከውጭ የነበረውን የጌታን ሥራ በማሰብ፣ በምድሪቱም ላይ ለሚሆን የወንጌል ሥራ የምንጸልይባቸው ነበሩ። እግዚአብሔርም መንፈሳዊ

ሕይወታችንን በዚህ ሁሉ ውስጥ እያበጃጀ ይቀርፅ ነበር::
በ1973 ዓ/ም በእጠገባችን ለነበሩና ክርስቶስ ኢየሱስን ለማያዉቁ እስረኞችም ከምን ጊዜውም በበለጠ ድፍረት መስክርንላቸው:: በቁጥርም ጥቂት ያይደሉ ሰ ዎች በእምነትና በንስሐ ወደ ጌታ ዘወር እሉ:: ሕይወታቸውም ተለወጠ:: ሲጃራ አጫሾች፣ ጫት ቃሚዎች፣ የእልኮል መጠጥ ሱሰኞች፣ ወዘተ ከታሠሩበት እስራት እየተፈቱ በክርስቶስ ብቻ የሚገኘውን ነፃነት ተለማመዱ:: ከዚህ ጋር በተያያዘም በየክፍሉ ማታ ማታ የፀሎት ስብሰባ ይደረግ ነበር:: ወደ ጌታ የሚመለሱትም ቁጥር ከቀን ወደ ቀን በየክፍሉ እየጨመረ መጣ::

ተስፋ የመቁረጥና የማዘን ፈተናም በድንገት ብቅ እያለ ማስፋ አልቀረም:: ሰይጣን፣ አንዳንድ ጊዜ፣ እግዚአብሔር ፈጽሞ የጣለንና የተወን በማስመሰል፣ ከእጃችን የወጡና ያጣናቸውን ነገሮች በማስታወስ፣ የወደፊቱን ተስፋ ለማጨለም የሞከረባቸው ጊዜያት በእርግጥ ነበሩ:: ከዚህም የተነሳ፣ ይህ ሁሉ ከሆነ በኋላ፣ ተመልሶ ወንጌሉን የማገልገል ዕድል ይገኛል ብሎ ለማሰብ የከበደበት ወቅት እንደ ነበረም አስታውሳለሁ:: መንፈስ ቅዱስ ግን፣ *ኢዮብምኮ ምርኮው የተመለሰለት ሁሉንም ካጣ በኋላ ነበር!* የሚል የሚያጽና ድምጽ በልቤ ውስጥ አመጣና ተስፋዬ ታደሰ::

1973 ዓ/ም፣ ከሞላ ጎደል ይህን በሚመስል ሁኔታ ሊጠናቀቅ ሲል በክረምቱ ላይ አንድ ካድሬ ወህኒ ቤት ድረስ መጥቶ አነጋግሮናል:: ስሙ ጓድ እምሻው ይባላል:: በመጀመሪያው ቀን ያገኘን በጅምላ ሲሆን፣ በሁለተኛው ቀን በተናጠል እየጠራ ነበር ያነጋገረን::

ካድሬው በአነጋገሩ ሰዘብ ያለና ሰፋ ያለ አመለካከት ያለው ይመስላል:: እስከዚያ ጊዜ ድረስ ያየናቸው ካድሬዎች ሁሉ በሁኔታቸውና በንግግራቸው ሲበዛ የሚያስፈራሩ፣ የመናገርና የመጠየቅ ዕድል ለመስጠት የማይወዱ ዓይነት ነበሩና ይኸኛው የተሻለ ሆኖ እየነው:: ሆኖም የተሳከበትን የማንቃት ተልዕኮ በሚመለከት፣ ማስተማሩን ፈጽሞ ከመመለስ በስተቀር ሌላ ውጤት አልተገኘ ም:: የእኛ አቋም የማይለወጥ ስለነበረ በእርጋታ መካከረንና ተመልሶ ሄደ:: ስለዚህም፣ ይኸኛው ቀለል ያለ ፈተና ነበር ማለት ይቻላል::

በሌላ በኩል ደግሞ፣ ከካድሬው ትምህርት የተነሣ ባይሆንም፣ እህታችን ምንትዋብ እረሩ ባጋጠማት ቤተሰባዊ ችግር ሳቢያ ብዙም ሳይቆይ ተለቃለች:: ይህም በነሐሴ ወር ውስጥ ሆነ:: ቀደም ሲልም ከአለታ ወንዶ የአንድ ዓመት ቆይታ አድርገው በየካቲት 1973 ላይ ከተመለሱት ከእህታችን ሙሉ እመቤት መንበረ፣ሰለሞን ኃጢያና ከበደ እርጋው ጋር ቁጥራችን 19 ሆነና ዓመቱ አለቀ:: ያኔ፣ እነ ሙሉ እመቤት ሲመጡ፣ ሥዩም ካዴሶ - ከይሖዋ ምስክርና ከበደ ሣሣሞ ከገኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተ እምነት አብረዋቸው እንደመጡ ይታወሳል::





## ውስጣዊ ስደት - በእስር ቤት

በ1973 ዓ/ም የነበረው የወንጌል ምስክርነትና የነፍሳት መዳን መነቃቃት ግን በ1974 ዓ/ም መግቢያ ላይ የእስር ቤት ውስጥ ስደትን ማስነሳቱ አልቀረም :: ከዕለታት አንድ ቀን ቀድሞ በሌላ ክፍል ያድር የነበረ አንድ ወጣት እስረኛ ያሰወትሮው ከእኛ ገሚሶቹ ወደምናድርበት ክፍል መጥቶ አደረ:: ክፍሉ ለባት ቁጥር ተብሎ የሚጠራ ነበር:: በዚያውም ምሽት ላይ ከሌሎች አማኝ እስረኞች ጋር የነበረንን መንፈሳዊ ፕሮግራም ተመለከተ::

በዚህች ክፍል ውስጥ በእምነት ማጉደል ወንጀል ተከሶ የታሰረ አንድ ልብስ ሰፊም ነበር:: በተደጋጋሚ በሌብነት ወንጀል እየታሰረ ማረሚያ ቤት የተመላለሰና ከልብስ ሰፊው ጋር አብሮ ጫት ይቅም የነበረ እቶ ዑስማን የሚባል ሰውም ነበር:: ያ ወጣት ደግሞ በእኛ ክፍል ውስጥ ልብስ ሰፊው ጋ በማደር ሁኔታችንን ታዝቦ በማግሥቱ ወደ ቦታው ተመለሰ:: በቀጣዮቹም ቀናት በግቢው ውስጥ እየዞረ በእኛ ላይ ስደት ለመቀስቀስ የሚችለውን ሁሉ አደረገ:: ከዚህ በኋላ በሌብነት ወንጀል የታሰረው ሰውዬ ማታ ማታ ሰክሮ እየገባ እኛ በጸሎት ስብሰባ ላይ ሳለን ይሰድበን ጀመር::

ሁኔታው ቀስ በቀስ እየከፋ መጣ:: ከዕለታት አንድ ቀን ማለትም ጥቅምት 10/74 ዓ/ም ላይ ሰውየው እንደ ልማዱ ከማዶ ሆኖ ለጸሎት የተሰበሰብነውን መሳደብ ጀመረ:: በመሐሉ እንዱ፣ የራሱ ጓደኛ የሆነ ሌባ፣ *አንተን ምን አደረጉህ? ምን አገባህ?* ይለዋል:: ከዚያም ‹‹አንድ ሁለት፣ አንድ ሁለት›› እያሉ ቃላት ይሰዋወጣሉ:: ያኛው ሌባ ከተቀመጠበት ብድግ ብሎ በእጁ ባገኘው ነገር ይኸኛውን ይመታዋል:: እርስ በርስ ይያያዛሉ:: ከጅምሩ አንስቶ ሲቆጭ የቆየ ሌላው ታዛቢ እስረኛ ደግሞ ተነስቶ ከደባዳቢው ጋር ይተባበራል:: ይረባረባል:: የልብስ ሰፊው የግድግዳ ጥግ ይዞ *በህግ አምላክ! በህግ አምላክ! በህግ አምላክ!* ይላል:: በመጨረሻ ዑስማንን የክፍሉ ነዋሪዎች አስረው ያስተኙትና ሰዓታት ካለፉ በኋላ ይፈቱታል::

በማግሥቱ በማረሚያ ቤቱ ጽ/ቤት ክስ ተመሠረተብን:: ዋናው ከሳሽ ተደብዳቢው ይሆንና ልብስ ሰፊው በእጋዥነት ይቆማል:: ክሱ ***ጴንጤዎች ደበደቡኝ*** የሚል ነበር:: ጉድክ ነው!! ከሳሹም፣ እጋዡም የፖሊሶቹ ጓደኞች በመሆናቸው ቃላቸው ተደማጭነት እገኘ:: የነገሩም እውነተኛነት ሳይመረመር የማረሚያው ፖሊስ እባላት እንዳሉ ገቡና ከሰዓት በኋላ ከነዕቃችን እያወጡን በየክፍሉ በታተኑን:: ከመካከላችን አንድ ሰው፣ጌታሁን እጋፋሪ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ በእግር ብረት ታሠረ:: ይህ የሆነው የማረሚያ ቤቱ ዋና አዛዥ ፣ሻምበል አበበ በሌሉበት ነበር:: እርሳቸውም ማምሻውን ገቡና ሁኔታው በተዛባ መንገድ ተነገራቸው::

በማግሥቱ ጥቅምት 12 ቀን 1974 ዓ/ም ጠቅላላ የእስረኞች ስብሰባ ተደረገ። ሻምበሉ እኛን በሚመለከት በቁጣ የተሞላ ንግግር አደረጉ። ከንግግራቸው፡-

> *እኔ! እነዚህን ሰዎች ለማስፈታት ያላደረግሁት ነገር የለም። በእግራቸው ላይ ወድቄ ለምኜያቸው እምቢ ብለውኛል። ዛሬ የኑሮ ውድነት አለ። መፈታት የማይፈልጉት እንጀራ በአገልግል ስለሚመጣላቸው ነው። አሁን ደግሞ ይሰብካሉ። እኔ በየክፍሉ ካድሬ አላስቀምጥም። ሁሉንም አውጡልኝና ወደዚያ አስገቡልኝ።* .... ወዘተ የሚል ሃሳብ ይገኝበታል።

የአዛዡንም የቁጣ ንግግር የተሳሳተ መነሻ ስለተረዳነው አልፈረድንባቸውም። «እንጀታቸው» ጨክኖ የማይጨክን ዓይነት እንደ ሆነም በጊዜው አውቀናል።

የሆነው ሆኖ፣ ሁላችንም በአጠቃላይ - በሌላ ጉዳይ ታስሮ በመግባት በኋላ ወደ ጌታ የተመለሰውን አሳምነው መስፍንን ጨምሮ- 16 የምንሆን፣ በአንዲት ጠባብ ክፍል እንድንታጎር ተደረገ። በዚያችም ትንሽ ክፍል ውስጥ፣ ከነንዛችን ገብተን ተጨናነቅን። መኝታችን፣ ምግብ ማብሰያችንና የምግብ ቁሳቁስ ማስቀመጫችን እዚያው በአንድ ቦታ ነበር። ከክፍሉም ጥበት የተነሣ በንተኛ የአንዳችን እግር በሌላው ላይ እያሰፈ ይመሳቀል ነበር።

ወደዚያች ክፍል ስንገባም፣ ዕቃችን በጥብቅ ተፈተሸ። ፍራሻችንና ትራሳችን ሳይቀር በጥንቃቄ ታየ። የተደበቀ ትርፍ ትርፍ ሰዓት አላቸው ተብሎ ነው። ይገርማል! እንኳንስ ለአንድ ሰው ትርፍ ሰዓት ሊኖረው ይቅርና፣ ምንም ሰዓት የሌላቸው በመካከላችን ነበሩ።

ከዉስጥ ከእስረኞች፣ ከውጭ ከዘመዶች እንዳንገናኝ ተከልከልን። ጠዋት ጠዋት ለመጸዳዳት የምንወጣውና ዉኃ ከጉድጓድ የምንቀዳው ማንም እስረኛ ሳይወጣ በፊት እየተከፈተልን ሆነ። ይህም የተደረገው ከማንም እንዳንገናኝ ታስቦ ነው። ሆኖም ያልደፈረሰ ንጹህ ውኃ በቅድሚያ የመቅዳት ዕድል ስለሆነልን ይህም ቆይቶ በእስረኞች ዘንድ ቅናት ማስነሳቱ አልቀረምና በዚህም ተከሰናል።

እንዲህም ሆኖ ከጠያቂ ዘመዶቻችን ጋር ከ5 ቀናት በኋላ እንድንገናኝ ተ ፈቀደልን። በዚህ መሐል ግን እኛ ሳናውቅ ስንቃችንን ሌሎች እስረኞች ተ ቀብለው በልተውታል። ያንንም ለሻምበል አበበ አመልክተን ስንቃችን በሌሎች እስረኞች እንዲበላ ታዝዞ እንደሆን በጠየቅንበት ነው ከአሁን ጀምሮ ራሳችሁ እየቀረባችሁ ተቀበሉ ያሉን።-

በዚያች ጠባብ ክፍል ውስጥ ጌታ ሕይወታችንን አነቃቃልን። የማያምን ሌላ ሰው ባልተገኘበት በአንድነት ተገናኝተን ጌታን የምናመልክበት መልካም ጊዜ ሆነልን። *እግዚአብሔርን ለሚወድዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለንና* (ሮሜ 8:28)።





በኋላ ደግሞ ከጠባብዋ ክፍል በ3 ወር ከ12 ቀናችን ወጣን። በመቀጠል፣በኢሕአፓ አባልነት ተይዘው በቆዩና ወጣት የፖለቲካ እስረኞች ሉበት ትንሽ ሰፋ በምትል ክፍል ውስጥ እንድንገባ ተደረገ። አብረናቸው እንድንሆንና በእነርሱም እንድንጠበቅ ታስቦ የተጨመርንባቸዉ የፖለቲካ እስ ረኞች 9 ነበሩ። ከመካከላቸውም ያልሆነ መረጃ ለማረሚያ ቤቱ አስተዳደር በመስጠት ችግር ሊፈጥሩብን የሞከሩ ጥቂቶች አልጠፉም። የሚበዙቱ ግን ቀና ልብ ያላቸው ነበሩ። ከእነርሱም መካከል ከተፈቱ በኋላ በክርስቶስ አምነው፣ ታን ለማምለክና ለማገልገል የበቁትን ለማየት ችለናል።

ሁንና፣ በዚያችው ክፍል ውስጥ እያደርንም ቢሆን፣ ከሌሎች እስረኞች ጋር መገናኘቱ ሁኔታ እንደገና እየቀጠለ ሄደ። በዚህ ሁሉ ጊዜ ውስጥ ለሌሎች ክርስቶስን አዳኝነት መመስከራችንም ሆነ ለራሳችን ማምለካችን ይበልጥ እየተ በናከረ መሄዱ አልቀረም። ነፃነታችንም እየሰፋ መጣ።

974 ህዳር ላይ ደግሞ፣ መቆየቴ ከበደ፣ አባትዋ በጠና በመታመማቸው ክንያት ካጋጠማት የተለያየ ጫና የተነሣ ተለቀቀች።

ዚህ ዓመት አብዛኛውን ጊዜ የተለመደውን የእስር ቤት ኑሮ በሰላም ካሳለፍን ኋላ ግንቦት ላይ «ነገር» መጣ። ከነገሩ መምጣት በፊት የማረሚያ ቤቱ አዛዥ ነው የሠሩት ሻምበል አበበ ወደ ሌላ ሥፍራ ተዛውረው በቦታቸው ሻለቃ ርሃኑ የሚባሉ ተሹመው መጥተዋል። ይህም የሆነው በመጋቢት ወር ውስጥ ው። ከዚህ በኋላ ጓድ ባሕሩ የሚባል የፖሊስ ካድሬ እስረኞችን ለማንቃት ስቦ ዝግጅት ማድረግ ጀመረ። በመጨረሻም ግንቦት 25 ቀን 1975 ዓ/ም ላውን የይርጋ ዓለም ማረሚያ ቤት እስረኛ ሰብስቦ ስለ ሃይማኖት ጉዳይ ሰፊ ለፃ አደረገ። ከንግግሩ መሐል፡- *በአገራችን ሁለት ዓይነት መንግሥትና ሁለት ይነት ርዕዮተ ዓለም ከእንግዲህ አይኖርም* ያለው ይታወሳል። በዚያው ዕለቱ ስረኞችን በሁለት ትልልቅ ቡድን በመክፈል ለወደፊት በተከታታይ እየመጣ ፖለቲካ ንቃት እንደሚሰጣቸው «ቃል ገብቶ» ሄደ።

ግቦት 29/1975 ዓ.ም ደግሞ 13 ወንድሞች ዜሮ ቁጥር በመባል ሚታወቀውና ከጥር 25 ቀን 1974 እስከ ግንቦት 29 ቀን 1975 ዓ.ም ኖርንበት ወጥተን በቁጥር 1፣2፣4፣5፣6ና 7 እንድንበተን ተደረገ። ይህም ድሬው ሥራ ውጤት መሆኑን ቆይተን አወቅን። በአንድነት መሆናችን ሚያጠናክረንና መበታተናችን የሚያዳክመን ስለ መሰለው ያን አስደረገ። ጥቂት ቀናት በኋላ አቶ ብርሃኑ ላንቃሞ የሚባለውን፣ ተፈቅዶለት ውጭ የዋለ ይገባ የነበረውን «ታማኝ እስረኛ»፣ ከተማ ውስጥ አግኝቶት፣ *እነዚያ ንጤዎች አሁንም አልተሻላቸዉም?* ብሎ እንደ ጠየቀው ሰማን። እርሱ ግን ስረኞቹን ሊያነቃ በየጊዜው እንደሚመጣ የገባው ቃል በዚያው ቀረ። ሁለተኛ ልተመለሰም።

ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ በወቅቱ በ28/10/75 የኢትዮጵያ ማረሚያ ቤቶች ዋና አዛዥ የነበሩት ሻለቃ ኃ/ማርያም ሌንጮ ማረሚያ ቤቶችን እየጎበኙ ይርጋ ዓለም ማረሚያ ቤት ደረሱ። ጓድ ባሕሩም በሪፖርቱ ላይ *የመጤ ሃይማኖት ጉዳይ ያስቸገረን በመሆኑ... ነጥብ እንዲያዝልን* በማለት አመለከተ። የሻለቃውም እስረኞችን ሰብስበው ንግግር ሲያደርጉ፣ በመካከላችሁ ያሉትን *የመጤ ሃይማኖት ተከታዮች ምክሩአቸዉ* ከማለት የዘለለ ምንም የከፋ ነገር አልተናገሩም።

በሌላ በኩል ደግሞ፣ በእስራታችን ዘመን ውስጥ፣ አንድ ሌላ የስደት ምዕራፍ ሊከፈት ጀመረ። ይህንን በግልጽ የተረዳነው አምስቱ እህቶቻችን 1ኛ ወርቅነሽ ይመር፣ 2ኛ. ማርታ ጋዲሰ፣ 3ኛ. ሙሉ እመቤት መንበረ፣ 4ኛ ዝናሽ ኃይሉና፣ 5ኛ. ያዲድያ መስፍን፣ ከእኛ ተለይተው ሰኔ 16 ቀን 1975 ዓ/ም በድንገት ወደ ሀዋሳ ማረሚያ ቤት እንዲዛወሩ ከተደረገ በኋላ ነው ማለት ይቻላል።

እህቶቻችን የተዛወሩበትን ምክንያት *እነርሱን የምትጠብቅ የሴት ወታደር ስለሌለች ነው* ሲባል ሰምተናል። የእኛም ወደ ቦረና ነጌሌ የመዛወር ጉዳይ በወታደሮች አካባቢ እንደ ቀልድ ተወራና እያደር ቀዘቀዘ።

የሆነው ሆኖ የእነርሱ - የእህቶች - መሄድ ለእኛ ትልቅ ማስጠንቀቂያ ሆኖን ቀስ በቀስ ዕቃችንን እየቀነስን የሚላከውን እየላክን፣ የሚሸጠውንም እየሸጥን ዝግጅት ማድረግ ጀመርን።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ነሐሴ 14 ቀን 1975 ዓ..ም ቅዳሜ ወንድማችን ሰለሞን ሐጢያ ከውጪ ዘመድ እንደሚፈልገው ተነግሮት ይወጣና እንዳይገናኝ ይከለከላል።ምክንያቱ ቢጠየቅ ከአውራጃ አስተዳደር ተደውሎ ከዘመድ እንዳንገናኝ መታዘዙን የማረሚያ ቤቱ ጸጥታ ኃላፊ ከሆኑት ከሃምሳ አለቃ ወ/ገብርኤል ይሰማል። በድጋሚም ተጠይቆ ይረጋገጣል።

አሁንም ዝግጅታችንንና ጥንቃቄአችንን በመግፋት ከነሐሴ 23-25/1975 ድረስ ከፊታችን ለሚኖረው ማንኛውም ነገር ነፍሳችንን ለእግዚአብሔር አደራ ለመስጠት ተከታታይ የጾምና ጸሎት ፕሮግራም አደረግን። ከእስረኞች አካባቢ ግን *የረሃብ አድማ ማድረጋቸው ነው* የሚል ወሬ ግቢዉን አዳርሶ እንዳናወጠና ለወታደሮችም ተነግሮ ድንጋጤ እንደ ፈጠረ ሰማን። ከመካከላችንም ሁለት የምንሆን ሄደን ለጸጥታዉ ኃላፊ፣ *ይህ ጸሎት ነው እንጂ አድማ አይደለም* በማለት ስላስረዳን ሁኔታው ተረጋጋ፤ነገሩም በአጭር ተቋጨ።

ጳጉሜ 3ና 4 ቀን 19፸፭ ዓ/ም ደግሞ የዓመቱ ማጠቃለያና የመጨረሻ ራስን የማስረከቢያ ጸሎት አድርገን 1975ን ተሰናበትነው። በዚህ ጊዜ ሁሉ ወደ 1976 ዓ/ም እያመለከትን፣ ስለጠቅላላው የእግዚአብሔር ሕዝብ ምልጃና ምስጋና አቅርበናል።





## ዕንቁ - ጣጣሽ!

መስከረም 1 ቀን 1976 ዓ/ም ጠዋት የአገራችን የዘመን መለወጫ በዓል - ዕንቁጣጣሽ - ነው። ዕለትዋ ሰወሩ ቀጣይ ቀናትና ለዓመቱም ጭምር የሚሆን ነገር ይዛልናለች!

በዚህች ዕለት፣ ጠዋት ከእንቅልፌ እንደ ተነሣሁ፣ በቀጥታ የሄድሁት በቁጥር 6 ወደ ሚኖሩት ወንድሞቻችን ወደ ሰገሠ ዲኬና ወደ ማርቆስ ተፈራ ነበር። ከዚያም፦ *ሕይወትን የሚፈቅድ ሰው ማነዉ? በጎንም ዘመን ለማየት የሚወድ። አንደበትህን ከክፉ ከልክል፣ከንፈሮችህም ሽንገላን እንዳይናገሩ።* የሚለውን ቃል ከመዝ 34:12፣ ሰፋ አድርገን ከተወያየንበት በኋላ አመስግነን ወደ 7 ቁጥር ተመለስኩ። የተወያየነው በጎውን ዘመን ስለማየት ነበር።

በእርግጥ ዛሬ ደስ ብሎኛል። ደስታው የመንፈስ ቅዱስ ማጽናናት ነበር። የተለየ ዝግጅት ማድረግ ባይቻል አንድ ነገር ሳድርግ ብዬም አሰብኩ። ከዚያም፣ የእያንዳንዳችንን ትራስ እየገለበጥኩ አስተካክልኩና ቀና ቀና እያደረግሁ በየትራስጌአችን አቆምሁ። ትራሶቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በጥልፍ በፊት የተጻፉባቸው ነበሩ።

> *ኢየሱስ ጌታ ነው* ይላል የሰሎሞን ትራስ ጨርቅ ላይ የተጠለፈው ጥቅስ።
> *እግዚአብሔር የሕይወቴ መታመኛዋ ነው* ይላል የእኔው።
> *እግዚአብሔር እረኛዬ ነው* ይላል ከጎኔ የሚያድረው የሺመልስ።
> *እግዚአብሔር ረዳቴ ነው* ይላል የአዳነ።
> *ምነው ዛሬ* እሰኝ ከእነርሱ አንዱ።
> *በዛሬይቱ ዕለት ኢየሱስ ጌታ ነው፣እግዚአብሔር የሕይወቴ መታመኛዋ ነው፣ እግዚአብሔር እረኛዬ ነዉ፣ እግዚአብሔር ረዳቴ ነው።»* አልኩት።
> አሁንም ደስ ብሎኛል። የደስታዬ ምስጢር ግን ምን ይሆን

ረፋዱ ላይ የክ/ሀገሩ ዋና አስተዳዳሪና የአውራጃው ዋና አስተዳዳሪ መጡ ተ ባሰና የተወሰኑ እስረኞች ስም ተጠራ። መፈታት መሆኑ ነው። ብዙም ሳይቆይ እኛ ተጠራንና በሰልፍ ወጥተን በጽ/ቤቱ አደባባይ ላይ እንድንቆም ተደረገ። አሰልፈው ያወጡን የአውራጃው አስተዳዳሪ ነበሩ። ወደ እስረኛውም ክልል እንደዘለቁ፦ *ተስፋዬ ጋቢሶ ማለት ማነው?* አሉና ጠየቁ። *እኔ ነኝ* አልኩ። ትንሽ ቀይ ጃኬትና ትንሽ ፎጣ ትከሻዬ ላይ ጣል አድርጌአለሁ። በዚያ ላይ አጭር ነኝ። ትክ ብለው በመገረም አዩኝ። ምናልባት ስለ እኔ የተነገራቸው ነገርና ቁመናዬ አብሮ አልሄደላቸውም። ይህ ችግር የእርሳቸው ብቻ ሳይሆን የሌሎችም ሆኖ ኖሮአል። አሁንም አስተዳዳሪው ለማጣራት ይመስላል፦ «*ዘማሪ ተስፋዬ ጋቢሶ አንተ ነህ?*» ሲሉኝ፣ *እምን እኔ ነኝ* ብዬ መለስኩላቸው። ወዲያውም፣ *በሉ ተሰለፉና ተከተሉኝ። ካላመናችሁ ተመልሳችሁ እዚሁ ነው የምትገቡት* እያሉ አስከትለውን ወደ ጽ/ቤቱ አደባባይ አወጡን።

ከዚያ በኋላ፣ የይርጋ ዓለም ከተማ ሹም የነበሩት አቶ ዜና ስማችንን እየዞሩ መዝግበው ሲያበቁ ከእኔ በመጀመር ተራ በተራ ወደ ዋናው የክ/ሀገር እስተዳዳሪ እየቀረብን ተጠየቅን::

የቀረቡልን ጥያቄዎች አጫጭር ነበሩ:: መልሶቻችንም እንዲሁ እንደ ጥያቄዎቹ:: አሁንም የመነሻ ጥያቄው የመራንም ያለመራንም ነበር፤ መድረሻውን ደግሞ እናውቀዋለን:: መልሳችን ግን የአሉታ ሆነ:: በመካከሉ ከብዙዎቻችን በዕድሜው አነስ የሚለውን ለገሠ ዲኬን የክ/ሀገሩ ዋና አስተዳዳሪ በጥፊ መቱት:: ሊደግሙት ሲሉ ሳቱትና ወዲያው የገዛ እጃቸውን ሲያሹት ተመለከትን:: ሕመም እንደ ተሰማቸው ያስታውቅ ነበር:: ለገሠ በመጀመሪያው ምት ብቻ እዙሮት ሊወድቅ ሲል የዕለቱ ዘብ ኃላፊ የሃምሳ አለቃ በላይነህ ሮጠው ያዙት:: በመጨረሻ በመልስ አሰጣጣችን አሉታዊነት ዋናዉ አስተዳዳሪ ተቆጥተው ከያሁዋ ምስክሮች አንዱ የሆነውን ሶሥዩም ካየሰን ወደ ፖሊስ ጣቢያ ይዘውት ሄዱ::

በዚያችው ዕለት ከሰዓት በኋላ ከየነበርንበት ክፍል ወጥተን ሌሎች እስረኞች በማይገኙበት ቁጥር 16 እየተባለ በሚጠራው ክፍል በአንድነት እንድንገባ ተደረገ:: ያ ክፍል ጨለም ያለ፣ዝግ ሆኖ የቆየና ሞት ተፈርዶባቸው የቅጣት ቀናቸውን የሚጠብቁ እስረኞች ማቆያ እንደ ነበረ ሰምተናል:: እኛ ከመግባታችን በፊት ክፍሉን ከቁንጫና ከጓይጥ ያጸዱልን እስረኞች፣ ስለ ክፍሉ የነበራቸውን ፍርሃት *ሰይጣን ውጣ!* በማለት መግለጻቸው ይታወሳል:: ስለዚያ ክፍል ታሪክ ዕውቀቱ የነበራቸው አንዳንዶችም፣ ቀረብ እያሉ *ሊገድሉአችሁ ነውና አትደናገጡ*፣ በማለት ሲያጽናኑን መክሩ አድርገዋል:: በኋላ ስንሰማ፣ የክ/ሀገሩ አስተዳዳሪ ለብቻ እንድንታሠር፣ ሥራ እየሠራን ራሳችንን እንዳንረዳ፣ እርሳቸው እስኪመለሱ ድረስ በጥብቅ እንድንጠበቅ አዝዘዋል ተብሎ ተነግሮናል::

> *ይህን ያህል ጥንካሬ እንዳላቸው ብናውቅ ኖሮ የራሳችንን እርምጃ ልንወስድ እንችል ነበር:: እናንተ ሽፋፍናችሁ ሪፖርት እያደረጋችሁልን ነው፣እናንተ አቀማጥላችኋቸው፣ እንደላቀቃችኋቸው ነው እንዲህ የሆኑት:: ከውጭ ምንም እንጀራ እንዳይገባላቸው:: ቢቻል ይህንንም የመንግሥት መኖ ቀንሶ መስጠት ነበር፤ አይቻልም እንጂ . . .* ወዘተ የሚሉ ሃሳቦችን ተናግረውም ነበር አሉን:: ይሆቺ ናት ዕንቁጣጣሽ!!

*ማምሻውን ግን ምሕረቱ አያልቅምናን፣ ልቤ በእግዚአብሔር ጸና...* ወዘተን ስናዜምና ስናመሰግን፣ ምስክርነትም ስንለዋወጥ፣ በጌታም በኢየሱስ ሐሴት ስናደርግ አመሸን :: በእርግጥ፣ልዩ ጊዜ ሆነልን:: የዘመን መለወጫው ጣጣ ይዞ የመጣ ቢመስልም፣ መንፈስ ቅዱስ ልባችን ሳይሸበር ሁኔታውን ተረጋግተን እንድናስተናግደው፣ ገና ከማለዳው በማጽናናቱ ሊጎበኘን ጀምሮአል::

ከዚያን ቀን ጀምሮ፣ በየምሽቱ በነበረን የጸሎት ሕብረት አማካይነት እግዚአብሔር የእያንዳንዳችንን ነፍስ በሐሴት ወደ ላይ ከፍ ከፍ እያደረገ ሲያወጣት





ይሰማን ነበር:: እንደበታችን «ተፈቶ» በልዩ ልሳን ጌታን እመሰገንን:: የደስታ ዕንባ ፊታችንን አጠበው:: ልባችንን የጌታ መንፈስ ሲያበረታው፣ ሁለንተናችንንም በዘይቱ ሲያረሰርሰው ይታወቀን ነበር:: እግዚአብሔር በተአምራት ሊጎበኘን መጀመሩም ተሰማን:: መጽናናት በመጽናናት ሆንን:: የጌታን ቃል ስናነብ ይጥመን፣ መዝሙር ስናዜም እንረካ ነበር:: ጌታ፣ ከፊታችን የሚጠብቀንን እንግዳ ነገርም በጥቅሉ ሳያመለክተን አልቀረም:: እግዚአብሔር ስመጪው አስቸጋሪ ሁኔታ እያዘጋጀን እንደ ነበረም በግልጽ አወቅን::

በአንድ ክፍል፤ በቁጥር 16 ውስጥ፣ በአንድነት እንድንሆን ከተደረገበት ቀን አንስቶ፣ በየምሽቱ፣ ቅዱስ ቃሉን መሠረት በማድረግ፣ከተካፈልናቸው መልእክቶች መካከል የሚከተሉት ይገኛሉ:-

> *ተጠበቅ ዝምም በል፤ ስለ እነዚህ ስለሚጤሱ ስለ ሁለት የእንጨት ጠለሸቶች፣ ስለ ሶሪያና ስለ ረአሶን ስለ ሮሜልዩም ልጅ ቁጣ አትፍራ፤ ልብህም አይድከም:: ሶሪያና ኤፍሬም የሮሜልዩም ልጅ:- ወደ ይሁዳ እንውጣ እናስጨንቀውም፣ እንስበረውም፣ የጣብኤልንም ልጅ እናንግሥበት ብለው ክፉት ስለ መከሩብህ፤ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል:- ይህ ምክር አይጸናምና አይሆንም ::* (ኢሳ 7:4-7) እግዚአብሔር የሰዎችን ክፉ ምክር ከንቱ የሚያደርግ አምላክ ነው::
>
> *እግዚአብሔር እረኛዬ ነው*(መዝ 23:1) ስለዚህ ለብቻ የተተውን አይደለንም::
>
> *በጭፍራውም ውስጥ የወጡ ለሰልፍም የተዘጋጁ፣ የማያመነቱ፤ መሣሪያም የያዙ የዛብሎን ሰዎች ሃምሳ ሺ ነበሩ*(1ዜና 12:33):: ስለዚህ ለቆምንለት ዓላማ መጨከን ነው እንጂ የምን ማመንታት!
>
> *የእሥራኤልም ንጉሥ የአገሩን ሽማግሌዎች ሁሉ ጠርቶ፡- ተመልከቱ ይህም ሰው ክፉ እንዲሻ እዩ፤ስለ ሴቶቼ ስለ ልጆቼ ስለ ብሬና ስለ ወርቁ ላከብኝ፤ እምቢም አላልሁም አለ:: ሽማግሌዎቹም ሁሉ ሕዝቡም ሁሉ፡- አትስማው፣ እሺም አትበለው አሉት* (1ነገሥ 21:7 - 8):: ለሕይወትና ለጽድቅ ጉዳይ እምቢ ካልተባለ ኪሳራው የከፋ ይሆናል::
>
> *ጭልፊት በገደል ላይ ይኖራል፤ በድን ባለበት ስፍራ እርሱ በዚያ አለ* (ኢዮ 39:26-30):: - የበድኑ ጠረን ችግሩ አይደለም ለማለት ነው:: በጠረኑ መካከል ሕይወትን የሚቀጥል መብል አለና! እኛም በማይመች ቦታ ተቀምጠናል፤ የእግዚአብሔር ጸጋ ግን በትዕግሥቱ በሕይወት ያከርመናል::
>
> *ያዕቆብም እንዲህ ብሎ ስዕለት ተሳለ:- እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ቢሆን፣ በምሄድባትም በዚህች መንገድ ቢጠብቀኝ፣ የምበላውንም እንጀራ የምለብሰውንም ልብስ ቢሰጠኝ፣ ወደ አባቴ ቤትም በጤና ብመለስ፣ እግዚአብሔር አምላኬ ይሆንልኛል፤ ለሐውልት የተከልሁት ይህም ድንጋይ የእግዚአብሔር ቤት ይሆናል፤ ከሰጠኸኝም ሁሉ ለአንተ*

*ከእሥር እጅ እንዱን እስጥሃለሁ*:፡(ዘፍጥ 28:20-22) ይህ ለጥበቃችን ለሚሆን የተማጽኖ ጸሎት ያነሣሣናል፡፡

***እግሮቹ በእግር ብረት ደከሙ፣ እርሱም በብረት ዉስጥ ገባ*** (መዝ 105:18፤)፡፡ ይህ ስለ ያዕቆብ ልጅ ስለ ዮሴፍ እስራት የተጻፈ ነው፡፡ «እርሱም» የዛሬው ታሳሪ፣ እግዚአብሔር ሰውን የሚያድንበትንና የሚባርክበትን ሥራ፣ ወንጌል መስበክን፣ ተክልክሎ የዘንባባ ዘንቢል ሠራ፡፡ እርሱም ጥራቱ እጅግ ዝቅተኛ የሆነና ያለ ጥንቃቄ ተሠርቶ የቀረበ «እስቤዛ» በላ፡፡ እርሱም በምግብ ስጥረት ተራበ፡፡ እርሱም ልብሱ እልቆ ታረዘ፡፡ እርሱም ከቁንጫ፣ ከትኋንና ከቅማል ጋር ታገለ፡፡

***ጉማሬ ... እንደ በሬ ሣር ይበላል ... ኃይሉም በሆዱ ጅማት ውስጥ ነው*::** (ኢዮ40:15-16) በኃይል ግን ከበሬ ይበልጣል፡፡ እኛም ደካሞችና ተራ ሰዎች መሰሰናል፤ ኃያሉ አምላካችን ግን ከጎናችን ስለሆነ፣ ከኃያላንና ከአሸናፊዎች ያስበልጠናል፡፡

በእነዚህ ባለፉት 19 ቀናት ውስጥ፣ መነሻው ከየት እንደሆነ የማይታወቅ፣ መዓትን ያዘለ ወሬ፣ እስረኛው ሲያናፍሰው፣ የእኛ ልብ ግን ሰሞት እንኳ ቢሆን የቆረጠ ሆነ! ከወሬውም እንዳንዱ ወደ ቦረና ነገሌ፣ ሌላው ወደ አዲስ አበባ ጦር ፍ/ቤት ሊወስዱ ነው የሚል ነበር፡፡ በመጨረሻ፣ በ19/1/76 ዓ/ም፣ ዓርብ ቀን ከሰዓት በፊት፣ የማረሚያ ቤቱ የአስተዳደር ጸሐፊ የሆነው ወ/ር ብዙነህ እክፍላችን ድረስ በመምጣት *ወደ ቦረና ነጌሌ እንድትዛወሩ ስለ ተባለ ዕቃችሁን አዘጋጁ* በማለት ሲነግረን ወሬው እልባት አገኘ፡፡

በምን ዓይነት መንገድ ከቢሯቸው ወጥቶ በ1978 ዓ/ም በአንድ ተራ እስረኛ እጅ እንደ ተገኘ የሚገርመንና በወቅቱ ከሲዳማ አውራጃ አስተዳደር የተጻፈ ደብዳቤ እንዲህ የሚል ነበር፡፡

*ቁ/149/9/5*
*መስከረም 19 ቀን 76 ዓ/ም*
*ለሲዳማ አውራጃ ወሀኒ አስተዳደር ጽ/ቤት*
*የስም ዝርዝራቸዉ ከዚህ በታች የተመለከቱት የመጤ ኃይማኖት ተከታዮች አሁን ካሉበት ወሀኒ ቤት ወደ ቦረና ነጌሌ እንዲዛወሩ በክፍለ ሀገሩ ዋና አስተ ዳደር በተሰጠው መመሪያ መሠረት ተከ/ሀገሩ ወሀኒ ጽ/ቤት እንድታስረክቡ ይሁን፡፡*

1. *ተሾመ ወርቁ*
2. *ሺመልስ ለማ*
3. *ለገሠ ዲኬ*
4. *ማርቆስ ተፈራ*
5. *ከበደ አርጋው*
6. *ታፈሰ ቦኤ*
7. *ሥዩም ካዬሶ*
8. *ጌታሁን አጋፋሪ*
9. *በራሣ ባንቡሮ*
10. *ከበደ ሳሳሞ*
11. *ሰሎሞን ኃጢያ*
12. *ኃይሉ በቀለ*
13. *አዳነ አለማየሁ*
14. *ተስፋዬ ቃሚሶ*
15. *ተስፋዬ ጋቢሶ*





| | |
|---|---|
| *ግልባጭ ለሲዳሞ ክ/ሀገር አ/ጽ/ቤት* | *ማሕተም (የማይታይ)* |
| *›› ወ/አ/ጽ/ቤት* | *የሲዳማ አ/አ/ጽ/ቤት* |
| | *ዋና አስተዳዳሪ* |
| *አዋሣ* | *ፊርማ (የማይታይ)* |

የትዕዛዙን ደብዳቤ ተከትለው፣ የክ/ሀገሩ የሕዝብ ደኅንነት ጽ/ቤት ዋና ኃላፊ የነበሩት ሰው መጥተው፣ የደብዳቤው ምስጢር እንዲጠበቅ እንጂ ለእኛ እንዳይነገር አስጠንቅቀው ሄዱ የሚል ዜናም ከእስረኞች እንደበት ሰምተናል፡፡ የማረሚያ ቤቱ አስተዳደር ጸሐፊ የነበረውን ወታደር ብዙነህን ግን የእኛ ጌታ አዝዞት ኖሮ በመጣደፍ መጥቶ ስለነገረን እኛስ ምስጢሩን ቀድመን አውቀናል፡፡ ከዚህም የተነሣ ሰምን ተነገራቸው በሚል መነሻ፣ የማረሚያ ቤታችን የጸጥታ ኃላፊ የሃምሳ እለቃ ወ/ገብርኤል ከወ/ር ብዙነህ ጋር መጣላታቸው ተሰምቷል፡፡

ያም ሆነ ይህ፣ሳይታሠር የቀረውን ዕቃችንን እሥረን፣ የሚከተተውንም ከትተን፣ በተጠንቀቅ ሆንን፡፡ የሚጭነን መኪና ግን ባለመምጣቱ እዚያው አደርን፡፡ ዕቃችንም እንደ ታሠረ እስከ እሁድ ቀን ድረስ ቆይቷል፡፡ ሰመሆኑ፣ያች የመስከረም 19 ቀን 1976 ዓ/ም ምሽት ምን ትመስል ነበር;

## ያቺ ምሽት!

ማታ ላይ፣ የምንሠራው ሌላ የቀረ ምንም ነገር አልነበረምና ልክ በር እንደ ተዘጋ ሺመልስ አጠር ያለ መልዕክት ከእግዚአብሔር ቃል አቀረበልን፡፡ የመልእክቱ መነሻ ሃሳብ *ዳዊትም እያለቀሰ የደብረ ዘይትን አቀበት ወጣ* የሚል ነበር፡፡ በመቀጠል ወደ ጸሎት ገባን፡፡ በመጀመሪያ እያንዳንዱ በየግሉ ቃተተ፡፡ ያን እንደ ጨረስን፣ እጅ ለእጅ ተያይዘን ክብ ሠራንና *መንገዴን አደራ* በማለት ዘመርን፡፡ ከዚያም፣ አንገት ለአንገት ተቀቅፈን፣ ጌታ ኢየሱስም በመካከላችን እንዳለ በማመን፣ የተናገርነውና የጸለይነው በመጠኑ ሲታወስ የሚከተለውን ይመስላል:-

> *ጌታ ሆይ፣ አንተ እግዚአብሔር ነህ፡፡ እኛም ክርስቲያኖች ብቻ ነን፡፡ ሌላ ምንም አይደለንም፡፡ ወጣትነታችንን ስለ ወሰድከው እናመሰግንሃለን፡፡ ክበር፣ክበር፣ ተመስገን፡፡ ክብርን ለራስህ ውሰድ፡፡ መንገዳችንን አደራ፡፡ ቅደመን፤ ተከተለን፡፡ በዚህ የሚቀሩትን ጠብቅ፡፡ በውስጥም በውጭም ያሉትን አደራ፡፡ ይህችን ከተማ ተመልከት፡፡ እኛንና ለእኛ የሰጠኸንን ሁሉ ተረከብ* (ዕዝ 8:21-23)፡፡

የመጀመሪያዎቹ አምስት ዐረፍተ ነገሮች የወንድማችን የማርቆስ ተፈራ ነበሩ፡፡ በዚያች ምሽት ማርቆስ ባልተለመደ ሁኔታ ደስ ብሎት በየጸሎቱ መሓል ይስቅ ነበር፡፡ በይርጋ ዓለም እስር ቤቶች (በቀበሌ፣ በፖሊስ ጣቢያና በማረሚያ ቤት) በቆየንባቸው ዓመታት ሁሉ እንደዚያች ዓይነት በመንፈስ የመዳሰስ ጊዜ

ሲያጋጥመን ይህ የመጀመሪያ ነበር፡፡
በዚህም አላበቃም፡፡ ከጸሎት እንደ ተነሣን እራት በላልተን እንደገና ልንዘምር ተቀመጥን፡፡ ከሙሉ ወንጌሎቹ ዝማሬዎች መሐል፡-

*በኑሮዬ ሁሉ አንተን አስከብሬ*
*በመከራ ልለፍ ከአንተ ጋር አብሬ...ምሲጋና...*

*ስንጨነቅ የሚራራ ስንቆስል ፈዋሻችን*
*በበረሃ ዓለም እያለን ስንጠማ እርካታችን*
*ዞሮ መግቢያችን ኢየሱስ ማረፊያችን አንተ ነህ*
*ብንከዳህ አያዋጣንም የደሃ ጎጇችን ነህ...*
*ወደ ጌታ መንደር፣ ከቅዱሳን ሠፈር*
*ከዓለም ርቄ ተሰድጄ፣ እሰግዳለሁ ሄጄ*
*ኦ አምላኬ አማጸንሃለሁኝ ስማኝ - ጌታ እንድበረታ*

*ከታምራት ወልባ ዝማሬ ደግሞ፡-*

*መጻተኛው ተጽናና፣ ሲመጣ ጌታ ደርሶአልና*
*መልካሙን ገድል ተጋደል፣ ለመቀበል የድል አክሊል...* የተሰኘውን እንጎራጎርን፡፡

ዓርብ በዚሁ መልክ አለፈ፡፡ ቅዳሜ የመዝናናት ቀን ሆኖ ዋለ፡፡ ሥዩም ከዱሰዎ ከፖሊስ ባቢዮ ተመለሰ፡፡ ጉዟችንም ለማግሥቱ እሁድ እንደሚሆን ገምተ እደርን፡፡





# ምዕራፍ አራት - ቦረና ደርሶ መልስ

## ጉዞ ወደ ቦረና

መስከረም 21 ቀን 1976 ዓ/ም ከጠዋቱ 12 ሰዓት ላይ የመኪና ሞተርና የክላክስ (ጥሩምባ) ድምፅ ከእንቅልፋችን ቀሰቀሰን ፡፡ ልብስ መልበስ ብቻ ነበረብን፡፡ በሩን የከፈተልን የእሥር አሰቃ ተስፋዬ አርሺ ግን መዘጋጀታችንን አላወቀም ነበርና ዕቃችን ታስሮ እኛ ለባብሰን እንደ ቆምን ሲያየን ተገርሞ፡- *‹‹እነርሱም ተዘጋጅተዋል! ለምታችኋል እንዴ?››* አለን፡፡

ሌላው ቀርቶ ከሀዋሳ ማረሚያ ቤት፣እጅበው እንዲያደርሱን የተላኩት የሻለቃ ባሻ አድማሱና ሁለቱ ተራ ወታደሮች ሳይቀሩ ያልሰማን መስሏአቸው ነበር፡፡ እነርሱም እንደ መጡ ሳናስጠብቃቸው የታሰረ ዕቃችንን ብቻ እያወጣን ከች ከች ስንልባቸውና በመገረም ሲጠይቁ ነው‹‹በስሕተት መስማታችንን›› የተረዱት፡፡ ለሁሉም፣ ምስጢር ገላጭ የሆነውና ባለ ውስታችን የሆነው አምላካችን ስሙ የተመሰገነ ይሁን፡፡ ወታደር ብዙነህን ምስጢር እንዲነግረን አጣድፎ ልኮልናልና !

ይሁንና በእስደናቂ ቅልጥፍና፣ እያሰቀስን ላይሆን እየሳቅን፣ ከልብ በሚመነጭ ደስታና መጽናናት በመሞላት ዕቃችንንና ራሳችንን በቃረበልን መኪና ላይ ጭነን ያቺን ሥፍራ ስንለቅ እጃቸውን እያዉለበለቡ የሸኙን ‹‹ታማኝ እስረኞችና ›› ወታደሮች አይተውናል፡፡ በዚህ መልክ ይርጋ ዓለምን ከጠዋቱ 1:00 ሰዓት ላይ ለቀቅን፡፡

ከዚህ ሳንርቅ ሲጠቀስ የሚገባው፣ ከክፍለ ሃገሩ ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ጽሕፈት ቤት፣ ወደ ቦረና አውራጃ ማረሚያ ቤት፣ ስለ እኛ ተጽፎ ለሲዳማ አውራጃ ማ/ቤት፣ በግልባጭ የተላከውና ከፍ ብሎ ከተጠቀሰው እሥረኛ እጅ ያገኘነው ደብዳቤ ጉዳይ ነው፡፡ ይኸኛው ደግሞ እንዲህ ይነበባል፡-

*ቁጥር ዲአ/265/216/76*
*መስከረም 20 ቀን 1976 ዓ/ም*
*ለቦረና አውራጃ እስር ቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤት*
*ነገሌ*

*ጉዳዩ እስረኞችን ስለ መላክ*

| | |
|---|---|
| *1. ተስፋዬ ጋቢሶ* | *4. ተሾመ ወርቁ* |
| *2. ጌታሁን አጋፋሪ* | *5. ኃይሉ በቀለ* |
| *3. ሥዩም ካየሶ* | *6. ማርቆስ ተፈራ* |

| | |
|---|---|
| *7. ሺመልስ ለማ* | *12. ከበደ ሣሣሞ* |
| *8. ተስፋዬ ቃሚሶ* | *13. ሰለሞን ኃጢያ* |
| *9. ለገሠ ዳኬ* | *14. ታፈሰ በኤ* |
| *10. ከበደ አርጋው* | *15. በራሣ በንቡሮ* |
| *11. አዳነ አለማየሁ* | |

*የተባሉ በቤንጨ ሃይማኖት የታሰሩ ስለሆነ ከይርጋለም ወደ እናንተ ዘንድ ሄደው እንዲታሰሩ ከሲዳሞ ክ/ሃገር አስተዳደር የታዘዘ ስለሆነ እስረኞቹን 1ኛ/ በሻለቃ ባሻ አድማሱ ኃይሌ ሃላፊነት 2ኛ/ በወ/ር የኔነው ተስፋይ 3ኛ/በወ/ር ዘውዴ ደመና አጃቢነት የላከናቸው ስለሆነ ተረክባችሁ በጥንቃቄና ከውጭ ጠያቂ ሰው እንዳይገናኙ በብርቱ ቁጥጥር እንዲታሰሩ አስታውቃለሁ። የሲዳማ አውራጃ ወ/ቤትም እስረኞቹን ከነማህደራቸው ከላይ ስማቸው ለተጠቀሱት አባሎች እንዲያስረክቡ ይሁን።*

*ፊርማ(የማይታይ) ኮሎኔል ክፍሌ ቸርነት*
*የሲ/ክ/ሀ/ወ/ቤቶች ዋና እስተዳዳሪ*
*ማኅተም(የማይታይ)*

*ግልባጭ :- ለሲ/ክ/ሀገር አስተዳደር ጽ/ቤት -አዋሣ*
*ለሲዳማ አ/ ›› ›› ይ/ዓ*
*ለሲዳማ አ/ ወ/ቤት ጽ/ቤት ይ/ዓ*

የክፍለ ሀገሩ ማረሚያ ቤት ንብረት የሆነችው መጠነኛዋ ነጭ የጭነት መኪና አሥራ እምስታችንንና ዕቃዎቻችንን ከሁለት አጃቢ ወታደሮች ጋር አሳፍራ፣ሾፌሩንና የሻለቃ ባሻዉን ከነቢና ጨምራ ሞተርዋን በማንቀሳቀስ ጉዞ ጀመረች። ከይርጋለም ወደ አምስት ኪ/ሜ ያህል ርቃ የምትገኘውን የአቦስቶ ከተማ እንዳለፍን ከበደ አርጋውና አዳነ አለማየሁ ተራ በተራ በመጸለይ መንገዳችንን ለጌታ አደራ ሰጡልን።

*መንገዱ ተወልጄ ያደግሁባትን የደንጎራ እልሙቴን ቀበሌ አቋርጦ የሚያልፍ ነበረና፣ ሰዓት ባላሞላ ጊዜ ውስጥ በዚያ ስናልፍ፣ መንገድ ዳር አንድ ሰው አይቼ፣ እጄን በማወዛወዝ ‹‹ቦረና! ቦረና!›› የምትል ቃል ወርውሬ አለፍኩ። የለውየውን ማንነት ለጊዜው ባልለይም እርሱ ለይቶኝ ኖሮ ወዲያው በድንጋጤ ጭንቅላቱን ይዞ ቀረ።*

በዕለቱ ቡሌሳ ሌጎላ በምትባል ቀበሌ የቃለ ሕይወት ቤተክርስቲያን የአጥቢያዎች ወርሃዊ ስብሰባ እየተካኼደ ስለ ነበረ ወሬው እዚያ ሥፍራ ፈጥኖ ደረሰ። እስከዚያ ጊዜ ድረስ የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ገና አልተዘጋችም ነበር። በዕለቱም ጉባዔውን ይመራ የነበረ ሰው ማንነታችንን





ሳይገልጽ እጅን ወዳለፍንበት አቅጣጫ በመዘርጋት *በዚህ አቅጣጫ ጠላት ሰይጣን በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ እየሠራ ያለው ክፉ ሥራ ስላለ እግዚአብሔር እንዲቀድመው እጃችንን ወደዚያ ዘርግተን እንጸልይ* በማለት ተናገረ። በዚያ አቅጣጫ የተወሰዱ እስረኞች ብዙውን ጊዜ ዕጣ ፈንታቸው መረሸን እንደሆነ ይታወቅ ነበረ። በዚህ ምክንያት ወዲያው ትልቅ መቃተት የታየበትና በዕንባ የታጀበ የምልጃ ጸሎት ተደረገ። ይህን በኋላ የሰማሁት ከታናሽ ወንድሜ ከመሰፍን ጋቢሶ ነው።

ይሁንና፣ ጉዞአችንን ስንቀጥል፣ የመጀመሪያው አስቸጋሪ ሁኔታ የነፋሱ ጉዳይ ነበር። ሁለተኛው ደግሞ ውሃ ያቀረዘዘው ደመና ነበር። መኪናዋም ስክለላ የሚሆን ሸራ አልነበራትም። ለመዘመር ብንሞክር ግን ነፋስ ድምፃችንን እየበተነው ተቸገርንና ተውነው።

ነፋሱ ዳገት ላይ ስንሆን የመኪናውን ፍጥነት ስለሚቀንሰው ሻል ያለ ሁኔታ ይታይ ነበር። ደመናው ግን መንገዳችንን ሁሉ አጥልቶበት ነበር። ስለዚህ ፀሐይ አላጠቃንም። የደመናውን ጥቁረት ከርቀት ስናይ ከአሁን አሁን ዝናቡ ወረደብን ብለን መስጋታችን ባይቀርም፣ ዝናቡ እኛን እያለፈ እኛም እያለፍነው፣ እኛም ሆንን ዕቃችን ሳይበሰብስ በሰላም ነገሌ ገባን።

ያ ሁሉ መንገድ ማምሻዉን ዘንቦበት ያደረ ይመስላል። ስለዚህ መኪናይቱ ልታስነሣው ትችል የነበረ አቧራ ሳያስቸግረን ገብተናል። ሌላው ደግሞ፣ መንገዱ በግሬደር በመስተካከሉ ያ የጠጠር መንገድ ጉዞ ያለ ብዙ መንገጫገጭ ተጠናቀቀ ማለት ነው።

በዚያ ሁሉ መንገድ፣ የጌታን እጅ ሥራ ተራራዉን ሸለቆዉን፣ወንዙን፣ገደሉን፣ቋጥኙን፣ደኑን፣ጉሬዛውን፣ግመሉን፣ወዘተ እየተመለከትን፣ እያደነቅንና እያመሰገንን አለፍን። ታስሮ ለከረመ ሰው ዓይን እነዚህ ሁሉ ብርቅ ናቸውኮ!

ከቀኑ ስድስት ሰዓት ላይ ደግሞ ክብረ መንግሥት በሚባል ከተማ ላይ ምሳ ገዝተን እንድንበላ ስለ ተፈቀደልን ወርደን ጥቂት እረፍት አድርገናል። ባጀቡን ሰዎች ፊት እንኳ እግዚአብሔር ሞገስን ሰጥቶን ነበር።

ክብረ መንግሥትን በማለፍ ዋደራን አቋርጠን ሃረ ቃሉ በምትባል ከተማ ላይም እንዲሁ ፈቀዱልንና ቆም ብለን ወተት በመግዛት ለመጠጣት ችለናል። አጃቢዎቻችንም በእኛ ላይ የነበራቸው ስጋት በጣም እንደ ቀነሰ ያስታውቅ ነበር።በመጨረሻም ከሃረ ቃሉ ጥቂት በመጓዝ በጠቅላላው 285 ኪ/ሜ **ያህል**

ተጉዘን ቦረና ነገሌ ከቀኑ በ9:30 ከታማኙ እረኛችን ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር በሰላም ልንገባ ችለናል።

## እግዚአብሔር ሲረዳ

ከማረሚያ ቤቱ ስንደርስ ይርጋ ዓለም ሳሉ፣ ወደዚህ ሳይቀየሩ፣ የምናውቃቸው የ10 አለቃ አሸናፊና ወ/ር አፈወርቅ የዕለቱ ዘብ ነበሩ። የማረሚያ ቤቱ ጽ/ቤት ሠራተኛም ስነ-ሥርዓት በተሞላ ሁኔታ ነበር የተቀበሉን። ፍተሻ በማጥበቅም አላስቸገሩንም። በተጨማሪ የገረመን ደግሞ ከእስረኞች መካከል የምናውቃቸውን ማግኘታችን ነበር። ስለዚህ የማረፊያ ቦታ ለማግኘት አልተቸገርንም። እነርሱም የምንታጠብበትንና የምንጠጣውን ዉኃ ተሯሩጠዉ አቀረቡልን። የማያዉቁን ሳይቀሩ፣ የሚበላ ምግብም እያዋጡ ሊሰጡን ሞክረው ነበር፤ ከይርጋ ዓለም ስንነሣ ምግብ ይዘን ስለ ነበር ሙሉ ለሙሉ አልተቀበልናቸውም እንጂ። ሥፍራ የማይወስነው፣ ጊዜ የማይለውጠው አምላካችን እግዚአብሔር አሁንም እዚህ ሲረዳን ዝግጁ ለመሆኑ እነዚህ ሁኔታዎች አመላካች ሆኑልን።

እንግዲህ፣ 21/1/76ን በዚህ መልክ አሳልፈን፣ የነገሌን ኑሮ ሰኞ ዕለት ተያያዝነው። እንደ እኛው በሃይማኖት ጉዳይ የታሰሩ ሌሎች 6 ሰዎች በግቢው እንዳሉም አወቅን። እነርሱ ግን 6 ወር ተፈርዶባቸው መውጫ ቀናቸውን በመቁጠር ላይ የነበሩ ናቸው። ከእነርስም ጋር ተዋወቅን።

በዚሁ ዕለት ደግሞ፣በነፍስ ግድያ ወንጀል ተጠርጥረው ታስረዋል ከሚባሉት 5 ወታደሮች ጥቂቶቹ የታሠርንበትን ዝርዝር ጉዳይና ምን እንደሚሰማን በግልም ሆነ በጋራ ሲጠይቁን - ሲመረምሩን ዋሉ። ለምን እንደሚጠይቁን ግን በጊዜው ሊገባን አልቻለም ነበር። እውነቱን ለማወቅ ብቻ ይሆን? ምንም ይሁን ምን፣ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ለመሞት እንኳ ቢሆን መቁረጣችንን ቃለ ምልልስ ከተደረገልቸው ወንድሞች ሰምተዋል። በእርግጥም የተቆረጠ ነገር ነበርና ክርስቶስን መፈለጋችን ከምናፈቅራቸው ዘመዶቻችን ተለይተን ወደዚህ ሥፍራ እንድንወረወር አድርጎናል። አፍቅሮ ለሞተልንም መሞት አይበዛብንም ብለናል ::

ከዕለታት አንድ ቀን ከእነዚህ ወታደሮች አንዱ ካድሬ እኔን ሊያነጋግር ፈለገ። እሺ አልሁት። የራሱን ሃሳብ መናገር ሳይጀምር እኔ ሁለት ጥያቄዎችን ልጠይቀው አስፈቀድሁት። ፈቀደልኝ።

- *እስከ አሁን ድረስ ጓደኞቼን እየዞርክ ተራ በተራ አነጋግረሃቸዋል። ምን ገመገምክ?* ነበር የመጀመሪያው ጥያቄዬ።
- *ጥቅማቸው የተነካባቸው የአብዮቱ ጠላቶች እንዳልሆኑ፣ ይልቁንም የጭቁን ልጆች መሆናቸውን ተገንዝቤያለሁ››* አለ።





- ሁለተኛው ጥያቄዬ ፣ *ስለ እግዚአብሔር ምን ታስባለህ?* የሚል ነበር።
- *ጥያቄዎችህ ከባድ ናቸው። ሆኖም ልሞክር። በቅርብ ጊዜ መንግሥት ካድሬዎችን ሰብስቦ ከአሁን በኋላ በሕዝብ መሐል ‹እግዚአብሔር የለም› ብላችሁ እንዳትናገሩ የሚል መመሪያ ሰጥቶናል። ምክንያቱም በሶቭየት ሕብረት፣ ወጣቱና ምሁሩ በከፍተኛ ቁጥር ወደ እምነት እየተመለሱባቸው ስለሆነ ባለ ሥልጣናቱ ተቸግረዋል። ... ጉዳዩም እየተጠና ነው። ስለዚህ ውጤቱ እስኪታወቅ ድረስ ጥንቃቄ እንድናደርግ ነው የተነገረን* ሆነ ምላሹ። ምስጢር ተገለጠ !! እኛን ለመከራ የዳረገን ርዕዮተ ዓለም በሞስኮ፣ ከመሠረቱ ላይ ከፍተኛ የሆነ መናጋት እንደ ገጠመው *የምሥራች* ለማን ማለት ነው።

ቦረና ነገሌ እንደ መጣን ለሞን ሥራ በጣም ይበዛብን ነበር። የእርሻ መሬት ቁፋሮ አከናውነናል። ጭቃ በእግራችን እያቦካን ቤት መርገናል። ይህን አገልግሎት ለማረሚያ ቤቱ ብቻ ሳይሆን በትውስት መልክ ለሌላ መሥሪያ ቤትም እንድንሰጥ ተደርጓል።

በአውራጃ አስተዳደር ጽ/ቤት ያረጁ ፋይሎች መመዝገብና ማደራጀት፣ በገንዘብ ሚ/ር ጽ/ቤት ዕቃዎችን ተሸክሞ መጓጓዝ፣በጦር ሠራዊት ካምፕ አሸዋና ኮረት እየበተንን መሬትና መንገድ መደልደል፣ የመጸዳጃ ቤት ጉድጓድ መቆፈር ...ወዘተ ከግዴታዎቻችን መካከል ጥቂቶቹ ነበሩ። የሠራተኛ ኃይል ፈላጊ መሥሪያ ቤት ባመለከተ ቁጥር *ጴንጤዎቹን አስወጡዋቸው* ይባል ነበር። እኛም የክርስቶስን መከራ መካፈል የመታሰራችን ዓላማ እንደ መሆኑ መጠን እግዚአብሔርን እያመሰገንንና እያከበርን እንታዘዝ ነበር።

ይህን ሁሉ እየፈጸምን ከዘመዶቻችን መገናኘት ግን አይፈቀድልንም ነበር። በመጀመሪያ ሰሞን *ጠባያችሁን እስክናጠና ነው* ይሉን ነበር። በኋላ ግን ከዘመድ እንዳንገናኝ የሚከለክል ትዕዛዝ እንደ ተላከላቸው ተረዳን።

በዚህ ሁኔታ ላይ ቆይተን ጥቅምት 27 ቀን 1976 ዓ.ም ከሰዓት በኋላ ድንገት ወደ አውራጃው አስተዳደር ጽ/ቤት ተጠርተን ተወሰድን። ተራ በተራም እየተጠራን ወደ ቢሮ ስንገባ በውስጡ የክፍለ ሀገሩ ዋና አስተዳዳሪ፣የቦረና አውራጃ አስተዳዳሪና አንድ ሌላ ሰውም ተቀምጠው ነበር። የአውራጃው ማረሚያ ቤት አስተዳዳሪም እዚያው ነበሩ።

በክፍለ ሀገሩ ዋና አስተዳዳሪ በነፍስ ወከፍ የቀረበልን ዋና ጥያቄ ‹‹ለውጥ አለ ?›› የሚል ነበር። የሁላችንም መልስ ወደ ቦረና በመምጣታችን ምክንያት

በእምነታችን ላይ ምንም ለውጥ እንደሌለ የሚያረጋግጥ ሆነ። የትም ብንሄድ የት፣ ምንም ለውጥ እንደማይኖርም አስረዳን። የምናመልከው እግዚአብሔርን ብቻ በመሆኑ እንደምንንቀሳቀስና ሌላ ዓላማ ቢኖረን ኖሮ ግን ይህን ያህል ችግር እንደማይደርስብንም ገልፀን ተናገርን። እዚህ ላይ ለየግላችን የቀረቡትን ጥያቄዎችና የሰጠናቸውን መልሶች በዝርዝር ለማስፈር ቦታና ጊዜ ስለሚያንስ ዋና ነገሩ ብቻ ተጠቅሷል።

በየተራ ተጠይቀን ከቢሮው ከመውጣታችን በፊት ግን የከ/ሀገሩ ዋና አስተዳዳሪ ኪሳችንን እየፈተሹ የተገኘውን ገንዘብ አጠረቃቅመው ከ14 ሰው በድምሩ ብር 268 .00 /ሁለት መቶ ስልሳ ስምንት ብር/ በማስመዝገብ ለማረሚያ ቤቱ አስተዳዳሪ አስረከበዋል። ይህን ያህል ብርም የተገኘው ከአንዱ ብር 3 ከሌላው 10፣25፣.... ወዘተ ተሰቃቅሞ ነው። ተስፋ የተደረገው ግን ከዚያ በላይ ይገኛል ተብሎ ሊሆን እንደሚችል ገምተናል። ይህ *ኢምፔሪያሊስቶች ገንዘብ ልከውላቸዋል* ተብሎ ለማስወራት የታቀደ መሆኑም ይገባን ነበር። ሆኖም ከ14 ሰዎች 268 ብቻ መገኘቱ ከተገመተው እጅግ አንሶ ስለተገኘ ሳይወራለት ቀርቷል። አምላካችን እግዚአብሔርም በእያንዳንዱ ነገር ንጽህናችንን እያረጋገጠ በከንቱ ሊከሱን የሚነሳሱትን ሲያሳፍር አየን። ይህ በማረሚያ ቤቱ አስተዳደር በአደራ የተቀመጠው ገንዘብ ግን በኋላ፣ በየካቲት 21/1976 ዓ/ም፣ ወደ ያርጋ ዓለም ስንመለስ ለሁላችንም ተመልሶልናል።

በ27/2/76 ከአውራጃው አስተዳደር ጽ/ቤት ወደ ማረሚያ ቤቱ ከእስረኛ ቆጠራ በኋላ ተመለስንና በማግሥቱ ቀድሞ ከነበርንባቸው 4 ክፍሎች ወጥተን ወደ ቁጥር 2 እንድንገባ ተደረገ። ይህም ክፍል እነዚያ አምስት ወታደሮችና ሌሎች እኛን ለመጠበቅ ይበቃሉ ተብለው የተገመቱ የሚኖሩበት ነበር። ከዚህም በላይ የግላችንን ሥራ እንዳንሠራ ተከለከለ። ሺመልስም የሸማኔ ዕቃውን ጠቅልሉ ገባ። ወደ ረፋዱ ላይ ደግሞ የክፍለ ሀገሩ ዋና አስተዳዳሪ መጡ። እኛ የገባንበትን ክፍል ሊጎበኙ ሲገቡ ሰሎሞን ሐጢያን በውስጥ አገኙትና በጥፊ መቱት። ከዚያ በኋላ እኛ ከመኻላቸው እንዳንገኝ የተደረገበት የጠቅላላ እስረኞች ስብሰባ ተደረገና ዋናው አስተዳዳሪ እኛን የሚመለከት የማስጠንቀቂያ ንግግር አደረጉ። ከንግግራቸው ውስጥ *እነርሱን አትጠጓቸው፣አትስሟቸው፣ከተፋ ቃል ከአፋቸው አይወጣም። በጣም ለስለስ ብለው ስለሚናገሩ እንዳያስቷችሁ ተጠንቀቁ። እኛ ለእነርሱ በቅርብ ጊዜ ዋጋቸውን እንሰጣቸዋለን* የሚሉ አረፍተ ነገሮች ይገኙበታል። ይህንንም በስብሰባው ተገኝተው ያዳመጡት ናቸው የነገሩን።

ከሰዓት በኋላ፣ ማለትም ጥቅምት 28 ቀን 1976 ዓ.ም ወታደሮች ለፍተሻ ገቡ። መጽሐፍ ቅዱሶችን፣ ሌሎች የአካዳሚ ትምህርት መጻሕፍትን፣ ማስታወሻ ደብተሮችን፣ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ሳይቀር ሰብስበው ወሰዱና ወጡ





።በዚህም አላበቃም። ወዲያው፣ « *ዕቃቸው በሙሉ ወደ ጽ/ቤቱ ለደብዳቤ ይምጣ»* ተባለ። የምግብ ዕቃ፣ ፍራሽ፣ የብርድ ልብሶች፣ የቀን ልብስ፣መቀየሪያ ሳይቀር ይውጣና ይመዝገብ ተባለ። ተመዘገበ። ቀጥሎ ከአንድ አንሶላና ከአንዲት ኬሻ በቀር ሁሉም ወደ ዕቃ ማስቀመጫ መጋዘን ይግባ ተባለ፣ የሚከተተውን እየከተትን፣ የሚታሠረውን ጠቅልለን እያሠርን አስገባን። ጫማ አውልቁ ተባልን። እያወለቅን ሰጠን። ኮት፣ ሸሚዝ፣ ሱሪ ሁሉ አስወለቁን። በውስጥ ቁምጣና በካናቴራ ብቻ ኬሻቸውንና አንሶላቸውን ይዘው ይግቡ! በማለት አዘዙ - የማረሚያ ቤቱ አዛዥ።

*የብርድ በሽታ ለሰብን፣ ያመናል* አልን። ማን ሊሰማን! የማረሚያ ቤቱ አዛዥ : - *እስቲ እግዚአብሔር ከሰማይ ወርዶ ሲረዳችሁ እናያለን* / አሉን። እኛም ለጌታ ለኢየሱስ ለመሞት እንኳ የተዘጋጀን መሆናችንን ተናገርን። ይህ ኢየሱስ ለእነርሱ ለራሳቸው ሕይወት ሳይቀር አስፈላጊያቸው መሆኑንም ነገርናቸው። ጊዜው ከሰዓት፣ ከምሳ በኋላ፣ ሁሉም ነገር «ሞቅ» የሚልበት ስለነበረ የተደረገብንም ነገር ያንኑ የሚያንጸባርቅ ሆነ። በመጨረሻም፣ የለበስናትን አንዲት ሸሚዝና አንድ ሱሪ በላያችን ላይ ትተውልን አንሶላችንንና ኬሻችንን ይዘን ገባን። ጌታ ኢየሱስም ልብሱን ተገፎ ራቁቱን ሆኖ እንደ ተሰቀለልን አስታወስን። ከዚህ አንጻር በእኛ የሆነው ትንሽ ነበር።

ተመልሰን እክፍላችን ስንገባ የመጸዳጃ ወረቀት እንኳ አልነበረንም፤ እልተፈቀደልንም ነበርና። በጉዳዩ ላይ ለማረሚያ ቤቱ አዛዥ ጥያቄ ስናቀርብ ድንጋይ እንድንጠቀም አዘዙን ። በሆነው ሁሉ ግን እግዚብሔርን አከበርን። አመሰገንንም።

ከዚያም በኋላ በእኛ ላይ የእምነት ለውጥ ለማምጣት ከፍ ያለ ዘመቻ ተካሄደ። ማክሰኞ ማክሰኞ ለእስረኞች የፖለቲካ ንቃት ፕሮግራም ወጥቶ አንቂዎች ከፖሊስ መምሪያ ይመጡና ያስተምሩ ጀመር። ኃይማኖትን በተመለከተም ደግሞ ሁለት ጊዜ ንግግር ተደረገ። ቢሆንም የተጠበቀው ለውጥ ሳይታይብን ቀረ።

የሌሊትም ሆነ የቀን ቅያሪ ልብሶቻችን ከተወሰዱብን በኋላ አንድ ሁለት እያለ ሦስት ወር ተቆጠረ። የቅማል ነገር አይወራ! የማታ ብርድ ነገር አይነሣ! ማታ በብርድ የተቆራመደ ሰውነታችንን በፀሐይ ሙቀት ለማፍታታት ብዙዎቻችን ጠዋት ጠዋት በር እንደ ተከፈተ የፀሐይ ጨረር ወዳረፈበት ሥፍራ እንሽቀዳደም ነበር።

የምግቡ ሁኔታም አስልቺ ነበር። ጧት የበቆሎ ቂጣ፣ ማታም ቂጣ ከሚጎረናና ካረረ ወጥ ጋር ቀናትን እልፈን ለወራት ተያያዝነው። በዚህም ሁኔታ ውስጥ

ልባችን በጌታ ይበረታ ነበር። እንጀራና ልብስ የምናመልክ አለመሆናችንን ዓለም የምትረዳበትም ሰዓት ያቺ ነበረች። ከዚህ ችግር የተነሣ በበሽታ ላይ ወድቀን ሞታችን ተፋጥኖ ቢሆን ኖሮም ትልቅ ደስታ ይሰማን ነበር። እግዚአብሔር ግን ከሁሉ ጠበቀን።

*ሥራ* አዘውትረን እንወጣ ነበር። አንዳንድ ጊዜም ተውሶ የወሰደን *መሥሪያ* ቤት የሠራንበትን ይከፍለን ነበር። በዚያም ክፍያ ሳሙናና የጽዳት ወረቀት እየገዛን *መምጣት* ጀመርን። የጤፍ እንጀራ በአፋችን ከገባ ብዙ ቀናት አልፈውናል። አንዳንዴ በሚከፈለን ገንዘብ ምግብ ቤት ጎራ እያልን እንጀራ እንበላ ነበር።

ወንድማችን ፓስተር ተሾመ ግን ብዙ ጊዜ ከሕምም የተሣ *ለሥራ* አይወጣም ነበር። ከዕለታት አንድ ቀን ደግሞ እንዲህ ሆነ። ክፍለ ጦር *ለሥራ* እንድንሄድ ታዘዝንና ተሰልፈን ወጣን።

- *ጴንጤዎች ሁሉም ይውጡ* ተባለ። ወንድማችን ፓስተር ተሾመም የግድ ካልወጣህ ተባለ።
- *ያመኛል፣ ያዞረኛል፣ ደግሞም ራቁቴን ነኝ እንዴት እወጣለሁ* አለ። ያለችውን አንድ ሱሪ አሳጥቦና አስጥቶ ለሰ ነበር በዕለቱ የለበሰው እንሶላ በማሸረጥ ነበር።
- *መሄድ ካለብኝ ልብስ ስጡኝ፣ራቁቴን ነኝ* አለ።
- *ትወጣለህ። ወድደህ አትወጣም አሉ* የማረሚያ ቤቱ አዛዥ፣ የመቶ አለቃው።
- *ብዙዎቻችን ለሥራው ወጥተናል። አንወጣም አላልንም። አንድ እርሱ ቢቀር ምን ይጎዳል; ደግሞ ራቁቱን ነው* በማለት ሌሎቻችንም ተናገርን - ማን ሊሰማን!
- *እስቲ እግዚአብሔር ከሰማይ ወርዶ ሲረዳችሁ እናያለን!* አሉ የመቶ አለቃው - አሁንም።
- *እግዚአብሔርስ ከሰማይ ወርዶ እንደሚረዳን እናውቃለን። አንተ ግን እንደዚህ ባትናገር ጥሩ ነው*›› አለ ከመኻከላችን ፓስተር ተስፋዬ ቃሚሶ። ያቺ ዕለት ትንሽ ‹‹ሞቅ›› ያለች ዕለት ነበረች።

በመጨረሻ ፓስተር ተሾመ እንደ ምንም ቀርቶ ሌሎቻችን በክፍለ ጦሩ መኪና - በእይፋ - ተጭነን ሄድንና የኳስ መጫወቻ ሜዳ ስናስተካክል ዋልን። ከውስጡ ኮረት እየለቀምን። የመቶ አለቃውም በንዴት ተከትለውን መጥተው እሠሪዎቻችንን፦ *ሰምሳ እንዳትለቋቸው! ቀኑን ሙሉ አሠሯቸው!* ብለዋቸው እንደ ሄዱም ሰማን። እግዚአብሔር ግን በአሠሪዎቻችን ፊት ሞገስን ሰጠን። እንዲያውም፣ እነርሱ ፦ *ቀስ እያላችሁ ሥሩ፣ እያረፋችሁ* - እያሉ አጽናኑን።





በመጨረሻም፣ ለዕለቱ *ሥራ* ለወጣን ሁላችን፣ *ሦስት ሦስት* የቆርቆሮ ምግብና ኬክ ሰጥተውን፣ ተሸልመን *መግባታችን* በጣም እንድንገረምና እግዚአብሔርን እንድናመሰግን አድርጎናል። ይህም በሐዋርያው ጳውሎስ የእስር ጉዞ ታሪክ ላይ *የደሴቲቱ ነዋሪዎችም የሚያስገርም ደግነት አሳዩን* ተብሎ በሐዋ 28:2 የተጻፈውን አስታወሰን።

በእነዚህ ጊዜያት ሁሉ ስለ ዕቃችን አልፎ አልፎ ለመጠየቅ ብንሞክርም ቀና መልስ አይሰጠንም ነበር። የማረሚያ ቤቱ አስተዳደሪ *እኔስ ታዝዤ ነው ይህን ያደረግሁት* ቢሉንም እኛ አልመሰለንም ነበር። ምክንያቱም የክፍለ ሀገር አስተዳዳሪን የሚያከል ትልቅ ማዕረግ ያለው ሰው እንደዚህ ዓይነት ርኅራኄ የጎደለው ትዕዛዝ ይሰጣል የሚል ግምት አልነበረንም። ምግብ፣ ልብስና መጠለያን ማግኘት ለሰው ልጅ ሁሉ መሠረታዊ ፍላጎቱና መብቱ ነው ሲባል ሰምተናል። ምግብና መጠለያውስ እንደ ነገሩ፣ በእርግጥ ነበረን። ከሞላ ጎደል የተገፈፍነው ልብሳችንን ነበር። ይህ በደል ከሕግ አንፃር የሚታይ ሊሆን ይችላል። ከእምነታችን አንፃር ግን ይህ ሁሉ የምንጠብቀው፣ ሊሆንም፣ ሊደርስም የሚችል ችግር መሆኑን እናውቃለን። ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቶስን መከተል ሁሉን አያጡ መከራ መቀበልን ሊያስከትል እንደሚችል ያስተምረናል (ዕብ 11:37)።

ሁኔታዎች በዚህ ዓይነት ቀጥለው ከቆዩ በኋላ፣ ጥር 12 ቀን 1976 ዓ.ም የማረሚያ ቤቱ አስተዳዳሪ ጠሩንና፣ ከዛሬ ጀምሮ ከዘመድ እንድትገናኙ ስንቅም እንዲገባላችሁ ተፈቅዶላችኋል ብለው ነገሩን። ከጥቂት ጊዜ በፊት፣ ከክፍለ ሃገር ስልክ ተደውሎ እንደ ነበረም በኋላ ሰማን።

ቀጥሎም ጥር 16 ቀን 1976 ዓ.ም የብርድ ልብስና የምግብ ዕቃ ውሰዱ አሉን። የተሰጠንን ወስደን የቀረውን ዕቃ ስንጠይቅ ግን *ይህንንም ራሴ አስተያየት አድርጌላችሁ ነው! ያዘዘኝ ሰው መልሰላቸው ካላለኝ አይመለስላችሁም* አሉን።

በነገሩ ብዙ ካሰብንበት በኋላ፣ ለክፍለ ሀገሩ *ማረሚያ* ቤት አስተዳዳሪ *ለማመልከት* ወሰነን፣ *ማመልከቻውንም* አሰናድተን *ለመላክ* ስናመቻች፣ ሰኞ ዕለት የካቲት 5 ቀን 1976 ዓ.ም ላይ ቢሮ ጠሩንና *ዕቃችሁን* በሙሉ ለመውሰድ ትችላላችሁ አሉን። ከበላይ ታዞ እንደሆነ አላወቅንም። ሁኔታው ግን እንደዚያ ይመስላል። በዕለቱም ፍራሽና ልብስ ወስደን፣ *መጻሕፍታችንና* ገንዘባችን ግን ቀርቶ ነበር። ቅዳሜ ዕለት ደግሞ *መጻሕፍቱንና* ክራሩን ልንረከብ *መቻላችንን* ነገሩን ። *እስቲ እግዚአብሔር ከሰማይ ወርዶ ሲረዳችሁ እናያለን* እያለ በመደጋገም ሊሳለቅብን የነበረ እንደበት *መልሶ ኑና ዕቃችሁን*

*ውሰዱ ሲለን አያስደንቅም?*
**በማረሚያ ቤት ኑሯችን፣ *የመጀመሪያ ማመልከቻችን ሲሆን የነበረውን ደብዳቤ ለመጻፍ ስንወስን፣ ጌታ ሆይ የምትፈቅደውን ነገር እንድናደርግ ገፋፋን፤ የማትፈቅደውን ነገር እንዳናደርግ ደግሞ ከልክለን* በማለት ጸልየን ነበር።** እግዚአብሔርም ቀደመንና እንደ ጠየቅነው ይህን እርምጃ **ከመውሰድ ከለከለን ።**

ሁኔታውን አስመልክቶ፣ ከአምስት ቀናት በኋላ፣ በ10/6/76፣ **በማስታወሻዬ** ላይ ያሠፈርሁት ጸሎት እንዲህ የሚል ነበር፦ ***ጌታ ሆይ ይህ በአንተ ዓይን*** *ቀላል ነው። ከዚህም የሚበልጥ ብታደርግ **የሚከለክልህ የለም። ይህንን** አውቀናል። ሥራህን ቀጥል። ምድርም አምላክነትህን ትወቅ ።* ***እኛም እስከ*** *መጨረሻ እንገዛልሀ። ግዛን ።*

ከንብረት ጋር አልተፈጠርንም። ከንብረት ጋርም አንሞትም። **ንብረቱ ሳይመለስልን** ቢቀርም የወሰዱብን ወገን እንጂ የእኛ ነፍስ አትጎዳም። **ስለ ስሙ** የተደረገውን ሁሉ ተመልክቶ የፍትሕ ***ሥራውን*** **ሰፈጸመ ለእግዚአብሔር** ክብርና ምስጋና እስከ ለዘላለሙ ይሁንለት። ***እግዚአብሔር ከሰማይ ወርዶ ሲረዳን*** *ታይቷልና።* እንግዲህ፣ ይህንና ይህን ከመሰለ ሁኔታ **ውስጥ ነበር** የሚከተለው የዝማሬ ሃሳብ ሊመጣ የቻለው።

1. በሕይወት ጎዳና ፈተና ቢበዛም
   ጌታን እየጠራ ንፁህ ሰው አይጠፋም
   እጁን ያዘኝ ብሎ ሲጮህ ይሰማዋል
   ክረግረግ አውጥቶ በድል ይመራዋል
      እግዚአብሔር ሲረዳ ከሰማያት ወርዶ
      በደልን ሲያስወግድ በቅንነት ፈርዶ
      አላያችሁም ወይ ወጥመዱ ሲሰበር
      ምርኮኛው ተለቆ ማዳኑን ሲናገር

2. ችግረኛን ሲዉጥ ጠላት ሲገዳደር
   በሚያስፈራራ ቃል በትዕቢት ሲናገር
   ደርሶ የሚታደግ እግዚአብሔር ብቻ ነው
   በሰዉ መታመን ግን የከንቱ ከንቱ ነው።

3. ያለዉን ተነጥቆ ሁሉን ነገር አጥቶ
   በእጠገቡ የሚቆም ጌታ ብቻ ቀርቶ
   በእንግድነት አገር ተገፍቶ ለሚያልፈው
   ተስፋዉ መሠረቱ እምላኩ ብቻ ነው።

4. የቅዱሳን ረድኤት ከሰማይ ይመጣል
   ዘመናትን ቆጥሮ ጌታ ይመለሳል
   የልጆቹን እንባ ከዓይናቸው ያብሳል
   ክብርና ምስጋና ለስሙ ይሆናል።





## መለኮታዊው ጥንቃቄ

ቦረና ነገሌ፣ በተለይ በበጋ ወራት፣ **ልምላሜ** አምብዛም የማይታይባት፣አሸዋ የሚበዛባት፣ነፋስና ፀሐይ የሚበረቱባት ቦታ ናት። በዚህ ላይ «**ሩቅ አገር**» ናት። ይህ ብቻ አይደለም። እዚያ የተወለድነው ከምናውቀው ሕዝብ፣ዘመድና አካባቢ ርቀን ያለ ጠያቂና ያለ አንዳች «ወሬ» (Information) **ቀርተን** እንድንጨነቅ ታስቦ ነበር። ሆኖም፣ ቦረና ነገሌን አስቀድሞ **የሚያውቃት** ከመካከላችን አልታጣም ነበር ። እኔ በበኩሌ ከ8 ዓመት በፊት ሁለት **ጊዜ ሄጄ** ወንጌል አገልግዬባታለሁ። ቢያንስ ቢያንስ የከተማይቱን አቀማማጥና የአየሩን ጠባይ አይቻለሁ።

እግዚአብሔር *የምድርም ዳርቻ ፈጣሪ* (ኢሳ 40፡28) ነው። ይርጋ ዓለም በእጁ እንደነበረች ሁሉ ነገሌም በእጁ ናት። በዚያ የጠበቀን በዚህ ሊጠብቀን አልተሳነውም። በዚያ የተጠነቀቀልን በዚህም ሲጠነቀቅልን አላቃተውም።

በይርጋ ዓለም ባሳለፍናቸው ያልቁንም እጅግ በጣም አስቸጋሪ በሆኑ ወቅቶች እንኳ ሳይቀር እግዚአብሔር ለእኛ የሚጠነቀቅበትን መንገድ አጥቶ አያውቅም። ፈጽሞ የማናውቃቸውንና ያላሰብናቸውን ሰዎች እያስነሳ ወደ እኛ ሲልካቸው አይተናል። በቀበሌ፣ በፖሊስ ጣቢያና በማረሚያ ቤት፣ በሁሉም *ሥፍራ* ጊዜያቸውን፣ ጉልበታቸውንና ገንዘባቸውን *መሥዋዕት* እያደረጉ የሚያገለግሉንን ሰዎች እግዚአብሔር አልነሣንም ነበር።

ከእነዚህ መካከል ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል፣ በይርጋ ዓለም፣ተማሪ በሳይነሽ ናሩሞ የክርስቶስን እስሮች በጉልበትዋ በማገልገል፣ ከገበያ ለብዙዎቻችን የሚያስፈልጉንን ቁሳቁሶች ተላልካ እየገዛችና እንደ አስፈላጊነቱ የበሰለ ምግብን እያዘጋጀች ለማቅረብ ብዙ ደክማለች።

እስማረ ፀጋዬ፣ ቦጋለ አደም፣ተሾመ ኩራቱ፣ገዛኸኝ እበራ፣ጌታሁን ቶማስ፣ተማሪ በቀለች ፀጋዬ፣ፍቅርተ ገ/ሃና፣እስቴር ኃይሌ፣የሲፐ *መሥሪያ* ቤት ሠራተኛ የነበረችውና የአሁንዋ ባለቤቴ ወ/ት ሃና ጎሹ፣ታደለች ጸጋ፣ በቀለ ቦሮጄ፣ ወዘተ፣ በየዓመታቱ እኛን በጉልበታቸው ለወራትና ለዓመታት እንዲያገለግሉን እግዚአብሔር ከሰጠን ወገኖቻችን መሐል ነበሩ። **ኤልያስን ወደ** ሰራፕታ እንዲዛወር እግዚአብሔር ሲያዝዘው፣ **ትመግበው ዘንድ እንዲት** ባልቴት አዘጋጅቶ እንደነበር ማለት ነው። (ነገሥ 17፡8፡9) ። **የወንጌላዊት ቤተ** ክርስቲያን የመካነ ኢየሱስ አገልጋይ፣ **ቄስ ዓለሙና ባለቤታቸው ወ/ሮ ራሔል ሐደሮም በኋለኞቹ ወራት ላይ ቤታቸውን ለማዕድ ዝግጅት በመፍቀድ ያደረጉልን ቸርነት የሚታወስ ነው።**

ወደ ነገሌ ስንዛወርም የሚቀበሉንንና በተቻላቸው መጠን በሚያስፈልገን ነገር የሚረዱንን ክርስቲያን እስረኞች ከውስጥ፣ ኩርኩራ ዋፎ ፣በቀለ ምሬሳ እንዲሁም ጌዲዎን ሥዩም የሚባሉ ወገኖችን ደግሞ ከውጭ፣ በጉልበታቸው እንዲያገለግሉን አዘጋጅቶልን ነበር። እነርሱም ቅማሎቻችንን እየለቀሙ ልብሶቻችንን አጠቡልን። የሚያስፈልገንን ጥቃቅን ቁሳቁስ ገዙልን፤ ለመቀየሪያ የሚሆን የበሰለ ምግብ እየተዘጋጀ እንዲቀርብልንም አደረጉ።

በአጠቃላይ፣በየነበርንበት ከርቀት እየተመላለሱ የጠየቁን አያሌ ቅዱሳንና የአብተክርስቲያን መልዕክተኞች፣ በማያቋርጥ ጸሎት ተሸክመውን የቆዩና በደብዳቤ ልባችንን የደገፉ ሁሉ በሰማይ መዝገብ የሚታሰቡ ናቸው። የተደረገልን ጥንቃቄና ክብካቤ ተካፋይ ናቸውና።

በእርግጥ፣ የአምላካችንን ጥንቃቄ ያየንባቸው መንገዶች በርካታ ናቸው። አንዱ የጤንነታችን ሁኔታ ነው። ለምሳሌ ያህል፣ ይርጋ ዓለም ላይ ከደረሱብን ጉዳቶች የተነሳ ብዙዎቻችን በተለያየ በሽታ የምንታመም ነበርን። ነገሌ ግን የመፈወስ ሥፍራ ሆነልን ! ይህ ሁላችንንም አስገርሞናል። የባሰና የከፋ ነገር እንዲያጋጥመን ታስቦ በተላክንበት በረሃ ላይ አምላካችን በእጅጉ ተከባከበን።

ነገሌ ሳለን፣ ለየትና ከበድ ያለ ሁኔታና አስደናቂ የሆነ መለኮታዊ ጥበቃም አይተን አልፈናል። ለሥራ በወጣንባቸው ጊዜአት፣ ለጥቂት ቀናት በወታደሮች ካምፕ የመሣሪያ ግምጃ ቤት ውስጥ መሣሪያዎችን እያስተካከልን እንድንደረድር ተደርጎ ነበር። ያንን ተግባር እየፈጸምን ሳለን አንድ የሻለቃ መጥቶ ያየናል። በመቀጠል ሁኔታው ዘግንኖት *እዚህ ያስገቡአችሁ ራሳችሁን በራሳችሁ እንድታጠፉ ተፈልጎ ነው እንዴ?* ይለናል። መሣሪያዎቹ ከሶማሌ በኩል ተማርከው የመጡ ነበሩ ተብሎአል። የግምጃ ቤቱ ከትናንሽ ፈንጂዎች እስከ ትላልቅ መሣሪያዎች ድረስ የተከማቹበት ነበር። የሻለቃውም ያሠራን የነበረውን ሻምበል ባሻ በመጥራት፦ *ስለ መሣሪያ ምንም ዕውቀት የሌላቸውን ሰዎች እዚህ ውስጥ ያስገባችኋቸው ራሳቸውንና ከተማይቱን እንዲያቃጥሉ አስባችሁ ነው ወይ ?* ብሎ ሲቆጣው ሥራውን ልናቋርጥ ችለናል። የሻለቃው፣ ከእነዚያ መሣሪያዎች መካከል አንዳንዶቹ ድንገት ቢፈነዱ ኖሮ ያቺን ከተማ ጭምር የማቃጠል አቅም እንደ ነበራቸው ገልጸውልናል።

በዚህና በሌላ ነገር ሁሉ እግዚአብሔር እጅግ በጣም ረዳን። ይህን ከመሰለ አስከፊ አደጋም በታላቅ ምሕረቱ ታደገን። *በልዑል መጠጊያ የሚኖር ሁሉን በሚችል አምላክ ጥላ ውስጥ ያድራል።* (መዝ 91፡1)። ስለ ድንቅ ጥበቃውና ጥንቃቄው የእግዚአብሔር የአምላካችን ስም ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ የተባረከና የተመሰገነ ይሁን።





## <u>በሩቅ አገር ሳሉ</u>

ምንም እንኳ ራቅ ያለ ሥፍራ ተወስደን ብንጣል፣ የሩቅ ሳይሆን የቅርብ የሆነው አምላካችን በልባችንና በሕይወታችን እንደ ነገሠ ነበረ። እኛም ለእርሱ የሚሆነውን አምልኮአችንን አላቋረጥንም። ነገሌ እንደደረስን የአምልኮአችን ሁኔታ ጠበብ ያለ ነበር። የሥራው ብዛት ባያመችም የጾምና የጸሎት ጊዜ እየወሰድን በጌታ ፊት መሆናችንም አልቀረም። ብዙም ሳንቆይ መጽሐፍ ቅዱሶቻችን ስለ ተወሰዱ እግዚአብሔር በራሱ ጥበብ እጃችን ያስገባልንን ጥቂት መጽሐፍ ቅዱሶች በስስትና በጥንቃቄ ነበር የምንጠቀመው። ከራር እየተዋስን በየግል እናንጎራጉር ነበር። እየቆየን ስንሄድ ግን በቡድን በቡድን እየሆንን መዘመርም ቻልን። እግዚአብሔርም የመንፈስ ነፃነትን ከጊዜ ወደ ጊዜ ሰጠን።

እኛም በጌታ ስም ደፍረን በአሕዛብ ፊት ባከበርነውና ባመለክነው መጠንም ነፃነታችን በጌታ እየሰፋ ሲሄድ አየነው። እስረኞችም፣ ተቃዋሚዎቻችን ሳይቀሩ የአምልኮ ዝማሬያችንን በጽሞና ያዳምጡ ነበር።

በነገሌ ምድር ሳለን፣ ያለፈውን የጌታ የኢየሱስን ልደት በዓል በድፍረትና በይፋ አከበርን። ያ ወቅት እንጀራ ከውጭ እንዳይገባልን የተከለከለበት ወቅት ቢሆንም የእስረኞች ሊቀመንበር የነበረ ሰው ራሱ በገንዘባችን እንዲመጣልን በማስደረጉ እንጀራ በላን። ጌታንም በዝማሬ አብዝተን አመሰገንነው።

ስዚያ ሰሞን በልባችን የነበረ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ የሚከተለው ነበር፦ *አቤቱ በፍርድህ መንገድ ተስፋ አድርገንሃል። ስምህም መታሰቢያህም የነፍሳችን ምኞት ነው* (ኢሳ 26፡8)። አምላካችንን በሩቅ አገር ሳለንም እንድናስበው ጸጋው ረዳን። እግዚአብሔርም እኛን የሚያስብበት ጊዜ መጣ። ዕቃችን ተመለሰልን፤ እኛም ወደ ይርጋ ዓለም የምንመለስበት ወቅት ተቃረበ። *በአሕዛብ መካከል ብዘራቸው እንኳ በሩቅ አገር ሳሉ ያስቡኛል፤ከልጆቻቸውም ጋር በሕይወት ይኖራሉ፤ ይመለሱማል* የሚለው ቃልም ታወሰን። (ዘካ 10፡9) ቃሉ በዐመጻቸው ምክንያት ለምርኮ ለተዳረጉት እስራኤላውያን የተነገረ ተስፋ ቢሆንም፣ ስለ ጌታ ተሰደን ለምንገኝ ወገኖችም ሳይሠራ እንዳልቀረ እናምናለን።

በጌታ ልደት በዓል ቀን፣ ትልቅ ደስታ ተሰምቶን ነበር። በዚህ ዕለት፣ ወንድማችን ለገሠ፣ *ከዚህ የሚበልጥ ነገር ታያለህ* የሚል ቃል ከ(ዮሐ 1፡51) በልቡ እንደ መጣለት አካፈለን። ከዚያን ቀን ጀምሮ፣ ተራ በተራ የአምላካችንን ተጨማሪ ረድኤት በግልጽ እያየን መጣን። በየጊዜውም አዳዲስ ተአምራት ተመለከትን።

## ተመልሶ ይርጋ ዓለም

በ20/6/76 የቦረና አውራጃ አስተዳዳሪ ጓድ ኤልያስ፣ ነገሌ ማረሚያ ቤት ድረስ መጥቶ፣ ነገ ወደ ይርጋ ዓለም ትንቀሳቀሳላችሁና ተዘጋጁ። አትደንግጡ! ሊፈቷችሁ ይመስለኛል። ግን ምን ዓይነት Cult - የሃይማኖተኞች ክፍል - እንደ ሆናችሁ አይገባኝም፤ ይህን ያህል ግትር የሆናችሁበት ለማለት ነው። ይኼን ጊዜ "You could have become Doctors" ብሎን ሄደ። ይህን ሲል፣ ብትማሩ ኖሮ ሐኪሞች መሆን የምትችሉበት ጊዜ ነበር ማለቱ ነው።

በ21/6/76 ከጠዋቱ 5 ሰዓት ገደማ ከቦረና ነገሌ ወጣን። ከምሽቱ 3 ሰዓት ገደማ አለታ ወንዶ ገባተን፣ ግማሾቻችን ሆቴል፣ ሌሎቻችን በየዘመድ ቤት አደርን። ያን ያህል የመሸብን መኪናው ተበላሽቶ በየቦታው ሲቆም ስለ ነበር ነው። አሥራ አምስታችንን አጅቦ ያመጣን አንድ የማረሚያ ቤት ወታደር - አፈወርቅ - ብቻ ነበር። በማታው አዳራችንም በየፈለግነበት ስናድር ወታደሩ አምኖን ስለ ነበረ ችግር አላጋጠመንም።

በ22-6-76 ረፋዱ ላይ ይርጋ ዓለም ማረሚያ ቤት በደህና ደረስን። እኛን የጫነ መኪና ሲገባበትም፣ የማረሚያ ቤቱ ትልቅ በር ፈረሰ።

የማረሚያ ቤቱ አስተዳዳሪ አሁን አዲስ ከመሆኑ በቀር ወታደሮቹ በአብዛኛው የምናውቃቸው ነበሩ። ሁለቱ ብቻ ተቀይረዋል። እንደ መጣን ሰሞን ከዘመዶቻችን ጋር እየተገናኘን መጫወት ችለን ነበር።

የይርጋ ዓለም ማረሚያ ቤት በሲዳሞ ክፍለ ሀገር ውስጥ ከነበሩት ማረሚያ ቤቶች ሁሉ ከባዱ እንደ ሆነ የተነገረለት ነበር። ከሌሎች በምን በምን እንደሚለይ ብዙ ባናውቅም ከነገሌው ይልቅ እንደሚከብድ መገንዘብ ይቻላል።

አጥሩ ረጃጅምና ድርብ ነው። የቤቱ መሠረት ጠንካራ ግንብ ነው። የሚበዙት ወታደሮች እስረኛውንም ሆነ የእስረኛውን ዘመድ እያመናጨቁ ለማዋረድ እንዲችሉ ሆነ ተብሎ የተመከሩ ይመስላሉ። አሁን ደግሞ ይባስ ብሎ እስከ ዛሬ ድረስ ካየናቸው የማረሚያ ቤቱ አስተዳዳሪዎች ሁሉ ይልቅ እጅግ «ጠንከር» የሚል አስተዳዳሪ ተሹሞ ሳለ ደረስን። ይህም ሰው፣ ሁኔታችንን ቀስ በቀስ ካጠና በኋላ፣ ብዙም ሳንቆይ፣ ከዘመድ የመገናኘታችንን ሁኔታ እያጠበበው መጣ። በመጨረሻም፣ በ3/12/76፣ ከዘመድ ስንቅ ከመቀበል በቀር ምንም መነጋገር እንደማንችል ወታደሮቹ ነገሩን። *አስተዳዳሪው አዞናል* አሉ።

*ነገሌ ላይ ልብሳችን ተገፎ፣ ለሦስት ወር ያህል ብርድ ሲያንቀጠቅጠን፣ በቅያሪ ልብስ እጦት ቅማል በወገባችን ላይ ሲርመሰመስብን፣ ከዘመድ*





*ዓይን ርቀን ከተቀጣን በኋላ፣ ተመልሰን አሁንም በተጽዕና ሥር እንገኛለን። ይሁን። ለክርስቶስ፣ ካስፈለገ እስከ ሞት ድረስ እንታገሳለን። «ፍቅር እንደ ሞት የበረታች ናት። (መኃ 8:6)» በፍቅር ለጠራንና ለዋጀን ነፍሳችንን ሰጥተናል። የጌታ ጸጋ ግን ትልቅ ነገር ይሠራል። «የያዕቆብ ቅሬታ...ሰውን እንደማይጠብቅ፣ የሰውንም ልጆች ተስፋ እንደማያደርግ ይሆናል።(ሚክ 5:7)» «አሁንስ ተስፋዬ ማነው? እግዚአብሔር አይደለምን ?(መዝ 39:7)»* (በዕለቱ፣ በማስታወሻዬ ላይ ካሠፈርሁት።)

ከቦረና መልስ፣ በይርጋ ዓለም ማረሚያ ቤት 1976 ዓ/ም ከፍ ብሎ በተመለከተው ሁኔታ ተጠናቀቀና ወደ ቀጣዩ ዓመት በዚሁ መልክ ተሸጋገርን።

በ1977 ዓ/ም የዘመን መለወጫው ዕለት፣ እንደተለመደው በጋራ የአምልኮ ፕሮግራም አደረግን። በዕለቱም፣ ከመስከረም 1/1976 እስከዚህች ቀን ድረስ ያሳለፍነውን በጥቂቱ ለማስታወስ ይህች ግጥም ተነባ ነበር።

በሕይወት እኖራለሁ አልሞትም እያለ
አንዱ ወንድማችን ወረቀት አደለ
መስከረም አንድ ቀን ሰባ ስድስት ነበር
ይኼው ሰባ ሰባት ዓመቱ ሲከበር
እንደታየው ሆኖ ቀኑ አለፈና
ቁጥር 16 ከሰዓት ገባና!
ጌታም አድሳቱን ወዲያው ጀመረና
አንስቶ አቆመን ብርታቱን ሞላና

--------------------

በጸሎቱ ጊዜ በእነዚያ ምሽቶች
የተካሄደው ስልፍ የተገኙ ድሎች
ራስን የመመርመር የመስተካከሉ
የኃጢአት ኑዛዜ ሸክም መቃለሉ
እናብስቱን ሁሉ በኢየሱስ ስም ብለን
በተሰጠን ሥልጣን ሁሉን አስረን አስረን
ከሞትም ፍርሃት ፍፁም ነፃ ሆነን
በጌታ ስም ገባን በጌታ ስም ወጥተን
በሥፍራችን አለን እግዚአብሔር ይመስገን

--------------------

በየትኛው ምሽት ነው ጌታ ያልተናገረን
የሶሪያን ንጉሥ የወልዴ አዶርን
አድራጎቱን ሁሉ እናስታውሳለን
ሴቶችና ልጆች ብሩንና ወርቁን
መውሰዱ ሳይበቃው ጭማሪ መሻቱን

የእስራኤል ንጉሥ በጣሙን ተናደ
አዛዉንቱን ጠራ መልዕክተኛ ሰድዶ
ነገር ይፈልጋል ይህ ሰው ተመልከቱ
ብሎ ምክራቸውን ጠየቀ በብርቱ
አትስማው ፈጽሞ እሺ አትበለው
የፈለገውን ያምጣ እንግዲህ ዝም በለው
የፈለገውም መጣ ስልፉ ተከፈተ
‹‹ወልዱ››ም ነፍሱን ይዞ ጥቂት አመለጠ!

------------------------

ተጠበቅ ዝም በል ልብህ እንዳይደክም
ዛሬ ምታያቸውን ዘላለም አታይም
የእንጨት ጠለሸቶች እነዚያ ሁለቱ
አይስብሩህምና አትፍራ በከንቱ
ብሎ የመከረን የቃልህ እውነቱ
በእኛ ታይቷልና ተመስገን አቤቱ!

------------------------

ቅብጥብጡ ፈረስ ስልፍን የለመደ
ቁጣን የተሞላ ወኔው ያልበረደ
ሠራዊት ሲያወካ አለቆች ሲጮኹ
ልጓም አይገታውም ይነሣል እልሁ

------------------------

የሚገርመው ደግሞ የጭልፊቱ ነገር
በገደል ገመገም በየጥጉ ሲያድር
ሕይወቱ ለምልማ በደስታ ሲኖር
በድን በሞላበት በሞት ጥላ መንደር

------------------------

የአዞ ቅርፊቶች ያስፈራል ግርማቸው
አንዱ ከሌላው ጋር በመጋጠማቸው
በጠባብ ማተሚያ የታተሙ ናቸው
ነፋስ አያስገቡም በመካከላቸው

------------------------

ጌታ ሆይ ውስታህ ከቁጥር ይበዛል
ትንሽ ብናወሳ ከዚያ ሁሉ መኻል
ከብዙ ጥቂቱ ይህንን ይመስላል
የጥቂት ነገር ቀን እንደ ምን ይናቃል
እንግድነት ሄደን እዚያም አይተንሃል





የምድርን ዳርቻ በእጆችህ ይዘሃል
ሁሉን ቻይ አንተ ነህ ምንስ ያቅትሃል?
አሁንም ልባችን አንተን ይናፍቃል
የቅዱሳን ጩኸት ጌታ ሆይ ና ይላል
እስክትመጣ ግን እምነት ይጨምራል
ምርጫችን አንተ ነህ እስከ ለዘላለም
አጥበኸናልና ክቡር በሆነ ደም
እረኛችን ሆነህ አላላጣኸንም
ከኃያል መዳፍህ የሚነጥቀን የለም
ክብር ለአንተ ይሁን ለዘላለም ዓለም!!!

በ2/2/77 ከዘመድ ስለ መገናኘት ጉዳይ የማረሚያ ቤቱን አስተዳዳሪ በማመልከቻ ጠየቅን፡፡ የተሰጠንም መልስ ፦ *በጽሑፍ የደረሰኝ ትእዛዝ ባይኖርም እኔ ራሴ የክ/ሀገሩን ማረሚያ ቤት ጠይቄ በተነገረኝ መሠረት ተከልክላችኋልና ጽፈን ስለ ሁኔታው እስከንረዳ ጠብቁ* የሚል ነበር፡፡ ቢጠበቅ ቢጠበቅ ግን መልስ ጠፋ፡፡

በ21/3/77 የክፍለ ሀገሩ የማረሚያ ቤቶች አስተዳዳሪ፣ ኮሎኔል ክፍሌ ቸርነት፣ ለሥራ ጉብኝት ይርጋ ዓለም ስለ መጡ እኛም ከዘመድ ስለ መገናኘት ጉዳይ በማመልከቻ ጠየቅናቸው፡፡ እርሳቸውም ስለ ሁኔታው የመቶ አለቃውን ሲጠይቁ የሰጠው መልስ፦ *ከዚህ በፊት፣ በ1975 ዓ.ም ከክፍለ ሀገሩ አስተዳደር መመሪያ ተሰጥቶበት ነበር፡፡ በተጨማሪም ከዚሁ ከእኛ ቤት፣ከአውራጃው ማረሚያ ቤት አስተዳደር መመሪያ ተሰጥቶበታል* የሚል ነበር፡፡

ኮሎኔሉም ማመልከቻችንን ተቀብለው፣ ስለ ጉዳዩ ከክፍለ ሀገሩ አስተዳዳሪ ጋር እነጋገራለሁ ብለው ሄዱ፡፡ በ23/4/77 አዋሣ የሚገኙት እስረኛ እህቶቻችንም ከዘመድ መገናኘት መከልከላቸውንና ብዙም ሳይቆይ እንደ ተፈቀደላቸው የወሬ ወሬ ሰማን፡፡

## የሰማይ መስኮቶች

ሰዎች የራሳቸውን በር ሲዘጉብን እግዚአብሔር የበረከቱን በር ‹‹የሰማይን መስኮት›› ለእኛ መክፈቱ አልቀረም፡፡ የሰዎች በር ለ1 ዓመት ከ6 ወር እንዲዘጋ ሲደረግ ይህንን ወቅት እግዚአብሔር የእኛን መንፈሳዊ ሕይወት ለመሥራትና በፊታችን ላለው ‹‹መፈታት›› ለማዘጋጀት ተጠቅሞበታል፡፡ በዚህም በሮሜ 8፡28 ላይ *እግዚአብሔርን ለሚወድዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን፡፡* የሚለውን የጌታ ቃል እውነተኛነትም እንድናረጋግጥ ሆኗል፡፡

መስከረም 1 ቀን 1977 ዓ/ም በዘመን መለወጫው ዕለት በነበረን የወንድሞች ሕብረት ላይ ጌታን በዝማሬና በአምልኮ አከበርነው። የእግዚአብሔርም መንፈስ በድንገት አነቃቃን። ይህም የሆነው በተለይም *እግዚአብሔር ሲረዳ* የሚለውን ዝማሬ ለመጀመሪያ ጊዜ በጋራ ሆነን ስናዜም ነበር። በዚህ ወቅት የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ፈለለብን። ተስፋዬ ቃሚሶ ከተቀመጠበት ብድግ ብሎ እጆቹን ወደ ላይ ዘረጋ። ያለነው በእስረኞች መሐል ነበር። ተስፋዬ ድምጹን ከፍ አድርጎ በመደጋገም *ሃሌ ሉያ! ሃሌ ሉያ! የተፈታ ሕዝብ ነው! የተፈታ ሕዝብ ነው.../* ካለ በኋላ መልሶ ተቀመጠ። ከድምጻችን ያልተለመደ አወጣጥ አኳያ ፖሊሶች ሮጠው አለመምጣታቸው የሚገርም ነበር። እግዚአብሔር አምላክ ገዛቸው። እኛን ደግሞ ወደ መንፈሳዊ የአርነት ከፍታ አወጣን። ስሙ ይባረክ። ያች ዕለት ለእኛ እውነተኛ የሆነ ትንቢታዊ መልዕክት ‹‹ከሰማይ›› የተቀበልንባት ሆነችልን። ከአንድ ዓመት ከ9 ወር በኋላ ምርኮኛው ‹‹ተፈቶ›› ታይቷልና።

ለሕይወታችን መነቃቃትና መባረክ ምክንያት አድርጎ እግዚአብሔር የተጠቀመው ሌላው መንገድ‹‹ ACTS ›› በመባል የሚታወቀው የቤ/ክ አገልጋዮች መጽሔት ነበረ። ይህን መጽሔት እስከ ተፈታንበት ጊዜ ድረስ በተከታታይ ተጠቀምንበት። መጽሔቱን ይልክልን የነበረው የዚያኔው የወርልድ ቪዥን ሠራተኛ፣ ጋሼ በቀለ ወልደ ኪዳን ነው።

በ1978 ዓ/ም ልንፈታ ጥቂት ጊዜ ሲቀረን ‹‹Let God arise›› ‹‹እግዚአብሔር ይነሣ፣ ጠላቶቹም ይበተኑ›› የሚል ሃሳብ የያዘ መጽሔት ደረሰንና በእጅጉ አጽናናን። በጥብቅ ተዘግቶ የነበረውን ደጅ እያለፈ በመካከላቸው ተገኝቶ ደቀ መዛሙርቱን ያጽናና የትንሣኤው ጌታ፣ እኛንም አልፎ ሊያጽናናን፣ ሊያንጸንና ለላማችንን ሊያበዛ ችሉአል። ክብር ለእርሱ ይሁን!

ሰይጣን በእኛ ላይ ድል ለመቀዳጀት የመጨረሻ ጥረት በማድረግ ደጆቻችንን የዘጋ መሰሉታል። ቢሆንም የሰማይን ደጆች ማንም ሊዘጋ ስለማይቻለው ከላይ ከብርሃናት አባት በሚወርድ የበረከት ጠል ህይወታችን እየረሰረሰች ትረካ ነበር። እኛም በበኩላችን በጌታና በኃይሉ ችሎት እየበረታን ስንሄድ ይሰማን ነበር።

በዚህ ጊዜ፣ እጅግ በጣም ድንቅ በሆነ መንገድ የአገልግሎት አጃችንን ከቅርብ እስረኞች ጀምሮ በሩቅ እስከ ነበሩት ወገኖች ድረስ እንድንዘረጋ ጌታ ረድቶን ነበር። በእጠገባችንም የነበሩት ብዙዎች ፊታቸውን ወደ ጌታ ክርስቶስ እየመለሱ ሕያውና እውነተኛ የሆነውን አምላክ ሲያመልኩ ለማየት ችለናል። ከእነዚህም መካከል ተፈተው በአካባቢያችን የቤተ ክርስቲያን መሪ እስከ መሆን የደረሱ አሉ። ክብር ለታላቅ ስሙ ይሁን።





ይህንንም የእኛን አለመድከምና የሰዎችን ወደ ክርስቶስ መመለስ ያየ ዲያቢሎስ፣ ቁጣው እየጨመረ መጣ። በዚህም ምክንያት 15-9-77 የሙቶ አለቃው ይቀርበውና ያቀርበው ለነበረ ወታደር ወንድሙ ቴማ *እነዚህ ጴንጤዎች ግዜውን በከለውታል ስለዚህ ለበላይ አካል ጽፈን ኃላፊነታችንን ከራሳችን ማውረድ አለብን።* .... ሲል ተሰማ። በዚሁ ዕለት፣ የግቢው እስረኞች ሊቀ መንበር ለነበረው ለሻምበል ጉልላት ዘውዴም፣ እኛን አስመልክቶ ሪፖርት ለአውራጃው ማረሚያ ቤት ጽ/ቤት እንዲያቀርብ ትዕዛዝ ተለጥፏል።

በ19/9/77 አንድ እንግዳ ማረሚያ ቤታችንን ጎበኘ። እንግዳው ከአገር አስተዳደር ሚኒስቴር ተልኮ እንደ መጣ ተነገረን። ለዚሁ እንግዳ ከዘመድ መገናኘታችንን ስለ መከልከላችን በቃል አመለከትን፤ መልሱ ግን *የመጣሁበት ጉዳይ ሌላ ነው! እዚህ ውስጥ አልገባም* የሚል ሆነ ። ይህም ማመልከቻ በሙቶ አለቃው ዓይን እርሱን እንደ መክሰስ ተቆጠረብን።

## የእግዚአብሔር ድምጽ

የማረሚያ ቤታችን መንፈስ እንደ ገና እየከበደ ሲመጣ ይታወቀን ነበር። እጅግ ቆየት በሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ የአማርኛ ትርጉም ላይ‹‹ጸላት እንደ ጽኑ ፈሳሽ ቢመጣ የእግዚአብሔር መንፈስ ምልክት ያነሣል›› ተብሎ በኢሳይያስ መጽሐፍ(በምዕ 59:19) ተጽፎአልና፣ የአምላካችን መንፈስ በእኛ ዘንድ፣ ከበድ ብሎ የተነሣውን ክፉ መንፈስ ለመቋቋም፣ የማገጃ ምልክትን አነሣ ። በዚሁ መሠረት፣ ሁኔታውን ለመቋቋም፣ ከ23/9/77 - 15/10/77 ድረስ የዘለቀ የግል ጾምና የፀሎት ጊዜ በመውሰድ የአምላኬን ፊት ፈለግሁ። ርዕሶቼ

1. እስራታችንን በሚመለከት ልቤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዲያስተውል፣
2. እግዚአብሔር የማይከብርበትን ነገር ሁሉ ከእኛ እንዲለይና
3. በእኛ፣ በእምነት እስረኞች ላይ በስውር የተተነኮለውን ነገር ሁሉ እግዚአብሔር እንዲሽር የሚሉ ነበሩ(አስቴር 7:3)።

ጸሎቱ በመጀመሪያ ሳምንት ላይ መጠነኛ ተግዳሮት የታየበት ሆነ። ኃይለኛ ጉንፋን ያዘኝ። በ3/10/77 በየክፍሉ እንድንበተን ተደረገ። ጾሙን ለማቋረጥ ተፈትኜ ነበር። የእግዚአብሔር መንፈስ ግን እንድቀጥል ገፋፋኝና ቀጠልሁ።

በእነዚህ ጊዜያት ውስጥ፣ ትንቢተ ሆሴዕንና መጽሐፈ መክብብን አጠናሁ። በዚህ ወቅት፣ በእነዚህም መጻሕፍት እግዚአብሔር ለልቤ ተናግሮአል። ከሁሉም ይልቅ፣ ወደ ልቤ ጠልቆ የገባው ቃል (በሆሴዕ 2:17) ላይ ያለው ነበር። ቃሉ እንዲህ ይላል:-

> *ከዚያም የወይን ቦታዋን፣ የተስፋ በርም እንዲሆንላት የአኮርን ሸለቆ እሰጣታለሁ፤ በዚያም ከግብፅ ምድር እንደ ወጣችበት ቀን እንደ ሕፃንነቷ ወራት ትዘምራለች።*

ይህንን የተስፋ ቃል፣ ከራሳችን ሁኔታ ጋር በእምነት እንዳዛምደው መንፈስ ቅዱስ ያመለከተኝ፣ የጾምና የፀሎት ፕሮግራሜን ባበቃሁበት ዕለት፣ ማለትም በ15/10/77 ነበር። እኔም በራችን ሊከፈት እንደሆነ አመንሁ። በእነዚህ 22 ቀናት ውስጥ በተጨማሪ ከብዶኝ የነበረ ሌላው ሃሳብ፣ ይህን ያህል ዓመት ጸንተን ቆይተን፣ በሕይወታቸው ደክመው ከመካከላችን የሚለዩን ወገኖች እንዳይኖሩ የሚል ነበረ።

ለዚህም ስጋቱ የሚሆን መልስ ጌታ በሚቀጥሉት ተከታታይ ጊዜያት ውስጥ ሰጠኝ። በ16/10/77 የሐዋ 27ን በሙሉ ሳነብ ልቤ በቁጥር 44 *እንዲሁ ሁሉ በደህና ወደ ምድር ደረሱ።* በሚለው ቃል ላይ አረፈ። በዚያው ሳምንት ውስጥ ከወንድም ተስማ ሎዴቦ ከመዝ (107፣30) *ወደ ፈለጉትም ወደብ መራቸው* በሚል መክፈቻ የተጻፈ መልዕክት ደረሰን። በከተማችን በያርጋ ዓለም ውስጥ፣ ስለ እኛ ሲጸልዩ ከነበሩት ወገኖቻችን ደግሞ *እግዚአብሔር፡- አፈታቸው ዘንድ ቆሜያለሁ፣ከእነርሱም አንድ አይጎድልም* ብሎናል የሚል ትንቢታዊ መልእክት መጣልን። በልቤ ውስጥ የነበረውን ሸክምና ጸሎት ፈጽሞ ካላወቁት ይህ መልእክት መምጣቱ የሚያስደንቅ ነበር !

*እግዚአብሔር በወጀብና በዐውሎ ነፋስ ውስጥ መንገድ አለው፣* (ናሆም 1:3)። የነፍሳችን ጠላት አስጨንቆ ሊያዳክመንና ሊጥለን በሚያነሣው ወጀብና አውሎ ነፋስ ውስጥ፣ ጌታ የተስፋን ቃል እየሰጠ ያበረታንና ያጽናናን ነበር።

በ28/11/77 ተጽፎ በ10/12/77 የደረሰን የወንድማችን ፓስተር በቀለ ወ/ኪዳን ደብዳቤ ደግሞ የሚከተሉትን ቃሎች ያዘለ ነበር፡-

- *ብርሃንሽ መጥቷልና፣ የእግዚአብሔርም ክብር ወጥቶልሻልና ተነሺ፣ አብሪ* (ኢሳ 60:1-2)።
- *የእስራኤል ድንግል ሆይ፣ እንደ ገና አሠራሻለሁ አንቺም ትሠሪያለሽ፤ እንደ ገናም ከበሮሽን አንስተሽ ከዘፋኞች ጋር ወደ ዘፈን ትወጫለሽ* (ኤር 31:4)።
- *እነሆ ክረምት አለፈ ... የዜማም ጊዜ ደረሰ ... በዓለት ንቃቃትና በገደል መሸሸጊያ ያለሽ ርግብ ሆይ፣ .... ድምፅሽንም አሰሚኝ* (መኃ 2:11-19)። ‹‹ክረምቱ›› ግን ሊያልፍ ገና አንድ ዓመት ቀርቶት ነበር።

## ኃጢአት ስታሳድድ

በ3/10/77 በየክፍሉ እንደ በተኑን ከፍ ብሎ ተገልጾአል። ብተናውም የሚከተለውን ይመስል ነበር። ፓስተር ተሾመ በክፍል ቁጥር 1፣ ጌታሁንና ሰሎሞን በቁጥር 2፣ ሺመልስና ከበደ አርጋው በቁጥር 3፣ ለገሠና ታፈሰ በቁጥር 4፣ ተስፋዬ ቃሚሶና አዳነ በቁጥር 5፣ ኃይሉና ማርቆስ በቁጥር 15፣ እኔና በራሣ በቁጥር 16፣





ይህ ለምን ሆነ ? በወቅቱ የነበረውን ሁኔታ ለማስታወስ የተጻፈ ማስታወሻ በከፊል እንደሚከተለው ይነበባል፡- ‹‹የማረሚያ ቤታችን አስተዳዳሪ በሥራው ዙሪያ ክስ እንደ ተመሠረተበት ከሰማን ሰንበት ብሏል። ከሳሾቹም ከእስረኞች መካከል እንደ ነበሩ በግቢው ሲወራ ቆይቷል። ሰውየው ግን ማን እንደ ከሰሰው በውል ማወቅ ስላቃተው እኛን መጠርጠር ጀመረ። ስለዚህም፣ የግቢውን ሰው ሰብስበው በከሉብኝ የሚል ሽፋን በመጠቀም ካለንበት ማረሚያ ቤት ሊያስነሣንና ሊያስቀይረን ወደ ክፍለ ሀገሩ ማረሚያ ቤት ደውሎ መጠየቁን ሰማን። በመጨረሻም፡- ‹‹...*ተጠርቻለሁ። ምናልባት ከታሠርኩ ያሣሠሩኝ ጴንጤዎች እንደሆኑ እወቁልኝ*›› የሚል መግለጫ ለፖሊስ መምሪያ ካድሬና ለማረሚያ ቤቱ ፖሊሶች መስጠቱን ሰማን።

የሚገርም ነው። ተከስሶም ከሆነ ማን እንደ ከሰሰው እያደር ራሱም ቢሆን ሳያውቀው አይቀርም። እኛስ እዚያ ደረጃ ላይ አልደረስንም ነበር። እውነቱ ሲገለጥ ግን የሰው ሃሳብ ከንቱ ሆኖ፣ ጌታ በደረሰብን በደልና ግፍ እንደሚከበር እናውቃለን። አሁንም ስሙ የተመሰገነ ይሁን ብለን ተውነው።

በከንቱ ይጫነን የነበረውን ይህን ሰው የራሱ ችግር ሲያስጨንቀው ነበር(ምሳ 5፣22)። በተጨነቀም መጠን እኛን ያስጨንቅ ነበር። ነገሩ *ንጉሥ አካዝ በተጨነቀ ጊዜ እግዚአብሔርን መበደል አበዛ* የሚለውን ይመስላል(2 ዜና 28:22)። እኛ ደግሞ እንደ ቃሉ ለአስተዳዳሪው መፈታትና በእውነት እርነት እንዲወጣ ጸልየናል። ይህን ሰው፣ እኛ የከሰስነው መስለው እንጂ ከሳሹስ የገዛ ወዳጁ ነበር። እርሱም በወቅቱ የእስረኞች የኅብረት ሱቅ ዕቃ አቅራቢ የነበረ እስረኛ ነበር። ተከሳሹም ብዙ ጊዜ በጭንቅ ካሳለፈ በኋላ ጉዳዩ ቀዘቀዘለት። ቢሆንም በእኛ ላይ የነበረው በጎ ያልሆነ ዝንባሌ አልተለወጠም።

በ23/12/77 ከአለታ ወንዶ አግዳቸው አኔቦ፣ አበባየሁ ዘውዴ፣ተስፋ በራሣና አስናቀች ገብሩ የተባሉ ክርስቲያን እስረኞች በእምነታቸው ምክንያት እያንዳንዳቸው የ3 ወር እስርና የ300 ብር ቅጣት ተወስኖባቸው እኛ ወዳለንበት ማረሚያ ቤት ገቡ። የፈረደባቸው የአለታ ወንዶ ቀበሌ ነበር።

እነርሱ ከመጡ በኋላ ከእኛ ጋር እንዳይገናኙ ማስጠንቀቂያና ማስፈራሪያ ከመቶ አለቃው ተሰጥቷቸው ነበር። ከዘመዶቻቸው ጋር እንዳይገናኙ ለማድረግ ተሞከረ። ሆኖም ከጥቂት የውዝግብ ቀናት በኋላ ከዘመድ እንዲገናኙ ተፈቀደላቸው። ሁኔታውም ሁሉ እየቀለለ መጣ። በመጨረሻም የእስር ቅጣታቸውን ሁሉ ፈጽመው፣ የቅጣት ገንዘቡንም በሙሉ ከፍለው፣ ህዳር 4 ቀን 1978 ዓ.ም በእምነታቸው እንደ ጸኑ ተፈቱ።

> ***ኃጥእ ማንም ሳያሳድደው ይሸሻል፤ ጻድቅ ግን እንደ አንበሳ ያለ ፍርሃት ይኖራል።***

*ሰውን ዓመፃ አያጸናውም፤ የጻድቃን ሥር ግን አይንቀሳቀስም።(ምሳ 28:1፤12:3)*

## <u>የመዝጊያው መነቃነቅ</u>

ይርጋ ዓለም ማረሚያ ቤት በገባንበት ዓመት ከዘፍጥ 45:6 ላይ ***ይህ ሁለቱ ዓመት በምድር ላይ ራብ የሆነበት ነውና፤ የማይታረስበትና የማይታጨድበት አምስት ዓመት ገና ቀረ*** የሚለው ቃል ትኩረቱን ስቦት ***እንዳለፈ*** አስታውሳለሁ። የእነኚህ ዓመታት ድምሩ ሰባት ነው። በተመሳሳይ መልኩ ልንፈታ ጥቂት ቀናት ቀርተው ሳሉ በ2ዜና 23:1 ***‹‹በሰባተኛውም ዓመት ዮዳሄ በረታ››*** የሚለው ቃል በልዩ ሁኔታ ወደ ልቤ ገብቶ ነበረ። ዮዳሄ የበረታው ከአደገኛዋና ከሕገ ወጥዋ ንግሥት ከጎቶልያ ተሸሽጎ የቆየውን ኢዮአስን ለሕጋዊው ንግሥና በማብቃት የይሁዳን ነገሥታት ታሪክ ለመለወጥ ነበር። በተሰፋ ቃሉ ብቻ ሳይሆን በተግባርም ብርቱ የሆነው ጌታችን፤ ንቅናቄና ነውጥ አስነስቶ የእኛንም ታሪክ ለመለወጥ፣ ሰባተኛውን ዓመት ሊጠቀምበት ነው!! ዛሬ ስለዚህ ሁሉ እግዚአብሔርን እያከበርኩ አስታውሳለሁ።

1978 ዓ/ም ፣ሰባት ዓመታት ያህል ከወገኖቻችን ተለይተን እንድንቆይ የተዘጋብንን፤ እግዚአብሔር የናሱን ደጅ፤ መዝጊያውን በጽኑ አነቃንቆ የሰባበረበትና የብረቱን መወርወሪያ የቆረጠበት ዓመት ነው። ዓመቱ የመንብኝታችንና የመፈታታችንም ተስፋ ይበልጥ ብሩህ የሆነበት ሲሆን ተስፋው መታየት የጀመረው በ1977 ዓ/ም ኢጋማሽ ገደማ ነበር።

ከዘመድ እንዳንገናኝ ተከልክለን ባለንበት በዚያ ወቅት፣በ1977 ዓ/ም ኢጋማሽ ላይ፤ አንድ የማናውቀውና ስሙን ገ/ሚካኤል ነኝ ብሎ ያስተዋወቀን ሰው፣ እግዚአብሔር ልኮት እንደ መጣ የሚገልጽና *ሐና ሳሙኤልን ያቆየችው ጡት እስኪተው ድረስ እንደ ነበረ ሁሉ፣ እናንተንም እግዚአብሔር ያቆያችሁ ጡት እስክትተው (እስክትጸኑ) ብቻ እንደ ሆነ እንጂ በቅርብ ጊዜ ውስጥ እንደሚገበኛችሁ ነግሮኝ ይህንኑ ልነግራችሁ መጣሁ የምትል ጽሑፍ በእርሳስ ጽፎ በተላላኪ እጅ ላከልን። በዚህ የጀመረ መልእክት እስከ ተፈታንበት ጊዜ ድረስ ቀጥሎ ቆየ ።*

*እስናቀች ገብሩም በተፈታች ጊዜ በተወችልን መልእክት መጨረሻ ላይ ዳንኤል የኢየሩሳሌም መፍረስ የሚፈፀምበትን ዘመን በቃሉ አስተውሎ እንደ ጸለየ፣ዳን 9:1-27ን ለእናንተ ትቼአለሁ ያለችንም* የሚረሳ አይደለም። ይህን የጻፈችልን ህዳር 1 ቀን 1978 ዓ.ም ልትፈታ 3 ቀን ሲቀራት ነበር። ህዳር 4 ፣ እነርሱ በተፈቱበት ቀን፣ ዕለቱ ረቡዕ ሲሆን ሳምንታዊው የጾምና የጸሎታችን ቀን ነበር። ጠዋት ላይ ስንሰናበታቸው አበባየሁ ዘውዱና አግዳቸው አኔቦ በእንባ ነበር የተለዩን።





የመጣ ሁሉ እኛን ከኋላ እየተወ ሲወጣ ቅሬታ ተሰምቷቸው እንደሁ በማለት አብረውኝ የታሠሩትን ወንድሞች ፊት ስመለከት የሁሉም ፊት ብሩህ ነበረ።

ከዚያም ተመልሰን ስንጸልይ ዋልን ። እኔ ደግሞ፤ በተለይ ከሰዓት በኋላ፣ ልቤ በታላቅ ደስታ ስለተሞላ የምሆነውን አጣሁ፣። በጸሎት መቀጠል አልቻልኩም። ተነሥቼ አንዳንድ ነገር ልጽፍ ብሞክር፣ ደስታው አላሠራህ አለኝ። ፓ/ተሾመን፦ እስቲ ወንድሞችን ሰብስበን የምስጋና ጊዜ ይኑረን አልኩት። እምቢ አላለኝም። ተስማማ። በየፊናችን ወንድሞችን ልንጠራ ወጣን ። ጊዜው አሥር ሰዓት ገደማ ነበር።ተመልሰን ወደ የክፍላችን ስንመጣ፣ብርሃኑ ላንቃሞ የሚባል እስረኛ ቢሮ ትፈለጋላችሁ አለን። ሁላችንም ወደ ማረሚያ ቤቱ ጽ/ቤት ሄድን። ከዚያ በኋላ የአውራጃው ባለ ሥልጣኖች ማለትም የኢሠፓ - የኢትዮጵያ ሠርቶ አደሮች ፓርቲ - ጽ/ቤት አባላት፣ የአውራጃው አስተዳዳሪዎች፣ የህዝብ ደኅንነት ሃላፊ፣ ከነበርንበት ድረስ መጥተው አነጋገሩን።

ወሳኝ የሆነው ንቅናቄ ተጀመረ ማለት ነው። ባለ ሥልጣኖቹ፣ መቼ እንደ ታሰርን፣ለምን እንደ ታሰርንና ምን ይደረግልን ዘንድ እንደምንፈልግ እየጠየቁን ቃላችንን ጻፉት። ጥያቄዎቹን ይጠይቁን የነበሩት አዲስ የተሾሙት የአውራጃው ኢሠፓ ኮሚቴ ጸሐፊ ጓድ አምባቸው እንደ ነበሩ በኋላ ሰማን። አጠያየቃቸው ክፋት ያዘለ ሳይሆን መፍትሔ የሚሻ ዓይነት መስሎ ታይቶናል። በመጀመሪያው ዙር ፦ ሰሎሞን ሃጢያን፣ ሰገሠ ዲኬን፣ታፈሰ ቦኤን፣ኃይሉ በቀለንና ማርቆስ ተፈራን አነጋገሩ።

በሁለተኛው ዙር፣ ሺመልስ ለማን፣ጌታሁን አጋፋሪን፣ ተስፋዬ ቃሚሶን፣ ሰዩም ካዩሶን፣ በራሣ ባንቡሮንና እኔን አነጋገሩና፦ ከበደ አርጋው፣ ከበደ ሣሣሞ፣ ተሾመ ወርቁና አዳነ አለማየሁ ሲቀሩ ጊዜው በጣም ስለ መሸ ትተው ሄዱ። እነርሱም ሊፈቱን እንዳልመጡና ለሚፈታው ክፍል ሃሳብ እንደሚያቀርቡ ጠቁመው ሃሳባችንን - አቋማችንን - እስከዚያው ድረስ እናሻሽል እንደሆነ ለመቶ አሰቃው እንድንነግር አሳስበውን ነበር የሄዱት። ***ምን እንዲደረግላችሁ ትፈልጋላችሁ*** ለተባለው ተደጋጋሚ ጥያቄ የመለስነው መልስ ፦ ***የሚቻል ከሆነ ብንፈታ ደስ ይለናል*** የሚል ነበር።

ንቅናቄው ቀጠለ። ከ6 ቀን በኋላ ደግሞ በ10/3/78 አዲሱ የክፍለ ሀገር ማረሚያ ቤቶች ዋና አስተዳዳሪ ወደ ይርጋ ዓለም ማረሚያ ቤት መጡ። በዚሁ ዕለት እኔ፣ ወደ ክፍለ ሀገር አስተዳደር እንድቀርብ መፈለጌ ተነገረኝና ከአስተዳዳሪው፣ ከኮሌኔል ዘገየ በርሄ ጋር ወደ ሀዋሳ ማረሚያ ቤት ሄጀ እዚያው አደርኩ። በማግሥቱም በ11/3/78 ወደ ክ/ሃገሩ ዋና አስተዳዳሪ ቢሮ

አቀረቡኝ። አስተዳዳሪው ከአንድ ሌላ ግለሰብ ጋር በቢሯአቸው ተቀምጠዋል። እኔም እጅ ነስቼ በሩ አካባቢ ቆምሁ። ከዚያም ቃለ ምልልስ ተደረገልኝ። ከመጠይቆቹና ከመልሶቹ መካከል የሚከተሉት ይገኛሉ።

- *አንተ ሰውዬ አሁንም አልተሻለህም?*
- *እንዴት ?*
- *አሁንም አልተሰወጥክም?*
- *እንደዚያው ነው።*
- *ና ወደዚህ!*
- *ቀረብ ብዬ ቆምኩ።*
- *ማነው ያሠረህ? ሰምዖን ጋሎሬ ነው?*
- *አይደለም፤ የሲዳማ አውራጃ አስተዳዳሪ የነበሩት ናቸው።*
- *ከታሠርክ ስንት ጊዜ ሆነህ?*
- *ሰባተኛዬን ይዤያለሁ።*
- *አሁን ምን ትጠብቃለህ?*
- *እናንተ የምትወስኑትን።*
- *ከቦረና አንተ ብቻ ነህ የመጣኸው ወይስ ሁላችሁም መጥታችኋል?*
- *ሁላችንም መጥተናል።*
- *ይርጋ ዓለም ናቸው?*
- *አዎን።*
- *ከአንተ ጋር የታሠሩ ሴቶች አሉ?*
- *አዎን።*
- *ገንዘባችሁን መለሱላችሁ? (ቦረና ሳለን የተወሰደውን ማለታቸው ነበር።)*
- *አዎን።*
- *ያኔ በጥፊ የመታሁህ አንተ ነህ?*
- *አይደለሁም፣ ሌላ ነው።*
  *ይገርምሃል ያኔ እርሱን የመታሁበት እጅ እስካሁን ያመኛል ታውቃለህ!-አሉ፣ አጠገባቸው ተቀምጦ ወደ ነበረው ሰው እጃቸውን እያሳዩ።*
- *ብሔረሰብህ ምንድንው?*
- *ሲዳማ።*
- *አንተ አሁን ሲዳማ ነህ? እንዴት ሲዳማ ትሆናለህ? ሊ.ሊ ዘመድ የለህም?*
- *ከእኔ ብሔረሰብ የሆነ?*
- *አዎን።*
- *ሊኖረኝ ይችላል።*
- *የት ነው የተወለድከው ?*





- *ሲዳማ።*
- *ቀይ ሽብር ምንድነው?*
- *ያኔ በኢሕአፓ ጊዜ የተካሄደው ነው...*
- *እናንተም እንደዚያው እንደ ኢሕአፓ ናችሁ እኮ !*
- *በዚህ አባባል እንደማልስማማ ገለጽሁ።*
- ዋናው አስተዳዳሪ ከመደርደሪያው ላይ አንድ መፅሐፍ ቅዱስ አምጥተው ሰጡኝና *አስቲ መፈክር አታሰማ የሚለውን ክፈትና አሳየኝ* አሉ።

1ኛ ሳሙኤል 17፡41- 45 ያለውን ከፈትሁና ሰጠሁዋቸው። ትንሽ ለማንበብ ሞከሩና እኔኑ *ለንብብ* አሉኝ። ማንበብ ጀመርኩና፣ ዳር ሳላደርስ ስላቋረጡኝ፣ ጎልያድ ዳዊትን እየረገመው ሊገድለው ሲመጣ፤ ዳዊት ግን ወደ ጎልያድ ሊገድለው ሲሄድ፣ እየተራገመ ሳይሆን የአምላኩን የእግዚአብሔርን ስም እየጠራ እንደ ነበረ አስረዳሁ። ለተጠየቀው ጥያቄ ቀጥተኛ ምላሽ ባይሆንም እንደ መርሕ የወሰድሁትን ማሳየቴ ነበር።

- *ሃይማኖትህ ምንድነው?*
- *በክርስቶስ የማምን ክርስቲያን ነኝ።*
- *አትጣመም፤ የትኛው ክርስቲያን ነህ?*
- *ፕሮቴስታንት።*
- *ከፕሮቴስታንት የትኛው ነው?*
- *የሙሉ ወንጌል አማኝ።*
- *ይሁንና አሁን ብትፈታ የት ነው የምትሄደው? ትፈታለህ ማለት ላይሆን ይችላል።*
- *ወደ ቤተሰቦቼ።*

ለዓመታት ያለ ፍርድ በመታሠራቸው የተማረሩ ስለሆኑ ከለቀቅናቸው በኋላ የት ይገቡ? ምንስ ያመጡብን ይሆን? የሚለው ጥያቄ ትንሽ ሳያሳስባቸው እንዳልቀረ ሲወራ ሰምተናል። በመጨረሻ ያጀበኝን ወታደር፡- *ይዘኸው ሂድ መመሪያውን ኋላ እልክልሃለሁ* ብለውት ወጣን። በዚያው ዕለት ወደ ይርጋ ዓለም ተመለስኩ። ከማረሚያ ቤቱ እስከ መኪና ተራው ድረስ በእግር፣ በጠራራ ፀሐይ፣ በሁለቱም እጂ እቃዬን አንጠልጥዬ፣ በብዙ ድካም መጣሁ።

በ13/3/78 የስም ዝርዝራችንንና የታሠርንበትን ጊዜ የሚጠይቅ ደብዳቤ ከክ/ሀገሩ ማረሚያ ቤት ወደ ይርጋዓለም ማረሚያ ቤት መምጣቱን ሰማን።

በ30/3/78 የክፍለ ሀገሩ አስተዳዳሪ ስልክ ደውለው እዚህ ስለመኖራችን መጠየቃቸውን ሰማን። ከስልኩ መደወል አስቀድሞ የስማችንን ዝርዝር፣ ማን እንዳሰረንና የፀባያችንን ሁኔታ፣ እንዲሁም መቼ እንደታሰርን የሚጠይቅ ደብዳቤ ከእርሳቸው ተልኮ፣ መልስም ተሰጥቶበት እንደ ነበረ ተነግሮናል።

በ14/4/78 የክፍለ ሀገሩ የሕዝብ ደህንነት ኃላፊ ከሌሎች ሁለት ሰዎች ጋር መጥተው ከመካከላችን ክበደ አርጋውን ጠርተው የተለመዱትን ጥያቄዎች ጠይቀውት የተለመደውን መልስ ሰጣቸው። በመጨረሻ፡- *ሂድ እሺ ... እዚሁ ትበሰብሳለህ* ብለውት *ሄዱ። የእናንተ ሃላፊዎች መሬክር እያሰሙ እናንተ እዚህ ታች ያላችሁት እምቢ ማለታችሁ ብቻ ነው የማይገባኝ ብለውትም ነበር።*

በ17/4/78 ክክፍለ ሀገሩ የሕዝብ ደኅንነት ጽ/ቤት ስለ እያንዳንዳችን ፀባይ የሚጠይቅ አስቸኳይ ደብዳቤ መምጣቱን ሰማን። አዝጋሚ ቢመስልም፣ የባለ ሥልጣኖቹ እንቅስቃሴ አልተቋረጠም። በ5 ሰዓት ተኩል ገደማ የክ/ሀ/ዋና አስተዳዳሪ ወደ አውራጃው ወደ ይርጋ ዓለም ማረሚያ ቤት መጡ። የመጡት የክፍለ ሀገሩን ፊናንስ ፖሊስ አዛዥ የተባሉትን፣ የአውራጃውን ፖሊስ ዋና አዛዥ፣ የአውራጃውን የህዝብ ደህንነት ኃላፊ፣ የአውራጃውን ምክትል ዋና አስተዳዳሪ ጓድ ዘገየ ሌሊሶን፣ የአውራጃውን ማረሚያ ቤት አዛዥ አስከትለው ነበር። የአውራጃው ዋና አስተዳዳሪም ዘግይተው ደርሰዋል። አሁንም ተጠራንና ተጠየቅን። ሁኔታው በከፊል የሚከተለውን የመስል ነበር።

- *እዚህ ከገባችሁ ስንት ሰው መለመላችሁ?* ስንት ሰው ወደ ክርስቶስ *መለሳችሁ ማለታቸው?* ነበር።
- *ወደ ፊትስ ብትወጡ ትሰብካላችሁ?* የሚሉ ዋና ጥያቄዎች ሆነው ቀረቡ የሁላችንም መልስ በአጠቃላይ ፡-
- *እያንዳንዱ እስረኛ እዚህ ሲገባ ወንጀሉን ያወራና ‹አንተስ በምን ታሠርክ› ብሎ ሲጠይቀን ከእስረኛ የምንግባባበት ሌላ ቋንቋ የለንምና እምነ፣ ስለ ክርስቶስ መስክረናል። ወደ ፊትም ቢሆን እንመሰክራለን የሚል ነበር።* ይህችን ምላሽ የሰጠው በተለይ ወንድማችን ኃይሉ ነበረ።
- በመጀመሪያ ላይ ሺመልስ ለማ በተጠየቀው ተመሳሳይ ጥያቄ ላይ *የወደ ፊቱ ከተፈታሁ በኋላ ይታያል* በማለቱ ምክንያት ወዲያው በእግር ብረት እንዲታሰር ተደረገ። ዋናው አስተዳዳሪ፡- *አሁኑኑ አውጥታችሁ እግሩን በእግር ብረት እሰሩት። መታሰሩን በዓይኔ ላይ እፈልጋለሁ* ስላሉ።
- ሺመልስ ለመታሰር ክወጣ በኋላ የቀረነው ድፍረት አገኘን።
- *ማርቆስ ገና ለገና እፈታለሁ ብዬ አልዋሽም። ለክርስቶስ ተሸንፌያለሁ። እመሰክራለሁ* አለ።
- *ፓ/ር ተሾመ ክርስቶስን ማምለክ የጀመርሁት ዛሬ ሳይሆን ገና አብዮት ሳይመጣ በፊት ነበር። አሁንም አመልከዋለሁ። ወድቁም አስግድለታለሁ። እንኳን ሌላ ቀርቶ እዚህ ያላችሁት እናንተ ጌታን ብትቀበሉ ደስ ይለኛል* ሲል ሁሉም ክት፣ ክት፣ ክት ብለው በጣም ሳቁ።





- *እስቲ የሚያሳምን ቃል ከመጽሐፍ ቅዱስ ንገረኝ* አሉ።
- *በእውነት ከፈለጋችሁት እነግራችሁኋለሁ።*
- *እንፈልጋለን* አሉ።
- *በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዷል።*
- *‹‹ወዷል›› ሳይሆን ‹‹ሰውጧል›› ነው የሚለው* አሉ።
- *‹‹አይደለም ወዷል ይላል።››*
- *የት ነው እንደዚህ የሚለው? እስቲ መጽሐፍ ቅዱስ አምጡ። መጽሐፍ ቅዱስ አላችሁ አይደል?*
  ዝም አልን።
- *እኔ እዚህ ‹ሊ አይዲ አለኝ።› አዲስ ኪዳን እንዳላችሁ አውቃለሁ።*
- *እኔ አውቃለሁ። እናንተ ውሸታሞች ናችሁ።* በዚህ መኻል ወታደሮች ክቢሮ አንድ መጽሐፍ ቅዱስ አመጡና ሰጧቸው ።
- *የት ነው እንደዚያ የሚለው?*
- *በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 3 ቁጥር 16።*
- ጥቅሱን ማውጣት ሲቸግራቸው ቀደም ሲል የክርስትና ዕውቀቱ የነበራቸው የሲዳማ አውራጃ ምክትል አስተዳዳሪ አቶ ዘገየ ሌሊሶ ተቀበሏቸውና አውጥተው በትክክል አነበቡ። ቀስ ብለውም *ሸምድዷታል* አሉ።
- *ተስፋዬ፣ እነዚያ ካሴቶች የት አሉ?* *‹You know, he is the toughest of all!›* *አሉ ወደ ም/አስተዳዳሪው ዞረው። ከሁሉም የሚጠነክረው እርሱ እንደሆነ ታውቃለህ ሊሉት የፈለጉ መሰለኝ።*
- *በታሠርኩ ጊዜ በእጄ የነበረውን ፖሊሶች ወስደውታል።*
- *ምን ብለህ ነው የዘመርከው ?*
- *የምስጋና መዝሙሮችን ነው የዘመርኩት።*
- *እስቲ ከዘመርካቸው መዝሙሮች አንዱን ቀስ ብለህ እስረኞች ሳይሰሙ ዘምርልኝ።*
- *ላመስግንህ ዛሬም የእኔ ጌታ፣ ስለማይነገር ሥጦታህ፣ ስለማይቆጠር ውለታህ፣ በእውነት አንተ ታማኝ ነህ፣ ዘላለም ይወደስ ይክበር ታላቅ ስምህ።* እንዳልኩ አቋረጡኝና
- *አመሰግናለሁ ይበቃል* አሉ።
- *አሁን ስትወጣ ለኪነት አትዘምርም ?*
- *የእግዚአብሔር ቃል ለሁለት ጌቶች መገዛት የሚቻለው ማንም የለም ይላል።*
- ክት፣ ክት፣ ክት ብለው አሁንም በጣም ሳቁና *‹‹ይኼኮ የባሪያና የጌታ ነገር አይደለም››* አሉ።

- ሚስት አለህ?
- የለኝም::
- እጮኛ የለህም? እንዳለህ እኔ አውቃለሁ!
- በእግዚአብሔር ፊት እውነት እናገራለሁ፣ የለኝም::
- እጮኛም፣ ሚስትም ሆነ ልጅ የለኝም::
- በቃ ተው፣ እንደሌለህ እኔም አውቃለሁ::
- ያን ጊዜ (በ1976 መስከረም) በጥፊ የመታሁት ማነው?
- ሰገሠ ዲኬ እኔ ነኝ አለ::
- ለምን እንደ መታሁህ ታውቃለህ?
- አላውቅም::
- ያን ጊዜ ልክ አልነበርኩም፣ አንተ ነህ ያሳሳትከኝ::
- ገንዘባችሁን መለሱላችሁ?
- አዎን::
- ምንም የጠፋባችሁ ነገር የለም?
- አንድ ሸርጥና አንድ የእንግሊዝኛ መዝገበ ቃላት ጠፍተውብናል:: እነዚህ የተስፋዬ ቃሚሶና የሺመልስ ለማ ዕቃዎች ነበሩ::
- ወደ መቶ አለቃው ዞሬው - በአስቸኳይ ጽፈህ ጠይቅና ውጤቱን ግለጽልኝ:: ችግር ከገጠመህ ደውልልኝ:: ይኼ ሌብነት ነው:: ሰውን ማሰር ሌላ፣ ንብረቱን መዝረፍ ሌላ ነው::
- ከአንተ ጋር የታሠሩ ሴቶች የሉም ?
- አሉ ::
- የት ናቸው ?
- አዋሣ::
- ለምን ሄዱ ?
- በዚያን ጊዜ እኔ እዚህ አልነበርኩም፣ አለ የመቶ አለቃው::
- በእስር ቤት ሳለህ የደረሰብህ ነገር አለ ? በማለት ፓ/ር ተሾመን ጠየቁ::
- እርሱም ከቀበሌ ጀምሮ የደረሰበትን ከወገብ በላይ እራቁት ሆኖ በዶቢ ላይ መንከባለሉን፣ ሁለት ሙሉ ሌሊቶች በብርድ ላይ ውጭ ማደሩን፣ አሁንም ከበረና ከተመለስን በኋላ ከዘመድ እንዳንገናኝ ተደርገን መቆየታችንንና ለለዚህም ሁኔታ ስንጠይቅ የከለከሉት የክፍለ ሀገሩ አስተዳዳሪ መሆናቸው እንደ ተነገረን ገለጸ::
- መቶ አለቃ ይህ ነገር እንዴት ነው ?
- ከክፍለ ሀገሩ ወህኒ ቤት 1975 ክረምት ማብቂያ ላይ የተጻፈ ደብዳቤ አሳያቸውና መሸሪያው ስላልመጣልን ነው አለ::
- እኔ አላዘዝኩም:: ያደረጋችሁት ግን ትክክል ነው::
- አሁን እግዚአብሔር ያወጣናል ነው የምትሉት?





- አዎን::
- እንዴት አድርጎ?
- ፓስተር ተሾመ :- የእግዚአብሔር ቃል ‹የናሱን ደጆች ይሰብራል:: ብረቱን መወርወሪያ ይቆርጣል› ይላል አለ::
- የወህኒ ቤቱን አጥር ሰብሮ ያወጣችኋል?
- አይደለም::
- ታዲያ የእኛን ልብ ሰብሮ ነው የሚያወጣችሁ?
- አዎ፣ ቃሉ ‹የንጉሥ ልብ እንደ ውኃ ፈሳሾች በእግዚአብሔር እጅ ነው፣ ወደ ወደ ደውም ያዘነብለዋል› ስለሚል እግዚአብሔር የእናንተን ልብ አራርቶና ለእኛ እንድታዝኑ አድርጎ ሊያወጣን ይችላል::
- አሁን ምን ትምህርት ትሰጡናላችሁ? ተስፋዬ!
- ስለምን ?
- ስለዚህ ስለምናካሂደው ሁኔታ::
- እንደገባኝ ከሆነ ስለ እስራታችን ሁኔታ ነው::
- ራሳቸውን በመነቅነቅ አዎን አሉ ::
- ስለ ራሳችን እስራት ከሆነ ቅሬታ በማንም ላይ የለንም:: ለዚህም ማስረጃው ከታሠርንበት ጊዜ አንስቶ እስከ ዛሬ ድረስ ወደ እርስዎም ሆነ ወደ ማንም የላክነው አቤቱታ አለመኖሩ ነው:: አልከሰስናችሁም ማለቴ ነበር:: እምነታችን መታሠር ብቻ ሳይሆን መሞትም እንዳለ ስለሚያስተምረን እስራታችንን የምናየው ከእምነታችን አንፃር ነው::
- አሁን ከወጣህ ትሰብካለህ?
- ነፍሴ ከሥጋዬ እስክትለይ ድረስ ስለ ክርስቶስ አዳኝነት መመስከሬን አዎን አልተውም::
- እሺ እንግዲህ ወንድሞቼ፣ ልጆቼ፣ አገራችንን እማማ ኢትዮጵያን አስቡአት:: እናንተን ለማሠር የሚፈልግ ማንም የለም::' ዛሬ የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ መብት እንዲከበር የሚያደርግ መመሪያ ከአብዮታዊ መሪያችን ከጓድ ሊቀ መንበር ቢሮ በየቀኑ ይደርሰናል:: እንግዲህ እስከ መቼ ድረስ ጴንጤ፣ ጂሆቫ እየተባባልን ሆድና ጀርባ ሆነን እንኖራለን? እጅ ለእጅ ተያይዘን ይህችን ኢትዮጵያችንን መገንባት አለብን:: ውሳኔአችሁን በቅርብ ጊዜ ከአውራጃው ዋና አስተዳዳሪ ትሰማላችሁ አሉንና ሄዱ::

በዚህ ቃለ ምልልስ ወቅት ማጎደራችን እንዲቀርብ ተደርጎ የክ/ሀገሩ ዋና አስተዳዳሪ ከታሰርንበት ጊዜ አንስቶ እስከዚያች ቀን ድረስ በማረሚያ ቤቱ ስለ እኛ የተጻፈውን አልፎ አልፎ በእኛ ጆሮ እንሰማው ነበር:: እኛ ሳናውቅ የተጻፈብንን ክፉ ነገር ሁሉ እንድናውቀው ጌታ አደረገ ማለት ነው:: አጻጻፉ የክ/ሀገሩን ዋና አስተዳዳሪ አስቆጥቶ የመጡበትን ዓላማ እንዲለውጡ ሊያደርግ

እንኳ የሚችል ነበር። እርሳቸው ግን ሁሉንም አይተው ተውት። ጌታ ግን ከስንት ክፉ ዕቅድ ጠብቆ እንዳኖረን በዚያን ዕለት ተገነዘብን።

በ11/6/78 በስድስት ሰዓት አካባቢ ወደ ማረሚያ ቤቱ ቢሮ ተጠራን። ለነገ 8 ሰዓት ዘመዶቻችሁ ወደ አውራጃው አስተዳደር እንዲመጡ ልካችሁ አስጠሯቸው በማለት የመቶ አለቃው ነገረን። ለመላክ እንድትችሉ ለዛሬ ራሳችሁ እየቀረባችሁ የሚመጣላችሁን ሰው እንድታነጋግሩ ፈቅደንላችኋል አለን። እኛም ከሰዓት በኋላ ወደ ጥሪ ቦታ እየሄድን ዘመዶቻችንን ልናነጋግር ቻልን።

በ12/6/78 የአምስት ሰው ዘመዶች ሲቀሩ የብዙዎቻችን ዘመዶች መጡ፤ እንደ ተባለውም በ8 ሰዓት ወደ አውራጃው አስተዳደር ቀረቡ። አስተዳዳሪውም *ልጆቻችሁን እንፈታላችኋለን ነገር ግን ምክሯቸው* እንዳሉአቸው ተመልሰው ነገሩን። የአውራጃውም አስተዳዳሪ ከክፍለ ሀገር ደብዳቤ በመጠባበቅ ላይ እንዳሉና ደብዳቤው ከደረሳቸው እስከ ቅዳሜ ድረስ ወይም እስከ ዛሬ ሳምንት እንደሚፈቱን ገልጸዋል ተባለ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ከዘመድ መገናኘት ተፈቅዶልን ሳለ በ14/6/78 ግን የዕለቱ ዘብ ኃላፊ ከዘመድ እንዳንገናኝ ከለከለን። በኋላም፣ የክልከላው ፕሮግራም ለአንድ ቀን ብቻ ነበር፣ አበቃ አለን። በ15/6/78 የዕለቱ ዘብ ኃላፊ ሳይከለክለን ስንገናኝ ዋልን። ስንጠይቀውም መገናኘቱ የዘለቄታ እንደሚሆን የመቶ አለቃውን ጠይቄ አረጋግጦልኛል አለን። የተዘጋብን ደጅ ‹‹መዝጊያው›› አረፍ እያለም ቢሆን ከፍ ብሎ በተመለከተው መልክ በኃይል መነቃነቁ ቀጠለ ።

## <u>የመጨረሻው ዝምታ</u>

*ከእሳቱም በኋላ የዝምታ ድምጽ ሆነ። ኤልያስም ያን በሰማ ጊዜ ፊቱን በመጎናፀፊያ ሸፈነ* (1ነገሥ19 12:13)።

ሳንፈታ ሳምንቱ አለፈ። የካቲትም ገባ። እርሱም አልቆ መጋቢት መጣ። ሚያዝያም ገባ። ሚያዝያም አለፈ። ሁኔታው ሁሉ ቀዘቀዘ። ወሬውንም የሚያነሣ ጠፋ። ‹‹ሁሉም ነገር›› ተመልሶ ጸጥ፣ ዝም አለ። በዚህ መሐል እምነታችን ተፈተነ። በእነዚህ ወራት ውስጥ አዘውትሬ የዕለት ሁኔታዎቻችንን ለመመዝገብ ሞክሬአለሁ። ከእነዚያ መካከል ጥቂቶቹን ልጥቀስ፡-
በ23/6/78 በማታ ፕሮግራማችን ለ4 ወንድሞቼ ያካፈልኩት ቃል፡-- *የመንግሥትን ቃል ሰምቶ በማያስተውል ሕዝብ ላይ ክፉው ይመጣል... በመልካም መሬት የተዘራውም ይህ ቃሉን የሚያስተውል ነው። ማቴ 13፤18:23 ማስተዋል ፍሬያማ ያደርጋል። በዚህ ምሽት ቃሉን ለማካፈል ቀሎኝ ነበር። የምለው ነገር ያለ ችግር መጣልኝ ማለቴ ነው።*





በ21/7/78 የማታ ፕሮግራማችን ላይ ኃይሉ ስለ ማስተዋል ተናገረ *እናንተ የማታስተውሉ ... ልባችሁ ከማመን የዘገየ... መስማት በሚችሉበት መጠን ... ነግሯቸው ነበር... ይህን ሁሉ አስተዋላችሁን? ይላቸው ነበር። ይህ በደረሰ ጊዜ እኔ እንደ ነገርኋችሁ ታስቡ ዘንድ ... በማለት።*

28/7/78 እሁድ ማታ በራሣ ከሕዝቅኤል 36:8
*እናንተ ግን ቅርንጫፎቻችሁን ታቆጠቁጣላችሁ። ይመጡም ዘንድ ቀርበዋልና ለሕዝቤ ለእስራኤል ፍሬአችሁን ትሰጣላችሁ። ቀድሞም ካደረግሁላችሁ ይልቅ መልካም አደርግላችኋለሁ።* የሚለውን አካፈለን።

26-8-78 *እግዚአብሔር እንደሚያውቀው ሳላሰባችሁ፣ ልቤና አእምሮዬ ወዳላችሁበት ሥፍራ ሳይሻገሩ ውለው አድረው አያውቁም። ጌታ በእናንተ ስላደረገው የነፃነት ሥራና ምስክርነት ጸጋውንም እትረፍርፎ ስላበዛላችሁ፣ እያስታወስኋችሁ ዘወትር አባታችንን አመሰግነዋለሁ። አሁንም ክብር ለአብ፣ለወልድ፣ለመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ይሁን። ....ጌታ እንዳከበራችሁት አክብሯችኋል። እዚህ - አሜሪካ ማለት ነው - ለሥጋ ቢመችም ለመንፈሳዊ ሕይወት ግን እንቅፋት ነው። ምቾትና ድሎት ቢበዛ ሥጋ ይተኛል።*
*... መረታት የሚጀመረው በአእምሮ ወስጥ ስለ ሆነ አስተሳሰባችሁ ሁሉ በቃሉና በመንፈሱ ይጠበቅ። ለጥርጣሬ መንፈስ ሥፍራ አይኑር። ተንበርከኩ። ብዙዎች ስለ እናንተ ይንበረከካሉ። ወደፊት ለምትጽፉት የምስክርነት መጽሐፍም ተዘጋጁ።* ኢየሱስ የወደደው ደቀ መዝሙር ዮሐንስ እጅጉ(ካፕቴን)

እነኚህ ፍሬ ሃሳቦች በህዳር 20/78 የተጻፉ ቢሆኑም ልክ በሚያዚያ ወር ላይ ከደረሰን ደብዳቤ የተቀነጫጨቡ ናቸው። የእስር ቤት የመውጣት ተስፋው ሁሉ ወደ መጨለም በተመለሰበት፣ ሁሉም ነገር ዝም ባለበትና እርግጠኛ ያለመሆን በሚጫጫንበት በዚህ ወቅት ላይ ይህ መልዕክት መጣልን።

እኔም፣ ከአንድ ዓመት በፊት ጀምሮ ከሰበሰብኳቸው የእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች የተነሣ፣ በዚህኛው በ1978 ዓ/ም፣ ስለ መፈታት አዘውትሬ በድፍረት አወራሁ። ይህም ሁኔታዬ አንዳንድ ወገኖቼን ሳያሳስባቸውና ሳይከብዳቸው አልቀረም ። በዚህም ምክንያት፣ ስለ ክርስቶስ መከራን ለመታገሥ የነበራቸውን ጽናት፣ ንግግሬ እንዳይሸረሽረው መስጋታቸውን በቃልም በጽሑፍም የገለጹልኝ ነበሩ።

እምነት ፈተናው ቀላል አይደለም። በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን መፈታታችንን በተመለከተ፣ ልቤን ወደ ማመን ይስበው የነበረ እግዚአብሔር ነውና አመንሁ፤ ስለዚህም ተናገርሁ። ዝም ለማለት አልቻልሁም። ታህሣሥ 3 ቀን 1978 ዓ.ም የሚከተለውን ነገር በማስታወሻዬ ላይ አስፍሬያለሁ:-

- የመባረክ (የመጽናናት) ስሜት አልተሰማኝም።
- ለመዘመር ስሞክርም አልተነቃቃሁም።
- ጠዋት ከታፈስ በኋ ጋር መንፈሳዊ ነገሮችን ስለ አገልግሎት ጥቂት ተነጋግሬያለሁ ...
- ሌላ ብዙ ነገር አልሠራሁም።
- ምንም ነገር ለመሥራት አልቻልኩም፣ ለሞከርም አቋርጬ ስነሳ ነበር።
- አእምሮዬ ባዶ ነበር።
- እግዚአብሔር በዚህ ሁኔታ ውስጥ የሚያስተምረኝ ነገር እንዳለ እምርምር ነበር።
- ስሜትን መከተል መልካም አይደለም። አእምሮዬ ባዶ በሆነም ጊዜ እግዚአብሔር ሕያው ነው።
- አእምሮ ባዶ በሆነም ጊዜ፣ የሚታይ ነገር በሌለበትም ጊዜ በእግዚአብሔር ላይ ያለንን እምነት እናፀናለን።
- አብርሃም ተስፋ ባልሆነው ጊዜ ተስፋ ይዞ አመነ።
- ተስፋ ባልሆነው ጊዜ - በሥጋ ዓይን የሚታይ ድጋፍ ባለቀና በጠፋ ጊዜ በእምነት በረታ እንጂ ባለማመን ምክንያት በእግዚአብሔር ተስፋ ቃል አልተጠራጠረም(ሮሜ4:18)።
- እምነትም ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው(ዕብ11:1)።
- የተስፋው ፍጻሜ ዘመን የቀረበ ይመስለኛል።
- በዚህ ተስፋ ላይ እንድጸልይበት የሚያደርገኝ ግፊት በልቤ ውስጥ አለ።
- በዚህ ተስፋ ላይ መጸለይንና ማሰብን መተው አልቻልኩም።
- ጌታ የተስፋው ዘመን - መፈታታችን - መቃረቡን በማመልከት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በልዩ ልዩ መንገዶች የተናገረን መስሎኛል።
- በጊዜውም አለ ጊዜውም ልቤ ይህንን ወደ ማመን እየተሳበ ይገኛል።

በ17/9/78 ልቤ በመንፈስ ቅዱስ እየተነቃቃ ሐሴት እያደረግሁ ውዬአለሁ። ዕለቱ እሁድ እንደ መሆኑ መጠን ከዘመድ የመገናኛ ቀንም ነበር። በዚህ ዕለት ሊጎበኙን ከመጡት መሐል በጌታ ወገኖቻችን የሆኑት የወቅቱ የአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤ/ክ መሪ አገልጋዮች ነበሩ። እነርሱም የተውልን መልዕክት በጥቂቱ የሚከተለውን ይመስላል:-





- ጌታ ሰዎችን የሚጠራው በመጀመሪያ ከእርሱ ጋር ይኖሩ ዘንድ ነው። አገልግሎት ከእርሱ ጋር የመኖራችን ውጤት ነው። አሸንዳ ብቻውን ከሆነ ውኃ ሊሰጥ አይችልም። ከምንጩ ጋር ከተገናኘ ግን ውኃ ይሰጣል። የጥንት የልጅነት ጊዜ ልምምድን የሚተካ ነገር የለም። በዚህ ያላችሁ የጌታ ጸጋ ምን ያህል እንደ ሆነ የምታውቁት ውጭ ስትወጡ ነው። (ፓስተር መርዕድ ለማ)
- ሁልጊዜ በጌታ ደስ ይበላችሁ። ደግሜ እላለሁ ደስ ይበላችሁ።... በዚህ ሳላችሁ ጌታ ለወደ ፊት በእናንተ ላይ ስላለው ዓላማ ለማወቅ በጣም መፀለይ አለባችሁ። (ፓስተር ፈቃዱ ኦፍጋአ)
- የዘላለም ክንዶች ከአንተ በታች ናቸው። (አቶ ለማ ምስጋና)
- ስለ እናንተ ጌታን እናመሰግናለን። መንፈስ ቅዱስ የጸሎታችንን አቅጣጫ - ወደ ምስጋና ለውጦታል። (ስሎሞን ረጋሳ)

ዝምታው የመንግሥት ባለ ሥልጣኖች ነበር እንጂ እግዚአብሔርስ እየተናገረን ነበር። በዝምታ ድምጽ!

## ምዕራፍ አምስት - ቀንበሩን ሰበረው!

### «የታሰሩት በቁ ሆኖ»

የተናገረውን የማይረሳው አምላካችን፣ ቃሉንም የማያጥፍ የታመነው ወዳጃችን፣ የቀጠረው ቀን እስኪደርስ ዝም ያለ ቢመስልም፣ በቃል ብቻ ሳይሆን በተግባርም የሚናገርበት ጊዜ ደረሰ። ተግባሩም ተጭኖን ዓመታትን ያስቆጠረውን የእስር ቀንበር ከላያችን ላይ በይፋ መሰበር ሆነ። የሚሳነው የለምና!

በ26/9/78 ማክሰኞ የሐኪም ቀጠሮ ስለ ነበረኝ ይ/ዓለም ሆስፒታል ሄጀያለሁ። በዕለቱ ጌታሁንና ፓስተር ተሾመም የእኔው ዓይነት ቀጠሮ ነበራቸውና እዚያው አብረን ዋልን። ከሰዓት በኋላ ወደ 8 ሰዓት ገደማ ወደ ማረሚያ ቤቱ ተመለስን። በማግሥቱ፣ ማክሰኞ ዕለት ወደ ሀዋሳ ማረሚያ ቤት እንድንሄድ የስልክ ጥሪ መምጣቱንና ይኸንኑ መልዕክት ከይርጋ ዓለም ማረሚያ ቤት አስተዳዳሪ መስማታቸውን ወንድሞች ነገሩን። ማምሻውን ዕቃዎቻችንን ከትተን፣ በየክፍላችን ለሚገኙም እስረኞች አደራ ብለን አደርን።

በ27/9/78 ማለዳ በዚያ የተገኘን 15 የሃይማኖት እስረኞች በሙሉ በወታደር እርቅይሁን አጃቢነት ከንጋቱ 12:30 ከይርጋ ዓለም ማረሚያ ቤት በመነሣትና በንግድ ሊዎንቼና በመሣፈር ከጠዋቱ 3 ሰዓት ገደማ ሀዋሣ ከማረሚያ ቤቱ ደረስን።

ከሰዓት በኋላ ወደ ክፍለ ሀገሩ ማረሚያ ቤት ዋና አስተዳዳሪ ቢሮ ተጠርተን ቀረብን። በዚህ ጊዜ በሀዋሳ ማረሚያ ቤት ለሦስት ዓመት ገደማ ታሥረው የቆዩት እህቶቻችንና እኛ፣ወንድሞች ጭምር በአንድነት ቀርበናል። ከዚያም ዘመዶቻችንን ይዘን ወደ ክ/ሀገሩ አስተዳደር ቢሮ በ28/9/78 ከጠዋቱ 2:00 ሰዓት እንድንቀርብ ተነገረን። ዘመዶቻችን በአቅራቢያ እንደሌሉ ስንገልጽላቸው ያ ብዙ ችግር እንደሌለበት ተነገረን። ወደ ክ/ሀገሩ አስተዳደር ስንቀርብ በሥነ - ሥርዓት ሆነን የሚሰጠውን ትምህርት እንድንቀበል ምክር ተሰጠን። *‹‹እንደምትሉት ጊዜው የደረሰ ይመስላል››* አሉን፣ የማረሚያ ቤቱ አስተዳደሪ፣ ኮሎኔል ዘገየ በርሄ።

በ28/9/78 ከጠዋቱ 2:00 ሰዓት በኋላ ወደ ክፍለ ሀገሩ አስተዳደር ጽ/ቤት ደረስን። በቢሮውም ውስጥ የክ/ሀገሩ ዋና አስተዳደሪና የሕዝብ ደኅንነት ኃላፊው ነበሩ። ሁሉም በቅደም ተከተል አጫጭር ንግግር አደረጉ። ዋናው አስተዳዳሪ ከመደርደሪያቸው ላይ ለወርቅነሽ ይመር መጽሐፍ ቅዱስ በመስጠት ከ2 ጢሞ 2:1-2 ያለውን እንብቢ አሉአት። አነበበች። ክፍሉ :-





*አንግዲህ ልጄ ሆይ፣ አንተ በክርስቶስ ኢየሱስ ባለው ጸጋ በርታ፣ ብዙ ሰዎች የመሰከሩለትን ከእኔም የሰማኸውን ሌሎችን ደግሞ ሊያስተምሩ ለሚችሉ ለታመኑ ሰዎች አደራ ስጥ ይላል።*

ለምን እንዳስነበቧት ገረመን። ለእኛ ግን ከእስር የመለናበቻና አገልግሎት የማስቀጠያ መልእክት ሆኖልናል!! ቀጥለውም :-

*እናንተ መጽሐፍ ቅዱስን ምንም አታውቁም። ብታውቁ ኖሮ እንዲህ አትሆኑም (ይህን ያህል አትታሠሩም) ነበር። ያቺ የኢትዮጵያዊነት ወኔ ስላለቻችሁ ብቻ ነው። ...እናንተ ባትዎጉ ኢትዮጵያ በብዙ ሺ የሚቆጠር ተዋጊ ሠራዊት ለላት* አሉ - (እንዋጋም የተባለ ይመስል)።

ሌላም በኢየሱስ ስም ምንም ነገር እንዳንናገር! ‹‹መካከረውን›› የመናገር ዕድሉን ለሕዝብ ደኅንነት ኃላፊው ሰጡ። የሕዝብ ደኅንነት ኃላፊው በበኩላቸው፣ ላለመናገር ጥቂት ካመነቱ በኋላ፣


*እናንተ ብዙ ሰው አላውቅም፣ አንድ ሁለታችሁን አውቃለሁ(ወደ ፓስተር ተሾመ እያመለከቱ)። የታሰራችሁት እንታገልም ብላችሁ ነው። ጎይሉን ባለ መቀበላችሁ ነው። መታሠር ብቻ ሳይሆን ልትመቱም ትችላላችሁ። አሁን አብዮቱ ወደ አስተማማኝ ደረጃ ደርሷል። አሁን ወጥታችሁ አንዘበዘህ ብትሉት፣ ምንም ነገር ብትነግሩት፣ ሕዝቡ አይሰማችሁም። አይቀበላችሁም ። በሚሊዮናች ከሚቆጠር ከሰፊው ሕዝብ አንፃር ደግሞ እናንተ ኢምንት ስለ ሆናችሁ፣ ምንም ጉዳት ሊታደርሱ አትችሉም ተብሉ አሁን ተፈታችኋል። መልካም የሥራ ዘመን ይሁንላችሁ።* አሉን።

ከዚህ በኋላ ዋናው አስተዳዳሪ ከዛሬ ጀምሮ መፈታታችንን በመግለጽ መፈቻ ወረቀታችንን ስም ስማችንን እየጠሩ አደሉን። የእኔ ስም በመጨረሻ ነበር የተጠራው። ከተቀበልኩ በኋላ እጃቸውን ስጨብጥ የመገረም ሳቅ ስቀው *ማን ለምንድነው የጨበጥከኝ* ? አሉ። *ደስ ስላለን ነው* አልኳቸው። ክፉ የማናስብባቸው መሆናችንንም ለመግለጽ ይህን ማድረጉ መልካም መሰለኝ። የተፈታንበት ወረቀታችን ደግሞ እንዲህ ይላል:-

*ቁጥር ሲ9ህ/62/ዐሊ/ለ/*
*ግንቦት 26ቀን 1978 ዓ.ም*
*ለሚመለከተው ሁሉ*

*---------------------- የተባሉ አብዮቱ የማይፈልገውን አቅጣጫ ሲያስፋፉ በመገኘታቸው ከ22/5/72 እስከ 26/9/78 በቁጥጥር ሥር ከቆዩ በኋላ የታሰሩት በቂ ሆኖ እንዲፈቱ ስለ ተወሰነ ተለቀዋል።*

*ፊርማ (የማይነበብ)*
*የሲዳሞ ክፍለ ሀገር ዋና አስተዳዳሪ*


ቁጥር [illegible]
ግንቦት 26 ቀን 1978 ዓ.ም

ለሚመለከተው ሁሉ

[illegible] የተባሉ እስረኛ [illegible]
አቶ [illegible] በመንግሥታችን ከ 22/5/72 እስከ 26/9/78
በቁጥጥር ሥር ከቆዩ በኋላ የታሰሩበት [illegible] ስለተወሰነ
ተለቀዋል::

የተፈታንበት ማስረጃ በከፊል ሲታይ.

22/5/72 ግን ማረሚያ ቤት የገባንበት ብቻ ነው፣ በቀበሌ እንድንቆይ የተደረገበት ረዥም ጊዜ ከሂሳብ አልገባም ማለት ነው። ሆነም ቀረም፣ የጌቶች ሁሉ ጌታ፣ የኃያላንም ሁሉ ኃያል፣ ከፍ ካለው በላይ ከፍ ብሎ ለዘላለም የሚኖር ልዑል እግዚአብሔር፣ የቀንበራችንን መሰበር በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ግልጽ እንዲሆን አደረገው። በመቀጠልስ ምን ሆነ?

ወረቀቱን ከሰጡን በኋላ፣ ወደ ወረዳ ኢሠፓ ጽ/ቤት ሄደን ለሦስት ቀናት ትምህርት እንድንከታተል ተነገረን። ከሰዓት በኋላ በማረሚያ ቤቱ አስተዳደር መኪና ተጭነን ወደ ወረዳው ኢሠፓ ጽ/ቤት ሄድን። ከዚያም ጥቂት መግለጫ ከተሰጠን በኋላ ለማግሥቱ የሚሆን ቀጠሮ ተቀብለን ተመለስን። ማምሻውን ጥቂቶች በተገኘ ዘመድ ወዳጅ ጋ ሲሄዱ ሌሎቻችን ሆቴል አልጋ ይዘን አደርን። ክርስቲያን ወገኖቻችን በከተማይቱ ውስጥ ነበሩ፣ ቢሆንም





ለደኅንነታቸው ለመጠንቀቅ ስንል፣ ሙሉ ለሙሉ ሳንለቀቅ፣ ቶሎ ቶሎ ወደ ቤቶቻቸው ለመሄድ ብዙዎቻችን አልፈለግንም ነበር።



18ቱ ተፈቺዎች በሀዋሳ ሓይቅ ዳር (1978 ዓ/ም)
ከግራ ወደ ቀኝ የቆሙት፡- ተስፋዬ ጋዚሳ፣ ተሾመ ወርቁ፣ ኃይሉ በቀለ
ከጎን ረድፍ የተቀመጡት፡- ደጻዲዮ መስፍን፣ አዳነ ለለማየሁ፣ በረሳ ባንዙር፣ ሙሉ እመቤት ሜዝሬ
ከበደ አርጋው፣ ተስፋዬ ቀሚሶ፣ ማርታ ጋዲሳ፣ ሰለሞን ኃበይ
ከመሃል የተቀመጡት፡- ወርቅነሽ ይመር፣ ማርቆስ ተፈራ፣ ዝናሽ ኃይሉ
ከፊት ለፊት የተቀመጡት፡- ጌታሁን አጋፋሪ፣ ሺመልስ ለማ፣ ለገሰ ዳኬ፣ ታፈሰ በሌ

## የመጨረሻው ‹‹ንቃት››

ከ29/9/78 - 2/10/78 ድረስ በሀዋሳ ወረዳ ኢሠፓ ጽ/ቤት የፖለቲካ ትምህርት ተሰጠን። ትምህርቱ ከ1966-1978 በኢትዮጵያ የተደረጉትን ለውጦች የሚያስታውስ ሆኖ ዓላማው፡-

> *ከእስር ቤት ስትወጡ ይህ ሁሉ ለውጥ እንግዳ እንዳይሆንባችሁ፣ ከሁኔታው ጋር ራሳችሁን ለማጣጣምና ለማስተካከል ጥረት ማድረግ ያስፈልጋችኋል የሚል ነበር።*

ትምህርቱን ያቀረቡት ከተለያየ መሥሪያ ቤት የተውጣጡ ሰዎች ሲሆኑ በትምህርቱ ውስጥ የእምነታችን ጉዳይም አልፎ አልፎ ተወስቷል። ለምሳሌ፣

የወረዳው ኢሠፓ ጽ/ቤት ኃላፊ ነበሩ የተባሉት ከተናገሩት ውስጥ የሚከተሰው ይገኝበታል፦

> *በኢትዮጵያ የእምነት - የሕሊና- ነፃነት አለ። እምነትህን ግን በግልህ በውስጥህ ትይዛለህ እንጂ ወደ ሌላው ማስተላለፍ አትችልም። እምነታችሁን ሰው እስኪያውቅላችሁ ድረስ ማጥበቅ የለባችሁም። በክፉና በደጉ መካከል ያለውን ለይቶ ማወቅ በቂ ነው። እስከ ዛሬ በዚህ ሁኔታ ገብታችሁ የቆያችሁት አንድም ባለማወቅ - ከአእምሮ ጨቅላነት የተነሣ - ፤አንድም ደግሞ በጥቅም በመደለል፣ ወይም እንደ መተዳደሪያ በመያዝ፣ ወይም ደግሞ ከጸረ-አብዮት ድርጅት ውስጥ ፣ ወይም ከትግል ሽሽታችሁ፣ ወይም በማወቅ ፈልጋችሁ ገብታችሁ ይሆናል። በእምነታችሁ ቀጥሉም አንላችሁም። እምነታችሁን ተውም አንላችሁም። እንስሶች አይደላችሁም። በማመዛዘንና ከሕብረተሰቡ በመማር በራሳችሁ ላይ ዘመቻና ግለ ሂስ በማድረግ ራሳችሁን አስተካክላችሁ ነገ ካድሬዎች የምትሆኑ እንደምትኖሩ አንጠራጠርም ....ወዘተ።*

በኋላ የሆነው ግን የዚህ ተቃራኒ ነው። ብዙዎቹ በእምነት ከፊት ይልቅ ጠንክረው፣ የወንጌል አገልጋዮች ሆኑ እንጂ እንድም ሰው ካድሬ አልሆነም ! ይልቁንም፣ ታሪክ ተገልብጦ፣ የዚያን ዘመን ካድሬዎች ክርስቶስ በፍቅሩ ኃይል ማርኮአቸው ያኔ ሲያጠፉት የጣሩትን ወንጌል ዛሬ ሲያገለግሉት ስማየት በቅተናል።

በ2/10/78 ስኞ ከሰዓት በፊት፣ የትምህርቱ ማጠቃለያ ንግግር በወረዳው ኢሠፓ 1ኛ ጸሐፊ ተደርጎ፣ ከትምህርቱ ተሳታፊዎችም አስተያየት ተጠይቆ ነበር። አስተያየቱን ከሰጡት መካከል፣ ስይፈ ገ/ጊዮርጊስ ከይሖዋ ምስክሮችና ሺመልስ ሰማ ከሙሉ ወንጌል አማኞች ይገኙበታል። ስይፈ የሚከተሰውን ተናግሯል፦

> *ይህን እምነት የያዝኩት ከውጭ ሀገር የሚመጣ ገንዘብ ወይም ጥቡቆ ስለሚወረወርልኝ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ ስድስት ቀን ሥራ ተግባርህን አድርግ ‹‹ሊሠራ የማይወድ አይብላ ›› ‹‹ለሥራ ከመትጋት አትለግሙ ‹‹መልካም ሥራን ለመሥራት አንታክት›› ይላልና ሠርተን መተዳደር የምንችል ነን። እንዲያውም ብዙ ጊዜ ከጓደኛዬ ከሞላልኝ ጋር መንግሥት እኛን እዚህ ቁጭ አድርጎ ለቀለብ ይህን ያህል ወጪ ከሚያወጣ ውጭ እየወጣን በሙያችን ሠርተን እንድንገባ ቢፈቅድልን እንዴት ጥሩ ነበር! እያልን እንነጋገራለን።*

ሺመልስ ወደ ክርስቶስ ከመምጣቱ በፊት ታንቆ ሊሞት ተዘጋጅቶ እንደ ነበረና





ጌታ በሥጋም በነፍስም ከሞት እንዳዳነው ስለ ክርስቶስ አዳኝነት መስክሯል። በመጨረሻም፣ *ወደ የክልላችሁ መሄድ ትችላላችሁ* ተብለን ተሰናበትን።



*ከግራ ወደ ቀኝ ኃይሉ በቀለ፣ ተሾመ ወርቁ እና ተስፋዬ ጋቢሶ በተፈቱ ማግስት (1978 ዓ/ም) ሀዋሳ*

## <u>አንድም ‹‹ሰኮና›› ሳይቀር</u>

ትምህርቱ -ንቃቱ- በተፈፀመ ቀን የሚበዙቱ ስአዳር ወደ የዘመዶቻቸው ሲሄዱ፣ የቀረነው ሙሉ ከብረት በሚባል ሆቴል ነበር ያደርነው። ከዚህ በኋላ ወደ ይርጋ ዓለም ማረሚያ ቤት ተመልሰን ዕቃዎቻችንን ማውጣት ነበረብን። ከዚህ ጋር እንድ ሕልም አስታውሳለሁ። እርሱም ከመፈታታችን በፊት በ19/9/78 ዋዜማ ላይ ያለምሁት ሲሆን፣ ፍሬ ነገሩ እንደሚከተለው ነበር፦

> *ዛሬ ማታ፣ (ባለፈው ሌሊት) ሕልም አልሜአለሁ። ተፈትቼ ዘመድ ለመጠየቅ ወደ ሌላ ቦታ ስሄድ ነበረ። ወንድሞችም*

እንዳረውኝ ነበሩ:: እህቶችም ተፈትው ወርቅነሽ ይመር ወደ ዘመዶችዋ ወደ ስራ ስትሄድ፣ በመንገድ አብራን ነበረች:: እኔም ዕቃችንን ማረሚያ ቤት ትተን ስለወጣን ተመልሰን እንውሰድ እያልኩኝ ነበር:: ሕልም ከእግዚአብሔር ሊሆንም ላይሆንም ይችላልና መዝግቦ መፈተን ከፋት የለውም:: ትምህርት ይገኝበታልና::

ትምሕርቱም፣ ሕልሙ ከእግዚአብሔር የነበረ መሆኑ ነው:: ከዚያው ከይርጋ ዓለም መሆን ሲችል ሀዋሳ ተጠርተን መፈታታችን ማንም ያላሰበው ነበር፤ ዕቃችንን ትተን መሄዳችንም ጭምር::

ታዲያ፣ ሙሉ ለሙሉ ከተለቀቅን በኋላ፣ ትልቁ ሃሳባችን ለመጽሐፍ ቅዱሶቻችንና ለማስታወሻ ደብተሮቻችን ሆነ:: ጌታ ያስተማረንን መንፈሳዊ ነገር በማስታወሻ እያስቀረን ተጠራቅሞ ነበርና፣ ስንወጣ ይዘን እንዳንወጣ ፖሊሶቹ እንዳይከለክሉን አሰብን:: በዚያን ጊዜ ነበር በዘፀ10:26 ላይ ያለው ጥቅስ ወደ አእምሯችን የመጣው::

እስራኤላዊያን ከግብጽ ባርነት ነጻ በወጡበት ወቅት፣ ፈርዖን እነ ሙሴን፡ ሂዱ እግዚአብሔርን አገልግሉ፤ ነገር ግን በጎቻችሁንና ከብቶቻችሁን ተው፤ ልጆቻችሁ ደግሞ ከእናንተ ጋር ይሂዱ አለ:: ሙሴ ደግሞ አንድ ሰኮናም አይቀርም አለ (ዘጸ 10:24-27):: ስለዚህ እኛም በዚህ ቃል ሀዋሳ ባደርንባት በዚያች ምሽት፦

> ጌታ ሆይ፣ አንተ የእስራኤልን ሕዝብ ከግብጽ ምድር ስታወጣ፣ ከነከብቶቻቸው ነበር ያወጣኸው:: እኛም ከመጽሐፍ ቅዱሶቻችንና ከማስታወሻ ደብተሮቻችን ጋር መውጣት እንፈልጋለን:: አንድም ደብተር ሳይቀር ሁሉንም ይዘን እንድንወጣ አድርግ በማለት ፀለይን::

በማግሥቱም ማለት በ3/10/78 ከይርጋ ዓለም ማረሚያ ቤት አንድ ብጣሽ ወረቀት ሳይቀር ዕቃዎቻችንን ሁሉ ማንም ሳይከለክለን ይዘን ወጣን:: አብረውን «ከተፈቱት» ጸሑፎች መካከል በእስር ላይ እያለን የተጻፉ ከ40 የማያንሱ ዝማሬዎቼ ይገኛሉ:: ክብር ለእግዚአብሔር በእርያም ይሁን!!

## ዜናው ሲሰማ

በ3/10/78 ማክሰኞ ወደ ደንጎራ እልመቴ ወላጆቼ ጋ ሄድኩ:: እስከ ሐሙስ ጠዋት እዚያ ቆየሁ:: ልቆጥራቸው እስከማልችል ድረስ ብዛት ያላቸው የቅርብና የሩቅ ዘመዶች፣ ደስታቸውን ለመግለጥ፣ እግዚአብሔርንም ለማክበር፣ እኔን፣ ወላጆቼን፣ ወንድሞቼንና እህቶቼን እንኳን ደስ አላችሁ ለማለት ከየገጠሩበት መጡ::





የመፈታታችን ዜና በደረሰበት ሁሉ ሰዎች እጅግ በጣም ተጽናኑ:: ወይዘሮ ብጽዓት፣ የዶክተር መልሳቸው መስፍን ባለቤት፣ ሀዋሳ እያለሁ ደውላ ተስፋዬ፤ እኛ እዚህ አዲስ አበባ ያለን በጣም ደስ ብሎናል ... ከተማ ውስጥ በየመንገዱ የሚሄድ ሰው ሁሉ እንደ እኛ የተደሰተ ... ያለችኝ ትዝ ይለኛል::

ስለ እኛ ከሚመለከተው ባለ ሥልጣን ሁሉ ጋር በመነጋገር ለዓመታት ሲደክሙ የቆዩት እቶ ሰይፉ ተ/ሃይማኖት ደግሞ ምን አገርህ ... እኔ ቶፈታሁ እንጂ! ብለዋል ይባላል::

ጌታን የማያመልኩ ዓለማዊያን ሳይቀሩ ደስታቸውን ገልጸዋል ... ሁለት እህቶች በአዲስ አበባ ከተማ አውቶብስ ውስጥ ስለ እኛ መፈታት ሲያወሩ አንዲት አማኝ ያልሆነች ሴት ትሰማቸው ኖሮ ጣልቃ በመግባት «እናንተ፣ ተፈቱ እንዴ? እንኳን ተፈቱ! እኔ እንኳን እንደ እናንተ አልደሰትም:: ግን እንኳን ተፈቱ! እንኳን ተፈቱ!» ብላለች ይባላል::

ብዙዎች የደስታ እንባ አፍስሰዋል:: እንደ ሰማነው፣ የድንጋጤ ዝላይ ዘለዋል፣ወድቀው መሬት ላይ የተንከባለሉም አልጠፉም:: ዜናውን ሲሰማ፣ ሮጦ እውራ ጎዳና ውስጥ ስለ ገባ፣ ታክሲ ገጭቶት በመጠኑ የተጎዳ ሰውም አለ ተብለናል::ኧረ ምኑ ቅጡ ! የብዙ ቅዱሳን ልብ ከእኛው ጋር ምን ያህል ታስሮ እንደ ከረመ እነዚህ ሁኔታዎች ያስረዳሉ:: ደስታው የተገለጠበት መንገድም፣ጉዳዩ የእግዚአብሔርና የቤተ ክርስቲያን ጉዳይ እንደ ነበረ ያሳየናል::

*አቤቱ ጌታችን ስምህ በምድር ሁሉ እጅግ ተመሰገነ፣ ምስጋናህ በሰማዩች ላይ ከፍ ከፍ ብሎአልና (መዝ፣8:1)::*

## መልእክት ለተፈቱት

ከእስር ቤት እንደ ወጣን ከወዳጆቻችን ያገኘናቸው አንዳንድ የቃል መልዕክቶች ነበሩ:: የሁለት አገልጋዮች መልዕክት ፍሬ ሃሳቡ ሲጨመቅ እንደሚከተለው ይሆናል፦

> አንዳንድ ጊዜ፣ እግዚአብሔር የገባልን ቃል ሌላ፣ በተጨባጭ የምናየው ሌላ ይሆንብናል:: የሴፍ 11 ነዶዎች ለእርሱ ነዶ ሲሰግዱ፣ ፀሐይና ጨረቃ፣ 11 ከዋክብትም እንዲሁ ሲሰግዱለት አይቶ ነበር:: ሆኖም ጉድጓድ ውስጥ ተጣለ:: ከዚያም ለባርነት ተሸጠ:: ከዚያም በሐሰት

*ተከሶ ወህኒ ቤት ገባ።*

*ዳዊትን ሳኦል ባልሆነ መንገድ ተረዳው። ዳዊትን ባልሆነ መንገድ የተረዳ ሳዖል ብቻ አልነበረም። ወንድሙ ኤልያብም እንጂ!... «ትዕቢተኛ » ብሎታል። ዳዊት ግን ትዕቢተኛ አልነበረም። ዳዊት ትሁት ሰው ነበረ። በሌላ ቦታ... የዳዊትን ገርነቱን አሰብ ነበር የተባለው። ... ሁሉም አሰፈና የእረፍት ዘመን ግን መጣ።*

*እግዚአብሔር ሲያሳርፈው ዳዊት ከእኔ ይበልጥ ጌታ ሊመቸው ይገባል አለ። ስለዚህም ቤት ሊሠራለት አሰበ። ጌታ ግን ‹እኔ መች ተመችቶኝ ያውቃል? ከሕዝብ ጋር ስንከራተት ነው የኖርኩት አለ። እግዚአብሔርም ለዳዊት ቤት እንደሚሠራለት ነገረው።*

*ብዙ ጊዜ፣ እግዚአብሔር ከጠላቶች ሲያሳርፈን እንመቻቻለን። የእግዚአብሔርን ሥራ እንረሣለን። እግዚአብሔር ጊዜ ሊሰጠንና ሊያሳርፈን ጀምሮ ከሆነ፣ የእኛ ዓላማ የዳዊት ዓይነት ሊሆን ይገባል። ልናገለግለው ይገባል። ሁሉ የራሳቸውን ይፈልጋሉ። እንዴት አድርገው advantage እንደሚመቱ፣ ማለትም፣ ጥቅም እንደሚያገኙ ያስባሉ። ጢሞቴዎስ ግን ስለ ኑሯችሁ ይጨነቃል አለ፣ ጳውሎስ። ስለዚህ እግዚአብሔር ሲያሳርፈን የክርስቶስ ኢየሱስን እንፈልግ። (በፓስተር ጻድቁ አብዶ)*

*በመከራችሁ መጽናናትን እንዳገኛችሁ ሁሉ በመከራ ሁሉ ያሉትን ማጽናናት ያስፈልጋችኋል ከዚህ በኋላ ይህ ቃል(2ቆሮ 1:3-4) መመሪያችሁ ሊሆን ይገባል።*

*እግዚአብሔርን ባለ ዕዳ አታድርጉት (ዕብ 6:10) እግዚአብሔር የማንም ባለ ዕዳ አይደለም። እነዚህ ሰባት ዓመታት በከንቱ ያለፉ አይደሉም። በከንቱ ደከምኩ፣ ከሠርኩ አትበሉ። ትልቁ ነገር ገንዘብ ማግኘትና ባለጸጋ መሆን አይደለም ። እግዚአብሔር በሚሠራበት ጊዜ የእርሱ ገንዘብ ሆኖ መገኘት ነው እንጂ(ሚል3:3-15) ! (በወንጌላዊ መስፍን ተሰፋዬ)*

## ክብር ሁሉ ለእግዚአብሔር

በዚያን ጊዜ - በሰባቱ ዓመታት ውስጥ - አንድ ዓይነት እምነት ባለንና 18 በምንሆን ሕይወት ውስጥ እግዚአብሔር የፈፀመው ሥራ እጅግ ብዙ ነው። 18ቱም ሰዎች በየራሳቸው አቅጣጫ የደረሰባቸውንና ያለፉበትን ቢጽፉ ምናልባት ተነቦ «የማይጨረስ» ሰፊ ታሪክ ይሆን ነበር። እንግዲህ፣





በመጠኑም ቢሆን የጌታን ሥራ ለማስታወስ ይህ ተጽፏል። ስለ ስሙ፣ ለእኛና ለአካሉ፣ ለቤተ ክርስቲያን፣ ስላደረገው በጎ ነገር ሁሉ በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ክብርና ምስጋና ለእግዚአብሔር ይሁን።

*አቤቱ አምላኬ፣ ያደረግኸው ተአምራት ብዙ ነው፣ አሳብህንም ምንም የሚመስለው የለም፤*
*ባወራም ብናገርም ከቁጥር ሁሉ በዛ። (መዝ 40:5)*

*ነገር ግን የኃይሉ ታላቅነት*
*ከእግዚአብሔር እንጂ ከእኛ*
*እንዳይሆን ይህ መዝገብ*
*በሸክላ ዕቃ ውስጥ አለን (2ቆሮ 4:7)*

*ጌታ በእኔ አጠገብ ቆም አበረታኝ፣*
*ከአንበሳ አፍም ዳንሁ።*
*ጌታም ከክፉ ነገር ሁሉ ያድነኛል*
*ለሰማያዊውም መንግሥት ይጠብቀኛል፤*
*ለእርሱ ከዘላለም እስከ ዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን። (2ጢሞ 4:17:18)*

ስሙን እናመሰግን ዘንድ፣ ጌታ የቅዱሳኑን የማይታክት ጸሎት ሰምቶ፣ ነፍሳችንን ከወህኒ አወጣት(መዝ 142:7)። ጌታ ሆይ፣ እስከዚህ ያደረስከን እኛ እነማን ነን? አሁንም በሰጠኸን ቀሪ ዘመን፣ ለክብርህ ምስጋና እንድንውል እርዳን።

## ከዚያ በኋላ

በዚያን ጊዜ የሆነውን በመጠኑ ከተመለከትን፣ ከዚያ በኋላ የሆነውንና ሊሆን የሚገባውን በጥቅሉ መመልከቱ አግባብነት ይኖረዋል ።

ሀዋሳ ላይ ከእስር መለቀቃችንን እንዳረጋገጥን፣ ጌታን በጋራ ለማመስገንና የማስታወሻ ፎቶ ግራፍ ለመነሳት ወደ ሐይቅ ዳር አምርተን ነበር። በዚያም ሳለን በትንቢተ ኤርምያስ 51፡64 ላይ ያለ ቃል ወደ ልቤ መጣ። ቃሉም እንዲህ የሚል ነበር። *እንዲሁ ባቢሎን ትሰጥማለች ፣ አትነሣምም በል።* ኤርምያስም በወቅቱ በባቢሎን የነበረውን ሠራያን አዝዞት ትንቢቱ የተጻፈበትን ቃል ድንጋይ አሥሮበት በኤፍራጥስ ወንዝ ላይ እንደ ጣለው፣ ይህንኑ ቃል በወረቀት ጽፌ ከድንጋይ ጋር በማጣበቅ በሐይቁ ውስጥ ጥዬዋለሁ። በዚህ መልክና ተምሳሌት፣ የእግዚአብሔርን ሕዝብ በየቦታው ያስቃየ ያ ግፉና ሥርዓት፣ በጥቂት ዓመታት ውስጥ፣ በማይታመን ሁኔታ ተገርስሶና ለጥሞ

ከእይታ ሲሰወር ለማየት በቅተናል፡፡

በምክክሩ ውስጥ ሳለፍን እረፍት፣ በቅርብና በሩቅ ስለ እኛ በእግዚአብሔር ፊት ለማማለድ በፅንባቸውን ላፈሰሱ ትልቅ መጽናናት ሆኗል፡፡ በፀገሪቱ ስቆች በሚሊዮኖቻቸው ወንጌል በነጻነት ሲሰበክ ለማየት ችለናል፡፡ *ሰፊው ሕዝብ ነቅቷአል፣ እንሰበክህ ብትሉም የሚሰማችሁ የለም፡፡* እንደተባልነው አልሆነም፡፡ ወንጌልን የተጠማና የሚሰማ ሰው እጅግ በዝቶ፣ እኛም ወንጌሉን የምንናገርበት ጊዜ ሲያንሰን አየን፡፡

*በዚያን ጊዜ* እኛንና የክርስቶስን ወንጌል በፅኑ የተቃወሙና ያስቃዩን የደርጋ ዓለም ቀበሌ ሹሞች በገዛ እጃቸው የጸሎት ቤት *መሥሪያ ቦታ* ሲያስረክቡን ለማየትም በቅተናል፡፡ ቦታው፣ በቀበሌ 05 ወንድሞችና እህቶች በአብዮት ጠባቂዎች እጅ በየማለዳው እየወጡ እንዲንከባለሉ የተደረጉበትና የተንገላቱበት፣ የተገረፉበት፣ የተደበደቡበትና የተረገጡበት ነበር፡፡ ያንኑ ቦታ እግዚአብሔር ለስሙ ማስጠሪያ ከእጃቸው በመውሰድ ከእጃችን አስገባው፡፡

ከተፈታን በኋላ፣ ማረሚያ ቤቶች፣ በብዙ አካባቢዎች የእማኞች ማሰቃያ የመሆናቸው ታሪክ ተቀይሮ ፣ጸሎት ቤት ተሠርቶባቸው፣ወንጌል የሚገለገልባቸውና እዚያው ቦታ በክርስቶስ ወንጌል አምነው የተለወጡቱ በነጻነት ጌታን የሚያመልኩባቸው ቦታዎች ሲሆኑ ተመልክተናል፡፡ እኛም ራሳችን በደርጋ ዓለምና በሀዋሳ ማረሚያ ቤቶች ተጋብዘን በመግባት ወንጌሉን የመናገር ዕድል አግኝተናል፡፡ የመፈታታችንን 21ኛ ዓመት በደርጋ ዓለም ባከበርንበት ጊዜም፣ በ1997 ዓ/ም ወደ ጌታ ከተሰበሰበው ከወንድማችን ሰሎሞን በስተቀር፣ ሁላችንም አስተዳደሩን አስፈቅደን ወደ ወኅኒ ቤቱ በመግባት፣ በወቅቱ ከነበሩት አማኝ «ታራሚዎች» ጋር ድል አድራጊውን ጌታችንን አመስግነናል፣ ታላቅነቱን መስክረናል፣ ሰብከንማል፡፡

በእግዚአብሔር ጸጋ፣ ስእስር በተለቀቁ ወገኖችና በቅዱሳን ትብብር ከሀዋሳ አንስቶ እስከ ነገሌና ሞያሌ በገጠርና በከተማ የወንጌል ሥርጭት ተካሂዷል፡፡ በሙሉ ወንጌል ቤተ እምነት ውስጥ የተዋቀሩ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያኖችም ተመሥርተዋል፡፡ ይህ ጽሁፍ በሚዘጋጅበትም በአሁኑ ጊዜ፣ የቤተ ክርስቲያኖቹ ቁጥር ከመቶ በላይ ሆኗል፡፡

የሚበዙቱ ወንድሞቻችን፣ በተለያዩ አጥቢያዎች፣ በወንጌላዊነትና በመጋቢነት እያገለገሉ ይገኛሉ፡፡ አገልግሎታቸው ግን በአጥቢያና በአንድ ቤተ እምነት አልተወሰነም፡፡ ከዚያም በመሻገር በእግዚአብሔር ቸርነት ለሌሎች አብያተ ክርስቲያን እየተረፈ ይገኛል፡፡ እህቶቻችንም በያሉበት ጌታ በሰጣቸው ጸጋ የእግዚአብሔርን ሕዝብ በትጋት እያገለገሉ ናቸው፡፡





በሙሉ ሀገራችን፣ በአንጻራዊነት፣ታላቅ የሆነ መንፈሳዊ ትሕይትና መነቃቃት አይተናል፡፡ ወንጌልን በትጋትና በታማኝነት በመስበክ ቅዱሳን ሲያስተምሩ አገልጋዮች አማካይነት በክርስቶስ እያመኑ ከዘላለም ሞት የሚድኑ ብዙ ሰዎች ለማየት አምላካችን አድሉናል፡፡ በገጠር በከተማ ምድራችን እጅግ ብዙና የምስጋናና የዝማሬ ድምፅ የሚሰማባት ሆናለች፡፡ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሕዝቡን ያገለግሉ ዘንድ ጸጋውን አልብሶ ጌታ ለዘርፉ ካስነሳቸው የወንጌል አገልጋዮችና ዘማርያን በእጅጉ ተባርከናል፡፡ በእግዚአብሔር ፊት ቀንና ሌሊት ለሥራው በምልጃ የሚቃትቱና በሰው ዓይን ባይታዩም ብዙ የሚበረቱ፣ የሌሎች አገልጋዮችን ብዛት ማን ቆጥሮአል? …

ቤተ ክርስቲያን በአገር አቀፍ ደረጃ በምዕመናን ብዛት ቀላል የማይባል ዕድገት ታይቶባታል፡፡ በደርግ ዘመን ከጠቅላላ የሃገሪቱ ሕዝብ ወደ 4% ይገመት የነበረው የወንጌላዊያን አማኞች ብዛት አሁን ወደ 18% መድረሱ ይገመታል፡፡ ነቢዩ ኢሳይያስ፡- *ሕዝብን አብዝተሃል፣ደስታንም ጨምረህላቸዋል፣በመከር ደስ እንደሚላቸው፣ ሰዎችም ምርኮን ሲካፈሉ ደስ እንደሚላቸው በፊትህ ደስ ይላቸዋል* እንዳለው እየሆነ ነው(ኢሳ 9፡3)፡፡ በዚህ ረከተን መቃምጥ በደጋግሙ እኛም ከነቢዩ ጋር *አቤቱ ሕዝብን አበዛህ* እያልን የሥራውን ዋና ባለቤት ጌታን ማክበራችን ተገቢ ነው፡፡

## ማጠቃለያ

እንግዲህ፣ በጥቂቶቻችን ላይ ደርሶ ያለፈው የሰባት ዓመቱ እስርና መለኮታዊው ረድኤት፣ የዋዜማውና የማግሥቱ ሁኔታ፣ በምሳሌ ሲቀመጥ ይህንን ይመስላል፡፡ እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁንና፣ አሁን በሃገራችን የእምነት ነጻነትን የሚያረጋግጥ ሕገ መንግሥት አለ፡፡ በዚህ ጊዜ፣ እንዳለፈው ዘመን፣ ለምን በክርስቶስ አመንክ እየተባለ ሰው ወደ እስር ቤት አይወሰድም፡፡ አይንገላታም፡፡ ይህ ግን፣ የወንጌልና የጽድቅ ጠላት የሆነው ዲያብሎስ ጦርነቱን አቁሞ ታስሯል ማለት አይደለም፡፡ ስለዚህ፣ «በተራራ» ላይ ለሸነፍነው ለብሽለቃ ለመግጠም፣ ከውጭ አልሳካልህ ሲለው፣ ከውስጥ ለማዳከም መጣሩ ይቀራል ብሎ ማሰብ ሞኝነት ይሆናል፡፡ ከኃጢአትም ጋር የሚካሄድ ትግል ... የከበረውን ክርስቶስ፣ ወይም በኃጢአት የወደቀውን ዓለም በመምረጥ ... የሚደቀን ፈተና፣ በጥቅሉ፣ ጨለማው ከብርሃን ጋር የሚደርገው ውጊያ ሙሉ ለሙሉ የሚጠናቀቅበት ጊዜው ገና ወደ ፊት ነው፡፡

መነሻውና መጠኑ ይለይ፣ መልኩም ይቀየር እንደሆን እንጂ ለእውነተኛው አማኝ፣ ስለ ጽድቅ ዋጋ መክፈል የሚቀጥል እውነታ እንደሆነ መዘንጋት

የለበትም፡፡ አስደናቂው የእግዚአብሔር ጸጋ ግን በየትኛውም መንገድ ለሚያጋጥም መከራና ፈተና የሚበቃ ነው፡፡ *እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ ያለ* ክርስቶስ ዛሬም ሕያው ነው (ዮሐ 16:33)፡፡ ከእርሱም የተነሣ፣ አሸናፊነት የእኛ፣ ድምዳሜአችን የክብርና የድል እንደሚሆን የጠረጋገጠ ነው(ሮሜ 8:18)፡፡ ስለዚህም፣ የአምላካችን የእግዚአብሔር መንግሥት ወንጌል እየተሰበከ፤ በወንጌል አምነው የሚድኑም እየተጨመሩ መብዛታቸው ጌታ በክብሩ ዳግም እስኪገለጥ ድረስ ይቀጥላል፡፡

እንግዲያውስ፣ ሙሉ በሆነ መሰጠትና አስፈላጊውን ዋጋ ጨክኖ በመክፈል፣ ለክርስቶስ ወንጌል እንደሚገባ የመኖር ጥሪው አሁንም ይከበር፡፡ ዋጋ በመክፈል ማገልገል የክርስቶስና የሐዋርያቱ ፈለግ ነው፡፡ እንከተለው፡፡ ለክርስቶስ ወንጌል የማይበጅና አስናካይ የሆነ ማናቸውም አሰተሳሰብ፣ አካሄድና ልምምድ ቢኖር ፈጥኖ ይስተካከል፡፡ ፉክክር ሳይሆን ትብብር ይጠናከር፡፡ የእግዚአብሔር የአምላካችን ጽድቅና ቅድስናው በሕዝቡ ላይ ደምቆ ይብራ፡፡ ይህ እውን የሚሆነው፣ ለመንግሥቱ ወንጌል ስንል ግላዊ ፍላጎታችንን መሥዋዕት ስናደርግ ነው፡፡

ነጻነታችንንም ኃላፊነት በተሞላ መንገድ እንጠቀምበት፡፡ ዘመኑን ከአሁን የበለጠ በማስተዋል እንዋጅ፤ በጥቃቅን መናኛ ጉዳዮችና ያለ ልክ በመዝናናት የምናጠፋው ጊዜ የለንም፡፡ ደስታችን ከኃጢአትና ከአጋንንት እስራት በክርስቶስ አርነት ወጥተውና ተለውጠው ደቀ መዛሙርት በሚሆኑ ሰዎች፣ ማለትም በታላቁ የወንጌል ተልዕኮ መሳካት ይሁን፡፡ የተለወጡ ሰዎች የማያሳፍሩ የወንጌል ምስክሮች፣ የሕዝብና የሀገርንም ሁለንተና በጽድቅ የሚያገለግሉ ይሆናሉ፡፡ ጌታ በክብር እስኪመለስ ድረስ፣ እንደ ቤተ ክርስቲያን፣ ይህን ልንፈልግና ለዚህም ተግተን ልንጸልይ ይገባል፡፡ እግዚአብሔር እስከ ዛሬ ድረስ በጸጋው ረድቶናል፡፡ እስከ ፍጻሜውም ድረስ ይረዳናል፡፡

በየጊዜው፣ መፈለግንና ማድረግን በእኛ ለሚሠራ፣ ለታሪክ ባለቤት፣ ሁሉን ቻይ ለሆነው፣ ለአምላካችን ለእግዚአብሔር፣ በክርስቶስ ኢየሱስ በመድኃኒታችን ስም፣ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ክብር ይሁን፡፡

እግዚአብሔር ሕዝባችንን በሰላም በፍቅርና በፍትሕ በሌላም በጎ ነገር ሁሉ ይባርክ፡፡ አሜን፡፡